# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት

# The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order

www.ethiopianorthodox.org




www.ethiopianorthodox.org


የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org

# ት ን ሣ ኤ

# የሃያ አምስት ዓመታት መንፈሳዊ እርምጃ

በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፤ በ፴፯ኛ ዘመነ መንግሥታቸው
ይህ መጽሐፍ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
ተዘጋጅቶ ታተመ ።



የመጀመሪያው የኢትጵያ ፓትሪያርክ
ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ

# ማውጫ


| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| መቅድም | 11—12 |
| ፩ኛ. አዲሱ የቤተ ክህነት አስተዳደር ። | 13—15 |
| ፪ኛ. የኢትዮጵያ ጳጳሳት ። | 16—26 |
| ፫ኛ. የሕንፃ ቤተ ክርስቲያን በብዛት መሠራት ። | 26—47 |
| ፬ኛ. የቅዱሳት መጻሕፍት በብዛት መጻፍ ። | 47—50 |
| ፭ኛ. የመንፈሳውያን ትምህርት ቤቶች መቋቋም - | 51—58 |
| ፮ኛ. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በዓለም ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ፊት ። | 58—62 |
| ፯ኛ. የመንፈሳውያን ማኅበሮች መቋቋም ። | 62—74 |
| ፰ኛ. የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ልዩ ካቢኔ መንፈሳዊ ክፍል መቋቋም ። | 75—76 |
| ፱ኛ. የወንጌል ድምፅ ራዲዮ ጣቢያ በኢትዮጵያ መቋቋም ። | 76—81 |
| ፲ኛ. የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ጉባኤ ። | 82—93 |
| ፲፩ኛ. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት መቋቋም ። | 94—102 |

# መ ቅ ድ ም

ግርማዊ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለኢት
ዮጵያ ልማትና ዕድገት ለመንፈሳዊውም ሆነ ለሥ
ጋዊው እርምጃ ከእግዚአብሔር የተሰጡ እንደመ
ሆናቸው ከፍተኛውን የኃላፊነት ሥልጣን ከተረ
ከቡበት ጊዜ ጀምሮ ዕረፍትን ሳይሹ በመሥራታ
ቸው ድካማቸው ከንቱ ሳይሆን ስለቀረ ፤ የሰጠው
ውጤት ከፍ ያለ ከመሆኑም የተነሣ ሥልጣኔያቸ
ውን ከረጅም ጊዜ ታሪካቸው ጋር አዛምዶላቸው
ይገኛል ። ግርማዊነታቸው ለውድ ሀገራቸው የሠ
ሩት እጅግ ብዙ ነው ። ይኸን ሁሉ በየጊዜው
እየተከታተሉ ለመጻፍ ለዜና አዘጋጅዎች ብዙና
ከባድ ሳይሆንባቸው አልቀረም ። ሆኖም በሙሉ
እንኳን ባይሆን በከፊል በልዩ ልዩ አጋጣሚ እየ
ተገለጸ የቆየውን እንደማጠቃለያ እያደረጉ አሁን
ለብሩዊ ኢዮቤልዩ በየመሥሪያ ቤቱ የሚመለከ
ተውን ያህል ሳያወጣ አልቀረም ። ስለዚህ እኛም
ያለፈውን ጊዜ ሥራ አቆይተን ጠላትን አቸንፈው
በድል አድራጊነት ወደመናገሻ ከተማቸው ከገቡ
በኋላ በመንፈሳዊው ረገድ ብቻ ለኢትዮጵያ የሠ
ሩትን በአጭር እንዘረዝራለን ።

በኢትዮጵያ የዘመናዊ ትምህርት ቤት አሠ
ራር ፤ የወታደር አቅዋም ፤ የጤና አጠባበቅ ፤ የኑ
ሮም ደረጃ መሻሻልና ዕድገት ፤ በጠቅላላው ለአ
ንድ ሕዝብ ለኑሮ ደረጃ ተገቢ የሆነውን ነገር
ሁሉ በመልክ በመልኩ መሥራት የተጀመረው
በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ሲሆን፤
በአሳብ ፤ በገንዘብ ፤ በጊዜ ይኸንም በመሳሰሉ
ነገሮች ሁሉ ብዙ ችግር እንደገጠማቸው ዓይነ
ልቡና ያለው ሊገነዘበው ይችላል ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ግን ትዕግሥትን ገን
ዘብ በማድረግ ስለሠሩ ከመልካም ግብ ደረሱ ። ከዚ
ህም ሁሉ ጋር ደግሞ መንፈሳዊውን ተግባር ሳይ
ዘነጉ ለሀገር ፤ ለወገን ጠቃሚ መሆኑን በመገን
ዘብ ከሥጋዊው ጋር ጐን ለጐን በመሰለፍ ለቤተ
ክርስቲያን የዋሉት ውለታ እጅግ ከፍ ያለ ነው ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀደም አድርገው
በመንፈሳዊው ዓላማ የተጠቀሙበት ስለሆነ ፤ ወገ
ናቸው ሁሉ እንዲጠቀም በማለት በየቦታው ትም
ህርት ቤት እንዲሠራ ፤ ቤተ ክርስቲያን ያረጀው
እንዲታደስ ፤ የፈረሰው እንዲሠራ ፤ ለመኳንንትና
ለሻለቃ ለልዩ ልዩ ባለሥልጣኖች ከፍ ያለ ማስ
ጠንቀቂያ ሰጥተው ዐዋጅም ዐውጀው ነበር ።

ዐዋጁም ከዚህ የሚከተለው ነው ።
ሞዐ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

## ዐዋጅ

መኳንንትም ፤ የሻለቃም በየሰጠንህ ግዛት
ለነፍስህ ደኅንነት ፤ ለሰላም ኑሮ ዕረፍት የሚለመ
ንበት ቤተ እግዚአብሔር ሳይሠራ የመኖሪያ ቤት
ህን በማደራጀት ባላገሩም ተጐዳን ብሎ ይጮኻል
እንጂ ቤተ ክርስቲያን በመፍረሱ ፤ የተሠራውም
ከተበላሸ በኋላ ባለመታደሱ ተቆርቋሪ ስላላገኘ ፤
ለነፍስም ጉዳት ፤ ለሥጋም መቅሠፍት የሚያ
መጣ ሆኗልና በያውራጃህ የተተከሉትን አብያተ
ክርስቲያናት የፈረሰውንም አሠራ ። ያረጀውንም
አሳድስ የሃይማኖት መሠረት ፤ የክርስቲያን ምልክቱ
ቤተ ክርስቲያን መሥራት ነው ። ነገር ግን በዚህም
ምክንያት ባላገሩን አለወገን አዝዘህ ደኅ አትበድ
ልብኝ ። አጥቢያውም በገንዘቡም ፤ በጉልበቱም
ረድቶ ካወጣና ከሠራ በኋላ ከጉልበቱና ከገንዘቡ
የሚተርፈውን ሥራ እኔ እረዳለሁና ችግርህን በደ
ጃዝማች ደስታ ዳምጠው በኩል አስታውቀኝ ።

ከዚህ ዐዋጅ ወዲህ ግን እስካንድ ዓመት
ድረስ ቤተ ክርስቲያኑ ሳይሠራ ቀርቶ መፍረሱን ፤
አለመታደሱንም የሰማን እንደሆነ ፤ ቤተ ክርስቲ
ያኑ የሚፈጀውን የሥራ አጠፌታ መቀጫ እየከፈ
ልክ ለቤተ ክርስቲያኑ ሥራና ጉዳይ ይገባል ።

ሐምሌ ፲፫ ቀን ፲፱፻፷፪ ዓ ም ተጻፈ ።



www.ethiopianorthodox.org

ይኸም ዐዋጅ የግርማዊነታቸውን ታላቅነት የሚገልጥ የመንፈሳዊነታቸው ምልክት ሆኖ ለሕዝባቸው አንድነትን ፤ ለኑሮው መግባባትን ፈጥሮ ይገኝ ነበር ። እንደ ዐዋጁም መሠረት ሁሉ በየግዛቱ በሚሠራበት ጊዜ ጠላት በግፍ አገራችን ሲወራት ለአርበኞቻችን ብርታትን የሰጠው ይኸ መንፈሳዊ ዐዋጅ ነው ። ለነፃነታችንም መመለስ ዋና ምክንያት የሆነው በንጹሕ ሕሊና የሚያመልኩት በንግግራቸው የሚመሰክሩለት ለአምልኮቱ የሚያውጇለት እውነተኛው አምላክ ነው ። አርበኞች በቆራጥነት ፭ቱን የመከራ ዓመት ሲዋጉ ያሳለፉት መንፈሳዊ ቅንዓት ጽኑዕ ሃይማኖት ስለነበራቸው ነው ። ቤተ ክርስቲያን ራሷ በስደትም ነበረች ። በአርበኝነትም ነበረች ፤ በከተማውም ፤ በመንደሩም ከሚሠቃየውም ጋር አብራ ትሠቃይ ነበረች ። በጠቅላላው ለሀገር መድኃኒት የሆነች ለአገዛዝም ነፃነትን የሰጠች ቤተ ክርስቲያን ናት ፤ በአንድ ቃል ለመግለጥ ስንፈልግ ቤተ ክርስቲያን ውለታ መላሽ ነበረች ። ናትም ወደፊትም ትሆናለች።

ስለዚህ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ለቤተ ክርስቲያን የዋሉትን ውለታ የሠሩትን በጎ አድራጎት ሁሉን ሳይሆን በጣም የጐላውን በመጠኑ ከፍለን እንናገራለን ። ይኸውም ፤

፩ኛ እኛን ኢትዮጵያውያንን የቀደመ ታሪክ ያለው ሕዝብ አሰኝቶ በአፍሪካ ሽንገ በጠቅላላም በዓለም አደባባይ ላይ ከፍተኛ ግምት እንድናገኝ አድርጎናል ።

፪ኛ የጥንቱን ሥርዓት ሳንለቅ አዲሱን ሥልጣኔ ስንቀበል ለውጣችን መልክ ያለው ደረጃው የተጠበቀ ስለሆነ ፤ ሕጋዊ ለውጥን ለማግኘት የቻለ ዐዋቂ ሕዝብ አሰኝቶታል ።

፫ኛ አንድ ሕዝብ በግብረ ገብነቱ የበረታ የሚሆነው በሃይማኖት ሲጸና በምግባር ሲቀና በሥነ ሥርዓት የተደገፈ እንደሆነ ነው ። ይኸም ዓይነት ሕዝብ እርምጃው ለመልካም ግብ ይሆናል ። ያለዚያ ግን ግብ የሌለው ሩጫ ሆኖ ሊቀር ይችላል ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ታላቅ ሰውነት ፤ ጥልቅ አስተያየት ስላላቸው በፖለቲካ ሽንገ የመጀመሪያውን ደረጃ ይዘው ዓለምን ወደ አድናቆት የሳቡ ንጉሠ ነገሥት ሁነው ይገኛሉ ። በአስተዳደርም በኩል ከደረጃ ወደ ደረጃ ሕዝብን ለመምራት ከፍተኛ ችሎታ ካላቸው መሪዎች የመጀመሪያውን ደረጃ ያገኙ ንጉሠ ነገሥት ናቸው ። በመንፈሳዊውም በኩል ጥልቅ የሆነ አስተያየት ስላላቸው ፤ የበለጠ ችሎታና ስጦታ ያላቸው ፤ እውነተኛ መንፈሳዊ ናቸው ። ስለዚህ በውድ ሀገራቸው መንፈሳዊው ዕውቀት ለሥጋዊ ሥልጣኔ ደገፉ እንዲሆነው በማለት ለመንፈሳዊው ሥልጣኔ በር ከፋች ሆነው ትምህርት ቤት በማቋቋም የመጀመሪያውን ደረጃ ይዘው ቤተ ክርስቲያናችውንም በዓለም ቤተ ክርስቲያን ሽንገ ተገቢ ደረጃዋን እንድታገኝ ብዙ ጥረት አድርገዋል ። መልካም ውጤትንም አስገኝተዋል ። ይኸን የመሰለ ሥራቸውንም የተረዳ ፤ መንፈሳዊ አቅዋማቸውን ያወቀ የምሥራቅ ኦብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ጉባኤ ተስማምቶ በአንድ ድምፅ «የክርስቲያን ሃይማኖት ጠባቂ» ብሎ የክብር ስም ሰጥቷቸዋል ። ይኸን ሁሉ ስንመለከት ግርማዊነታቸው በንጉሥነት የተነሡት በተለይም እንደ ዓይን ብሌን ተጠብቀው ከብዙ አደጋ ድነው የመጡት ለኢትዮጵያ ዕድገት ፤ ለሀገሯ ስፋት ፤ ለቤተ ክርስቲያንም ደገፉነት እንደሆነ ፤ ሕዝቡም ዕድለኛ ጥቅሙን ከጉዳት ለይቶ የማወቅ ኃይል ስላለው ፤ የንጉሠ ነገሥቱን ዕቅድ በመደገፍ ስለረዳ ፤ ጥቅሙ የራሱ ሆኖ አግኝቶታል ። ስለዚህ ሕዝቡም ከሌላው ነገድ የተለየ የመረዳዳት ኃይል ስላለው ሊመሰገን ይገባዋል ። እንዲህ ያለ መሪ ለሰጠን አምላክ ክብርና ምስጋና ይግባው ። የአምላክ ኃይሉ መታወቂያ ሁነው እየተገኙ የተጣለባቸውን አደራ በትክክል የፈጸሙ ንጉሠ ነገሥት በጣም ይመስገናሉ ። ስለዚህ እኛም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የሥጋዊና መንፈሳዊ ዕውቀትን እንድንገበይ ወርቃዊ ዕድል ስለሰጡን እያመሰገን በራሳችንም ፤ በቤተ ክርስቲያናችንም ስም ሆነን ለብራዊ ኢዮቤልዩ የሚሆን የኻያ አምስት ዓመት መንፈሳዊ የሥራ ፍሬዎችን በየመል ቸው በቅደም ተከተል ዘርዝረን እናቀርባለን ።



www.ethiopianorthodox.org

# አዲሱ የኢትዮጵያ ቤት ክርስቲያን አስተዳደር

አስተዳደር አዲስም ሆነ አሮጌ በመሠረቱ በጊዜው ያሉት ልዩ ልዩ የሆኑ ሥራዎች የሚጠቃለሉበት ለወደፊትም ሊፈጸሙ የሚገባቸው የሥራ ፕሮጀክቶችና ፕላኖች የሚጠኑበት በጠቅላላው ሠራተኞች ከሥራ ጋር የሚተዋወቁበትና ግንባር ቀደም እየሆኑ ሠርተው የሚያሠሩበት የማጋፈርና የማስተናበር ዘዴ ነው፤በዓለም ላይ የማንኛውም በመልካም አስተዳደር የማይሠራ መሥሪያ ቤት ሥራው ይደክማል ፤ አንካሳና ሽባም ይሆናል።ጊዜውንና የሚተዳደረውን ሠራተኛ ፍላጐት ተመልክተው በዚሁ ላይ የተመሠረተ ሕግ በማውጣት የሚመሩና የሚያስተዳድሩ የዕውቀት ሰዎች የሌሉበት መሥሪያ ቤት ንቡ ሔዶ ተሐዋስያን እንደሚፈነጩበት ባዶ ቀፎ ያለ ነው ፤

ስለአዲሱ የኢትዮጵያ ቤት ክርያን አስተዳደር ስንናገር ይህ ያሁኑ አስተዳደር ከጥንቱ በምን ይለያል ? የተመሠረተው ከመቼ ጀምሮ ነው ? በዚህስ አዲስ አስተዳደር ምን ምን ዓይነት ሥራዎች ተፈጽመዋል ? የሚሉ ጥያቄዎች ይገጥሙናል ።

## አዲሱ ደንብ የተፈቀደበት አስረጅ ፤

አዲሱ የኢትዮጵያ ቤት ክርስቲያን አስተዳደር የምንለው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በድል አድራጊነት ከስደት ከተመለሱ ወዲህ ያለውን ነው ። እውነት ነው ከዚያም በፊት ራሱን ችሎ እንዲሠራ በግርማዊነታቸ መልካም ፈቃድ ተቋቁሞ ነበር ፤ ነገር ግን በዐዋጅ የጸናውና መልክ ያገኘው ነፃነት ከተመለሰ ወዲህ ነው ። መጋቢት ፩ ቀን ፲፱፻፴፬ ዓ/ም አዲስ ደንብ ተሰጥቷል ። በዚህም ደንብ ከቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ መሬት የሚገኘው ግብሩም አሥራቱም አብሮ ተፈቅዷል ። ይህንንም በሚከተለው ደብዳቤ አማካይነት ለመረዳት እንችላለን ።

ጥቅምት ፳፬ ቀን ፲፱፻፴፭ ዓ/ም ቁጥር ፩፻፲፮

ለክቡር የገንዘብ ሚኒስቴር

አዲስ አበባ ፤

ከዚህ ቀደም ለቤተ ክርስቲያን እርዳታ ከቤተ መንግሥት ግምጃ ቤት ሲሰጥ የነበረው ስላቀባበሉ ያለበትን ችግር ግርማዊነታቸው ተመልክተው ለቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ቀለብና ደመወዝ ፤ ለቤተ ክርስቲያን ፤ ተማሪ ቤትና ሆስፒታል ለደኅ መርጃ እንዲሆን ለቤተ ክርስቲያን ማደሪያ የተፈቀደው ግብሩም አሥራቱም በሙሉ እየተሰበሰበ መንፈሳዊ ጉባኤ እያቀረበች በግርማዊነታቸው ፈቃድ በሚሾሙት በቤተ ክህነት ሹሞች እጅ መንግሥት በተለይ ባቋቋመው ግምጃ ቤት እየተቀመጠ ይወጣል ። ይህንኑም የተፈቀደውን ለገደዳማትና ለአድባራቱ ብፁዕ እጭጌ ገብረ ጊዮርጊስ በማኅተማቸው እንዲያስተላልፉ ተደርጎ ዋናው በታላቁ መዝገብ ላይ ተጽፎ ታትሞ ተቀምጦል ። በዚሁ ትእዛዝ እንደተጻፈው እንዲፈጸም በበኩልዎ የሚደረገውን አፋጥነው እንዲያከናውኑ መታዘዝዎን በማክበር አስታውቃለሁ ።

ከማክበር ሰላምታ ጋር

ማኅተም የጽሕፈት ሚኒስቴር

ፊርማ ጸ/ ት/ ወልደ ጊዮርጊስ

በዚህም መሠረት ከተፈቀደው ግብርና አሥራት የሚገኘው ገቢ ለሠራተኛ ፤ ለካህናት ፤ ለመምህራን ፤ ለሰባክያን ፤ ለሥራ ማስኬጃያና እነዚንም ለመሳሰሉ ተግባሮች የሚውል ነው ።

እንግዲህ በአዲሱ አስተዳደር መሠረት ቤተ ክህነት ተቋቁሞ በየሀገረ ስብከቶችም ቅርንጫፎችን መሥርቶ አዲሱን ሥራ ከጀመረ እነሆ ኻያ አምስት ዓመት መሆኑ ነው ። ለቤተ ክርስቲያን ይህ አዲስ ደንብ የተሰጠው ጥንት በመንግሥት በኩል ይፈጸም የነበረውን ቤተ ክርስቲያንን የሚመለከተውን ጉዳይ ሁሉ ተረክባ ራሷን በራሷ እንድትመራ ታስቦ ነው ። ጥንታዊው የቤተ ክርስ



www.ethiopianorthodox.org

ያን አስተዳደር መልክ የለውም ነበር ማለት እን
ደዛሬው ራሱን የቻለ መሥሪያ ቤት አልነበረም ፤
ከዚህም የተነሣ ጥንት ቤተ ክርስቲያናችን ከውጭ
አብያተ ክርስቲያናት ጋር ይልቁንም ከእስክንድ
ርያ ቤተ ክርስቲያን ጋር የነበራትን ሁኔታ ዘርዝ
ረው የሚያስረዱት ዶክሜንቶች በሙሉ ሊገኙ አል
ቻሉም ። ፪ኛም የጥንት ነገሥታት ለቤተ ክርስቲ
ያችን በየጊዜው የሰጧትን የሀብት ልክ የሚያሳ
ዩት ማስረጃዎች መሥሪያ ቤት ባለመኖሩ ምንም
እንኳን በየወንጌሉ ላይ እየተጻፉ ቢገኙም ሁሉም
ተመዝግበው አልተገኙም ። ከላይ እንደጠቀስነው
የቤተ ክህነት መሥሪያ ቤት መልክ ይዞ የተቋቋ
መው ግርማዊነታቸው በድል አድራጊነት ከተመ
ለሱ ወዲህ ነው ። ስለዘመናዊ ትምህርት ቤቶች
መከፈትና ስለሐዋርያዊ ተግባር መስፋፋት ማሰብ
የተጀመረው አሁን ነው ፤ ጥንት ግን በየጊዜው
ከእስክንድርያ ወደ ሀገራችን ይመጡ የነበሩት ጳጳ
ሳት ለብሔራዊቱ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን
ፍላጐትና ችግር እንግዳ ይሆኑ ስለነበርና ይልቁ
ንም የጸሎትንና የቡራኬን እንዲሁም ተግባረ ክህ
ነትን ማከናወን በይበልጥ ይፈቅዱ ስለነበር የአድ
ሚኒስትራስዮኑ ክፍል ተወዝፎ ኖሯል ። በዚህም
ምክንያት ቤተ ክርስቲያናችን ከጥንቱ አስተዳደር
አያሌዎች የሥራ ውዝፎችን ወርሳለች ለማለት
ይቻላል።ዛሬም ወደፊት አልሰዳት ያለ አንዱ እንቅፋት
ይኸው ውዝፍ ገፋጋፊነት ነው ብንል አንሳሳትም
ከዚህ ላይ የምንወቅሰው ከውጭ አገር ይመጡ
የነበሩትንም ሆነ የሀገራችንን የቤተ ክርስቲያን
አባቶች ብቻ ሳይሆን ጊዜውንም ጭምር ነው ።
ዘመኑ የጥናት ዘመን ነበር ። ከዚህም የተነሣ ሊቃ
ውንቱ የዕድሚያቸውን አጋማሽ ይፈጁት የነ
ረው « ድጓ በጉንጩ » የመባል ቅጽል እየተሰጣ
ቸው ለዜማ ለከበሮ አመታትና ለጸናጽል አጸና
ጸል እንዲሁም « የጎንደር ላይ ቤት ታች ቤት»
በማለት ስለነበር በጊዜው ይጮኽ የነበረ የማኅበ
ራዊ ኑሮ ሥራ ማለት የስብከተ ወንጌል ፤ የበጎ
አድራጎት ፤ የክርስቲያናዊ ኑሮ ማጠንከርና የማ
ጽናት ተግባር ተወዝፎ ኖሯል ።

ቤተ ክርስቲያናችን አዲሱ የአስተዳደር ደንብ
ከተሰጣት ወዲህ ቤተ ክህነትን አቋቁማ እንዲሁም
ብዙ የሥራ ክፍሎችን ከፍታ ትሠራለች ይህንንም
ሐላፊነቷን ለመወጣት ሥራዋን በሦስት ዐበይት
ክፍሎች ከፍላለች ። እነርሱም ፤

፩ኛ/ ቅዱስ ሲኖዶስ ሲሆን እርሱም ሃይማ
ኖት ነክ ለሆኑና ለከፍተኛ መንፈሳዊ ነገሮች ውሳኔ
ይሰጣል ። የሲኖዶሱም አባሎች ሊቃነ ጳጳሳት ጳጳሳ
ትና ኤጲስ ቆጶሳት ሲሆኑ ሊቀ መንበሩ ፓትርያሪኩ
ናቸው ።

፪ኛ/ የአስተዳደሩን ጠቅላላ ባጀት የሚወስ
ነው ቦርድ ነው ። ቦርዱ በንጉሠ ነገሥቱ ይሾማል
እርሱም ባጀትንና የመሳሰሉትንም ከፍተኛ ጉዳ
ዮች ይወስናል ።

፫ኛ/ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤቱ የጠቅላላው የአ
ድሚኒስትራሲዮን የበላይ ኀላፊ ነው ። እርሱም
ማንኛውንም ሲኖዶስ የወሰነውንና ቦርዱ የፈቀደ
ውን በሥራ ላይ የማዋል መብት አለው ። የየክፍ
ሉን ሹማምንት የሚደለድል ሥራ አስኪያጁ ነው ።
ሥራ አስኪያጁም በንጉሠ ነገሥቱ ይሾማል ።
ይሁን እንጂ በእንዲህ ያለ አስተዳደር አቋም እን
ድትመራ ንጉሠ ነገሥቱ በአርቆ ተመልካችነታ
ቸው መብት ቢሰጡም ቅሉ ቢደግፉዋትም እርሷ
ወደፊት ልትሔድ አልቻለችም ። ቤተ ክርስቲያን
ልትሠራው የሚገባት የሥራ ብዛት ከሠራችው ጋር
ሲመዛዘን በጣም ያነሰ ሆኖ ይታያል ። እውነት ነው
ጥንታዊትና ብዙ አባሎች ያሏት ብሔራዊት ቤተ
ክርስቲያን እንደመሆኗ መጠን ችግሯም ብዙ ነው ።
ከዚህም የተነሣ እንጋጠው በተስፋ የሚጠባበቁት
የምእመናኗን ፍላጐት ለማርካት አልቻለችም ። ከች
ግሮቹ ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል ፤

፩ኛ/ የተሰጠውን አዲስ የአስተዳደር ደንብና
ሀብት በሥራ ላይ ለማዋል ሥራን ከሠራተኛ ጋር
በማገናኘት ግንባር ቀደም ሆነው የሚሠሩ ለዘመ
ናዊ ችግር ዘመናዊ ፍች የሚፈጥሩ በዘመናዊ ትም
ህርት የሠለጠኑ በውሶጧ ያሉት ሰዎች በጣም ያነሱ
በመሆናቸው ።

፪ኛ/ የሚፈለገውን ያህል ዘመናዊያን ትምህ
ርት ቤቶች ለመክፈትና የስብከተ ወንጌል ድርጅቶች
በብዛት ለማቋቋም የገንዘብ ኃይል ስለሚያጥራትና
ያለውንም አስፋፍቶ ደንበኛ የገቢ ምንጭ እንዲ



www.ethiopianorthodox.org

ጥራት የሚያደርግ የጠነከረ የልማት ክፍል ባለ መኖሩ ።

፫ኛ/ ከጥንቱ አስተዳደር የተወረሰ የሥራ ውዝፍ በጣም የበዛ በመሆኑ እርሱን በመገፍገፍ ፤

፬ኛ/ ከምእመናን ዘንድ ያለው ድጋፍና የሥራ ተካፋይነት በጣም ያነሰ በመሆኑ ፤

፭ኛ/ የሥራ ኃላፊዎቹ በወጣው ደንብ መሠረት ባለመሥራታቸው (የሥራ ቻናል ባለመጠበቁ) ነው ማንኛውም ሰው እንደሚያውቀው ምንም እንኳን ግርማዊነታቸው ይህን ያህል ድካም አደረጉ ፤ መልክ ባለው አቅድ ተቋቁሞ እንዲሠራ ደንብ ሰጡ ፤ ብንልም እስካሁን በታየው ቤተ ክህነት ከጥንቱ የተሻለ ሁኔታ አላሳየም በጠቅላላው የአሁኑ የቤተ ክርስቲያናችን የአስተዳደር ሁኔታ ከሕዝብ ዘንድ ብዙ ጥያቄዎችን አስከትሏል ።

ስለዚህ ለማስታወስ የምንፈልገው ቤተ ክህነትና በውስጡ ያሉት የሥራ ክፍሎች ያለንበት ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን ብዙ ዓይነት የሥራ እርምጃ ስለሚጠይቅ ጠንክረው ካልሠሩና የሚፈለግባቸውንም መንፈሳዊ ተግባር በቅልጥፍና ካላከናወኑ በቤተ ክርስቲያን ላይ አትሠራም እየተባለ ከሕዝብ ዘንድ ከሚወረወርባት የወቀሳ ፍላጻ ሊያድኗት አይችሉም ። ቤተ ክርስቲያን ባሁኑ ጊዜ የቀለጠፈ በዘመናዊ አቅድ የሚመራ አስተዳደር ያስፈልጋታል ። ይህም እንዲሆን ከተፈለገ ዘመናውያን ወጣቶች በብዛት ገብተው እንዲሠሩ ያሻል ። ይሁን እንጂ የሚገቡት ወጣቶች ሥልጣን ካልተሰጣቸው የሰዎች መግባት ብቻ ለውጥ ሊያመጣ አይችልም ። ቤተ ክርስቲያናችን አሁን ያላት የሥራ አቅድ ካልተሻሻለና አሁንም የያዘችው ባለህበት - - - - - የሚል እርምጃ ከቀጠለ ከሚቀርባት የሚርቃት እየበዛ መሔዱ አይጠረጠርም ፤ ይህም እንዳይሆን የብዙዎችን መንፈሳውያን ወጣቶች መሥዋዕትነት ይጠይቃል ። መሥዋዕትነትም የግል ጥቅም አሳዳጅ አለመሆንን ስለራስ ክብር በቤተ ክርስቲያን ስም አለመገደድን እኔነትን ክዶ ለቤተ ክርስቲያን ብቻ ማሰብን ያስከትላል ።

አእምሮ ወንድም አገኘሁ



www.ethiopianorthodox.org

# ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት

ይህች አጭር ጽሑፍ በዘመናት መካከል የኢትዮጵያን ቤት ክርስቲያን ታሪክ አኮስሶ ዓላማዋን ደምስሶ በዚህም ምክንያት የክርስቲያን አገር ብቻ ልትሆን ትችል የነበረችውን ኢትዮጵያን የኢአማንያ ንም መኖሪያ እንድትሆን ያደረጋት የጳጳሳት ማነስ በአጭሩ ለመግለጥ የተዘጋጀች ጽሑፍ ናት ፤ የክርስትና ሃይማኖት ዓላማው የተቀደሰ ሲሆን የክርስትና መሪዎች ብዙ ጊዜ ቅዱሳን ሁነው አልተገኙም፤ ለምሳሌ ጽርአውያን በሙሉ የምሥራቁ ክፍል ጵጵስና ለግሪካውያን ብቻ ነው የሚገባ በማለት የጵጵስናን ማዕርግ ለግሪኮች ብቻ አድርገውት መኖራቸው የታወቀ ነው ።

የመስኮብ ፤ የዩጐዝላቪያ ፤ የቡልጋሪያ ፤ የአልባኒያ ፤ የሩማኒያ እንዲሁም በቅርብ ምሥራቅ የሚገኙት በግሪክ መንግሥት ውስጥ አግባብ ያላቸው የፓትሪያርክ መንበሮች ለምሳሌ ያህል እስክንድርያ ፤ አንጾኪያ ፤ ኢየሩሳሌም ምእመናኑ ዓረቦች ሲሆኑ ከመካከላቸው መርጠው ሊቃነ ጳጳሳትና ፓትሪያርክ ለመሾም መብት የላቸውም ፤ እስከ አሁን ድረስ በነዚህ ወንበሮች የሚቀመጠው የግሪክ ተወላጅነት ያለው ሰው ብቻ ነው ። በቅርብ ጊዜ ውስጥ የአንጾኪያው ብቻ የዓረብ ተወላጅ ሁኗል ። የቀሩት ግን መንግሥት ያላቸው አብያተ ክርስያናት ቀስ በቀስ የመስኮቡ በ፲፰ኛው መቶ ዘመን ነፃነቱን ሲያገኝ የቀሩት በ፲፱ኛው መቶ ዘመን እየተከራከሩ አንዱ ከአንዱ በኋላ የግሪኩን ተወላጅ እያጠፉ የራሳቸውን ተወላጅ ሹመዋል። ይህ ለክርስቲያን ሃይማኖት ቀላል ልምድ አይደለም ። በሮማም በኩል ለጥቂት ጊዜ መልከት ብናደርግ የሰዎች ዝርዝር አብዛኛው ሮማዊ ሆኖ መገኘቱ የታወቀ ነው ። አሁን የአለንበት ክፍለ ዘመን በጣም ተላፋፊ በመሆኑ እስያውያንና አፍሪካውያን ወደ ጵጵስና ደረጃ ደርሰው ይታያሉ ። ግን ወደ ታሪክ መለስ ያልን እንደሆነ በጣም አጭር ሆኖ እናገኘዋለን ።

ይህ መንፈስ በኛም ቤት ክርስቲያን ላይ ወድቆ አገራችንን ሲያስቸግራት እንደኖረ ይታወቃል ፤ የግብፅ ቤት ክርስቲያን የቤት ክርስቲያናችን ሞግዚት በነበረችበት ጊዜ በትምህርት ፤ በስብከት ወንጌል ማስፋፋትና በአድሚኒስትራሲዮን በኩል የተፈጸሙ ነገሮች የሉም ፤ ከዚህም የተነሣ ፩ሺህ፮፻ ዘመናት በከንቱ አልፈዋል ፤ ለማለት ይቻላል ። የኢትዮጵያ ሊቃውንት ከፍተኛ ደረጃ ሳያገኙ የሚማሩበት ትምህርት ቤት ሳይሠራላቸው በየደጀ ሰላሙና በየመቃብር ቤቱ ሲንከራተቱ ኑረው አልፈዋል ። ወንጌል የሚስፋፋበትን መንገድ ያሳያቸው ባለማግኘታቸው ጊዜያቸው በከንቱ አልፎ ብዙ ጊዜ የክርስቲያኖች ቁጥር አንሶ ኑሯል ። የቤት ክርስቲያናችንም ሀብት እንደ ዓባይ ውኃ ወደ ግብፅ ሲፈስ መኖሩ ለማንም ሥውር አይደለም ።

ይህን ቀንበር ሰብሮ ለኢትዮጵያ ቤት ክርስቲያን ነፃነትን ለማጐናጸፍ ሰፋ ያለ ትግል በየ ጊዜው ተደርጓል ። እግዚአብሔር በፈቀደው ጊዜ በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት እነሆ የተፈለገው መብት ለቤተ ክርስቲያናችን ተሰጥቶ ማየት ቀላል ነገር አይደለም ከዚህ ቀጥለን በየጊዜው የተደረገውን ትግል በመጠኑ ለአንባብያን ለመግለጥ እንሞክራለን ።

፩ኛ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት አስቀድሞ ጵጵስናን ስለማግኘት የተደረገው ተጋድሎ ፤

ፍትሐ ነገሥት በተባለው በሕግ መጽሐፍ ውስጥ በመንፈሳዊው ክፍል ስለጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት በ ሚናገርበት ጊዜ የኢትዮጵያን ቤት ክርስቲያን አንሥቶ «ወሰብአ ኢትዮጵያሰ ኢይሚሙ ሊቀ እማእምራኒሆሙ አላ ይሚም ሎሙ ሊቀ»



www.ethiopianorthodox.org

የግብፁ ሊቀ ጳጳሳት ይሾምላቸው እንጂ ኢትዮ
ጵያውያን ከሊቃውንታቸው መካከል ሊቀ ጳጳስ
አያምረጡ ተብሎ ተጽፎ የ ሚገኘው ነገር በጣም
ከባድ ቀንበር ሆኖባት ኑሯል ። ልትለውጠው አል
ቻለችም ፤ የኒቅያ ጉባኤ ትእዛዝ ነው የዓለም ጉባኤ
የወሰነውን አንዲት ቤተ ክርስቲያን ልትለውጠው
መብት የላትም የሚል ስሜት ነበር ፤ ደግሞም
በዚያን ጊዜ ሃይማኖትና ሥርዓት በእኩልነት
ያረጅ ነበሩ ።

ይህንም ዳግም ለማሻሻል መሰብሰብ ያስ
ፈልግ ነበር ፤ ግን በዘመናት መካከል የቤተ ክርስ
ቲያኗ መሪ ግብፃዊ በመሆኑ እንዲህ ያለውን
ጉዳይ ለማጥናት ሊቃውንት ለመሰብሰብ ፈጽሞ
አያፈልጉም ነበር ። ተሰብስበውም የተገኙ ሊቃው
ንት የተሰማባቸው እንደሆነ ተገዝተው ከምእመ
ናን ይለዩ ስለነበር ነገሩን እያወቁት ፤ እየተረዱት
ዝም ማለት ነበረባቸው ፤ አይጦች በድመት አንገት
ቃጭል አሥረው ቃጭሉን እያዳመጡ ሲመጣ
ለመሸሽ እንዲመቻቸው ጥሩ ምክር ከመከሩ
በኋላ አንዱ ተነሥቶ ምክሩ ጥሩ ነው በጣም ውብ
ነው ፤ ነገር ግን ቃጭሉን ከድመቱ አንገት የሚያ
ሥረው የመጀመሪያው ጉበዝ አይጥ ማነው እኔ
በበኩሌ አልፈልግም አልችልም የ ሚል ድምፅ
በአሰማ ጊዜ ሁሉም ተመልሰው በየጉድጓዳቸው
ገቡ ተብሎ እንደ ሚነገረው የኢትዮጵያ ሊቃው
ንት ይህን አንቀጽ አንብበው ሲተረጉሙ ይህ
እንኳ የግብጻውያን ተንኮል ይመስላል ብለውት
ያልሩ ነበር ። የግብጻውያን ተንኮል ነው ብሎ እን
ኳን ለመናገር የደፈረ የለም ፤ በይመስላል አልፈው
ታል ፤ ምሥጢሩ ጠፍቷቸው አይደለም፤ ግን ነገሩ
የከረረ እንደሆነ ከጳጳሱ የሚመጣውን ቅጣት
በመፍራት መሆኑ ግልጽ ነው ። ሊቃውንቱ በአ
ጭሩ ይህ የግብጻውያን ተንኮል ይመስላል ከማ
ለት በቀር ሌላ ዐረፍተ ነገር ለመጨመር አልፈለ
ጉም ፤ ነገሥታቱስ ምን እርምጃ ወስደው ነበር ?
በጊዜው የተነሡት ነገሥታት በነገሩ ሳያስቡበት
አልቀሩም ፤ ግን በግልጥ ጥያቄውን ያቀረቡት ነገ
ሥታት ለጊዜው የሚከተሉት ናቸው ።

፩ኛ/ ክቡር ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂር
ቆስ «የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፓትሪያርክ» በሚ
ለው መጽሐፋቸው እንደገለጡት በ፲፭ኛው መቶ
ዘመን ላይ የነበረው ሐርቤ የተባለው የነገደ
ዛጔው ንጉሥ የሀገሪቱን ስፋት ተመልክቶ ኢትዮ
ጵያውያን ጳጳሳት እንዲሾሙለት ጠይቆ ነበር ፤
ቢሆንም ጥያቄውን የግብጹ ፓትሪያርክ ሳይቀ
በለው በመቅረቱ አሳቡ ፍሬ ሳያገኝ ቀርቷል ።
ከዚህም በኋላ በአፄ ቴዎድሮስ ዘመን ነገሩ በጣም
የከረረ መልክ ወስዶ ነበር ። በአፄ ቴዎድሮስ
ዘመነ መንግሥት የነበረው ጳጳስ ሰላማ ይባል
ነበር። የግብጹም ፓትሪያርክ የቤተ ክርስቲያናችንን
ገንዘብ ለመሰብሰብ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ሳለ
በቱርክና በኢትዮጵያ መካከል በነበረው ፖለቲካ
ነክ በሆነ ነገር እየገባ ስለአስቸገራቸው አንተ የክ
ርስቲያኖች መሪ ስትሆን እኔን ክርስቲያኑን ንጉሥ
መርዳት ነበረብህ እንጂ ከዚህ ውስጥ ምን አገ
ባህ ብለው ተቆጥተው የኢትዮጵያውንም የግብጹ
ንም ሊቃነ ጳጳሳት አሥረዋቸው እንደነበረ አቶ
ተክለ ጻድቅ መኩሪያ በጻፉት የአፄ ቴዎድሮስ
ታሪክ ውስጥ ይገኛል ፤ እንዲህ ያለው ውርደት
በግብጻውያን ላይ ሲወርድ የመጀመሪያ ጊዜ ነው።
አፄ ቴዎድሮስ ለቤተ መንግሥትና ለቤተ ክህ
ነቱ ሕግ ለማውጣት አስበው እንደነበር ታውቋል ፤
ለቤተ ክህነቱ ከአሰቡት ውስጥ አንደኛው የግብ
ፅና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ግንኙነት
እንደነበረ ታውቋል ፤ ጳጳሳቱን አሥረው ዝም አላ
ሉም ፤ ሊቃውንቱን ጠርተው በነገሩ እንዲመክሩ
በት አድርገዋል ። የዚህን ጉባኤ ውሳኔ ለማግኘት
በጣም መድከም ሳያስፈልግ አይቀርም ። ግን ጉባኤ
መደረጉንና የጉባኤውም አሳብ ምን እንደነበረ
ከዚህ በሚከተለው ቅኔ ለመረዳት ይቻላል ።

ቅኔውም - - « ተገብረ ዘኢተገብረ ክልኤቱ
አኀው ኀበ ሀለው እስመ ለሃይማኖት ጽዮን ማኅ
ደሮ ከመ ትኩኖ ኅረያ ፤ ቴዎድሮስ ለተግባረ
ነፍሱ ዘኮነ ኬንያ ፤ እመከመዝሰ ኮነት አርአያ ዳግ
ሚት ኒቅያ ፤ ምንት ይእቲ ቁስጥንጥንያ ፤ ቁስጥን
ጥንያሰ ኮነት ኢትዮጵያ ፤ ወኒቅያ ደብረ ታቦር ነያ »
የሚል ነው ፤ ትርጓሜውም የሚከተለው ነው ።
ሁለት ወንድማማቾች በአሉበት ያልተሠራ ተሠራ፤
ያልተደረገ ተደረገ ፤ ለነፍሱ ሥራ ብልሀተኛ የሆ



www.ethiopianorthodox.org

ነው ቴዎድሮስ ጽዮን ሃይማኖት ማደርያው እንድ ትሆን መርጧልና ካለ በኋላ የሁለተኛዋ ኒቅያ መል ክ ወይም ምሳሌ እንዲህ ከሆነ ቁስጥንጥንያ ምን ድንናትን ብሎ ቁስጥንጥንያስ ኢትዮጵያ ናት ፤ ኒቅ ያም ደብረ ታቦር ናት በማለት ባለ ቅኔው ቅኔ ውን ዘግቷል ።

ይህ ቅኔ በደብረ ታቦር የሊቃውንት ጉባኤ መደረጉን ከማስረዳቱም በላይ ጉባኤውንም በኒቅ ያና በቁስጥንጥንያ ከተደረገው ጉባኤ በማወዳደር የራሱን አክብሯል ፤ በቅኔውም መጀመሪያ ሁለቱ ጳጳሳት ባሉበት ከዚህ በፊት ያልተደረገ ነገር መደረጉን ተናግሯል ። የጉባኤውም ምክንያት አፄ ቴዎድሮስ መሆናቸውን ገልጧል ።

ይህ ቀላል ትግል አልነበረም ፤ ቢሆንም ብዙ ዎች አማካሪዎች በተለይም እቴጌ ምንትዋብ እን ዲያውም ጠላቶችዎ አበደ እያሉ ያስወሩብዎ ታል ፤ ይህም ታላቅ ምክንያት ይሆናቸዋል ስለአሏ ቸው ጳጳሳቱን መፍታታቸው ይነገራል ።

አፄ ቴዎድሮስ መሬት የመንግሥት ነው ለአ ንድ ቤተ ክርስቲያንም አምስት ሰዎች ይበቃሉ የሚል አሳባቸው ይነገራል ፤ ይህንም ዓላማቸውን የሚያስረዳን ከዚህ ቀጥሎ ያለው ያልተጻፈ አነጋ ገር ነው ፤ አንድ የተማረ ነገር ዐዋቂ ሊቅ ባጠገ ባቸው ይኖር ነበር ይባላል ። እነዚህን ሁለቱን የአፄ ቴዎድሮስን አሳቦች በጣም ያውቅ ነበር ፤ ሰውዬው ተላፋፊ ነው ፤ አፄ ቴዎድሮስም ምንም ቢሆን እንዲህ ያለውን ሰው ማስደሰት ጥሩ ነገር መስሎ ስለታያቸው መቶ ብር ሰጥተው አለቃ ! ወስደህ እንዳትቀብረው እንድትሠራበት ነው የሰ ጠሁህ ቢሉት ጃንሆይ «ብቀብረው መሬት የመ ንግሥት ነው» ብለዋል ማን ይወስደዋል ? ወደ ባለቤቱ ተመለሰ ማለት አይደለምን ? ብሎ ቀለደባ ቸው ፤ ይህ ነገር ሆድ ሆዳቸውን ሲበላቸው ሳለ የደብረ ታቦር መድኃኔ ዓለምን ቤተ ክርስቲያን ሲያሠሩ ወደ አለቃ ዘወር ብለው አለቃ ይህ ቤተ ክርስቲያን ጠበበ ይሆን ? ብለው ቢጠይቁት ለአ ምስት ሰዎች ምን ይጠባል ይበቃል ብሎ የቀ ልድ መልስ ቢመልስ በግርፋት ቀጡት ይባላል ። ይህ አነጋገር በመሠረቱ ስለቤተ ክርስቲያን የነበራቸውን አስተያየት ይገልጣል ፤ ቤተ ክህ ነትን በባጀት መልክ በደመወዝ ለማሳደር ሲፈ ልግ የመጀመሪያው ሥራ የሰዎችን ቁጥር መቀነስ መሆኑ ለዛሬም ሰዎች ግልጥ ሆኖ መታየቱ ይታወ ቃል ፤ ይሁን እንጂ የአፄ ቴዎድሮስ አሳብ ምንም የበሰለ ቢሆን ፍሬ ሳያስገኝ ቀርቷል ።

ሁለተኛው ለዚህ ጥያቄ በጣም አሰበውበት የነበሩት ንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ አራተኛ ናቸው። አፄ ዮሐንስ በአፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግ ሥት ከግብጽ ጳጳስ ማምጣት ባለመቻሉ ምክን ያት የኢትዮጵያ ሊቃውንት ተሰብስበው አቡነ ተክለ ሃይማኖትን መርጠው መሾማቸውን በማስ ታወስ አንድ ሊቀ ጳጳስና ብዙ የኢትዮጵያ ኤጲስ ቆጶሳት እንዲሾሙላቸው የዚያን ጊዜ የነበሩትን የእስክንድርያውን ፓትሪያርክ አቡነ ቄርሎስ ፭ኛን ጠየቋቸው በዚህ ጊዜ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ኢትዮጵያውያን ኤጲስ ቆጶሳትን ለመሾም ባለመፍ ቀዷ ነገሩን በማሻሻል አንድ ሊቀ ጳጳስና ሦስት ግብጻውያን ጳጳሳት እንዲሾሙ በመወሰኗ አቡነ ጴጥሮስ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ሲሆኑ አቡነ ማቴ ዎስ ለሸዋ አቡነ ሉቃስ ለጐጃም ቡነ ማርቆስ ለበጌምድር ኤጲስ ቆጶሳት ሁነው በካይሮ በ፲፰፻ ፸፫ ዓ. ም. ተሹመው በ፲፰፻፸፬ ዓ. ም. ወደ ኢትዮ ጵያ መጡ ። በዚህ ጊዜ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን የሠራችው ታክቲክ በከፊል የንጉሠ ነገሥቱን ጥያቄ ስለአረካ ነገሩ በረድ ብሎ ቆየ ፤ አፄ ዮሐንስ ለሃይማ ኖታቸው ከፍ ያለ ቅንዓት ስለነበራቸው በአ ንድ ጳጳስ ኢትዮጵያን ለመስበክ ስለማይቻል በርከት ያሉ ጳጳሳት ይሾሙ የሚል ጥያቄ አቅር በው ነበር ፤ በመሠረቱ በአፄ ዮሐንስ አስተያየት ሊቀ ጳጳሱ ግብጻዊ ሲሆን የቀሩት ኢትዮጵያው ያን መሆን አለባቸው ብለው መጠየቃቸው ቢታ ወቅም የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ስትፈራው የነበረ ችው ነገር በመነሣቱ ደንግጣ የራሷን ልጆች መርጣ ሹማለች ፤ ቢሆንም እነዚህ ጳጳሳት የሀገሩን ባሕል የማያውቁ የማስተማር ዘዴ ያላጡኑ በመ ሆናቸው ግብር ተጨመረ እንጂ የስብከተ ወንጌል መስፋፋት ጉዳይ ምንም አልተሻሻለም ፤ የኢት ዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንደገና ዕውር አሞራ መቀ



www.ethiopianorthodox.org

ለብፁን ቀጠለች ፤ አብዛኞች ጳጳሳት ለብዙ ጊዜ አልቆዩም ። የሸዋ ጳጳስ የነበሩት አቡነ ማቴዎስ በ፲፰፻፸፫ ዓ ም አፄ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ሲሆኑ ዕድለኛ ጳጳስ በመባል የሊቀ ጵጵስናውን ማዕርግ ወሰዱ ፤ አቡነ ጴጥሮስ ግን የትግሬ ሀገረ ስብከት ተሰጥቷቸው ሲኖሩ በ፲፱፻፲ ዓ/ ም/ አርፈው እቲሳ ላይ ተቀብረዋል ። አቡነ ጴጥሮስ በሕይወታቸው ያልተደሰቱ ሰው ነበሩ ፤ አቡነ ማቴዎስ ከዚያ በፊት ለጳጳሳት ያልተሰጠውን ዳኝነት ጨምረው ይዘው ለ፵ ዓመታት ያህል የኢትዮጵያን ቤተ ክር ስቲያን በኃይል ሲገዙ ኑረው በ፲፱፻፲፰ ዓ/ ም/ አርፈው በአዲስ አበባ መካነ ሥላሴ ተቀበሩ ፤ በኋላ ግን አስከሬናቸው ወደ መታሰቢያ ቤት በአታ ተዛውሮ ከነገሥታቱ ዐፅም ጋር ይገኛል ፤ አቡነ ማቴዎስ የኢትዮጵያን ወርቅ በብዛት ወደ ግብጽ የጫኑ ፤ ሊቀ ጳጳስ ከመሆናቸውም በላይ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያን ገዳም ለግብጻውያን አሳ ልፈው የሰጡብን እርሳቸው ናቸው ፤ በቀላሉ አሳ ልፈው የሰጡትን ገዳም የኢትዮጵያ ቤተ ክር ስቲያንና የኢትዮጵያ መንግሥት በብዙ ድካም ሊመልሱት አልቻሉም ። እቴጌ ጣይቱ በነ ቀኝአዝ ማች መሸሻ ወርቄ አማካይነት ነገሩን ተረድተ ው ምነው አባታችን እንዲህ አደረጉ? አሁንም የገዳሙን ቦታ ማስመለስ አለብዎት እያሉ በየጊ ዜው ያስቸግራቸው ስለነበር እቴጌ ጣይቱን አንግ ሡኝ እያለች አስቸገረችኝ በማለት ከመኳንንቱ ጋር አጋጭተዋቸው ነበር ይባላል ።

## ፪ኛ ክፍል ፤

በ፲፱፻፲፰ ዓ/ ም/ አቡነ ማቴዎስ ሲያርፉ የግብጽ ቀንበር በጣም ከፍ ያለ ምልክት በኢት ዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ትቶ ነበር ። አልፈው አልፈው ከሊቃውንቱም ከመኳንንቱም መካከል ይህ የግብጽ ቀንበር የሚወድቅበትን ዘዴ የሚ ያስቡ አልጠፉም፤ እንደ አጋጣሚ ሆኖ በዚህ ወራት ማስተዋልን የተመላው የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥልጣን በኢትዮጵያ ዙፋን ላይ የን ጋት ጮራውን ፈንጠቅ አድርጎበት ነበር ። ንግሥት ዘውዲቱ በዙፋናቸው ላይ ነበሩ ። ግን የእርሳ ቸው አስተያየት ይህን ያህል ጠለቅ ያለ አልነረበ ረም ፤ ምናልባት የግብጹ ጳጳስ የቀረ እንደሆነ እግ ዚአብሔር ዝናም የከለከለ እንደሆነ ሕዝቤ በረ ኃብ ያልቅብኝ ይሆን ? የሚለው ሐሳብ ፈጽሞ የጠ ፉ አይመስልም ፤ ከኢትዮጵያውያንም መካከል እን ዲህ ያለውን የግብጽ ድጋፍ የሚሰጡ ሰዎች ምን ጊዜም አልጠፉም፤ አንድ ቀን ጧት የዚያን ጊዜው አልጋ ወራሽ የአሁኑ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ብርዐቸውን አንሥተው በዚያን ጊዜ ለነበሩት ለአቡነ ቄርሎስ አምስተኛ ኢትዮጵያው ያን ጳጳሳት ለኢትዮጵያ የሚያስፈልጉ መሆናቸ ውን ጻፉላቸው ፤ ቄርሎስ አምስተኛ ነገሩን በማጥ ናት ላይ ሳሉ በ፲፱፻፲፱ ዓ/ ም/ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ ፤ እኒህ ፓትሪያርክ ከአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት አንሥቶ እስከ ንግሥት ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት መጨረሻ ግድም ድ ረስ ለ፵፪ ዓመታት ያህል በግብጽ መንበር የቆዩ ስለነበሩ የኢትዮጵያ ነገሥታተ ምኞት ምን እንደ ነበረ ያውቁ ነበር ፤ በኢትዮጵያም ቤተ መን ግሥት የታወቁ ነበሩ ፤ ይህ ማለት አፄ ዮሐንስ ለጠየቁት ጥያቄ በኢትዮጵያውያን ፈንታ ግብጻ ውያንን የሾሙ ፓትሪያርክ እርሳቸው ነበሩ ማለት ነው ። ይሁን እንጂ እንደ ትልቅ ወዳጅ ሞታቸው በአዲስ አበባ በተሰማ ጊዜ ፯ ጊዜ መድፍ ተተኩ ሶላቸዋል ፤ ቤተ ክርስቲያንም ከፍ ያለ ሥርዓት ጸሎት አድርሳለች ፤ ስለ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት የተጠየቀውም ጥያቄ ሌላ ባለሥልጣን በመንበሩ እስኪተካ መቆየት ግድ ሆነበት ።

## የመጀመሪያዎች የኢትዮጵያ ጳጳሳት ፤

አቡነ ዮሐንስ ፲፱ተኛ በ፲፱፻፳፩ ዓ ም የግብጽ ፓትሪያርክ ሁነው ተሾሙ ፤ ከዚህ በኋላ የግብጽ ሲኖዶስ በኃይል ከመከረ በኋላ አንድ ግብጻዊ ሊቀ ጳጳስ አምስት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት እንዲሾሙ ፈቅዶ አባ ቄርሎስን ከገዳመ ቁስቋም መነኩሳት መካከል ለሊቀ ጵጵስናው ማዕረግ የመረጠ መሆ ኑን ለኢትዮጵያ መንግሥት አስታውቋ ። በዚህም ውሳኔ የኢትዮጵያ መንግሥት በመስማማቱ ግንቦት ፳፭/ ፲፱፻፳፩ ዓ ም በዕለተ እሑድ አንድ ግብጻዊ



www.ethiopianorthodox.org

ሊቀ ጳጳስና አራት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ካይሮ ላይ በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን በአቡነ ዮሐንስ እጅ ተሾሙ ፤ አቡነ አብርሃም ኢትዮጵያዊ የጎንደርና የጎጃም ጳጳስ ፤ አቡነ ይስሐቅ ኢትዮጵያዊ የትግሬና የስሜን ጳጳስ ፤ አቡነ ጴጥሮስ ኢትዮጵያዊ የወሎና የላስታ ጳጳስ ፤ አቡነ ሚካኤል ኢትዮጵያዊ የኢሉባቦርና የምዕራብ ኢትዮጵያ ጳጳስ ሁነው ተሾመዋል ፤ ፓትሪያርክ አቡነ ዮሐንስ ኢትዮጵያን ለመጎብኘት በመርከብ በጅቡቲ በኩል መጥተው ታኅሣሥ ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም አዲስ አበባ በደረሱ ጊዜ ከፍ ያለ አቀባበል ተደርጎላቸዋል ። የመንግሥትም እንግዳ ሁነው ተቀምጠዋል ፤ ባለፈው ዓመት ለጵጵስና ከተመረጡት መካከል እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በሕመም ምክንያት ይባላል ፡ ወይም ደግሞ ወደግብፅ ለመሔድ ባለመፈለግ ይባላል ፤ ሳይሾሙ ቀርተው ነበርና በጥር ወር ፲፱፻፳፪ ዓ. ም. ሥርዓተ ቅብዓቱን ፈጽመው ስማቸውንም ሳዊሮስ ብለው ሰይመው ሹመዋቸዋል ፤ ከዚህ በኋላ ፓትሪያርኩ በዚሁ ወር ተመልሰው ወደካይሮ ሔዱ ። የኢትዮጵያም ቤተ ክርስቲያን የጠየቀችው ጥያቄ በከፊል ተፈጸመላት ፤ እነዚህ ጳጳሳት ሁሉም የተማሩና መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው አባቶች ስለነበሩ ስብከተ ወንጌልን በጣም አስፋፍተው ነበር ። አቡነ አብርሃም በተለይ በጎጃም አገር የቅብዓትን ሃይማኖት በመቃወም ብዙ ሥራ ሠርተዋል ፤ በዚህም ምክንያት አባ ማርቆስ የተባለው የቅኔ መምህር ፤ «አብርሃም ነድ የቅብዓት ማቅለጫ» የሚለውን ቅኔ ሰጥቷል ። በጠላት ወረራ ጊዜ ጣሊያኖች ሦስት ዓይነት ሰዎችን ለማጥፋት ፈልገው ነበር ፤ አንደኛ የመኳንንትን ልጆች ፪ኛ የተማሩ ካህናትንና ጠንቋዮችን ሦስተኛ የውጭ አገር ቋንቋ የሚያውቁትን ወጣቶች ከኢትዮጵያ ምድር ማጥፋት ነበር ፤ ከነዚህ መካከል በብዛት ተገኝተው የተጎዱት ካህናት ነበሩ ፤ በየደብሩ በየገዳሙ በመድፍና በመትረየስ የተደበደቡት ካህናት ቁጥር በቀላሉ የሚገመት አይደለም ፤ ይህ ብቻ አይደለም ፤ አብያተ ክርስቲያናት በብዛት ተቃጠሉ ፤ ከጳጳሳቱም መካከል የወሎው አቡነ ጴጥሮስና የኢሉባቦሩ አቡነ ሚካኤል በሰማዕትነት ሞቱ ፤ አቡነ ጴጥሮስ ሐምሌ ፳፪/ ፲፱፻፳፰ ሲሞቱ አቡነ ሚካኤል በጥቅምት ወር ፲፱፻፳፱ ዓ. ም. እርፈው የካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ. ም. በግራዝያኒ ላይ በወደቀው ቦምብ ምክንያት ብዙዎች ኢትዮጵያውያን በየመንገዱ ያለፍርድ ተገደሉ ፤ ግብጻዊውም ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ በሐምሌ ወር ፲፱፻፳፱ ዓ.ም. ዱቼ ሙሶሊኒን ለማየት ወደሮማ ሔዱ ፤ ወደ ሮማ የሔዱበት ምክንያት አንደኛው ለአቡነ ማቴዎስ ተሰጥቶ የነበረው መብት ተቀንሶብኛልና ለኔው ይሰጠኝ እጨጌው ሥልጣኔን መካፈል የለበትም ብለው ለመጮህ ነበር ይባላል ፤ አንዳንዶች ደግሞ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስለተበደለች በጠቅላላው ጩኸት ለማቅረብ ነው ይላሉ ፤ በዚህ ጊዜ አቡነ አብርሃምን ወክለው ለቤተ መንግሥቱም ለቤተ ክህነቱም ይህንኑ አስታውቀው ነበርና አቡነ አብርሃም በሊቀ ጵጵስናው መንበር ተቀምጠው ሥራውን ያካሔዱ ጀመር ፤ አቡነ ቄርሎስ ከሮማ መንግሥት ምንም ተስፋ በማጣታቸው ወደ አዲስ በባ መመለሱን ትተው ወደ ካይሮ አስፈቅደው ሔደው በዚያው ቀሩ ። ተመልሰውም የማይመጡ መሆናቸውን አስታወቁ ፤ መቅረታቸውም አንድ ሌላ ነገር ፈጠረ ፤ በ፲፱፻፴ ዓ. ም. የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ማዘኗን ዐውቀው ደስ ለማሰኘት ፈልገው የግብጹ ጳጳስ አልመለስም ስላሉ ከመካከላችሁ መርጣችሁ ሊቀ ጳጳሳት ሹሙ ይህንን ካላደረጋችሁ የሮማ ፓፓ የዓለም ሊቀ ጳጳስ በመሆኑ እሱ ይሾማል እንጂ እንግዲህ ወዲህ ከግብጽ ጳጳስ ማምጣት አይቻልም የሚል ድምፅ አሰሙ ፤ በዚህ ጊዜ ምን አልባት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በሮማ ቤተ ክርስቲያን ሥር እንዳትወድቅ/ በመሥጋት ደግሞም ጳጳስ ለመሾም ከሞት የተረፉት አቡነ አብርሃም አቡነ ይስሐቅ ብቻ በመሆናቸው እነዚህ የሞቱ እንደሆነ ለመሾምም አስቸጋሪ መሆኑን በመመልከት የኢትዮጵያ ገዲማትና አድባራት መምህርንና ሊቃውንት በአዲስ አበባ ስብሰባ አደረጉ ፤ መምህራኑም ነገሩን በደንብ አድርገው ከአጠኑ በኋላ አቡነ አብርሃምን ሊቀ ጳጳሳት አድርገው መርጠው በሊቀ ጵጵስናው ቦታ እንዲቀመጡ ከአደረጉ በኋላ እርሳቸው ጳጳሳትን እንዲሾሙ የሚል ውሳኔ ሰጡ ፤ በዚህ ውሳኔ መሠረት አቡነ አብርሃም



www.ethiopianorthodox.org

የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ሁነው ኅዳር ፳፭ ቀን ፲፱፻፴ ዓ. ም. ተሾመው፡ ዕለቱን አምስት ጳጳሳትና አንድ ኤጲስ ቆጶስ ሾሙ፤ የተሾሙትም ሰዎች ስም የሚከተለው ነው።

፩ኛ/ አቡነ ዮሐንስ/ ንቡረ ዕድ ተክለ ሃይማኖት የነበሩት/ እጨጌና የሸዋ ጳጳስ

፪ኛ/ አቡነ ማርቆስ የኤርትራ ጳጳስ

፫ኛ/ አቡነ ሰላማ የሐረር ጳጳስ

፬ኛ/ አቡነ ገብርኤል የጎንደር ጳጳስ

፭ኛ/ አቡነ ማቴዎስ የወሎ ጳጳስ ሲሆኑ

፮ኛ/ አቡነ ሉቃስ የወለጋ ኤጲስ ቆጶስ ሁነው ተሾመዋል፤ ይህ አድራጎት በግብጽ በተሰማ ጊዜ የግብጽ ሲኖዶስ ስብሰባ አድርጎ አቡነ አብርሃምን አወገዘ፤ ግን ግዝቱ ወደ ኢትዮጵያ ምእመናን ጆሮ ሳይደርስ በዚያው በግብጽ ተወስኖ ቀረ። አቡነ አብርሃም ሐምሌ ፲፬ ቀን ፲፱፻፵፩ ዓ. ም. አረፉ፤ ከዚያም በኋላ አዲስ ሊቀ ጳጳሳት ለመምረጥ ፹፪ ሊቃውንትና መምህራን ተሰብስበው አቡነ ዮሐንስን መረጡ፤ አቡነ ዮሐንስ መስከረም ፮ ቀን ፲፱፻፵፪ ዓ ም የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ሆነው ተሾሙ። እርሳቸውም በተሾሙ ጊዜ አራት ጳጳሳትና አንድ ኤጲስ ቆጶስ ሾሙ፤ ስማቸውም የሚከተለው ነው ።

፩ኛ/ አቡነ ፊልጶስ የሊቀ ጳጳሳቱ ጸሐፊ፤

፪ኛ/ አቡነ ጐርጐርዮስ የወሎ ጳጳስ፤

፫ኛ/ አቡነ ማትያስ የሸዋ ጳጳስ፤

፬ኛ/ አቡነ አትናቴዎስ የጎጃም ጳጳስ፤

፭ኛ/ አቡነ ቄርሎስ የኤርትራ ኤጲስ ቆጶስ ከአምስት ወር በኋላ በጥር ወር በ፲፱፻፵፩ ዓ. ም. አቡነ ዘካርያስን የኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ አድርገው ሾመዋል። በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያ ጳጳሳት ቁጥር ወደ አሥር ደርሷል፤ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ሁናቴ ሳለች ፋሽስት ኢጣሊያ ... ኃይለ ሥላሴ በድል አድራጊነት ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰዋል፤ በዚህ ጊዜ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሌላ አዲስ ምዕራፍ ተከፍቷል።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከሚጣት በኋላ

በ፲፱፻፴፫ ዓ ም ግርማዊነታቸው በድል አድራጊነት ተመልሰው በዙፋናቸው በተቀመጡ ጊዜ የግብጽ ሲኖዶስ የሰጠውን ውሳኔ (ግዝት) መሠረት በማድረግ በሙሉ በሥራ የነበሩት በኢጣልያ ጊዜ የተሾሙት ሊቀ ጳጳሳትና ጳጳሳት በየቦታቸው እንዲቀመጡ ተደረገ፤ የቤተ ክህነት ሥራ በእጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ይካሔድ ጀመር፤ ተቋርጦ የነበረው የግብጽና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ግንኙነት ታደሰ፤ በዚህም ምክንያት አቡነ ቄርሎስ ከሌሎች ሦስት ሰዎች ጋር ወደ አዲስ አበባ የፓትሪያርኩን ደብዳቤ ይዘው መጡ። ከዚህም በኋላ ከቤተ ክህነትና ከቤተ መንግሥት ሰዎች ተመርጠው ስለሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ጉዳይ ከግንቦት ፴- እስከ ሰኔ ፲፫ ፲፱፻፴፬ ዓ ም ድረስ ጉባኤ ተደርጎ የግብጽም ግዝት እንዲነሣ ንግግር ተደርጎበት ነበር።

ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አስተያየት ምን እንደሆነ የሚገልጥ ጽሑፍ ተሰጣቸው ና መልእክተኞቹ ይዘው ወደ ግብጽ ተመለሱ፤ አቡነ ቄርሎስ ግን ተለይተው በአዲስ አበባ ቀሩ። በዚህ ጊዜ አቡነ ዮሐንስ የሊቀ ጳጳስነቱን ቦታ ለቀው እንዲወጡ ተነገራቸው፤ ቦታውንም አቡነ ቄርሎስ ያዙ፤ አብዛኛውን ጊዜ የኢትዮጵያ ጳጳሳት የተጋዙበት ምክንያት የግብጽን ቤተ ክርስቲያን ደስ ለማሰኘትና ወደ አንድ ስምምነት ለመድረስ ሲባል ነበር። የተላከው ደብዳቤ ሳይደርስ የግብጽ ፓትሪያርክ አቡነ ዮሐንስ መሞታቸው ተነገረ፤ ከዚህ በኋላ የጓርጓው ሊቀ ጳጳስ አቡነ ዮሳብ ተጠባባቂ ፓትሪያርክ ሆነው ተሾሙ፤ የግብፅም ሲኖዶስ በርሳቸው ሰብሳቢነት ሰኔ ፲፱ ቀን ፲፱፻፵፩ ዓ/ም ተሰብስቦ ስለግዝቱ አንድ ውሳኔ ሰጠ። ውሳኔው በከፊል ነበር እንጂ በሙሉ አልነበረም፤ በዚህ ምክንያት አዲስ ፓትሪያርክ እንዲሾም መጠበቅ ግድ ሆነ። በኢትዮጵያ በኩል ደግሞ መንፈሳዊ ጉባኤ ተቋቁሞና የዚህኑ ጉዳይ ለማጥናት የገዳማትና የአድባራት መምህራንና ሊቃውንት በአዲስ አበባ ተሰብስበው በክርክር ላይ ነበሩ፤ ኅዳር ፲፩ ቀን ፲፱፻፴፰ ዓ ም ፹፪ ሊቃውንት ፳፬ መምህራን ሁለት ጊዜ ስብሰባ አድርገው ነገሩን በሰፊው ተወያዩበት፤ ቤተ ክህነቱ ከዚህ በፊት ወደ ግብጽ ቤተ ክርስቲያን ልኮ የጠየቃቸው ጥያቄዎች አጥጋቢ ሆነው ባለመገኘታቸው የግብጽም ቤተ ክርስቲያን የሰጠችው ምክንያት በቂ ያልሆነ የማጭበርበርና የማ



www.ethiopianorthodox.org

ወናበድ መንፈስ የተመላበት መሆኑን በመገንዘብ
ቁርጥ ያለ ውሳኔ ወስዶ ነበር ። ይኸውም ካልፈ
ለጋችሁ እኛው ራሳችንን እንችላለን የእስከ ዛሬው
ይበቃናል እንግዲህ ወዲህ የግብጽን ቤተ ክርስቲ
ያን የምንለማመጥበት ምንም ምክንያት የለንም
የሚል ነበር ፤ ለዚህም የረዳቸው ምንም በጠላት
ዘመን ቢሆን ከዚህ በፊት የተደረጉት ስብሰባዎች
የኢትዮጵያን ሊቃውንት አንጎል አብስለውት ነበር ።
በስብሰባውም የነበሩት ሊቃውንት በጠላት ጊዜ
ተሰብስበው በአቡነ ቄርሎስ ፊንታ አቡነ አብርሃም
ንና አቡነ ዮሐንስን የመረጡት ሊቃውንት መሆ
ናቸው ታውቋል ፤ በዚህ ዓይነት ቤተ ክርስቲያን
በብዙ ወገን ተዘጋጅታ ስለስለነበር በ፲፱፻፴፮ እን
ዲሁም በ፲፱፻፴፰ ዓ ም በአዲስ አበባ ስብሰባ በተ
ደረገ ጊዜ የቅኔው ነጐድጓድ ሲወርድ አልፎ አል
ፎ ፉከራም ነበረበት ፤ የግብጽ ቤተ ክርስቲያንን እም
ነት አንለውጥም ግን ከእንግዲህ ወዲህ የግብጽን ሊቀ
ጳጳሳት አንፈልግም በቋንቋችን የሚናገር የሚያስ
ተምር ሊቀ ጳጳሳት እንፈልጋለን የሚለው ድምፅ
ጐልቶ በመሰማቱ ለጊዜው የግብጽና የኢትዮጵያ
ቤተ ክርስቲያን ግንኙነት የተቋረጠ መስሎ ነበር ።
የሊቃውንቱ አስተያየት ከመበርታቱ የተነሳ አቡነ
ቄርሎስም አዲስ አበባን ለቀው ወደ ግብጽ ሔደው
በገዳማቸው እንዲቀመጡ ተደርገዋል ። በዚህ ጊዜ
የቤተ መንግሥቱ ድምፅ ተለይቷል ፤ ሐሳቡም
በጽሑፍ ብቻ ከምንለያይ ሰው ልከን የመጨረሻ
ውን መልስ እስክናገኝ ድረስ ቤተ ክርሀነቱ እንዲ
ታገሥ ከቤተ መንግሥት አንድ ጥያቄ ቀርቧል ፤ በዚ
ህም ጊዜ ታላቁ የተቀደሰው ጉባኤ ውሳኔ ከአስተ
ላለፈ በኋላ ለቤተ መንግሥቱ ጥያቄ ጊዜ እንዲሰ
ጠው በሚለው ተስማምቶ ብፁዕ እጨጌ ገብረ ጊዮ
ርጊስ የዚያን ጊዜው እጨጌ የአሁኑ ፓትሪያርክ ለግ
ርማዊነታቸው የሚከተለውን ደብዳቤ አቅርበዋል ፤
በጥያቄምውም ውስጥ እንዲህ የሚል አለበት ፤
መላው ጉባኤ ለኢትዮጵያ የሚገቡት ነገሮች እን
ዲሰጡ ሊቀ ጳጳሳትም ከኢትዮጵያ ተወላጆች ውስጥ
እንዲመረጥ ማስፈለጉን ተስማምቶበታል ፤ ይኸ
ውም አሳብ በመንግሥታችን ወገን የተደገፈ ስለ
ሆነ መንግሥታችን መልእክተኞችን ልኮ አሳቡን
ለማስፈጸም የሚከናወንለት ከሆነ ጉባኤው ተቃ
ዋሚ አይደለም ፤ ስለዚህ የቤተ መንግሥታችን አሳ
ብና ምኞት መልእክተኞቹን ልኮ የኢትዮጵያ ቤተ
ክርስቲያን የጠየቀችውን ሁሉ ከእስክንድርያ ፓት
ሪያርክ ተጠባባቂ ወይም ከጉባኤው ጋር በሰላም
ለመጨረስ ስለሆነ ይህንኑ በቶሎ ከፍጻሜ እንዲ
ያደርስላት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ግርማዊነት
ዎን በጸሎት እየደገፈች ትለምናለች ፤ ነገር ግን ግር
ማዊነትዎ መለእክተኞችን ልኮ ካሁን በፊት በዚሁ
ነገር ቤተ ክህነት የደከመችውን ያህል በነገሩ
ደክመውበት ከእስክንድርያው ፓትሪያርክ ተጠባ
ባቂ ወይም ከጉባኤው ፍሬ ያለው ምላሽ ያልተገኘ
እንደሆነ ግርማዊነትዎ የተስማማ እንደሆነ ባለመ
ጠራጠር እናምናለን ። ።


ኅዳር ፱/ ፲፱፻፴፰ ዓ. ም. አዲስ አበባ እጨጌ
ገብረ ጊዮርጊስ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የሚል
ነው ከዚህ ላይ የቤተ ክህነት ትግል አልቆ ቤተ
መንግሥቱ ወደ ካይሮ መልእክተኞችን በመላክ
ትግሉን ቀጥሏል ።

ወደ ግብጽ የመልእክተኞች መላክ ፤

ቤተ መንግሥቱ በአሳቡ መሠረት ክቡር ፊታ
ውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤልንና ብላታ መርስዔ ኅዘን
ወልደ ቂርቆስን ወደ ካይሮ ላከ ፤ ጊዜው ጥር ፩ ቀን
፲፱፻፴፰ ዓ ም ነበር ፤ በዚህ ጊዜ አቡነ ቄርሎስ ኢት
ዮጵያን ትተው ካይሮ ይገኙ ነበር ። እነሱ ወደ
ካይሮ ከመድረሳቸው በፊት የግብጽ ቤተ ክርስቲያን
ሲኖዶስ ስብሰባ አድርጎ ውሳኔ አስተላልፎ ነበር ፤
በውሳኔውም ውስጥ ከኢትዮጵያ ጳጳሳት ጋር ሁለት
የግብጽ ጳጳሳት አብረው እንዲሾሙ የሚል ስለነበ
ረበት ክርክሩ እንደገና ቀጠለ ፤ ከብዙ ንግግርም
በኋላ በግንቦት ወር የፓትሪያርክ ምርጫ ስለሚደ
ረግ አምስቱ ኢትዮጵያውያን መነኮሳት ወደግብጽ
ይምጡና ይሾማሉ የሚል መልስ ከተጠባባቂው
ፓትሪያርክ ተቀብለው መጋቢት ፲፩ ቀን ፲፱፻፴፰
ዓ ም ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ ፤ በዚህ ውሳኔ መሠ
ረት በግንቦት ወር ፲፱፻፴፰ ዓ. ም. ከዚህ ቀጥሎ
ስማቸው የተዘረዘረው አባቶች ለሹመት ወደ ካይሮ



www.ethiopianorthodox.org



ባ፲፱፻፵፩ ዓ. ም. የተሾሙት የኢትዮጵያ ሊቃነ ጳጳሳት ።

አመሩ ፤ ፩ኛ ብፁዕ እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ፪ኛ/ መምህር ገሪማ ወልደ ኪዳን ፫ኛ/ ሊቀ ሥልጣናት መልአከ፡ ወልደ ማርያም ፬ኛ/ መምህር ዘፈረ ብርሃን ገብረ ጻድቅ ፭ኛ/ መምህር ጌታሁን ወልደ ሐዋርያት ነበሩ ። ከነሱም ጋር ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤልና ብላታ መርስዔ ኀዘን አብረው ሔደው ነበር ። የተመረጡት መነኮሳት ወደ ካይሮ ደርሰው ግንቦት ፪ ቀን ፲፱፻፴፰ ዓ ም አቡነ ዮ ብ ፓትሪያርክ ሆነው ተሾሙ ፤ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ከመሾማቸው አስቀድሞ አንድ ውል ተዘጋጅቶ ቀረበ ፤ ይኸውም ውል የኢትዮጵያው ሊቀ ጳጳስ በበታቹ ጳጳሳትንና ኤጲስ ቆጶሳትን አይሾምም የሚል ነበር ። በዚህ መሥመር ላይ ስምምነት ባለመገኘቱ፡ የኢትዮጵያ አባቶች ሳይሾሙ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው መጡ ።

ከዚህም ላይ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን የሠራችው ሀመዕ ከፍ ያለ ነበር ፤ ግን ሳትከፍለው የቀረች አይመስልም ። በዚህ ምክንያት ለሁለት ዓመት ያህል ግንኙነት ተቋርጦ ቆየ ።

ሐምሌ ፬ ቀን ፲፱፻፵ ዓ·ም ብፁዕ አቡነ ዮሳብ ለግርማዊነታቸው አንድ መልእክት ላኩ ፤ ይህም መልእክት የግብፅ ሲኖዶስ ኢትዮጵያውያንን ፤ ለመሾም መወሰኑን የሚገልጥ ነበር ፤ በዚህም መሠረት ከዚህ በፊት ወደ ግብፅ ሔደው የነበሩት መነኮሳት ወደ ካይሮ ሔደው የጵጵስና መዓርግ አገኙ ፤ ግን ሊቀ ጵጵስናው እስከ አባ ቄርሎስ ዕረፍት ድረስ ተጠብቆ እንዲቆይ ተወስኖ ነበር ፤ ጥቅምት ፲፬ ቀን ፲፱፻፵፩ ዓ·ም ካረፉ በኋላ ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ጥር ፮ ቀን ፲፱፻፵፩ ዓ·ም በብፁዕ አቡነ ዮሳብ እጅ ተቀብተው የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ሆኑ ፤ ይህም ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ደስታና ስሜትን ጨመረላት ።

ብፁዕ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ባስልዮስ ነሐሴ ፳፫ ቀን ፲፱፻፵፩ ዓ·ም አምስት ጳጳሳትን ሾሙ ፤ ስማቸውም ቀጥሎ ያለው ነው ።

አቡነ ታዴዎስ የጐሬ ጳጳስ

አቡነ ገብርኤል የወሎ ጳጳስ ፤

አቡነ ፊልጶስ የኢየሩሳሌም ጳጳስ



www.ethiopianorthodox.org

አቡነ ማርቆስ ያው ሹመታቸው እንዲጸናላቸው ተደረገ ።

አቡነ ሳዊሮስ የገሙ ጳጳስ ሆነው ተሾሙ ። የትግሬ ጳጳስ የነበሩት አቡነ ይስሐቅ ነሐሴ ፫ ቀን ፲፱፻፵፪ ዓ-ም ስለ አረፉ በእርሳቸው ፈንታ የአክሱም ንቡረዕድ ገብረ መስቀል አቡነ ዮሐንስ ተብለው ሐምሌ ፳፩ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ-ም በአቡነ ባስልዮስ እጅ ተቀብተው የትግሬ ጳጳስ ሆነው ተሾሙ ።

## የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የባትሪያርክነት መዓርግ ስለማግኘቷ ፤

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሊቀ ጵጵስናውን ማዕርግ ከአገኘች በኋላ በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ከፍ ያለ ክርክር ተደርጎ ነበር ፤ መግባባትም በመታጣቱ ምክንያት የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርኳን ራስዋ በመሾሟ በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል የነበረው ግንኙነት ገብ ብሎ መቆየቱ ታውቋል ፤ ቢሆንም አዲስ የተሾሙት አቡነ ቄርሎስ የግብፅ ፓትሪያርክ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ማዕርግ ወደ ፓትርያርክነት ደረጃ ለማድረስ ያሰቡ መሆናቸውን የሚገልጥ ጽሑፍ አስይዘው ፫ ጳጳሳት ፬ ምእመናን ነገሩን በቃል እንዲያስረዱ ላኩ ፤ እነዚህ መልእክተኞች ወደ አዲስ አበባ መጥተው ከቤተ ክህነትና ከቤተ መንግሥት ሰዎች ጋር ንግግር ከአደረጉ በኋላ ወደ አንድ ስምምነት በመድረሳቸው የውሉ ስምምነት ተጠንቶ ተፈረመ ። በዚህ ውል ላይ በጣም አከራካሪ የነበረው ፤ ሀ/ የኢትዮጵያው ፓትሪያርክ የ ሚሰጠው ስያሜ፡ለ/ የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ ስለእሚሾማቸው ሊቃነ ጳጳሳት ሁኔታ ነገር ግን ይህ ሁሉ ተሻሽሎ ወደ አንድ ስምምነት በመዳረሱ ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ከሊቀ ጵጵስና ማዕርግ ወደ ፓትሪያርክነት ማዕርግ ሰኔ ፳፩ ቀን እሑድ ፲፱፻፶፩ ዓ-ም በብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ ተቀብተው የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ ሆነው ተሾሙ ፤ በዚህ ቀን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት እንደ ኦ ጋጣሚ ሆኖ በካይሮ ተገኝተው ስለነበር ለበዓሉ ከፍ ያለ ክብር ሰጥተውት ውለዋል ። በዚህ ዓይነት




የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፓትሪያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ሲሾሙ



www.ethiopianorthodox.org



በ፲፱፻፵፪ ዓ. ም. የተሾሙት ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት



ብፁዕ ወቅዱስ
አቡነ ባስልዮስ
የኢትዮጵያ ፓት
ሪያርክ የኤርት
ራን ሀገረ ስብ
ከት ሊቀ ጳጳስ
ሲሾሙ፡



www.ethiopianorthodox.org

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ቸርነት በግርማዊነታቸው ፍጹም ድጋፍና አስተዋይነት እን ዲሁም በሊቃውንቶቿ ስምምነት ከፍተኛውን ማዕርግ አግኝታ እነሆ የታሪክ ጉዞዋን በጸጥታ በመቀጠል ላይ ናት ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ራሷን ከቻለች ወዲህ ምን እርምጃ አደረገች ? ይህ ጥያቄ አስቸ ጋሪ ጥያቄ አይደለም በየጠቅላይ ግዛቱ ጳጳሳትንና ሊቃነ ጳጳሳትን አሠማርታ የወንጌልን ስብከት በሰ ፊው ታስተምራለች ። ጳጳስ ፍለጋ ከየጠቅላይ ግዛቱ ወደ ፋናው ከተማ ሲመጣ በኢትዮጵያውያን ልጆች ይደርስ የነበረው ድካም በኃይል ተቀንሶዋል ። ስብ ከት ወንጌል በጽሑፍም ሆነ በራዲዮ አማካይነት ተጀምሮ ይታያል ። እርግጥ ነው የጊዜው ፈጣን ነት የቤተ ክርስቲያንንእርምጃ ስለሸፈነው ለብዙ ዎቻችን አይታወቀንም እንጂ ብዙ እርምጃ ተደል ርጓል ። ካህናት በደመወዝ መተዳደር ጀምረዋል ፤ መንፈሳውያን ማኅበሮች በብዛት ተቋቁመዋል ፤ ምንም ቢሆን ጀምራለች ግን ወደ አሰበችው ግብ ለመድረስ ጊዜን ትጠይቅ ይሆናል ቢሆንም ይህ ጊዜ ዕሩቅ አይመስልም በጳጳሳትም አማካይነት ወደ ግብፅ ይሔድ የነበረው ሀብት ለቤታችን ውሏል ። ይህንን ሁሉ ጸጋ ስለሰጠን እግዚአብሔርን እናመስ ግነው አሜን ።

መላከ ሰላም ሳሙኤል ተረፈ ፤

# የሕንፃ ቤተ ክርስቲያን በብዛት መሠራት

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደሆኑ የኢትዮጵያ አገዛዝ መን ፈሳዊ እንደመሆኑ መጠን ሕዝቡ በግብረ ገብነቱ በሃይማኖቱ የጸና ስለሆነ በእግዚአብሔር ያለው እምነት በሀገሩ ላይ ያለው ፍቅር ከዕለት ወደ ዕለት እየጐላ ይሔድ ዘንድ በየጠቅላይ ግዛቱ በየ አውራጃው ፤ በየወረዳው ፥ ቤተክርስቲያን እንዲ ሠራ ፤ መንፈሳዊ ድርጅት እንዲቋቋም ፤ ሁሉም በሃይማኖቱ በበጎ ሥርዓት ጸንቶ እንዲኖር ዐዋጅ ዐወጁ ።

ሁሉም እንደ ዐዋጁ ይፈጽም ዘንድ ራሳ ቸው የሥራው ሁሉ ምሳሌ እየሆኑ መፈጸም ጀመሩ ፤ ለምሳሌ ስለ ቤተ ክርስቲያን ሥራ የሻ ለቃ ፤ ምስለኔ ፤ የወንድ መኳንንት ፤ የሴት ወይዛዝ ርት እንዲያሠሩ ሲናገሩ ራሳቸው በልዩ ገንዘባ ቸው በየጠቅላይ ግዛቱ በየከተማው ትልልቅ አድባራትንና ገዳማትን ማሠራት ጀመሩ ።

ምንም የኢትዮጵያ አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ከሆኑበት ጊዜ ጀምረው ቀዋ ሚ የሆኑ ሥራዎችን ሁሉ ቢሠሩ ፤ ጠላት በምቀ ኝነት አቋርጦት የነበረውን በመቀጠል ፤ ቀድሞ ጀምረውት የነበረውን በመፈ ጸም ፤ አዲስ ድርጅት በማቋቋም አዲስ ገዳም በመገደም ፤ አዲስ ደብር በመደበር ፤ ሕንፃውንም በማሠራት ለቤተ ክር ቲያን የዋሉት ብዙ ሲሆን ከዚህ እንደሚከተለው ከሞላ ጐደል በቅደም ተከተል እንገልጣለን ።

፩ኛ/ የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴ ድራል

፩ኛ/ የሕንፃው ታሪክ ፤

የመንበረ፡ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድ ራልን ሕንፃ ታኅሣሥ ፲፩ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ/ ም/ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የመሠረቱን ድን ጋይ በክብር አኖሩ ፤ በዚህም ጊዜ የግብፅ ፓትርያርክ አቡነ ዮሐንስ ፤ የሀገር ጳጳሳትም ተገኝ ተው ልዩ ጸሎት ደርሶ ልዩ ቡራኬም ተሰጥቶ ተመሠረተ ። በአዲስ አበባ የሚኖሩ የወንድ መኳ ንንት የሴት ወይዛዝርት በብዛት ተገኝተው የደ ስታው ተካፋዮች ሁነው ነበር ። ጥብቅ መቆጣ ጠር ተደርጎለት ልዩ መልክ ባለው አቅድ ሲሠራ ሳለ ጠላት አገራችንን በግፍ ለመውረር በ፲፱፻፳፰ ዓ/ ም/ ስለተነሣ ሥራው መቆም ግድ ሆነበት ፤ የሕንፃው ሥራ ግን አልቆ በር መገጣጠምና ጌጣ ጌጥ የሆኑት ነገሮችን ማስገባት ብቻ ነበር የቀ



www.ethiopianorthodox.org

ረው ። ጠላት የሀገራችንን ክብር ፈጽሞ ለመውሰድ ስላሰበና ወደፊትም ከፍተኛ ዋጋ ያለው ቦታ መሆኑን አውቆ የቤተ ክርስቲያኑንም ሥራ ማማር የቦታውንም የአቀማመጥ ምቹነት ተመለከተና የራሱ ካቴድራል ለማድረግ ስላሰበ በግድና በግፍ ወሰደው ከመባል ግምት ሰጥቶ መውሰድ ይቀላል ሲል በዚያን ጊዜ የነበሩትን የቤተ ክርስቲያን ሲመለሱ ሥራው እንደገና ተጀምሮ በቅልጥፍናም ተሠርቶ መልካም ፍጻሜ አግኝቶ በቅድስት ሥላሴ ስም ተሰየመና ጥር ፯ ቀን ፲፱፻፴፮ ዓ/ ም/ ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ ። በዚህም ጊዜ ብዙ መሳፍንት ፤ መኳንንት ፤ ሊቃውንት ፤ የሴት ወይዛዝር ፤ የጦር ሠራዊት በብዛት ይገኙበት ነበር ። ካቴድራሉም የንጉሣውያንና የአርበኞች መካነ መቃርብ ስለ



የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል

ኃላፊዎች ከማስፈራራት ጋር ግምት ከፍዬ ልውሰደው ሲል ጠየቃቸው ።

እነርሱም በዕለት ክብርና ሀብት የማይሸነገሉ በመሆናቸው ዛሬ መብቱ ያንተ ነው ፤ በግድ ለመውሰድ ትችላለህ ፤ ግን በፈቃዳችን አናደርገውም ብለው በቁርጥ ቃል ስለመለሱለት ያለ ፈቃዱ እግዚአብሔር ማንኛውም ሊሠራ ባለመሆሉ አንዳች ነገር ሳያጎድል ተወው። በ፲፱፻፳፫ ዓ/ ም ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በድል አድራጊነት

ሆነ መታሰቢያነቱ በፊቱ የጠላት ወረራ ዓመታት ለተዋጉት አርበኞች ነው ፤ ስለዚህ ቅዳሴ ቤቱ በተከበረ ጊዜ በባሕር የተጣሉትን ፤ ገደል የወደቁትን ፤ በማይታወቅ ቦታ የረገፉትን አርበኞች ዐፅም አሰብስበው በዚሁ ዕለት በታላቅ ሰልፍና በልዩ የጸሎት ሥነ ሥርዓት ስላስገቡ የአሸናፊነት ኃይል ተሰምቷቸው ፤ ከዚህ የሚከተለውን ንግግር አደረጉ ።



www.ethiopianorthodox.org

የሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ሲመረቅና የኢት ዮጵያ አርበኞች ዐፅም ሲገባ ግርማዊ ንጉሠ ነገ ሥት የተናገሩት መሪ ቃል «እጅግ ከፍ ያለው የዓለም ሁሉ ገዥ እግዚአብሔር ለኢትዮጵያና ለሕዝባችን ለእኛና ለአርበኞቻችን በየጊዜው ካደ ረገልን ፤ ወደፊትም ከሚያደርግልን ከታላላቅ ችሮታ ከሚቆጠሩት ሥራዎች አንደኛውን ዛሬ ስለፈጸ መልን ልናመሰግነው ይገባናል።

ለንጉሠ ነገሥት ቤተ ዘመዳችን ደንበኛ የዕረ ፍት ሥፍራ እንዲሆን በመሠረትነው የክብር ቦታ በሥራቸውና በመሥዋዕትነታቸው ውለታቸውን ልን መልስላቸው የተገባቸው አገልጋዮች ደንበኛ የር ስት ተካፋይ እንዲሆኑ ፈቀድን ። የሚገባቸውን ፈጽ መው ማረፋቸውን ስንመሰክርላቸው በዐፅማቸው ፊት የክብር ሰላምታ ንሰጣለን » ።

ቀ· ኃ· ሥ·

ጥር ፯ ቀን ፲፱፻፴፯ ዓ· ም·

ለልዩ ልዩ የጦር ሠራዊት መለዮ የሚሆነው ሰንደቅ ዓላማ በዚህ ካቴድራል እንዲውለበለብ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፈቀዱ ። ይኸም በጦር ሜዳ ለወደቁት አርበኞች ለሕያዋኑ ጦር ሠራ ዊት መታሰቢያና የጦሩ መለያ የሚሆን ነው ። ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ይኸ ሰንደቅ ዓላማ በዚህ ካቴድራል ውስጥ እንዲሰቀል በፈቀዱ ጊዜ ከዚህ የሚከተለውን ተናገሩ ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ

ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ኢትዮጵያን ከጠላት ለመከላከል በጦር ሜዳ ላይ ለወደቁት ጦረኞቻችን መታሰቢያ እንዲሆ ንና በጦር ሠራዊታችን ውስጥ ሆነው ለኢትዮጵያ ለተከላከሉና ለረዱ ወደፊትም ለሚከላከሉና ለሚ ረዱ ለታማኝ ዜጎቻችን ሁሉ በመልካም ፈቃዳ ችን ውለታቸውን በልዩ ለመግለጥ ምኞታችን ስለሆነ በሕገ መንግሥታችን በ፲፰ኛው ክፍል ተየ መለከተውን ዓይተን ይህንን ለመፈጸም ።

፩ኛ/ ፲፱፻፳፯ — ፲፱፻፴፫ ዓ/ ም/ የጦር ሠራዊ ታችን ሰንደቅ ዓላማ

፪ኛ/ ለክብር ዘበኛ ሰንደቅ ዓላማ

፫ኛ/ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የጦር ተማሪ ቤት ሰንደቅ ዓላማ

፬ኛ/ ከ፲፱፻፳፯ ዓ/ ም/ ጀምሮ እስከ ፲፱፻፴፫ ዓ/ ም/ ድረስ በጦር ሜዳ ለወደቁ ጀግኖች ሰንደቅ ዓላማ ። ታላቁን የሥላሴን ኒሻን ኮርዶን ሸልመናቸዋል ።

አዲስ አበባ ጥር ፳፩ ቀን ፲፱፻፴፯ ዓ/ ም/
ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ
የጽሕፈት ሚኒስትር

፪ኛ ስያሜ ፤

ይኸም ካቴድራል መንበረ ፀባዖት ተብሎ በቅድስት ሥላሴ ተሰየመ ። ይህን የመሰለ የቆየ ሥርዓት በኢትዮጵያችን ነበር ፤ ማለት የክርስትና ሃይማኖት አንድ አምላክ ከሚሉት የተለየበት ሥላ ሴን በአካል ሦስት ፤ በባሕርይ አንድ በማለት ስለ ሆነ ፤ አንድነትም ሦስትነትም ተለይቶ የታወቀ ከክርስትና ወዲህ ነው ። ኢትዮጵያም የክርስቲ ያን ደሴት በመሆኗ የኢትዮጵያ ታላላቅ ነገሥታ ትም ፍጹም ክርስትናቸውን ለማጠየቅ ሲሉ ሁል ጊዜ ከሚሠሯቸው አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የመጀመሪያውን በቅድስት ሥላሴ ስም ማድረግ ቅዱስ ዓላማቸው ነበር ።

ለምሳሌ ፤ ፩ኛ/ ፍጹም ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲ ያን በመሆናቸው ቆስጠንጢኖስ የተባሉት፤ አም ልኮተ ጣዖትን አጥፍተው የቤተ ክርስቲያንን ሥር ዓት የወሰኑት አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ከአሳነጿቸው አብያተ ክርስቲያን ውስጥ በጣም ትልቅና ታሪ ካዊ የሆነውን በሸዋ ጠቅላይ ግዛት ያለውን በሥ ላሴ ስም የተሰየመውን የደብረ ብርሃን ቤተ ክርስ ቲያን አሳንፀው በሥላሴ ስም ሰይመውታል ።

፪ኛ/ በጎንደር መንግሥትም የዜማንና የስ ብሐተ እግዚአብሔር ውሳኔን የሰጡት አፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ካሠሯቸው አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ከፍተኛ ደረጃ ያለውን ቤተ ክርስቲያን አሳንጸው በቅድስት ሥላሴ ስም ሰይመውታል ።

፫ኛ/ አፄ ዮሐንስም ንጉሠ ነገሥት እንደተ ባሉ ወዲያውኑ በአድዋ ከተማ የሚገኘውን የደ



www.ethiopianorthodox.org

ብረ ብርሃን ቤተ ክርስቲያን አሳንፀው በቅድስት ሥላሴ ስም ሰይመውታል ።

፱ኛ/ ግርማዊ አፄ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት እንደሆኑ ወዲያውኑ የአዲስ አበባውን መካነ ሥላሴ የተባለውን ቤተ ክርስቲያን አሳንፀው በቅድስት ሥላሴ ስም ሰይመውታል ።

፲ኛ/ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም በነገሡ በመጀመሪያው ዓመት በሥራው ጥብቅነት በሕንፃው አስደናቂ የሆነውን በሁሉ የተሟላ ይኸን ታላቅ ካቴድራል ሠርተው ሲፈጽሙ በቅድስት ሥላሴ ስም እንዲጠራ አድርገዋል ።

## ፫ኛ/ የ፪ኛው ጊዜ ሕንፃ ፤

በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በፊት የተሠራው በከተማው ይኖር የነበረውን የጊዜውን ሕዝብ ብዛት በመመልከት ነበር እየቆየ ሕዝቡ ሲበዛ በመጥበቡ ምክንያት እንደገና በ፲፱፻፴፱ ዓ/ም/ አዲስ ቅጥል ሥራ ተጀምሮ ስለተፈጸመ ፤ ይህ ዛሬ ያለውን ታሪካዊ መልክ ለማግኘት ቻለ ። የቤተ ክርስቲያኑ ወለል ስፋት ከምሥራቅ ወደምዕራብ ፴፰ ሜትር ሲሆን ከሰሜን ወደ ደቡብ ፳፯ ሜትር ነው ። ቁመቱም መካከሉ ፴፰ ሜትር ነው ። በውስጡ ካሉት ዓምዶችና ከቅድስቱ ጀምሮ ያለው ሕንፃ በመጀመሪያው ጊዜ የተሠራው ያልተነካ ነው ።

ግን በሰሜንና በደቡብ ያሉት ግንቦች በኋላ የተቀጠሉ ናቸው ፤ በጠቅላላው ይኸን አሁን ያለውን መልክ ሊያገኝ የቻለው ሁለተኛ ጊዜ በተሠራው ነው ። አሁንም ቢሆን በመጥበቡ ምክንያት ለሦስተኛ ጊዜ በመሠራት ላይ ነው ፤ ሥራው ባለቀ ጊዜ ይኸን የመሰለ መልክ ይኖረዋል ።

## ፬ኛ/ ክፍለ ቤተ ክርስቲያን ፤

በመቅደሱም ውስጥ ሦስት መንበሮች ይገኛሉ አንደኛው ወይም መካከለኛው በአጋእዝተ ዓለም ሥላሴ የተሰየመ ነው ፤ በዚህ መቅደስ የሚገኘው መንበሩ ከወርቅ ፤ ከብር ፤ ከዝሆን ጥርስ ፤ ከወይራ እንጨት የተሠራበት ዋጋው ፸፭ ሺህ ብር የፈጀ ሆኖ ይገኛል ። እርሱም ልዩ ልዩ የሥዕል ጌጣጌጥ አለው ፤ ለምሳሌ በምሥራቅ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሞኖግራምና ንጉሣዊ ዘውድ ከብር የተሠራ ሲሆን በቀኝና በግራው መላእክትም አሉበት ፤ ከፍ ብሎ ከአጎበሩ ላይ ደግሞ እንዲሁ ከብር የተሠራ ምሴተ ሐሙስን የሚያስታውስ ማዕድ ይገኛል ። በሰሜን የሰሎሞን ኒሻን ፤ ከአጎበሩ ላይ ግን ግንዘት ይገኛል ፤ በደቡብ ደግሞ በከርሠ ሐመሩ ላይ የንግሥት ሳባ ኒሻን በአጎበሩ ግን የጰራቅሊጦስ ሥዕል ይገኛል ። ባጎበሩ ተሸካሚ ዓምዶች ላይ የክርስቶስ የሕይወት ታሪክና የወይን ፤ የስንዴ ቅርጽ ይገኝበታል ።

በየ፬ቱ መዐዝን ላይ የኪሩቤልና የሱራፌል ቅርጽ ወይም በአራቱ ወንጌላውያን የሚመሰሉት የሰው ፤ የአንበሳ ፤ የላም ፤ የንስር ቅርጽ ከብዙ ዓይንና ከየስድስቱ ክንፍ ጋር ይገኛል ። ይህ የተሠራው በግርማዊነታቸው ልዩ ግምጃ ቤት ሹም በብላታ አድማሱ ረታ ተጠባባቂነት ሲሆን የሠሩት ደግሞ ኢትዮጵያውያን አርቲስቶች ናቸው ።

ከዋናው መቅደስ በስተቀኝ በቅድስት ማርያም የተሰየመው መቅደስ ይገኛል ፤ በቅድስት ማርያም የተሰየመበት ምክንያት የሥላሴን ሦስትነት ለማስታወስ ነው ። ምክንያቱም አንድነት ሦስትነት ፤ ሦስትነትም በአንድነት የታወቀው ወልድ ዋሕድ ከድንግል ማርያም ከተወለደ በኋላ ነውና ፤ ከዋና መቅደስ በስተግራ በቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ የተሰየመው መቅደስ ይገኛል ፤ በቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ የተሰየመበት ምክንያት አንድነት ሦስትነት የታወቀው ከጥምቀት በኋላ ስለሆነ መጥምቀ መለኮት ዮሐንስን ለማስታወስ ነው ። የመቅደሱ ግንብ ውስጡ በመላ በሞዘይክ የተሠራ ነው ።

ከቅድስቱ ውስጥ ፤ ቀኝና ግራ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትና የግርማዊት እቴጌ መንበር (ዙፋን) ከእንጨትና ከዝሆን ጥርስ የተሠራ በቅርጹ አስደናቂ የሆነይገኝበታል ። እንዲሁም በዚሁ ውስጥ በቀኝ ለሴት ወይዛዝር ፤ በግራ ለወንድ መኳንንት የተለየ የክብር መቀመጫ ይገኝበታል ።

## ፭ኛ/ የቤተ ክርስቲያን ጌጣ ጌጥ ፤

በሰሜንና በደቡብ በየመስኮቱና በየግንቡ የቅዱሳንና የመላእክት ፤ የቅድስት ማርያም ሥዕል



www.ethiopianorthodox.org

ይገኛል ። በተለይ ግን በቅድስቱ ውስጥ ከግንቡ ላይ ከምሥራቅ ከፍ ብሎ ሥዕለ ሥቅለት ፤ ዝቅ ብሎ ከበሩ ራስ ላይ ምስለ ፍቁር ወልዳ ይገኛሉ።

በዚህም ሥዕል ቀኝና ግራ ግርማዊ ጃንሆይና ግርማዊት እቴጌ እንደተማፀኑ ያመለክታል። ቀኝና ግራ ባሉት መቅደሶች ላይ ያሉት ሥዕሎች ደግሞ ፩ኛው ጥምቀትን ፪ኛው ኪዳነ ምሕረትን ያመለክታሉ ።

በደቡብ በኩል ደግሞ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያን ጉዳት ለዓለም መንግሥታት ያመለከቱበት የጄኔብን ጉባኤ የሚያመለክት ሥዕል ይገኛል ።

በሰሜን በኩል ደግሞ የግርማዊ ጃንሆይ ወደ ኢትዮጵያ መመለስና የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ የተሰቀለበትን ቦታና ጊዜ የሚያመለክት ሥዕል ይገኛል ።

በምዕራብ በኩል የሰማዕታተ ኢትዮጵያ ዐፅም በግርማዊነታቸው ትእዛዝ ከልዩ ልዩ ቦታ ተሰብስቦ በክብር ወደዚህ ቅዱስ ቦታ መግባቱን የሚያመለክት የትልቅ ሰልፍ ሥዕል ይገኛል ።

፩ኛ/ የክርስቶስ ዕርገትን የሚያመለክት ከፍ ብሎ ከኮፓላው ላይ

፪ኛ/ የክርስቶስን የ፪ኛውን ምጽዐት የሚያስታውስ ሥዕል ይገኛል ።

፫ኛ/ ከዚህ ዝቅ ብሎ የሀገርና የውጭ አገር ቅዱሳን ሥዕል በየዓምዱ ይገኛል ።

የነዚህ ሥዕሎች ሰአሊዎች ፤

፩ኛ/ አቶ አገኘሁ እንግዳ

፪ኛ/ አቶ እምአእላፍ ኅሩይ

፫ኛ/ አቶ አለ ፈለገ ሰላም

፬ኛ/ አቶ መዝሙር ዘዳዊት ናቸው ።

የብዙዎቹ ሠዐሊዎቻችን ሥራ በዚህ ካቴድራል ውስጥ በመገኘቱ በጣም ደስ ያሰኛል ። ልዑል እግዚአብሔር ለግርማዊነታቸው የአሸናፊነትን ዕድል ስለሰጣቸው በዚህ ካቴድራል በሥዕል ብቻ የሚገልጥ ልዑል እግዚአብሔር ያደረገላቸውን የቀደመውን ሥርዓት የሚገልጥ ትምህርት ነክ የሆኑ ቅርፃ ቅርፆችና ሥዕሎች ይገኙበታል ።

ይኸም ካቴዳራል ዘመናዊ እንመደሆኑ ከፍተኛው የአገልግሎት ሥርዓት በሚገባ ይከናወንበታል ፤ ስለዚህም ለቅዳሴ የተመረጡ ልዑካን ፤ ለዝማሬም የተመረጡ መዘምራን ይገኙበታል ።

ስለ ሀብቱ ፤

ሀ/ ቀድሞ የነበረው

ለ/ በድል አድራነት እንደተመለሱ ፴ ጋሻ መሬት ለካቴድራሉ በርስትነት የሰጡት

ሐ/ በካቴድራሉ አካባቢ የሚገኘውን ቦታ ለባለ ርስቶች ግምት ከፍለው በርስትነት የሰጡት ፤

መ/ አሁንም እንደገና ፴ ጋሻ መሬት በርስትነት ስለሰጡት ራሱን ችሎ ለሌላው በመርዳት ላይ ይገኛል ።

ውስጣዊ አገልግሎት ፤

ይህ ካቴድራል ለኢትዮጵያችን አንደኛ ካቴድራል እንደመሆኑ መጠን ማንኛውም ከፍተኛ የአገልግሎት ሥነ ሥርዓት ይፈጸምበታል ፤ ዓመት እስከ ዓመት ያለማስታጎል ይቀደስበታል ፤ ስለዚህም በቅዳሴ በዝማሬ ራሳቸውን የቻሉ መዘምራንና አገልጋዮች በብዛት ይገኛሉ ፤ እነርሱም ስብሐተ እግዚአብሔር ሁልጊዜ በሚገባ ያደርሱበታል ። ካቴድራሉ ፤ የሚመራው በቀጥታ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጎ አድራጎት ድርጅት ነው ፤ ስለሀብቱ ስለንብረቱ አያያዝ መልካም ክንውን ይኖረው ዘንድ ይኸው ድርጅት ይቆጣጠረዋል ፤ የውስጥ ሥራውን የሚያካሒደው ግን የተለየ ቆሞስ በንጉሥ ነገሥቱ የሚሾም የመዐርግ ስሙ ሊቀ ሥልጣናት የሚባል አለው ።

ካቴድራሉም ከዚህ የሚከተሉት የዕለትና የሳምንት ፕሮግራሞች ይገኙበታል ፤

ሀ/ የዘወትር ጸሎት

፩ኛ/ የጧት ጸሎት ዘወትር ከ፲፪—፩ ሰዓት ተኩል ይሆናል ፤

፪ኛ/ የማታ ጸሎት ዘወትር ከ፲፩—፲፪ ሰዓት ይሆናል ፤

፫ኛ/ ሁልጊዜ በየወሩ ከልደታ እስከ ሥላሴ ፤ እንዲሁም በሌላ ጊዜ በልዩ ልዩ በዓላት ጸሎተ ምሕላ ይደረጋል ።



www.ethiopianorthodox.org

ለ/ ቅዳሴ ፤

፩ኛ/ ቅዳሴ ሁልጊዜ ከጧቱ ፩ ፡ ፴ — ፪ ፡ ፴ ይሆናል ፤ በጾም ጊዜ ግን ከቀኑ ፯ ሰዓት ጀምሮ በ፰ ሰዓት ተኩል ይፈጸማል ።

፪ኛ/ በየሳምንቱ የቅዳሜ ዕለት ቅዳሴ በተለይ ለሕፃናት መታሰቢያ ስለሆነ ልዩ ጸሎት ይደረጋል ፤

፫ኛ/ እሑድ በየሳምንቱ ቅዳሴው ከ፩—፪ ፡ ፴ ይሆናል ።


፬ኛ/ ቅዱስ ቁርባንን ለምእመናን ለመስጠት ግን ሁልጊዜ ቤተ ክርስቲያን ዝግጁ ናት፤

፭ኛ/ በየሳምንቱ እሑድና በታላላቅ በዓላት የእግዚአብሔር ቃል (ስብከት) ያለማቋረጥ ይደረጋል ፤

፮ኛ/ ስብሐተ እግዚአብሔር (ማሕሌቱ) በታወቁ በዓላት በየወሩና እሑድ የበሳምንቱ እንዲሁም ከፍ ባሉ የዓመት በዓላት ጣዕም ባለው ዜማ ይደረሳል ።

የገዳሙ የሥራ አመራር ፤

መንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ራሱን የቻለ አስተዳደር እንዲኖረው በማለት በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጎ አድራጎት ድርጅት ሥር ይተዳደራል ። ነገር ግን ሀብቱም መብቱም የተለየ ሆኖ ራሱን በቻለ አስተዳደር እንደሚከተለው ይካሔዳል ።




## ፪ኛ| ምስካዬ ኅዙናን መድኀኔ

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የታወቁ መንፈሳዊ እንደመሆናቸው በሰላም በጦርነትም ጊዜ ከአምላካቸው እግዚአብሔር ርቀው ወይም ተለይተው አያውቁም ። ስለዚህ በአቅራቢያቸው የጸሎት ቤትና ካህን ተለይቷቸው አያውቅም ። በተለይም በመድኃኔ ዓለም ስም የተሰየመውን ጽላት በስደት ጊዜ ከሔዱበት አብረው ወስደው ሲኖር በድል አድራጊነት በተመለሱና በዙፋናቸው በተቀመጡ ጊዜ ለርሱም ይኸን ዓይነት ቤተ ክርስቲያን አሠሩለት ።

ስለምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ጽላት አመጣጥና ስለ ቤተ ክርስቲያኑ ሕንፃ አሠራር



www.ethiopianorthodox.org

እንዲሁም ስለ ማኅበራዊ ኑሮ አመሠራረት መግ ለጫ ።

፭ኛ/ ኢትዮጵያን ጠላት በወረራት ጊዜ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በስደት እንግሊዝ አገር በነበሩ ጊዜ ወደ ብፁዕ እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ አሁን ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ የተባሉትን አንድ ጽላትና ለአገልግሎት የሚበቁ አምስት መነኮሳት ወደ እንግሊዝ አገር እንዲልኩ ክቡር አባቴ ሐናን ከሚከተለው ጽሑፍ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ላኩ ።

የግርማዊነታቸው መልእክት ፤

ሞዓ አንበሳ ዘእምነ ገደሁዳ

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ

ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ይድረስ ከብፁዕ አባቴ እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ እንደምን ሰንብተዋል ፤ እኛ እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነን ። እስካሁን ባለነው አኳኋን የምናስበው ለናንተ ነው እንጂ ወደኛ ምንም የሚሐያሳስብ የለም ። ይልቁንም የኛ እዚህ መሆንና በየጊዜው ጀኔብ በሚደረገው ስብሰባ ፤ ቢፈቀድልን የኛ መሔድ ባይፈቀድልንም መላክተኞችንን መላክ ለመጣንበት ጉዳይ ዋና ረዳታችን ስለሆነ የፈጣሪያችን ፍርድ የኢትዮጵያን ጉዳይ እስካጠቃለለልን ድረስ እዚሁ ሁኖ ማዳመጥ የሚያስፈልግ መሆኑን ስለተረዳነው የፈጣሪያችንን ቁርጥ እስክናውቅ ድረስ በዚሁ በእንግሊዝ አገር ለመቆየት ቆርጠናል ።

የእግዚአብሔር ቸርነት ፈቅዶልንና አሰናብቶን ወደ ኢየሩሳሌም . እስከምንመጣበት ቀን ድረስ የሃይማኖት ችግር እንዳያገኘን የሚያድጉትም ልጆቻችን የሃይማኖታቸውን መሠረት እንዳያጡት አስበን አንድ ጽላትና አምስት መነኮሳት የሚያስፈልጉትን ንዋየ ቅድሳትና መጻሕፍት ሰጥተውት ይዞ እንዲመጣ አባ ሐናን ልኬዋለሁና ከመምህር ገሪማ ጋራ ተማክራችሁ ዐቢይ ጾም ሳይገባ እንዲደርስ አድርጋችሁ እንድትኩልን ይሁን

በየጠረፉችንም ተሰደው በሰው ግዛት ላሉትም ሰዎቻችን እንደዚሁ ሰው መላክ አስፈላጊ ሳይሆን አይቀርምና እየተመካከራችሁበትና ፈቃዱ የሚሆን መነኩሴ እየመረጣችሁ እስክናስታውቃችሁ ድረስ መጠበቅ ነው ፤

ጥር ፲፫ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ/ ም/ ለንደን

ብፁዕ እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስም የግርማዊ ጃንሆይ መልእክት ከደረሳቸው በኋላ በስመ መድኃኔ ዓለም የተጠራ ጽላት ለቁርባንና ለጸሎት የሚያስፈልጉትን ንዋየ ቅድሳትና መጻሕፍት ጭምር በአምስት መነኮሳት እጅ አስይዘው በፍጥነት ወደ እንግሊዝ አገር ላኩ ።

የመነኮሳቱ ስም

፩ኛ/ መምህር ገ/ኢየሱስ መነኮስ ወቅ ሞስ

፪ኛ/ አባ ሐና መነኮስ

፫ኛ/ አባ ማርቆስ መነኮስ

፬ኛ/ አባ ኃይሌ ብሩክ መነኮስ

፭ኛ/ አባ ገብረ ማርያም መነኮስ ፤ እነዚህ መነኮሳትም እንግሊዝ አገር ከደረሱ በኋላ አንድ መካነ ጸሎት ባርከው እንደ ቤተ ክርስቲያን ሕግ የጸሎትና የቁርባን ሥርዓት ያደርጉ ጀመር ፤ ከዚያም የተነሣ ያች ቤተ ክርስቲያን በስደት ያለች ኦርቶዶክሳዊት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተብላ ትጠራ ጀመር ።

የጸሎት መጽሐፍም የተዘጋጀው በአማርኛ ስለነበረ በግርማዊነታቸው ትእዛዝ በሊቶ ግራፍ ተባዝቶ በየጠረፉ ላሉ ኢትዮጵያውያን እንዲላክ ተደረገ ፤ በእንግሊዝ አገርም ሆነ በየጠረፉ ያሉት ኢትዮጵያውያን ምእመናን በዚህ መጽሐፍ እየጸለዩ የእግዚአብሔርን ምሕረት የኢትዮጵያን ማጣት እየጠበቁ ደጅ ሲጠኑ ከኖሩ በኋላ ጊዜው ሲደርስ የነፃነቱ ብርሃን ተገለጠ የጠላት ኃይል ተደመሰሰ ።

በ፲፱፻፴፫ ዓ/ም/ ሚያዝያ ፳፯ ቀን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ የነፃነት ሰንደቅ ዓላማ ይዘው በታላቅ ግርማ ተመልሰው በመንበረ መንግሥታቸው ተቀመጡ ። በስደት የነበረች ኦርቶዶክሳዊት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲ ያንም ወደርስቷ ተመለሰች ። በዘመን ስደት ም ራን ጸሎት ወመሥዋዕት የነበረው ታቦተ መድኃ ዓለም ግርማዊት እቴጌ መነን ከእንግሊዝ አገ



www.ethiopianorthodox.org

ወደ አዲስ አበባ በገቡበት ፲፱፻፴፫ ዓ/ ም/ ነሐሴ ፳፫ ቀን አብሮ አዲስ አበባ ገባ ። ከዚያም በኋላ ፲፱፻፴፰ ዓ/ ም/ ሚያዝያ ፳፯ ቀን በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሆስፒታል ግቢ በታነፀው ቤተ ክርስቲያን ምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ተብሎ ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ ።

ቅዳሴ ቤቱ ከተከበረ በኋላም በስደት አገር ሲጸለይ የነበረው የአማርኛ ጸሎት በክቡር አባቴ ሐና ፤ እንዲሁም በአባ ኃይሌ ብሩክ መሪነት ይካሔድ ጀመረ ። በዚህም አገልግሎት ለጊዜው ተካፋይ የነበሩ መነኮሳት ስም ዝርዝር የሚከተለው ነው ።

፩ኛ/ አባ ገብረ ጊዮርጊስ
፪ኛ/ አባ ገብረ ኪዳን
፫ኛ/ አባ አሥራት
፬ኛ/ አባ ተክለ ሃይማኖት
፭ኛ/ አባ ገብረ ሥላሴ

አስደናቂ የሆነው የአዲሱን የጸሎት ሥርዓት ለመመልከትና በጸሎቱም ለመጠቀም የአዲስ አበባ ምእመናን ጧትና ማታ ወደ ምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን በብዛት ሲጐርፉ ይታዩ ነበር ፤ በእንደዚህ ያለ አኳኋን እስከ ፴፯ ዓ/ ም/ ከቆየ በኋላ ስማቸው በአንደኛ ቁጥር የተጻፈው መነኩሴ ተተክተው አገልግሎታቸውን ቀጠሉ ። በዚህም ጊዜ ለአገልግሎት የተቀጠሩት አራቱ መነኮሳት ማኅበራዊ ኑሮ ጠቃሚ መሆኑን ስለተረዱት በማኅበራዊ ኑሮ ለመኖር ተመካክረው ከተስማሙ በኋላ ለገዳሙ አባት ለአባቴ ሐና ነገሯቸው ፤ አባቴ ሐናም አሳቡን በደስታ ተቀብለው ስለፈቀዱ አራቱም መነኮሳት ለጊዜው ከሚያገኙት ቀለብ አምስት አምስት ብር አዋጥተው የንፍሮ ጥሬ ሸምተው ንፍሮ ቀቅለው ብፁዕ አጨጌ አሁን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስንና እንዲሁም ሌሎች መምህራንን ጠርተው ፲፱፻፴፯ ዓ/ ም/ ግንቦት ፲፯ ቀን በቅዳሴና በብፁዕ አጨጌ ቡራኬ አሁን ተስፋፍቶ የሚታየው የማኅበራዊ ኑሮ የአንድነት መሠረት ተመሠረተ ። መነኮሳቱም ይህ አንድነት ከተመሠረተ በኋላ አሳባቸውን በመሰብሰብና ለጸሎቱም የተለየ መልክ በመስጠት ሲያገለግሉ ባዩ ጊዜ ሕዝቡ እየበዛ በመሔዱ ቤተ ክርስቲያኑ መጠነኛ ስለሆነ ከመጥበቡ የተነሣ ይበልጠው ሕዝብ በውጭ አስቀድሶና ጸልዮ ይሔድ ነበር ፤ ይልቁንም የተፈሪ መኰንን ወንዶች ተማሪዎችና የግርማዊት እቴጌ መነን ሴቶች ተማሪዎች እሑድ እሑድ የማይለዩ ስለነበረ አርቆ አስተዋይ የሆኑ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የተማሪዎቹን መንፈሳዊነትና ትጋት ተመልክተው ይህ ቤተ ክርስቲያን አሁን በሚገኝበት ቦታ ላይ እንዲሠራ ንጉሠ ነገሥታዊ ትእዛዝ ሰጡ ። የመሠረቱንም ድንጋይ ፲፱፻፴ ዓ/ ም/ ሚያዝያ ፳፯ ቀን አኖሩ ፤ የመሠረቱን ድንጋይ ባኖሩ ጊዜ ለሕዝቡም ሆነ ለተማሪዎቹ የሚጠቅም ንግግር አደረጉ ።

<u>የግርማዊነታቸው ንግግር ።</u>

ሚያዝያ ፳፯ ቀን ወደ መናገሻ ከተማችን የገባንበትና በናፍቆት ሲጠባበቀን የነበረ ሕዝባችን ከጠላት እጅ ወጥቶ የተገናኘንበት ዕለት ስለሆነ ከ፲፱፻፴፫ ዓ/ ም/ ጀምሮ በየዓመቱ የሚከበር የታላቁ በዓላችን መታሰቢያ ነው ።

የዚሁ በዓል ሰባተኛው ዓመት በሚከበርበት በዛሬ ቀን ሚያዝያ ፳፯ /፴ ዓ/ ም/ ለምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም አዲሱን ቤተ ክርስቲያን ስንመሠርትና የመጀመሪያውን ድንጋይ በመሠረቱ ላይ ስናኖር ከዚህ ሰዓት ላደረሰን ለእግዚአብሔር ምስጋና እናቀርባለን ።


የበዓሉን መታሰቢያ በየዓመቱ ሚያዝያ ፳፯ ቀንን የምናከብርበት ይህ ምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ጽላቱ በቅድስት ሀገር በኢየሩሳሌም በኢትዮጵያ ገዳማችን በዴር ሡልጣን ቤተ ክርስቲያናችን ይኖር ነበር ፤ በዘመነ ስደት አውሮፓ በነበርንበት ጊዜያት አምስት መነኮሳት ጽላቱን ይዘው ወደ እንግሊዝ አገር እንዲመጡ አድርገን ለጊዜው ማረፊያ ሆኖን በተቀመጥንበት ፤ ባት በሚባል ሥፍራ በሚገኘው ቤታችን አንድ ቤተ ጸሎት አሰናድተን በሚያዝያ ፳፯/ ፲፱፻፳፱ ዓ/ ም/ ቅዳሴ ቤቱን አክብረንለት ነበር ። በ፲፱፻፴፫ ዓ/ ም/ ተስፋው ደርሶ እንደዛሬው ቀን ሚያዝያ ፳፯ ቀን የነፃነት ምልክት ሰንደቅ ዓላማችንን ያቆምንበትና ድልን ያረጋገጥንበት ዕለት ሆነ ።



www.ethiopianorthodox.org

ከዚያም በኋላ ታቦተ መድኃኔ ዓለም ወደ አዲስ አበባ እንዲመጣ አድርገን ስማችን በሚጠራበት በሆስፒታላችን ክበብ ውስጥ በታነፀው ቤተ ክርስቲያን ሚያዝያ ፳፯ ቀን ፲፱፻፴፫ ዓ/ም/ ተከልነው ።

አሁን ደግሞ በተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት ክበብ ውስጥ ይህን የአዲሱን ቤተ ክርስቲያን መሠረት ስንመሠርት በዚህ ተማሪ ቤት የሚማሩት ክርስቲያናውያን ወጣቶች የኦርቶዶክሳዊት ዓ. ም. ቅዳሴ ቤቱ በታላቅ ሥነ ሥርዓት ተከበረ ። በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሆስፒታል በነበረ ጊዜ ይሠራ የነበረው ማንኛውም ሥራ የጨቱም ሆነ የማታው ጸሎት መጨመር እንጅ መጉደል ሳይኖርበት እየቀጠለ የአንድነቱ ሁናቴም ከላይ በተገለጠው አኳኋን ሥራውን እያስፋፉ ሔደ ።



የምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን

ሃይማኖታቸውን ሥርዓት. እንዲጠቀሙበት አስበን ነው ።

የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው ፤ ሃይማኖቱን የማያከብር ሃይማኖት የሌለው እርሱም የሚያምነው ደገፉ የሌለው እርሱንም ማንም የማያምነው የሁለት ዓለም ስደተኛ ነው ። ፍሬውን ለማየት ተስፋችን እርሱ ምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ነው ።

አ/ አ/ ሚያዝያ ፳፯ ቀን ፴ ዓ/ ም/

የቤተ ክርስቲያኑ ሥራም በተፋጠነ አኳኋን ቀጥሎ ልክ በሁለት ዓመቱ ተፈጽሞ ፲፱፻፴፪

<u>የሥራ አመራሩ ፤</u>

ይኸ ቤተ ክርስቲያን ለአዲሱ ዘመናችን አዲስ አቅድ ይዞ በመገኘቱ ሕዝቡ ሁሉ ከሩቅ ሰበካ ወደዚሁ ቤተ ክርስቲያን ሲጐርፍ ይገኛል። ለአገልግሎቱ ብቁ የሆኑ በትምህርታቸው የበሰሉ መነኮሳት ይገኛሉ ፤ ኑሮዋቸውም በማኅበር ፤ (በአ ንድነት) ነው ። የሥጋጃ ሥራ በመሥራት ኑራቸ ውን ያደረጃሉ ። በግል ስሜታቸውና በዘወትር ጸሎታቸው ብዙ ምእመናን ስለተጠቀሙ ለመር ዳት እጃቸውን እንደዘረጉላቸው ይኖራሉ ።


መነኮሳቱ በማኅበራዊ ሕይወታቸው ፤ በማኅ በራዊ ሥራቸው ተመልካቾችን ሳይስቡ አልቀ ሩም ። እንዲያውም አገር ጐብኝዎች የኢትዮጵያ ገዳማት መልክ ነው ሁሉም እንደዚህ ሳይሆን



www.ethiopianorthodox.org

አያተርም ብማለት በነርሱ ሥራ የሌሎቹ ገዳማት ስም ለመጠበቅ ቻለ ።

አሁን 15 -መነኮሳት 13 ዲያቆናት 14 ሠራተኞች የሚገኙ ሲሆን በጠቅላላ ድምር- 46 ሰዎች ይገኙበታል ።



አዲሱ የደብረ ሊባኖስ ቤተ ክርስቲያን

## ፫ኛ| የደብረ ሊባኖስ ገዳም ሕንፃ መሠረት

ይኸ ገዳም ከአፄ ይኩኖ አምላክ ጀምሮ የታወቀ ሲሆን ፤ በአተካከል ሌሎች ገዳማት ይቅደሙት (ይብለጡት) እንጂ ጻድቁ ስለ ሀገርና ስለ ክርስቶስ ፍቅር በበለጠ የሠሩ በመሆናቸው በኢትዮጵያውያን ሁሉ ዘንድ ተወዳጅነትን ፤ ዝናን በማግኘታቸው ፤ ፩ኛ/ በመንግሥት ዘንድ ከሁሉ የበለጠ ክብርን አገኘ ፤ ፪ኛ/ በቃል ጊዳኑም ሕዝቡ በይበልጥ ስላመነበት ከፍ ያለ ክብርን አገኘ ፤ ፫ኛ/ ከዘመናት ወደዘመናት ሲሸጋገር ከነመብቱ ከነሀብቱ ስለተገኘ እስካሁን ድረስ ገዳሙ እንደ ነበረ ይገኛል ።

በዚህ ሁሉ ምክንያት ከኢትዮጵያ ነገሥታት ብዙዎቹ ያማረ በመሰላቸው ጊዜያቸውም በፈቀደላቸው ጥበብ ሕንፃውን አሠርተዋል ። ለምሳሌ በቀድሞ ዘመን ከአሳነፁት ውስጥ ፩ኛው አፄ ይኩኖ አምላክ ሲሆኑ ፪ኛው አፄ ይስሐቅ ናቸው ፤ በቅርቡ ጊዜ ደግሞ አፄ ዮሐንስ ፤ እንዲሁም አፄ ምኒልክ በጊዜያቸው በአማረ ሁናቴ አሠርተውት ነበር ። አፈሩ ለሕንፃው የማይስማማ ነፋስ የሚጫወትበት በመሆኑ ግን ግንቡ ለብዙ ጊዜ ሊያገለግል አልቻለም ። በዚህም ምክንያት በተሎ ይናድ ነበር ። ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የቀድሞው ሕንፃ መንቃቱን ተመልክተው ሕንፃውን በአዲስ አቅድ ለመሥራት እንደነገሡ የገቡት ቃል ኪዳን ጽኑዕ ስለነበረ ፤ በየጊዜው ባለመዘንጋት ከፍ ያለ ጥናት ሲያደርጉ ከቆዩ በኋላ የእግዚአብሔር ቅዱስ



www.ethiopianorthodox.org

ፈቃድ በሆነ ጊዜ በመልክ የተዋበውን በሥራ ጥንካሬ ያለውን በስፋትም መጠነኛ የሆነውን ይኸን ታላቅ ሕንፃ አሠሩ ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ይኸን ገዳም በበለጠ ለማክበር ሕንፃውንም በበለጠ አቅድ ለማሠራት ቅዱስ አሳብ ስለኖራቸው ኅዳር ፲፯ ቀን ፲፱፻፳፰ ዓ/ ም/ ከገዳሙ ድረስ ሔደው ብጽዐታቸውን በጊዜው እጨጌ ለነበሩት አሁን ፓትረያርክ ለሆኑት ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ በወንጌል ዘወርቅ ላይ ጽፈው ሰጧቸው ። ቃሉም ይኸ ነበር «በገንዘብ የማትገዛ አምላክ መሆንህን አምናለሁ ያንተ ያልሆነ የለኝምና ? - - » ይኸም ወንጌል ዘወርቅ ገዳሙ ሲጠፋ አባቶች ሲሞቱ ንብረቱም ሲበዘበዝ አብሮ ተዘርፎ ሔዶ ስለነበር ከሰው ወደ ሰው ሲዘዋወር ከብፁዕ አቡነ አብርሃም እጅ ገባ እርሳቸውም የሀገር ፍቅር የሠፈረባቸው የንጉሠ ነገሥታቸው ፍቅር እንደእሳት ያቃጠላቸው ስለ ነበሩ ፤ በምሥጢር ጠብቀው አቆይተው በሚያርፉበት ጊዜ ትንቢት ተናግረው ለሚወዷቸው መንፈሳዊ ልጃቸው ለመምህር ሰይፈ ሥላሴ «ይኸን የንጉሠ ነገሥታችን የብፅዓት ቃል ያለበት መጽሐፍ ነው መምጣታቸው አይቀርምና እንደገቡ እንዲሰጡልኝ» ሲሉ ከአደራ ጋር ሰጧቸው ። እኚህ ቅዱስ መምህርም ይኸን ጊዜ ሲጠብቁ ቆይተው የመከራው ዘመን ተፈጽሞ ንጉሠ ነገሥታችን በድል አድራጊነት እንደገቡ ብፁዕ አቡነ አብርሃም ሰማይ ሩቅ አደራ ጥብቅ ብለው የሰጡኝን አደራ ይረከቡኝ ሲሉ ለግርማዊነታቸው አስረከቡ ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትም መጽሐፉን እንደ ተቀበሉ ሌላ የብፅዐት ቃል አሠፈሩበት ቃሉም «እንደሌለህ የቆጠረህን የሙሶሊኒን ኃይል ከነሠራዊቱ የሰበርክ ፤ የተጠቃችው የኢትዮጵያን በእውነተኛ ፍርድህ የተመካችውን ያላፈርክ ፤ ምስጋና ለአንተ ብቻ ይገባል ፤ የአገርህን የኢትዮጵያን ነፃነት ለአንተ አደራ እላለሁ ፤ እኔ እንደ አባቶቼ እንግዳ ነኝ ። ነሐሴ ፱ ቀን ፲፱፻፴፫ ዓ/ ም/ ቀ· ኃ· ሥ· ንጉሠ ነገሥት»

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ምቹ ጊዜና የእግዚአሔርን ቅዱስ ፈቃድ ሲጠብቁ ቆዩ ። ሁኖም ለገዳሙ ሕንፃ ማሠሪያ መነሻ ይሆን ዘንድ ከልዩ ግምጃ ቤታቸው ወጭ አድርገው ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስና ለክቡር አባ ሐና ጂማ ሰጡ ፤ በዚህም ገንዘብ አክሲዮን በመግዛት በልዩ ልዩ የልማት ሥራ ገቢ እያደረጉ ክቡር አባ ሐና ጂማ ስለሠሩበት ከ፲፱፻፴፬ ዓ/ ም/ ጀምሮ እስከ ፲፱፻፵፪ ዓ/ ም/ በጥሬ ገንዘብ የተገኘው ፩ ሚሊዮን ፪፻፳፯ሺ ፩፻፵፰ ብር ከ፵፩ ሣንቲም ሆነ ።

የቤተ ክርስቲያኑ የሥራ ጥናት ተጠናቆ አልቆና በ፲፱፻፵፪ ዓ/ ም/ ግንቦት ፳፬ ቀን ፶፪ ዓ/ ም/ የመሠረቱን ድንጊያ ግርማዊነታቸው አስቀመጡ ። ይኸንም የሥራ ክንውን የሚቆጣጠር በልዑል አልጋ ወራሹና በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ሰብሳቢነት የሚመራ ቦርድ ተቋቋመ ። እነዚህም ።

፩ኛ/ ልዑል ደጃዝማች አሥራተ ካሣ ፤ ፪ኛ/ ልዑል ደጃዝማች መንገሻ ሥዩም ፤ ፫ኛ/ አባ ሐና ጂማ ፤ በኋላ ክቡር ባላምባራስ ማኅተመ ሥላሴና ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ እንዲተኩ ሆነ ፤ ቦርዱም በአጥኚው ኩባንያ እየተረዳ በሥራ ሚኒስቴር መሪነት እየተቈጣጠረ ሥራውን በሚገባ አሠራ ። ሥራው ተጠናቆ ስላለቀ ኅዳር ፱ ቀን ፲፱፻፶፰ ዓ/ ም/ ተፈጽሞ ቅዳሴ ቤቱ ተመረቀ ።

<u>የደብረ ሊባኖስ ቤተ ክር/የፈጀው ገንዘብ</u>

ሀ/ ለዋናው ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ሥራ $ 742,375.33

ለ/ ለልዩ ልዩ ዕቃና ለሥዕል ሥራ $459,701.13

ሐ/ ለአጥር ሥራ ለድልድልና ለዕቃ ቤት ሥራ $88,919.82

መ/ ለእንግዶች ማረፊያ የግቢው አስፋልት ሥራ $165,479.87

ሠ/ ለጥናት መቆጣጠሪያ የወጣ 116,709.15

ረ/ ለመሐንዲሶች አበልና መጓጓዣ $20,000

ጠቅላላ ድምር $1,593,185.30 ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

## የምረቃው ሥነ ሥርዓት ፤

የደብረ ሊባኖስ ገዳም ሕንፃ ተፈጽሞ በተመረቀበት ፤ ቅዳሴ ቤቱም በተደረገበት ዕለት ሲመርቁት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ከንጉሣውያን ቤተሰብ ጋር ፤ እንዲሁም ክቡራን ሚኒስትሮች ፤ የአዲስ አበባ አድባራት መምህራን እንዲሁም የአዲስ አበባ ነዋሪ ሕዝብ የሰላሌ አውራጃ ሕዝብ በብዛት ከዋዜማው ጀምሮ በገዳሙ ክበብ አድሮ ነበር ። ሌሊቱን ሁሉ ስብሐተ እግዚአብሔር ሲደርስ አድሮ ከንጋቱ ፲፪ ሰዓት ሲሆን ጸሎተ ቅዳሴው ተጀመረ ። በዚህም ጊዜ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በየመንበር ተደልድለው ቀድሰዋል ፤ ጸሎተ ቅዳሴው ተፈጽሞ የምረቃው ሥነ ሥርዓት ሲጀመርና የሠሌዳውን ጽሑፍ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሲገልጡ ፳፩ ጊዜ መድፍ ተተኰሰ ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ያሰቡት ሁሉ በየመልኩ ስለተፈጸመላቸው በተለይም ይኸን ገዳም የገዳማት ሁሉ ራስ እንደመሆኑ ሥራው በልዩ አቅድ እንዲሠራ ባዘዙት መሠረት ስለተፈጸመላቸውና ሥራውም በተፋጠነ ሁኔታ መልካም ውጤቱን ስለሰጠ ፤ ፈጣሪያቸውን በማመስገን ከዚህ የሚከተለውን ተናገሩ ።

የጻድቁ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ስም በሚጠራበት በዚህ ገዳም የዛሬ ሁለት ዓመት የዚህን ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ የመሠረቱን ድንጋይ ባኖርን ጊዜ እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ፍጻሜውን እንዲያሳየን ተስፋችንን ገልጠን ነበር ። እነሆ ሁሉን ማድረግ የሚቻለውና የለመኑትን የማይነሣ አምላክ የሕንፃው ሥራ ተፈጽሞ ለማየት አበቃን ፤ ይህን ላደረገልን አምላክ ከምስጋና በቀር ምን ውለታ ልንመልስለት እንችላለን ?

ኢትዮጵያዊው ሐዋርያ አቡነ ተክለ ሃይማኖት «ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል ? መከራነውን ? ወይስ ጭንቀት ፤ ወይስ ረኀብ ፤ ወይም ራቁትነትነው ? ብሎ ቅ-ጳውሎስ የተናገረውን ቃል ተመልክተው የሐዋርያነት ተግባራቸውን የፈጸሙ ከፍ ያለ ተጋድሎና ትሩፋት የሠሩ የክርስትና ዓምድ እንደነበሩ የታመነ ነው ፤ ከሳቸውም የቆብ ልጅ ሆነው የታወቁት ገዳማት ብዙ ናቸው ። በያለበት ልጆቻቸው ያስተማሩትም ከፍ ያለ ቁጥር ነው ። ኢትዮጵያ በአረመኔነትና በእስላምነት እንዳትዋጥ አሥግቶ በነበረበት በዚያን ዘመን እርሳቸውና እርሳቸውንም የመሳሰሉት ሐዋርያት በሰጡት አገልግሎት ምክንያት ኢትዮጵያ የክርስትና ደሴት ተብላ ተጠርታበታለች ።

ይህን አጋጣሚ ጊዜ ምክንያት በማድረግ የኢትዮጵያ ጳጳሳትና የቤተ ክህነት መምህራን የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን አርአያነት በመከተል የክርስትናን ሃይማኖት ለማስፋፋት ድካማቸውን ባለመቆጠብ ፤ ራሳቸውን ለዚህ ታላቅ ሐዋርያዊ ተግባር መሥዋዕት በማድረግ እንዲሠሩና እንዲያሠሩ ልናሳስባቸው እንወዳለን ። ወንድም ለወንድሙ ከዚህ የበለጠ ትሩፋት ሊሠራለት አይችልም ።

እኛም በዚህ ገዳም አምላከ ተክለ ሃይማኖት ይህን ቤተ ክርስቲያን በዘመናዊ አቅድ ለማሠራት እንዲያበቃን ብፅዓት አቅርበንለት ነበር ፤ ልመናችንን ሰምቶ ብፅዓታችንን ስለፈጸመልን ለአምላካችን ክብር ምስጋና ይግባው ።

የሕንፃውን ሥራ እየተቆጣጠረ በሚገባ ለማስፈጸም አደራችንን የጣልንበት በብፁዕ አባታችን አቡነ ባስልዮስና በተወደደው ልጃችን በልዑል አልጋወራሽ አስፋ ወሰን ፕሬዚዳንትነት የሚመራው ቦርድ አባሎች ሥራውን በመልካም ስላስፈጸሙ ከልብ እናመሰግናቸዋለን ። ወደፊትም ለዚሁ ቤተ ክርስቲያን ንጽሕናና መልካም አጠባበቅ አስፈላጊውን ሁሉ እንዲያደርጉ አደራችንን ለፕሬዚዳንቱና ለቦርዱ አባሎች ጥለንዋል ።

በዚህ ገዳም በጻድቁ ስም ለተሰበሰቡት ምእመናንና አገልጋዮች የእግዚአብሔር ረድኤትና የጻድቁ በረከት እንዳይለያቸው እንለምናለን ።

በኋላም ስለበዓሉ ክብር ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ከፍ ያለ ግብር አግብተው በዚያ ያደረውና የዋለው ሁሉ ተጋበዘ ።

ስጦታ ፤ ፩ኛ/ ግምታቸው ሰባ ሺህ ብር የሆነ የፋርስ ምንጣፎች (ሥጋጃ) በያይነቱ ለገዳሙ ተሰጡ ፤



www.ethiopianorthodox.org

፪ኛ/ እንዲሁም ወርቅ ዘቦና ሙካሽ ሥራ ልብሰ ተክህኖ ለ፷ቱ ልዑካን የ፫ ገ ዜቅያሬ ተሰጠ።

፫ኛ/ ልዩ ልዩ ንዋየ ቅድሳትም እንዲሁ ተሰጥተዋል ።

# ፬ኛ የአክሱም ጽዮንን ቤተ ክርስቲያን

አክሱም የኢትዮጵያ የምሥራቅ ፀሐይ ክርስትና የወጣባት ፤ የኢትዮጵያ ቅድስት ከተማ ብዙ ሥራ የተሠራባት ናት ፤ በዚህም ምክንያት ነገሥታት ሁሉ አክብረውታል ፤ ሕጓና ሥርዓቷን ጠብቀውላት የምትኖር ገዳም ናት ። አክሱም ብዙ ጊዜ ፈርሳ ብዙ ጊዜም ተሠርታለች ። አሁን ያለውም ጥንታዊ በመሆኑ ብዙ ጉዳት ደርሶበት ስለሚታይ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በአዲስ ሕንፃ እንደሚያሠሯት የተስፋ ቃል ሰጡ ። በዚህም ቃል መሠረት የማዕዘን ራስ የሆነውን ድንጋይ ሲያስቀምጡ ከዚህ የሚከተለውን ተናገሩ ።

ለአክሱም ጽዮን ይህን አዲሱን ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ስንመሠርትላት ከዚህ ሰዓት ሳደረሰን አምላካችን ውለታውን ለመመለስየሚበቃ አቅም የለንም ፤ በ፲፱፻፳፰ ዓ/ም ስለአገራችን ነፃነት እየተዋጋን በትግሬ ግዛት ላይ በነበርንበት ጊዜያት ከሰላማዊ ሰዓት ደርሰን ይህን ሥራ እንድንሠራ ያበቃን ዘንድ ፈጣሪአችንን በሃይማኖት ለምነነው ነበር ። ሀገራችን በጠላት ከተወረረች በኋላም በስደት አገር በነበርንበት ዘመን ሁሉ ስለዚህ ነገር ሃይማኖትና ተስፋ ከልባችን አልተለዩንም ።

አምላካችን በይቅርታው በጎበኘን ጊዜ አገራችንን ከጠላት ቀንበር አውጥቶ እኛን ከዚህ ሰዓት አድርሶ የሐልዮው በገቢር እንዲፈጸም አደረገልን ። አክሱም በሐውልቶችዋ ስመ ጥሩነት በቤተ ክርቲያንዋ ጥንታዊነት የኢትዮጵያ የታሪክ ፋና ናት ። ሲያያዝ በመጣው ታሪክ እንደሚገኘው በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን የመጣችው ቅድስት ጽዮን በጥንቱ ዘመን አንበሳ ደግሞም መዝበር እየተባለ በሚጠራው በዚሁ አቅራቢያ በሚገኘው ቦታ በምኩራብ አሪት ነበረች ።

የክርስትናን ሥርዓት የጀመሩት አብርሃና አጽብሃ በነገሡበት ዘመን ግን ውኃ ሰፍሮበት የነበረው ይህ ሥፍራ ባሕሩ በተአምራት ደርቆላቸው የመጀመሪያይቱን ቤተ ክርስቲያን አሳነፁላት በዚያን ጊዜ ፲፪ የመቅደስ ክፍሎች እንደነበሩባት ይነገራል ። የጥንቱ ቤተ ክርስቲያን በጉዲት ከተቃጠለ በኋላም አንበሳ ውድም ባለሰባት ክፍል አድርጎ አሳንፆት ነበር ። ከዚያም ወዲህ በግራኝ ሠራዊት ስለተመዘበረች አንድ መቶ ዓመት ያህል ቆይቶ የተነሣው አፄ ፋሲል ይህን አሁን ያለውን ሕንፃ አሠርተውላት በየዘመኑም የነበሩ ታላላቅ ሰዎች እያደሱላት እስከ ዛሬ ቆይታለች።

እኛም በዚህ ቀን የዛሬ ፷፪ ዓመት ከኢትዮጵያ ተነጥላ የነበረችው ኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ እንድትመለስ ባደረግንበት በመጀመሪያው ዓመት ለእምነ ጽዮን የዚህን ቤተ ክርስቲያን የመሠረቱ ድንጊያ ስናኖር ስዕለታችን ከመፈጸሙ በላይ የደረሰው እጽፍ ደስታ የሚሰጠው የኤርትራ መመለስ አጋጣሚነት በፈጣሪያችን ፈቃድ የተፈጸመ ነው ።

በአብርሃ ወአጽብሐ ጊዜ የነበሩትም የቤተ መቅደስ ክፍሎች አሁንም እንዲኖሩ ምኞታችን ስለሆነ መካከሉ የእምነ ጽዮን መቅደስ ሆኖ በግራና ቀኝ ስድስት ስድስት መቅደሶች እንዲገኙባት አድርገናል ። የጥንቱ ቤተ ክርስቲያን ለሴቶች የተከለከለ ነበረ ይህ እኛ የምናሠራው መቅደስ ግን ሴቶችም ሳይከለከሉ እንደወንዶቹ ምእመናን ጸሎታቸውን ለማድረስ የተፈቀደላቸው እንዲሆኑ አድርገናል ። ። የጥንቱም ሕንፃ በየዘመናቸው ላሠሩት ለጥንታውያን ነገሥታት መታሰቢያነቱን እንደያዘ እንዲኖር ትተነዋል ።

በኢትዮጵያ ውስጥ ወደ አንደኛው ስመ ጥሩ ግዛታችን ትግሬ ለመጀመሪያ እንደደረስን የሥራ መጀመሪያ ያደረግነው ይህ የጽዮንን ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ መሠረት መጣል ስለሆነ አንድ የተከበረና የተቀደሰ ታላቅ ነገር ለመፈጸም ፈጣሪያችንን አበቃን ። ስለዚህም ለዘወትር እናመሰግነዋለን ።

ንግግሩም ካለቀ በኋላ መሠረቱ ወደ ሚጣልበት ሥፍራ ሔደው የወርቁን ማንካ ከሥራ ሚኒ



www.ethiopianorthodox.org

ሰትሩ ከክቡር ልጅ አርአያ አበበ ተቀብለው ሲሚ ንቶውን ፫ ጊዜ እያነሱ በማዕዘኑ ድንጋይ ላይ አ ስኖሩ ። የመሠረቱ ሥርዓት ፍጻሜ ካገኘ በኋላ ከዚያ የነበረው ሁሉ ደስታውን በጭብጨባ ገለጠው ።


ከመሠረቱ ላይ የተጻፈ ነዋሪ ቃል ፤
ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ቀዳ
ማዊ ኃይለሥላሴ ሥዩመ እግዚአብ
ሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

ቸርነቱን ያደረገልን በረድኤቱም ከዚህ ያደ ረሰን አምላካችን እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን በተወለድን በስድሳሁለቅ ዓመታችን የንጉሠ ነገሥት ዘውድ ደፋትን በነገሥን በ፳፫ኛው ዓመት ጠላታ ችንን ካገራችን አስወግደን የኢትዮጵያን ነፃነት ባስመለስን በ፲፪ኛው ዓመት ጥንት የኢትዮጵያ ግዛት የነበሩትን ብሔረ ኤርትራንና የባሕር ጠረ ፋችንን ወደ ኢትዮጵያ በመለስንበት በመጀበሪያ ዓመት ዛሬ በመስከረም ፲፪ ቀን ፲፱፻፵፭ ዓ/ም ባባ ቶቻችን በኢትዮጵያ ነገሥታት መዲና በአክሱም ለእመቤታችን ለቅድስት ጽዮን ማርያም ይህን አዲስ የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ መሠረትንላት ፤ይኸ ውም ቤተ ክርስቲያን እጅግ በማረ በዘመናዊ ሕንፃ እንዲሠራ ፈቃዳችን ስለሆነ ፤ ለቤተ ክርስቲ ያኑ ሥራ አንድ ሚሊዮን ሦስት መቶ ሽህ ብር ወጪ እንዲደረግለት አዘናል ።

ከወንዶች በቀር ሴቶች እንዳይገቡበት ሥር ዓት ተደርጎ የኖረው የጥንቱ ቤተ ክርስቲያን ለጥ ንቱ ሥራ መታሰቢያ ሆኖ ሥርዓቱን አጽንቶ እን ዲቆይ አድርገናል ። አሁን በመሠረትነው በዚህ በአዲሱ ቤተ ክርስቲያን ግን በሴትነትና በወንድ ነት ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ምእመናን ሁሉ ወንዶችም ሴቶችም ገብተው እንዲጸልዩበትና እግ ዚአብሔርን እንዲያመሰግኑበት ፈቅደናል ።

የዛሬ ፲፯ ዓመት አገራችን በጠላት ሳትወረ ርና ከተወረረችም በኋላ እኛ በስደት አገር ሳለን ከሃሌ ኩሉ አምላክ የኢትዮጵያን ነፃነት መልሶ ላገራችን ሲያበቃን ይህን ቤተ ክርስቲያን እን ድንሠራ ብፅዓት አድርገን ነበር ። ያንን ብፅዓት ለፈጸመልንና ይህን ለመሥራት ላበቃን እግዚአ ብሔር ምስጋና ይግባው ።

አሁንም እበውዕ ቤተከ ምስለ መባዕየ ወእ ሁብ ብፅዓትየ ዘነበበኩ በአፉየ ዘእቤ በክናፍርየ አመ ምንዳቤየ እያልን ከሕሊናችን የመነጨ ምስጋና በጸሎት እናቀርባለን ።



አዲሱ የአክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን



www.ethiopianorthodox.org

የመሠረቱ ሥነ ሥርዓት ከተፈጸመ በኋላ ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ቡራኬ ሰጥተው አሳረጉ ። ከዚያን ዕለት ጀምረው የአክሱም ቤተ ክርስቲ ያን ሥራ የ ጊቃናበትን ፕላኑ የሚዘጋጅበትን ዘዴ ካጠኑ በኋላ በልዩ ገንዘባቸው ለማሠራት ራሱን የቻለ ኮሚቴ አቋቋሙ ፤ ገንዘቡም በዚህ ኮ ሚቴ አማካይነት እንዲራባ ፤ ፕላኑም ከአጥኚው ኩባንያ ጋር ይህ ኮሚቴ እየተነጋገረ እንዲሠራ ትእዛዝ ሰጡ ።

የአክሱምን ቤተ ክርስቲያን የሥራ ውጤት ለሚጠባበቁ ኮሚቴዎች ሰብሳቢ ልዑል አልጋ ወራሽመርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ነበሩ ፤ ይኸም ቦርድ ፩ኛ ስለገንዘብ አወጣጥና አከፋፈል የሚመ ለከት ሲሆን ፤ ፪ኛ የሥራውን ሁናቴ የ ጊከታተል ነበር ፤ በዚህም ምክንያት የግርማዊነታቸው ረዳት የቅርብ ተመልካች ሁነው ይቈጣጠሩ ነበር ፤ በተ ለይም ሥራው መልካም ፍጻሜ ሊያገኝ የቻለበት ልዑል ደጃዝማች መንገሻ ሥዩም በቅርብ ሆነው በመከታተላቸውና በዕረፍት ጊዜያቸው በጉልበ ታቸው በመሥራታቸው ነው ።

የዚያ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ድንጊያ በተ ቀመጠበትና ሕንፃው በተሠራበት በመካከል ያለው ጊዜ ይርዘም እንጂ ሥራው በሚገባ ተፈጽሞ ይጠ በቅ የነበረው ተስፋ በደኅና ተፈጽሞ የቤተ ክርስ ቲያኑ ምረቃ ጥር ፳፬ ቀን ፲፺ ዓ/ም/ ሆነ ።

በዚህም ጊዜ ከዋዜማው ጀምሮ የጠ/ግዛቱ ገዳማትና አድባራት መምህራን እንዲሁም የአው ራጃው ካህናት ልብሰ ተክህኗቸውን በመልበስ ንዋየ ቅድሳታቸውን በመያዝ. ወደ አክሱም ይጐ ርፉ ነበር ።

ከሊቃነ ጳጳሳትም ውስጥ ከሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ከብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ሌላ የአሩሲ ሊቀ ጳጳስ ብጹዕ አቡነ ሉቃስ ፤ የጎንደር ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ የኤርትራ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ ፤ የኢሉባቦር ሀገር ስብከት ተጠ ባባቂ ብጹዕ አቡነ ቄርሎስ ፤ የመንበረ ጸባዖት ቅድ ስት ሥላሴ ካቴድራል አስተዳዳሪ ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ፤ የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ መምህር ገብረ ሥላሴ እንዲሁም ሌሎች ብዙ መነኮሳትና መምህራን በብዛት ይገኙ ነበር ።

በዚህም ጊዜ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ልዩ ግምጃ ቤት ሹም አድማሱ ረታ ፤ አሁን ብላታ የተባሉት ከሥራ ረዳቶቻቸው ጋር ለታላቁ ካቴድራል ለአክ ሱም ጽዮን ሊሰጥ የሚገባውን የዋጋው ግምት ሰማንያ ሺህ የኢትዮጵያ ብር የሆነውን አልባሳት ንዋየ ቅድሳት እንዲሁም ግምቱ ከፍ ያለ የሥጋጃ ምንጣፍ ይህንም የመሰለ ልዩ ልዩ ዕቃ ለመስጠት ና ሥነ ሥርዓቱን ለመጠበቅ ተገኝተው ነበር ። በዚህ ዕለት የተሰጠው የዕቃና የሽልማት ስጦታ ይህ ነበር ፤

በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገ ሥት መልካም ፈቃድ አዲስ ለተሠራው ለአክ ሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን የተሰጡ አልባሳትና ንዋየ ቅድሳት እንዲሁም ለካህናቱ የተሰጡ ልዩ ልዩ የሽልማት ልብሶች የሚከተሉት ናቸው ።

፩ ስድስት ቀይ ከፈይ ወርቅ ጥልፍ ካባ ላንቃ ግራና ቀኙ የመለአክ ሥዕል ቀንጐሥ ያለበት ፤

፪ ስድስት ቀይ ከፈይ ሙሻ ወርቅ ጥልፍ ሞጣ ሀት የጌታ ሥዕል ያለበት

፫ ስድስት ቀይ ከፈይ ሙሻ ከወርቅ ጥልፍ ድባብ ጥላ መያዣው ብርና ወርቅ ቅብ የሆነ ከው ጭ አገር ተገዝቶ የመጣ ፤

፬ ስድስት የቄስ ቀሚስ ብጫ አጥላስ ጨርቅ ለሙካሽ ጥልፉ ካባ ላንቃ የሚሆን

፭ ስድስት የቄስ ካባ ላንቃ ነጭ ሐር አጥላስ ጨ ርቅ

፮ ስድስት የቄስ ቀ ሚስ ሰማያዊ ባለዓይነት ጨርቅ

፯ ዘጠኝ የቄስ ካባ ላንቃ ባለዓይነት ጨርቅ

፰ ዘጠኝ የቄስ ቀሚስ ባለዓይነት ጨርቅ

፱ አሥራ ሁለት ባለዓይነት ጨርቅ የዲያቆን ቀሚስ ባለመደረቢያ

፲ ሁለት ብር ዘቦና ወርቀ ዘቦ መጎናጸፊያ

፲፩ አንድ ሙካሽ ጥልፍ ቀይ ከፈይ የሆነ መጐ ናጸፊያ



www.ethiopianorthodox.org

፲፪ ሦስት ወርቀ ዘቦ የዐውድ ልብስ
፲፫ ሦስት ወርቀ ዘቦና ብር ዘቦ ባለዘርፍ ሰማያዊ ጨርቅ የመጾር መስቀል መያዣ
፲፬ አሥራ ሁለት ማሕፈድ
፲፭ ሁለት ሰንና ብርት የብር ማስታጠ ቢያ ቀ. ኃ. ሥ. ያለበት ።
፲፮ አንድ የብር ማስታጠቢያ ከነሰሐኑ ቀ-ኃ-ሥ- ያለበት
፲፯ ሦስት ጻሕል ሀ ለቱ ከውጭ አገር የመጣ ቀ. ኃ. ሥ. ያለበት
፲፰ ሦስት ጽዋ ከነእርፈ መስቀሉ ቀ. ኃ. ሥ. ያለበት
፲፱ አንድ ወንጌል ባለብር ገበታ ወርቅ ቅብ የ ሆነ ቀ-ኃ-ሥ-ና የጌታ ሥዕል ያለበት
፳ ሦስት ከብርና ከወርቅ የተሠራ የእጅ መስ ቀል ቀ/-ኃ-ሥ- ና የጌታ ሥዕል ያለበት
፳፩ ሦስት ጽንሐሕ የብር የሆነ ቀ-ኃ-ሥ- ያለበት
፳፪ ሦስት የኒኬል ቃጭል
፳፫ ሦስት ባለመጾር መስቀል ብር ወርቅ ቅብ የሆነ ቀ. ኃ. ሥ. ያለበት
፳፬ ለንቡረ ዕዱ የሚሰጥ አንድ እጀታው የዝ ሆን ጥርስ የሆነ ብር ወርቅ ቅብ ጽናጽልና አንድ እጀታው ብር ቅብ መቋሚያ
፳፭ አሥር የብር ጽናጽል እጀታው ቀንድ የሆነ
፳፮ አሥር የብር መቋሚያ
፳፯ ሦስት ሱፍ ሥጋጃ ምንጣፍ መጠናቸው 4.80x3.50:4.45x 3.4.50x3
፳፰ አንድ የሐር ምንጣፍ መጠኑ 8.60x5. .80 የሆነ
፳፱ ሰላሳ ጥቁር ጁህ ሱፍ ካባ ቀ-ኃ-ሥ- ያለበት አስሩ እንገቱ ባለወርቅ ጥብጣብ
፴ አሥር አንደኛ ማዕርግ ባለወርቅ ጥብጣብ ቀሚስ አብደላ ከኒ
፴፩ አሥር ሁለተኛ ማዕርግ አብደላከኒ ቀሚስ
፴፪ አሥር ሦስተኛ ማዕርግ አብደላከኒ ቀሚስ
፴፫ አሥር አንደኛ ማዕርግ ድርብ
፴፬ አሥር ሁለተኛ ማዕርግ ድርብ
፴፭ አሥር ሦስተኛ ማዕርግ አረንጓዴ ጃኖ
፴፮ ሰላሳ ነጭ መብሩቅ ሱሪ
፴፯ አሥር ዱማስ እጀጠባብ
፴፰ አሥር ነጭ መርዶፋ ሱሪ
፴፱ አሥር ጥበብ ኩታ
፵ ለመጋረጃ የሚሆን ፩፻፲፩ ሜትር ከ፳ ሣን ቲም ቀይና አረንጋዴ ከፈይ ፪፻ ሜት ወርቅ ዘር ፍና ፶ ሜትር ወፍራም ብጫ ሐር ገመድና አሥር ብጫ ሐር ኳስ ተገዝቶ ለልዑል ደጃ ዝማች መንገሻ ሥዩም የተላከ ።

ሊቀ ጳጳሱ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስና ንቡረዕድ መኩሪያ አብዬ ሆይ እንዲሁም ቄሰ ገበዝ ተክለ ሃይማኖት ይኸን ንዋየ ቅድሳት ተቀብለው ለግር ማዊ ንጉሠ ነገሥት ልዩ ጸሎተ ቡራኬ አደረጉ ። ከዚህ በኋላ የዋዜማውን ሥነ ሥርዓት በአሮጌው ቤተ ክርስቲያን ከአደረሱ በኋላ አዲሱ ቤተ ክር ቲያን ቅዳሴ ቤት ሆነ ፤ ልዩ ጸሎትም ተደረገ ፤ በኋላም ሜሮን ተቀባ ይኸ ሁሉ ከተፈጸመ በኋላ ታቦተ ጽዮን ከአሮጌው ቤተ ክርስቲያን ወደ አዲሱ ቤተ ክርስቲያን በታላቅ ሰልፍ በዝማሬ ተዛወ ረች ። ይኸም በሆነበት ጊዜ ደወል ተደወለ እን ቢልታ ቀንደ መለከት ተነፋ ፤ የሕዝብ ሰልፍ ተደ ረገ ፤ መኳንንት ሴች ወይዛዝርት የደስታ ስሜታ ቸውን በዕልልታ ገለጡ ። አክሱም ታላቅ ነበ ረች ማለት ብቻ ሳይሆን በእርግጥም ታላቅነቷ ተገለጠ ። ማለት የቤት ክርስቲያኑ ስፋት የሥራው ጥብቀት የአቅዱ ማማር የስጦታውም ብዛት የሰ ልፉ ውጤት የሕዝቡ ብዛት በጠቅላላው ሥነ ሥር ዓቱን ለተመለከተው ሰው የአክሱም ጥንታዊ ክብር እንዴት እንደነበር ሊያስታውሰው ይች ላል ። በዚህ መልክ ታቦተ ጽዮን ወደ አዲሱ ቤተ መቅደስ ተዛወረች ። በመጨረሻውም ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ሰፋ ያለ ንግግር አድርገው የዋዜማው ምዕራገ ጸሎት ሆነ ። በአንድ በኩል ማህሌት ፤ በሁለተኛው በኩልጸሎቱ ሰዓታቱ ሲፈጸም አደረ ፤ ከንጋቱም አንድ ሰዓት ተኩል ሲሆን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በታላቅ አጀብ ታጅበው ለጸሎተ ቅዳሴው ደረሱ ፤ በዚህም ጊዜ ሕዝቡ -----የቀ



www.ethiopianorthodox.org

ደመ ክብሯን ስለመለሱ ቤተ መቅደስን ስለ ሠሩ በተለይም ለሴት ልጅ የእኩልነት አምልኮ ይገኝ ዘንድ ልዩነት የሌለበት ቤተ ክርስቲያን ስለመደረጉም ሁሉም በደስታ በሰልፍ ይጠባበቃቸው ነበር ፤ እንደደረሱም የደስታ ስሜታቸውን በልዕልታ ገልጠው ተቀበሏቸው ። ጸሎተ ቅዳሴው ፪ ሰዓት ተኩል ሲሆን ተፈጽሞ ዑደት ተደረገ ። በዚህም ጊዜ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ከዚህ የሚከተለውን ሰፋ ያለ ንግግር አደረጉ ።

ረቡዕ የካቲት ፫ ቀን ፲፱፻፶፯ ዓ/ም

# ግርማዊ ጃንሆይ የአክሱም ካቴድራል ሲመርቁ ያደረጉት ንግግር

ለአምላካችን ስሙ የሚጠራበት አገልግሎት የ ሚደረግበት ይህን ታላቅ የሆነ በታቦተ ጽዮን የተሰየመውን የአክሱምን ካቴድራል መርቀን እን ድንከፍት ስለፈቀ ደ ታላቅ ደስታ እየተሰማን ነው ። ታሪክ እንደሚመሰክረው የአክሱም ከተማ የተቆረቆረችው ከክርስቶስ ልደት በፊት በ፪ሺ፭፻፶ (በሁለት ሺህ አምስት መቶ አምሳ) ዓመት ግድም ኢትዮጲስ በተባለው በኢትዮጵያ ንጉሥ ነው ።

ከክርስቶስ ልደት በፊት በ፲፱፻፶ (በአንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃምሳ) ዓመት ውስጥ ቀዳማዊ ምኒልክ ሌዋውያንንና ከ፲፪ቱ የእሥራኤል ነገድ የበኩር ልጆችን ይዞ ወደ አክሱም መጥቶ ቤተ መቅደስን መሥርቶ ሕገ እግዚአብሔርን አቋቋመ ። ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ፫፻፴ ዓ. ም. ውስጥ ክርስትናንን የተቀበሉት አብርሃና አጽብሐ ለማሠራት ያሰቡትን ቤተ ክርስቲያን ዳግማዊ አጽብሐ በነ ግሠ በ፫፻፸፪ ዓ/ም ግድም ተጀምሮ በ፬፻፳፬ ዓ/ ም ውስጥ በንጉሥ ዩኢብ ተጠናቀቀ ።

ሁላችሁም እንደምታውቁት በሺ፭፻፴፩ ዓ/ም ብግራኝ ዘመን የአክሱም ቤተ ክርስቲያን ተቃጥሎ ነበር ። አክሱም ከክ ርስቶስ ልደት በፊ ት ጀምሮ የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ ብቻ ሳትሆን የሃይማኖት መዲናና የሕግጋት መነገሪያ ሆና የኖረች ቦታ መሆኗ የታወቀ ነው ። ቀዳማዊ ምኒልክና እናቱ ንግሥተ ሳባ ሕገ ኦሪትን እንደተቀበሉ አሁን ይህን ቤተ ክርስቲያን በሠራንበት ቦታ ላይ ታላቅ ቤተ መቅደስ ሠርተው አምልኮተ እግዚአ ብሔርን ይፈጽሙበት ነበር ።

ጥንታዊት ኢትዮጵያ ሰፊ ግዛትና ልዩ ነገዶች የነበሯት አገር ነበረች ። በታሪክ የታወቁ ብዙ ከተማ ዎችና ታላላቅ ሥራዎች የተፈጸሙባቸው ቦታዎች ነበሯት ። ከነዚህም ውስጥ እነመርዌን ፤ እነኖብያን ፤ እንሳባን እናስታውሳለን ። እንዲሁም ከደሴቶችና ከወደቦች እነ አዶሊስን ብናነሳ ታሪክ ይደግፈናል ። አክሱም ሥልጣኔ የገባባት ታላቅ የኢትዮጵያ በር ናት ። የፊደላትና የቅርጻ ቅርጽ አቅድ የተገኘው በአክሱም ዘመነ መንግሥት ነው ፤ አክሱም የግሪክ ፤ የፊኒቆስ ፤ የባቢሎን ሥልጣኔ ከኢትዮጵያ ሥልጣኔ ጋር በመቀነባበር ይታይባት የነበረች ዕውቀት በሰፊው ይሸመትባት ፤ ሕዝብ እንደልቡ ይገባባት ይወጣባት የነበረች ቦታ ናት ። አክሱም የሃይማኖት መዲና በመሆኗ ያለማቋረጥ ሕገ እግዚአብሔር የተነገረባት ከተማ ናት ፤ አክሱም የክርስትና ፀሐይ የወጣባት የኢትዮጵያ ምሥራቅ ናት ። አክሱም በኦሪትም በሐዲስም ተከብራ የኖረች የኢትዮጵያ ነገሥታት ታላላቅ ሥራቸውን የሠሩባት ፤ ግዳጃ ቸውን የፈጸሙባት ሕያው ታሪክ አላት ። ስለ ዚህ ነገሥታቶቿ ሁሉ አንዳንዶቹ ቤተ መቅደ ስን አንዳንዶቹ ልዩ ልዩ ሐውልቶችን አንዳን ዶቹ ልዩ ልዩ መታሰቢያዎችን የሠሩላት ስለሆነች እነዚህ ሁሉ እስከ አሁን ድረስ ቀዋሚ ምስክር ሆነው ለጐብኚዎች ሁሉ አስረጅዎች ናቸው ። አክሱምንም ስናነሳ የመጀመሪያው የአክሱምን ክብር ያስገኘውን ሕገ ኦሪትን ወደ አገሩ ያስመ ጣው ኢትዮጵያን ሀገረ እግዚአብሔር ያሰኘውን ቀዳማዊ ምኒልክ እንዲሁም ክርስትና ወደ አገራ ችን እንዲገባ አክሱም የክርስትና ፀሐይ መውጫ እንድትሆን የሠሩትን ለሥነ ጽሑፋችን መልክ የሰ



www.ethiopianorthodox.org

ሁለቱን ቅዱሳን ክርስቲያናውያን ነገሥታትን አብርሃና አጽብሐን በዚህ ሰዓት እናነሣቸዋለን ። ለኢትዮጵያ ስፋት ለወገን ኩራት በመሆን ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን የወሰኑትን የሥልጣኔና የነፃነት ደጋፊ የነበሩትን እነ አፄ ካሌብን ፤ እነ አፄ ገብረ መስቀልን ልናስታውሳቸው እንወዳለን ። በኋላም ዘመን ቢሆን የአክሱም ቅርስ እንዳይጠፋ ይህን ሁሉ በመመልከት እስከ፲ኛ ዘመነ መንግሥት ድረስ ለአክሱም የተለየ አስተያየት መደረጉ ታሪካዊ ሥራም መሠረቱ አልቀረም ፤ ለምሳሌ በጎንደር መንግሥት ጊዜ አፄ ፋሲል ይህን አሁን የሚገኘውን ሕንፃ በዘመናቸው ታላቅ ተብሎ የተገመተውን በጥበቅ ሥራ ሠርተውት እናገኘዋለን ። በቅርቡም ጊዜ አፄ ዮሐንስ ንጉሠ ጽዮን የሚለውን ማዕርግ ወስደው አክሱምን የቀድሞውን ክብሯን እመልሳለሁ ታሪኳን አድሳለሁ የማለት ምኞት ነበራቸው ። እኛም ከነገሥንበት ዘመን ጀምሮ ይህን መንፈሳዊ ተግባር ለመፈጸም ያላሰብንበት ጊዜ የለም ። ነገር ግን ታላቅ ሥራ ለመሥራት ሰፊ ጊዜና ረጅም ጥናት የሚጠይቅ ስለሆነ እስካሁን ቆየ ።

አሁን ግን በእግዚአብሔር ፈቃድ አሳባችን ተፈጽሞልን ይህን መርቀን የምንከፍተው ካቴድራል በታላቅነትም በዘመናዊነትም ከሌሎች ካቴድራሎች የበለጠ ለአክሱም ተስማሚ ይሆናል ብለን ያመንበት ነው ። የአክሱምን ካቴድራሉን ብቻ በመሥራት አልተወሰነም ። እንደጥንቱ የዕውቀት ምንጭ የጥበባት መገኛ የሃይማኖት መዲና እንድትሆን በማሰብ ወጣቶች ትምህርትን የሚገቡበት ትምህርት ቤት ሕዝቡ ጤናው የሚጠበቅበትን ሆስፒታል እንዲሠራ አድርገናል ።

ለቤተ ክርስቲያኑም አገልግሎት የሚያስፈልገውን ንዋየ ቅድሳት አልባሳትና መጻሕፍት ለጊዜው የሚስማማ በሙሉ ሰጥተናል ። በዳግማዊ አፄ ምኒልክ ጊዜ ከፍ ወዳለ ሥራ ለማድረስ አርኬዎሎጂስቶች መርምረው እየተቆፈረ በነገሥታቱ መቃብር ውስጥ አብሮ የተቀበረው ወርቅ ተገኝቷል ። የአክሱምን ያለፈውን ታሪኳንና ክብሯን በሰፊው ገልጠናል ። ይሁን እንጂ አክሱም በጥንት የሥልጣኔ መልክ ካልተገኘች የቀድሞ ታሪክዋ ብቻ የ ጊበቃ አይደለም ። ስለዚህ ካህናቱ በምስጋና በጸሎት ፤ በመማርና በማስተማር ፤ ለሌሎች አድባራትና ገዳማት ምሳሌ ሆናችሁ ካልተገኛችሁ ከሌላው የተለየ ታላቅነት ሊኖራችሁ ወይም ሊያሰጣችሁ አይችልም ።

ስለዚህ በዚህ ካቴድራል የሚፈጸመው አገልግሎት በውስጥም በውጭም የሚደረገው አስተዳደር ተሻሽሎ ካልተሠራ ላለን ምኞትና ለቀደመው ታሪክ ተቃራኒ ሆኖ እንዳይገኝ ያስፈልጋል። «ሕግ ይወጽእ እምጽዮን» እንደተባለው ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ትምህርት ከአክሱም ጽዮን ይመነጭ እንደነበረ የታወቀ ነው ። አሁንም እንደዚያው ሆኖ መገኘት ያስፈልጋል ። አንድ ሰው ትልቅ የሚባለው በሥራው ነው እንጂ በስም አይደም ። አክሱም በሥራ እንጂ በስም ብቻ ታላቅነት ሊኖራት እንደማይችል አምናችሁ ለሥራችንም ለአሳባችንም ተባባሪ እንድትሆኑ ተስፋችን ነው ። እግዚአብሔር ትክክል አድርጎ በፈጠራቸው ወንድና ሴት መካከል ልዩነት ማድረግ ታላቅ ስህተት ነው ። ስለዚህ ሰው ወይም ልማድ ሠራሽ በሆነ ምክንያት ሴቶች ሊለዩ የማይገባ ስለሆነ ይህ ልማድ ከዛሬ ጀምሮ ቀርቷል ።

በዚህ ባሠራነው ካቴድራል ወደፊት የጾታ ልዩነት ሳይኖር ወንድም ሴትም ባንድ እምነት ባንድ ትምህርት እንደየእድሉ ሊጠቀምበት ፤ የእግዚአብሔር ልጅነቱን ሊያስመሰክርበት ይችላል። ከዛሬ ጀምሮ ወደፊት ማንኛዋም ሴት መንፈሳዊ ስሜቷን ለማርካት ሕይወቷን በመንፈሳዊ ጎዳና ለመምራት እንድትችል ወደ ካቴድራሉ ገብቶ የመጸለይ ዕድል እንዲኖራት ወስነናል ። የሴት ልጅ መብት በመንፈሳዊም በሥጋውዊም እንዲጠበቅ የምንደግፈው ነው ። የሴት ቅዱሳት በበዙበት አገር የሕዝቡ ኑሮ ቅድስናን እንደሚጐናጸፍ ሴቶች መንፈሳዊ ስሜት ያላቸው እንደሆነ ለልጆች ቅድስና አላፊዎች እንደሚሆኑ በቅ/ መጽሐፍና በታሪክ ጐልቶ የሚታይ ነው ። በብሉይም በሐዲስም የወንዶችንና የሴቶችን እኩልነት ማን ሊሽረው ይችላል ? ሴቶች ገዳም የማይገቡት እነሱም ራሳቸው ገዳም ከፍተው ሥራን እንዲሠሩ በማ




www.ethiopianorthodox.org

ሰብ ብቻ ነው ። አክሱም ጽዮንን ለማየት የሚመጡ ጐብኝዎች ብዙዎች ናቸው ። ከ ሚያዩትና ከሚሰጡት ሁሉ አንዳንድ ነገር ተምረውና አጥንተው ለመሔድ የ ሚችሉበት መሣሪያው በእጃቸው ነው ። ለቦታው [ጽዳት] ለታሪኩ ታላቅነት ሁላችሁም ከልብ እንድትደክሙበት ቢሆን ጥቅሙ የአክሱም ጽዮን ሲሆን በተጨማሪ የመላው ኢትዮጵያ ነው ። ለስማችን ማስጠሪያ ያህል ቤተ ክርቲያኑን ሠርተን የምንተወው እንዳልሆንና ከፍ ያለ ጥናት እንዳለን ባለፈው ተናግረናል ።

አሳባችንን ወደ ፍጻሜ ለማድረስ የናንተን የክርስቲያንን ሁሉ ድጋፍና አገልግሎት ያስፈልጋል ሁሉን የ ሚያስችል እግዚአብሔር ይህን ታላቅ ሕንፃ አስጀምሮ ለማስፈጸም ስላበቃን ስሙ ቅዱስ ይሁን ።

ሰው ረዳት ያስፈልገዋል ፤ ሁሉም በየጊዜው ረዳት ይኖረዋል ፤ በዚህ ሥራ ረድቶ ከፍጻሜ ለማድረስ ለረዳን ለልዑል ደጃዝማች መንገሻ ሥዩምና የሥራ ሚኒስትራችንም እንደዚሁ በዚህ ሥራ ተባባሪ በመሆን የረዱትን ሁሉ ልናመሰግናቸው እንወዳለን ።

ቅዱስ ዳዊት « እበውእ ቤተከ ምስለ መባዕየ ወእሁብ ብፅአትየ ዘነበብኩ በአፉየ» ያለውን ያስፈጸመን አምላክ ምስጋና ለሱ ይሁን ።



ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በየጊዜው ለቤተ ክርስቲያን ስጦታዎችን ያደርጋሉ ፤ ይህ ሥዕል አዲሱ የአክሱም ጽዮን ካቴድራል በተመረቀበት ዕለት ለአክሱም ጽዮን የተሰጡትን ልዩ ልዩ ልብሰ ተክህኖዎች በከፊል ያሳያል ።



www.ethiopianorthodox.org

# ፳ኛ ደብረ ሰላም ቅዱስ እስጢፋኖስ

የደብረ ሰላም ቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን በነበሩበት በ፲፱፻፱ ዓ ም ተመሠረተ ። በዚያን ጊዜም ዘመኑ በፈቀደው መልክ ደንበኛ ቤተ ክርስቲያን ታንፆ ሲወደስ በነ ሳለ ፤ ባልታወቀ ምክንያት በጠላት ጊዜ በ፲፱፻፴፪ ዓ ም ተቃጠለ ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በአገልጋዮቹ ካህናትና በሕዝቡ ላይ ደርሶ የነበረው ችግር ከፍ ያለ ነበር ፤ ሁልጊዜም ችግር አቅላዪ ንጉሠ ነገሥት ፩ኛ የም እመናኑን ችግር ለማቃለል ፤ ፪ኛ ዱሮውን የመ ሠረቱትና ያቀኑት እንደመሆናቸው መጠን ፤ እርሳቸው ብቻ የሚያስቡለት እንደመሆናቸው ፕላኑ በሥራ ሚኒስቴር ተጠንቶ ዘመናዊ ቤተ ክርስቲያን እንዲሠራ አዘዙ ። ክቡር ባላምባራስ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል የሥራ ሚ/ር በመሆናቸው ለቦታው ትክለኛ በመሆናቸው በግል እንደሚያስቡለት ሁሉ በሚገባ እየተቈጣጠሩ ሥራው መልካም ፍጻሜ አገኘና ጥቅምት ፲፯ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ ም ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ ። በዚህም ቀን እንደአጋጣሚ ሆኖ የግብፅ ፓትሪያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ ፮ኛ ተገኝተው የቅዳሴ ቤቱን በዐል አብረው አክብረዋል ።

ግርማዊ ጃንሆይም ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን መሥራት ብቻ ሳይሆን ቀዋሚ አገልጋዮች የሚረዱበትን ሀብት የሚተዳደሩበትንም መብት ሰጥተዋል ። እንዲያውም ዛሬ ታላቅ ቤተ ክርስቲያን ሆኖ ንጉሠ ነገሥት ከንጉሣዊ ቤተ ሰባቸው ጋር ለልዩ ልዩ መንፈሳዊ አገልግሎት ይገኙበታል ። ሕንፃው ዘመናዊና ውበት ያለው አገልግሎቱም ቀልጣፋ በመሆኑ ዘመናውያን ሰዎች ልዩ ልዩ መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን በዚያ ለመፈጸም ይፈትዳሉ ። የቦታው አቀማመጥ ከአዲስ አበባ ውስጥ ከፍተኛውን ቦታ ይዞ ስለተገኘ ፤ ወደፊት የበለጠ ተወዳጅነት እንደሚኖረው የተመሰከረለት ነው።

የዚህም ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ መልአከ ሰላም ሳሙኤል ተረፈ በአገራቸው ከፍተኛውን ዕውቀት ካላቸው ሊቃውንቶች ውስጥ ፩ኛው ሲሆኑ ፤ በዘመናዊ ዕውቀትም ዲግሪ ካላቸው ካህናት ውስጥ የመጀመሪያው ናቸው ። ስለዚህም ከዕለት ወደዕለት ደብራቸው የሚገለምስበትን ምእመናን የሚበረክቱበትን በመሥራት ይገኛሉ።

# ፯ኛ ዝቋላ ገዳም

ይኸ ገዳም ከታላላቆቹ ገዳማት አንዱ እንደ መሆኑ መጠን የጥንቱ ቤተ ክርስቲያን ሳይፈርስ እንዳለ ሆኖ ሌላ በዘመናዊ አቅድ እንዲሠራ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ባዘዙት መሠረት ጥናቱና የሥራ ፕላኑ አልቆ በ፲፱፻፶፩ ዓ ም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የመሠረቱን ድንጋይ አስቀመጡ ። ሥራውም በሚገባ ተከናውኖ በ፲፱፻፶፩ ዓ ም ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ ።




www.ethiopianorthodox.org

# ፺ኛ የደብረ ብሥራት ቊልቢ ገብርኤል ገዳም

ይኸ ቤተ ክርስቲያን በልዑል ራስ መኰንን ተመሥርቶ ሕንፃው በዘመኑ አቅድ ተሠርቶ ፤ ቅዳሴ ከተጀመረበት ዕለትና ሰዓት አንሥቶ ገባሬ ተአምር በመሆኑ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆኑ ፤ የውጭ ዜጎዎችም በብዛት እየተገኙ በዓሉን በሚ ገባ ሲያከብሩ ፤ ከተአምራቱም ሲሳተፉ ይገኛሉ። እንዲሁም በሃይማኖት ረገድ ክርስቲያኑ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ፤ ከክርስትና ውጭ የሆኑ ሁሉ ይኸን ተግባር ሲፈጽሙት ይገኛሉ ። ግርማዊ ንጉሠ ነገ ሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በየጊዜው የሚሰበሰበ ውን የሕዝቡን ብዛት ፤ የቤተ ክርስቲያኑን ጥበት አይተው ሰፊ ቤተ ክርስቲያን በአዲስ አቅድ እንዲሠራ ትእዛዝ ሰጡ ።

በትእዛዙም መሠረት ልዩ ልዩ ፕላን ከቀረበ በኋላ በ፡መልኩ ተወዳጅነት ፤ በሥራው ጥብቅነት በስፋቱም ብዙ ሕዝብ ይይዛል ተብሎ የተገመ ተው ይኸ ቤተ ክርስቲያን በ፲፱፻፶፯ ዓ ም ተሠራ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑ የፈጀው ገንዘብ ፩፻፳፫ሺህ ብር ነው ። ቤተ ክርስቲያኑም ከስፋቱ የተነሣ ፤ ይይዛል ተብሎ የተገመተው ፳፻ ሕዝብ ነው ።



አዲሱ የቊልቢ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሁል ጊዜ በልዩ ልዩ ጠቅ ላይ ግዛት ቤተ ክርስቲያን ማሠራት ልማዳቸው ስለሆነ ፤ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን አሠርተዋል የጐላውን ታላላቁን ብቻ ከዚህ እንደሚከተለው እንናገራለን ።



www.ethiopianorthodox.org

## አዲስ አበባ ፡፡

፩ኛ/ የመናገሻ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ፤
፪ኛ/ የጉለሌ ቅዱስ ሚካኤል (ደብረ መዊዕ) ቤተ ክርስቲያን ፤
፫ኛ/ የቅዱስ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ ቤተ ክርስቲያን

## በሸዋ ጠቅላይ ግዛት ፡፡

፩ኛ/ ዘና ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ፤
፪ኛ/ የናዝሬት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፤
፫ኛ/ የደብረ ዘይት ቅዱስ ሩፋኤል ፤
፬ኛ/ የአምቦ ቤተ ክርስቲያን ሌላም ብዙ

## በወሎ ጠቅላይ ግዛት ፡፡

፩ኛ/ የደብረ ቤቴል ሥላሴን ቤተ ክርስቲያን ፤
፪ኛ/ የአሰብ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ፤

## በትግሬ ጠቅላይ ግዛት ፡፡

፩ኛ/ የደብረ ዐባይ አባ ሳሙኤልን ቤተ ክርስቲያን ፤

## በበጌምድርና ስሜን ጠቅላይ ግዛት ፡፡

፩ኛ/ የመካነ ኢየሱስን ቤተ ክርስቲያን ፲፱፻፶፪
፪ኛ/ የአደባባይ ኢየሱስን ቤተ ክርስቲያን ፲፱፻፵፫
፫ኛ/ የዋልድባን (ዳልሽሀ) ቤተ ክርስቲያን ፲፱፻፶፪
፬ኛ/ የማኅበረ ሥላሴን ቤተ ክርስቲያን »
፭ኛ/ የሰይኮ ኪዳነ ምሕረትን ቤተ ክርስቲ ፲፱፻፶፮
፮ኛ/ የአብረንታንት » » » ፲፱፻፵፰
፯ኛ/ ሰቋር » » » ፲፱፻፶፰

## በኤርትራ ጠቅላይ ግዛት

፩ኛ/ የምጽዋ ደብረ ምጥማቅን ቤተ ክርስቲያን ፤
፪ኛ/ የአሥመራ ተክለ ሃይማኖት ቤተ »
፫ኛ/ የአሥመራ ቅ/ሚካኤልን » »
፬ኛ/ የመንደፈራ ቅዱስ ጊዮርጊስን » »

## በወለጋ ጠቅላይ ግዛት ፡፡

፩ኛ/ ለየቀምት ኢየሱስን ቤተ ክርስቲያን ፲፱፻፶፰
፪ኛ/ የአሶሳ ቅድስት ማርያም » » ፲፱፻፵፯
፫ኛ/ የደብ ዶሎ መድኃኔ ዓለምን » » ፲፱፻፵፱

## በሐረር ጠቅላይ ግዛት

፩ኛ/ ሐረር መካነ ሥላሴ ፤
፪ኛ/ ኤጀርሳ ጎሮ ኪዳነ ምሕረት ፤
፫ኛ/ ዓለም ማያ ቅዱስ ሚካኤልን ፤

## ሙሉ እድሳት ፡፡

ከዚህ ሌላ ሙሉ እድሳት የታደሰ ፤ ክዳን በማርና በቆርቆሮ የለበሰ የተደበረ ፤ የተገደመ ፤ ከቁጥር በላይ ነው ፡፡ ለዚህም ወጭ የሆነ የዓመቱ ብዙ -------------ይሆናል ፡፡

አሁን ቤተ ክርስቲያን ረዳት የምትሻበት ትልቅ የችግር ጊዜ ነው ማለት እንደ ጃንሆይ ያሉ ታላላቅ ነገሥታት በብዛት ስለሠሯቸው ሥራቸው አንድ ጊዜ እንደመሆኑ ያረጁበትም ፤ የፈረሱበትም አንድ በመሆኑ ነው ፡፡ ድካሙ ይኸንም ከባድ ሸክም ማንም ሊያቃልለው ባልቻለም ነበር ፤ ግን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በታላቅ ትዕግሥት ሰፊ ልግሥናቸውን በማድረግ ቤተ ክርስቲያናችን ታላቅ ዓምድ ሆነው ደግፈዋት ይገኛሉ ፡፡ ለገዳማት ፤ ለአድባራት መደገፊያ ፤ ለሽማግሌ መጦሪያ ለድርጅቱ ማስፋፊያ የሚሆን የዓመት ወጭ ከልዩ ግምጃ ቤታቸው ይወጣል ፡፡ ብዙ በጎ አድራጎት የሚፈጸመው ችግረኛ የሚረዳው በዚህ ዓይነት ነው ፡፡ ብዙ ሽማግሎች የሚጦሩት ተስፋ የቈረጡ የሚጽናኑት መናያን የሚደገፉትም በዚህ ዓይነት ችሮታ ነው ፡፡



www.ethiopianorthodox.org

# ግርማዊት እቴጌ መነን ያሠሯቸው አብያተ ክርስቲያናት

ግርማዊት እቴጌ መነን ርኅርኂት እጀ ሰፊ ለጋስ ንግሥት ነበሩ ። ስለዚህ ብዙ በጐ አድራጎትን ፈጽመዋል ። ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን አሳንፀዋል ። የቤተ ክርስቲያን ልጅ እውነተኛ ማእምንት ሲሆኑ ፤ እርሳቸው ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን ወለዱ ፤ አሳደጉ ብንል አልተሳሳትንም ።

ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያናችን በርሳቸው ሞገስ አግኝታለች ። ከችግር ተጽናንታለች ። የግርማዊት እጅ ያልዳበሳቸው ፤ የግርማዊት ስጦታ ያልደረሳቸው አብያተ ክርስቲያናት በኢትዮጵያ አይገኙም ። የግል ንብረታቸው ለዚህ በጎ አድራጎት ብቻ ይውል ነበር ። በትክክ ልምይሠራበት ነበር ፤ ይኸው ዕድላቸው ሆኖ በየጊዜው መልካም ውጤቱን ይገልጥ ፤ የሥራ ፍሬውንም ያሳይ ነበር ። ሳይሰለቹ ፤ ሳይሠቀቁም ለመሥራት ይገፋፉቸው የነበር ይኸው መልካም የሥራ ፍሬው በየጊዜው መታየቱ ነው ።

ከአሁንም ጀምሮ በየጊዜው መታሰቢያ ሆኖ ሲያስታውሳቸው የሚኖረው ብዙ መልካም ሥራቸው ሲሆን ፤ በበለጠ ግን የሚያስታውሳቸው በቀላሉ የማይፈርሱ ሆነው የተሠሩት ሐውልቶች (አብያተ ክርስቲያናት) ናቸው ። ቤተ ክርስቲያን ውለታ መላሽ አደራ ጠባቂ እንደመሆኗ ፤ ለመታሰቢያ በሕይወት ሳሉ የሠሯቸውን አብያተ ክርስቲያናት ለተመልካች በዝርዝር ታቀርባለች ።

ግርማዊት እቴጌ መነን ያሠሯቸው የአብያተ ፤ ክርስቲያናት ቁጥር ብዛት የሥራውን ጥብቅነት የስጦታውን ዓይነት ስንመለከት ፤ ግርማዊት የኖሩት የሠሩት ለቤተ ክርስቲያን ብቻ ነው ያሰኛል ፤ ግን በየመልኩ በሁሉም በዚህ ዓይነት እንደሠሩ እያመን ፤ መንፈሳዊውን በተለይም የቤተ ክርስቲያንን ሥራ ብቻ እንናገራለን ።

፩ኛ የደልባ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን (ወሎ)
፪ኛ የፉሪ የቅድስት ሐና ቤተ ክርስቲያን፤
፫ኛ ኮልፌ ቅዱስ ጳውሎስ ፲፱፻፴፰ ዓ. ም.
፬ኛ የጌቴ ሴማኒ ማርያም (ሰበታ ፲፱፻፵) ዓ.ም.
፭ኛ የቦሩ ሥላሴ (ወሎ ፲፱፻፵፫) ዓ. ም.
፮ኛ የዋሮ ቅዱስ ሚካኤል (አንቦ) ፲፱፻፶)ዓ.ም.
፯ኛ የቅዱስ ራጉኤል (አዲስ አበባ)
፰ኛ የዮርዳኖስ ቅ/ ሥላሴ ( ኢየሩሳሌም)

እነዚህ ከዚህ በላይ የዘረዘርናቸው ግርማዊት እቴጌ ሕንፃቸውን ያሠሯቸው ማደሪያቸውን የሰጧቸው ፤ በጠቅላላም ሙሉ ድርጅት አድርገው ያቋቋሚቸው አብያተ ክርስቲያናት ናቸው እንጂ፤ ለሕንፃው ፤ ለክዳኑ ፤ ለአልባሳቱ ፤ ለንዋየ ቅድሳቱ ገንዘብ የሰጡት ፤ ዕቃውንም ያበረከቱት ቤተ ክርስቲያን በቁጥር እጅግ በርከት ያለ ነው ። እንዲያውም ከላይ እንደገለጥነው ሁሉ እጃቸው ያልዳበሰው ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ አይገኝም ።

ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ

# የቅዱሳት መጻሕፍት በብዛት መጻፍ

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከ፫ሺህ ዘመን ጀምራ ክብሯ ሳይገሠሥ ፤ ወሰኗ ሳይጣስ ፤ ደንበሯ ፤ ሳይፈርስ በታላቅ ክብርና በድንግልና ለኖረችው ፤ እንዲሁም በዚሁ ጸንታ ለምትኖረው ፤ ጥንታዊነቷ አዲስነቷን ፤ አዲስነቷ ጥንታዊነቷን ለማይሽረው ለታላቋ ኢትዮጵያ መሪና አስተዳዳሪ እንዲሆኑ በፈቃደ እግዚአብሔር የተመረጡ በመሆንናቸው በጠቅላላው ለሀገሪቱ የሠሯቸው ሞያዎች እጅግ በጣም የበዙና በዓይንም የሚታዩ ስለሆነ የታሪክን እውነተኛ መልክ ሳይለውጡ ለሚመዘግቡ በመተው ፤ ይህን የነፃነት ብር ኢዮቤልዮ ምክንያት በማድረግ በተለይ ለኢትዮ



www.ethiopianorthodox.org

ጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከሥር ጀምሮ ሳይሆን በዚህ የ፳፭ ዓመታት ጊዜ ውስጥ የዋሉትን በጎ አድራጎት በጽሑፍ ማቅረብ ስላስፈለገ ፤

ወደ አማርኛ የተተረጐሙትን ፤

በየጊዜው በቋም ጽሕፈት ተጽፈው የተራቡትን ፤

በማኅተም ታትመው የተባዙትን መንፈሳውያን መጻሕፍት ዓይነትና ብዛት ከዚህ እንደሚከተለው እናቀርባለን ።

ለውዲቱ ሀገራችን ኢትዮጵያ ልማትና ለጠቅላላው የሕዝቧ ኑሮ ዕድገት ቁልፍ የሆኑት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ለዚህ ታላቅ የመሪነት ኃላፊነት ከመመረጣቸው አስቀድሞ በመካከለኛ ሥልጣን ላይ ከነበሩበት ጊዜ አንሥቶ አርቆ አስተዋይና ፍርድ ዐዋቂ ብልህ አስተዳዳሪ እንደነበሩ ታሪክ በሰፊው የሚመሰክር ከመሆኑም በላይ ፤ በተለይ ለመንፈሳዊ ጉዳይ አሳቢና የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ደጋፊ ስለነበሩ ፤ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲንን ልትደረጅና የጊዜው ሁናቴ በሚፈቅደው መጠን ልትራመድ የምትችልበትን ዘዴ ሁሉ በብዛት ያዘጋጁ እንደነበር ይታመናል ።

<u>ይኸውም ዝግጅት</u> ፤

ሀ/ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የሚሆኑ ሊቃውንትን ቁጥር ማበርከት ፤ ማለት የከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት መስጫዎችን ድርጅቶች በብዛት ማቋቋምና እንዲደረጁም ማበረታታት ፤

ለ/ በልዩ ልዩ ቋንቋዎች የተጻፉ የመንፈሳዊያን መጻሕፍትን ወደ አማርኛ ቋንቋ ማስተርጎም ፤

ሐ/ እነዚህ የተተረጎሙ መጻሕፍት በብዛት እንዲራቡ ለማድረግ ጊዜው በሚፈቅደው ዕውቀት ወይም ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ቅርሶች የመጀመሪያው ከፍተኛ ደረጃ በያዘው በቋም ጽሕፈት ማስቀዳት ፤

መ/ ከዚህም ቀጥሎ የኢትዮጵያን ጥንታዊ እምነትና የቤተ ክርስቲያናችንን ባህልና ሥነ ሥርዓቱን አጉልተው የሚያሳዩትን መንፈሳውያን መጻሕፍት ባያሌው ለማበርከትና ለየአብያተ ክርስቲያናቱ ፤ እንዲሁም ለምእመናን በብዛት ለማዳረስ የሚያስችለውን ዘመናዊ የማኅተም መኪና ከአውሮፓ አስመጥተው ብርሃንና ሰላም የተባለውን ማተሚያ ቤት በማቋቋም ማሳተማቸው ሲሆን ፤ ይህን ሁሉ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በከፍተኛ ደረጃ የፈጸሙና የሚፈጽሙ ፤ ለሥጋዊ ጉዳይ በሚደክሙበት ጊዜ ሁሉ መንፈሳዊውን ወደ ጎን ሳይተው በትክክል የሚያስቡና የሚሠሩም በመሆናቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን ልጆቿ ይህን ታላቅ ውለታቸውን ምንጊዜም ቢሆን አይዘነጉትም ፤

በዚህም አኳኋን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በበጎ ፈቃዳቸውና በግል ገንዘባቸው ከግዕዝ ወደ አማርኛ ያስተረጎሟቸው የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ዓይነትና ብዛት ከዚህ በሚከተለው ሁኔታ ይገለጻል ።

የነፃዪቱ ኢትዮጵያ ጥንታዊ ድንበኛ ቋንቋ ግዕዝ ስለነበረ በመካከሉ የአማርኛ ቋንቋ ቦታውን ጥቂት በጥቂት እያለ ስለወረሰውና ተከታዩ ትውልድም ግዕዝን ትቶ አማርኛን መነጋገሪያ ቋንቋው ስላደረገው ፤ የግዕዝ ቋንቋ ከሥጋዊ ዓለም ሸሽቶ ወደ ገዳምና ታላላቅ አድባራት በመሰደድ ኑሮውን በመንፈሳዊው ዓለም ወሰነ ።

በዚህም ጊዜ ከመጀመሪያው የኢትዮጵያ መንግሥታዊ ቋንቋ ከግዕዝ ወደ ሁለተኛው ቋንቋ ወደ አማርኛ የተሸጋገረው ትውልድ ግዕዝን ስለአላወቀ ታላላቅ የኢትዮጵያ ጠቅላላ ጉዳይና የነገሥታት ታሪክ ሁሉ ፤ እንዲሁም በበለጠ የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዘኢትዮጵያን ታሪክና ባህል ፤ እምነትና ሥርዓት የያዙ መጻሕፍት ከግዕዝ ጋር ወደ ገዳም በመመነን ጠፍተው እንዳይቀሩ በማሰብ በመጀመሪያ በቋም ጽሕፈት ረገድ



www.ethiopianorthodox.org

ከፍተኛ ዕውቀት ያላቸውን ሊቃውንት ከየቦታው በመሰብሰብ ደመወዛቸውን እየከፈሉ ያረጁትን ማሳደስና ( ማስቀዳት ) ያነሱትን በቁጥር ማበርከትን የመጀመሪያ እርምጃ አድርገው በግል ገንዘባቸው የቁም ጽሕፈት መሥሪያ ቤትንና የትርጉም ክፍልን በ፲፱፻፲ ዓ-ም አቋቁመው እነሆ ፤ አሁን ዘመናዊ የማተሚያ መሣሪያ በብዛት ወደ ሀገራችን ከገባ ወዲህ የተቋቋመው የቁም ጽሕፈት ቢሮ በየጊዜው እየተስፋፋ ሔደ እንጂ ዘመናዊ የማተሚያ መሣሪያ ቦታውን ወስዶበታልና ይዘጋ አልተባለም ።

ይህም ግርማዊነታቸው የኢትዮጵያ ጥንታዊና ብሔራዊ ኪነ ጥበብ እንዲዳብርና እንዲስፋፋ ያላቸውን ጽኑእ ፍላጎትና ሰፊ ጥረት ፤ አጉልቶ ያስረዳል ።

አርቆ ተመልካች የሆኑት ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በተለይ ለቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዘኢትዮጵያ በማንኛውም ረገድ ገና ደጃዝማች ከነበሩበት ጊዜ አንሥተው የዋሉላት ውለታ ሥፍር ቁጥር የሌለው ስለሆነ ፤ በተለይ ግፈኛውን የኢትዮጵያንና የልጆቿን ጠላት ፋሽስትን አባርረው ለታላቋ ሀገራችን ኢትዮጵያ የድልንና በዓለም ታሪክ ዐምድ ተመዝግቦ በግልጽ የታወቀ የግል ሀብቷ የሆነውን የነፃነቷን አክሊል ካጎናጸፉበት ከ፲፱፻፴፫ ዓ- ም- ወዲህ ባለፉት ፳፭ ዓመታት ውስጥ ከግዕዝ ወደአማርኛ ያስተረጐሟቸውና በቁም ጽሕፈት ያጻፏቸው ፤ እንዲሁም በዘመናዊ ማተሚያ ያሳተሟቸው መንፈሳውያን መጻሕፍት ስምና ቁጥር ከዚህ እንደሚከተለው ነው ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት

፩ኛ/ የትርጉም ክፍል መሥሪያ ቤትን በ፲፱፻፲ ዓ- ም- መልካም ፈቃዳቸው ሁኖ እንዲቋቋም አደረጉ ፤

፪ኛ/ የቁም ጽሕፈት መሥሪያ ቤትንም በዚሁ በ፲፱፻፲ ዓ- ም- መሠረቱ ፤

፫ኛ/ የዘመናዊ ማተሚያ ክፍል ( ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤትን ) በ፲፱፻፲፬ ዓ- ም- አቋቁመው ጊዜው በሚፈቅድላቸው መጠን ሁሉም የሥራ ድርጅቶች የየክፍል ተግባራቸውን በመልካም አኳኋን ሲያከናውኑ ሳሉ ፤ ግፈኛው ጠላታችን ፋሽስት ለ፫ሺህ ዘመናት ጸንቶና ተከብሮ ፤ የኖረውን ነፃነታችንን ለመግፈፍ በመርዝ ጭስ በመጠቀም ባደረገብን ወረራ ምክንያት ተጓጉለው ከቆዩ በኋላ ፤ ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባውና በታላቁ መሪያችን በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ብርታትና ባርበኞቻችን ቆራጥነት ፳፩ የመከራ ዓመታት አልፈው ድል አድራጊነትን ተጎናጽፈን ፤ የኢትዮጵያ ጠቅላላ እርምጃ በዘመናዊ ዐቅድ ሲቀጥል ፤ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የቤተ ክርስቲያናችን ቅርሶችም በዚሁ አንጻር የቀደመ ፕሮግራማቸውን አስፋፍተው እንዲያካሒዱ የግርማዊነታቸው ጽኑእ ፍላጎትና ቁርጥ አሳብ ስለሆነ ፤ ከነፃነት መመለስ ወዲህ ከጥንታዊው ቋንቋችን ከግዕዝ ወደ ዘመናዊው ቋንቋችን ወደ አማርኛ የተተረጐሙትና በብሔራዊ ቅርሳችን በቁም ጽሕፈት የተቀዱት መንፈሳውያን መጻሕፍት ቁጥራቸው በጣም የበዛ ሲሆን፤ከነዚህ ውስጥ በዘመናዊ ማተሚያ የታተሙት መጻሕፍት እንደሚከተሉት ናቸው ።

ሀ/ የዓለም መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር የተስማማበት ፤ ለሰባክያንና ለመንፈሳውያን ተማሪዎች በእጅ በመያዝ የሚያገለግል ፤ መካከለኛ መጠን ያለው መጽሐፍ ቅዱስ ፤ ከግዕዝ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ በዘመናዊ አቅድ ታትሟል ።

ለ/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንደምትቀበለው ሆኖ በታረመና በተሻሻለ አማርኛ በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ልዩ ጥናትና የውይይት ጉባኤ የተዘጋጀው ታላቁ መጽሐፍ ቅዱስ በጥሩ አማርኛ ተከናውኖ ታትሟል ።

ሐ/ የዓለም መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር የተስማማበት ሐዲስ ኪዳን በታረመና በተሻሻለ አማርኛ ተዘጋጅቶ ከላይ እንደጠቀስኳቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ታትሟል ።

መ/ ከረጅም ዘመን ጀምሮ በግዕዝ ቋንቋ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይተዳደርበትና ይፋረድበት የነበረው ታላቁ የሕግ መጽሐፍ ፤ ፍትሐ ነገሥት ወደ አማርኛ ቋንቋ በተመረጡ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ተሻሽሎ እንዲተረጐምና ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ



www.ethiopianorthodox.org

በብዛት እንዲታደል በማሰብ ፤ ሁሉም ተጠናቅቆ ጊዜው በፈቀደው የእትማት ደረጃ ላይ ደርሶ ማን ኛውም ሥራ ካለቀ በኋላ ፤ በግፈኛው የኢትዮጵያ ጠላት ፋሽስት ወረራ ምክንያት በመጽሐፉ ለመ ገልገል ብዙዎች በታላቅ ናፍቆት በሚጠባበቁበት ወቅት ከማተሚያ ቤቱ ጋር አብሮ ስለተቃጠለ ፤ ይህ ታላቅ የፍትሕ መጽሐፍ እንደሌሎቹ የኢት ዮጵያ ታሪክ ቅርሶች ድራሹ ጠፍቷል የሚል ፍር ኃት በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ወድቆ ሳለ ፤ የኢትዮጵያ ክብር ጠባቂና የግርማዊ ንጉሠ ነገ ሥት መልካም ሥራ ሁሉ ደጋፊ በሆነው እግዚ አብሔር ቸርነት መድበሉ ስለተገኘ ፤ እነሆ ፤ እን ዳለ በድጋሚ ለመታተም በቅቶ ስናይ ለሁላችንም ልባዊ ደስታ ይሰማናል ። እንዲሁም ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሥጋዊና መን ፈሳዊ ጥቅም የሚበጁ ዓበይት መጻሕፍት ጊዜ ባፈ ራው ጥበባዊ ማኅተም ተባዝተው ለመላው የኢ ትዮጵያ ሕዝብ በገፍ እንዲታደሉ ስላደረጉ ፤ ቅድ ስት ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያንና ደጋፊዎቿ ፤ እንዲሁም በእውነተኛ ፍርድ በመተዳደር ሕግን አክብሮ የሚኖረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ ለታላቁ መሪያቸው ለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ዘመን የማይሽረው ምስጋና ቸውን በኅብረት ያቀርባሉ ።

መንክር ተድላ



www.ethiopianorthodox.org

# የትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን የግር ማዊ አባታቸውን መልካም አርአያ በመከተል የኢትዮጵያ ኦርቶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ደጋፊ ስለሆኑና እርምጃዋን ለማሻሻል ጽኑ ፍላ ጐት ስላላቸው፤ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የሃይማ ኖትና የግብረ ገብነት ትምህርቷን ለምእመናን በሰ ፊው ለማዳረስ የሚያስችሏትን ልዩ ልዩ መጻሕፍት በገፍ እያራባች የምትናኝበት ለዚያን ጊዜው የሥራ ደረጃ ተስማሚነት የነበራቸውን ሁለት የማተም መኪናዎች በግል ገንዘባቸው ገዝተው በመስጠት «ትንሣኤ ዘጉባኤ» ተብሎ የተሰየመውን ማተሚያ ቤት እንዲቋቋም ቤተ ክህነቱን በልግስናቸው አነ ቃቅተውት ነበር ።

በ፲፱፻፴፮ ዓ ም በልዑልነታቸው የበጎ አድራጎት ስጦታ ተቋቁሞ በቤተ ክህነት ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት ባለቤትነት የሚካሔደው «የትንሣኤ ዘጉባኤ»ማተ ሚያ ቤት ሥራውን ከጀመረ ፳፪ ዓመታትን ያሳለፈ ሲሆን ፤ መጠነኛ በሆነው አገልግሎቱ ለቤተ ክህ ነቱ ከፍተኛ የገቢ ምንጭ በመሆን በገንዘብ በኩል መርዳቱና ሲደግፈው መቆየቱ ይታመናል ።

ቢሆንም ከዚህ በላይ በተገለጸው መሠረት የዚህ ማተሚያ ቤት ዕድሜ ረጂም ሁኖ ሳለ በኋላው የተቋቋሙት ሌሎች ማተሚያ ቤቶች በብዙ ዓይነት መንገድ ከጊዜ ወደጊዜ ይዞታቸውን እያሻሻሉ በመሐድና በሥራቸው በጣም ከፍተኛ የሆነ የገን ዘብ ገቢን በማስገኘት ሀ/ ባቀማመጥ በኩል ሲመ ሠረቱ ከነበሩበት አነስተኛ ቤት እየወጡ ሰማይ ጠቀስ ወደሆኑ ዘመናዊ ታላላቅ ሕንፃዎች ለመሸ ጋገር ችለዋል ።/ ሠርተዋል/ ለ/ በመሣሪያም በኩል በሽህ ሳይሆን በብዙ ሚሊዮን ብር በሚገዙት አዳ ዲስና ከፍተኞች መኪናዎች ለመጠቀም በቅተዋል። ሐ/ በሠራተኞችም በኩል በሀገር ውስጥ ልዩ ልዩ የማሠልጠኛ ኮርስ ከሚሰጧታቸው በላይ አውሮፓ ድረስ እየላኩ የረጂም ጊዜ ከፍተኛ የቴክኒክና ያስ ተዳደር ትምህርት ባስገበዩዋቸው ዐዋቂዎች በመ ገልገል በሁሉም ረገድ አስደናቂ የሆነ እርምጃን በማሳየት ለሀገር የልማት ዕድገት እውነተኛ ተስፋና ዋስትና ባለው የደንበኛ ኢንዱስትሪ ደረጃ ላይ ሲራ መዱ ይታያሉ ።

በሌሎች አንፃር ሲመለከቱት ረጂም ዕድሜ ያለው የትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ፤ ይዞታ ባለህበት ሒድ ሁኖ በመቅረቱ የነቀፋ አስተያየት በቤተ ክርስ ቲያን ደጋፊዎችና የዕድገቷ ጠባቂዎች በሆኑት ዘንድ ሲገለጥ ይሰማል ።

---

# ትምህርት በቤተ መንግሥት

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከማንኛውም ሥራቸው በፊት ዕውቀት እንዲስፋፋ የሚጥሩ ንጉሠ ነገሥት ናቸው ። ስለዚህ የዕውቀት ደጋፊ መሆናቸውን የሚገልጡ ፤ ፩ኛ/ ገና አልጋ ወራሽ በነበሩ ጊዜ የደብር አለቆች በየደብሩ ፤ የገዳማት መምህራን በየገዳማቸው እንዲያስተምሩ የታወ ጀው አዋጅ ያስረዳል ። ፪ኛ/ ምንም ታላቁን ዕቅዳቸውን የጠላት ወረራ ቢያቋርጥባቸው በድል አድራጊነት ወደመናገሻ ከተማቸው እን ደተመለሱ ዕውቀት በበለጠ እንዲስፋፋ በተለ ይም ካህናት ከፍ ያለ ኃላፊነት ስላለባቸው እነርሱ በአዲሱ አቅድ ሲሻሻሉ ለሌላው የበለጠ ይጠቅ ማሉ በማለት አስበው ቦታው እስኪዘጋጅ ቤተ መንግሥታቸውን ትምህርት ቤት አድርገው በቶሎ ደርሰው አገርን ፤ ቤተ ክርስቲያንን በበለጠ ይረ ዳሉ ተብለው የተገመቱትን ሊቃውንት ሰብስበው ከዚህ የሚከተለውን መሪ ቃል በመስጠት ትም ርት ቤቱን መርቀው ከፈቱ ።

«ባለፈው ስንፍናችሁ ልትፀፀቱበት ይገባል ዛሬ የምትሠሩባቸውን መጻሕፍት አባቶቻችን የውጭ አገር ቋንቋ ተምረው ወደቋንቋችን መል ሰው ባይተረጉሙልን ዛሬ አሕዛብ ተብሎ መጠ



www.ethiopianorthodox.org

ራት ያገኘን ነበር ። እናንተማ በደጃችሁ እያላችሁ ሳትማሩት መቈየታችሁ የሚያፀፅት ነው ። አሁ ንም ወርቁን እንደቀበረው አገልጋይ እንዳትሆኑ እኛ የፈለግነው በቤተ መንግሥት ሥር የቋንቋ ትምህርት ሲስፋፋ ቤተ ክርስቲያን በዚህ በኩል የሚደግፉት እንዳታጣ አስበን ነው» በቤተ መ ግሥቱ ውስጥ እንዲማሩ ዕድል ተሰጥቷቸው የነ በሩት ሊቃውንት አያሌዎች ናቸው ። ግን ከነ ዚህ ውስጥ ጥቂቶቹ በነገሩ አስበውበት ሲቀ ጥሉ የቀሩት ግን ጃንሆይ እንደተናገሩት በጅምር ትተውታል ። የሆነ ሆኖ ነገሩ ተገቢ መሆኑን ብዙ ዎች ሌሎች ስለአመኑበትና ወደትምህርት ቤቱ ሊገቡ በወደዱ ጊዜ ፤ ፩ኛ/ ተማሪዎቹ እንደልባቸው ለመውጣት ለመግባት እንዲመቻቸው ፤ ፪ኛ/ ትም ህርት ቤቱ የካህናት ማሠልጠኛ መሆኑ ታውቆ ሊቃውንቱ በብዛት እንዲገቡበት በማለት ራሱን ይቻል በማለት ራሱን የቻለ ባጀት ሰጥተው የሀገ ርም የውጭ ሀገርም አስተማሪ ቀጥረው አሁን የቅ ድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የሚባለውን የቅ ስት ሥላሴ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ብለው ሰይ መው በ፲፱፻፴፭ ዓ· ም· ከፈቱ ።

ይኸ ቦታ ቀድሞ የባሪያ መገዛት በነበረበት ጊዜ የነፃ አውጪ ጽሕፈት ቤት የነበረ ነው ። ቤተ ክርስቲያንንም ከባዕድ አገዛዝ ነፃ ለማውጣት ሊቃውንት ማሠልጠን ተገቢ ስለሆነ ፤ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ይኸን ቦታ ለዚህ መንፈሳዊ ሥራ መረጡ ።

## የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ፤

## አጭር ታሪክ ፤

### አመሠራረት ፤

ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ከኢጣ ልያ ወረራ በኋላ በድል አድራጊነት ወደ ኢትዮ ጵያ ተመልሰው ለሀገራቸው ሥልጣኔ ከፈጸሟ ቸው ቀደምትነት ካላቸው ቀዋሚ ነገሮች ውስጥ አንደኛው የቅድስት ሥላሴን መንፈሳዊ ትምህርት ቤት መመሥረት ነበር ። ግርማዊነታቸው በማን ኛውም ለኢትዮጵያ መሻሻልና ሥልጣኔ በሚደረ ገው የሥራ እርምጃ ሁሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም በብሔራዊ ትምህርት ብቻ የበ ሰለ ሳይሆኑ ከፍተኛ ጠቅላላ ትምህርትና ጠለቅ ያለ ዕውቀት ያላቸውን ቀሳውስትና ሌሎችም መንፈሳውያን አርበኞች በማሠልጠን የክርስትናን እምነት ከዘመኑ የኑሮ ችግር ጋር ለማዛመድና ለችግሩም መፍትሔ ለማግኘት የ ሚችሉ ሰዎች እንዲኖሩዋት አስፈላጊ መሆኑን በተለመደው አርቆ ተመልካችነታቸው ሳይገነዘቡት የቀረ አል ነበረም ። ይህ ዐቢይ ተግባር ወዲያውኑ ተከና ውኖ የሚታይ አልነበረም ። ሆኖም ከተፈላጊው ግብ ለመድረስ መጀመሪያ እንዲኖረው አስፈለገ ። ስለዚህ በ፲፱፻፴፭ ዓ/ ም/ ግርማዊነታቸው የቅድ ስት ሥላሴን መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ሕንፃ የመ ሠረት ድንጊያ አስቀመጡ ። ለዚሁ ሕንፃ ማሠሪ ያም ሆነ እንዲሁም ትምህርት ቤቱ ከተቋቋመ ጀምሮ ለብዙ ዓመታት ያህል ለትምህርት ቤቱ የሚውል ማናቸውም አስፈላጊ መሣሪያ የሚዘ ጋጅበትን ገንዘብ ፤ የመምህራኑና የሠራተኞቹ ደመወዝ የ ሚከፈለው ከግርማዊነታቸው የግል ሀብት ነበር ።

### የመጀመሪያው ዓመት የሥራ አመራር ፤

የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት በታኅሣሥ ወር ፲፱፻፴፯ ዓ. ም. በኦፌሴል ተመ ርቆ ተከፈተ ። የትምህት ቤቱ የአስተዳደር ኃላ ፊነት ከዚህ በ ሚቀጥለው ገጽ ስማቸው ለተ መለከተው የኮሚቴ ዓባሎች ተሰጠ ።

፩ኛ/ ቀሲ ሥልጣናት መልእክቱ አሁን (ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ) ሊቀ መንበር ፤

፪ኛ/ ሚስተር ሐፍዝ ዳውድ ፤ የት/ቤቱ ዲሬ ክተር ፤ አሁን አባ ማርቆስ ዳውድ

፫ኛ/ ሚስተር ሙራድ ካሜል ፤ (በት/ሚኒስ ቴር የሚሠሩ ፤) ዓባል ፤

፬ኛ/ ብላታ መርስኤ ኀዘን ወልደ ቂስቆስ ዓባል ፤

፭ኛ/ አለቃ ሐረገ ወይን ፤ አባል ፤

፮ኛ/ ባላምባራስ ወልደ ሰማዕት ፤ አባል

፯ኛ/ መምህር ፊላታዎስ ፤ »

፰ኛ/ መጋቢ ሐዲስ ወልደ ሚካኤል ፤ »

በዚያን ጊዜ የትምህርት ቤቱ መምህራን የነበሩት፤



www.ethiopianorthodox.org

፩ኛ/ ሚስተር ሐፍዝ ዳውድ ፤ የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር ፤

፪ኛ/ ሚስተር ሳአድ አዘዝ ፤ (አሁን ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል በካይሮ)

፫ኛ/ መምህር ፊላታምስ ፤

፬ኛ/ አለቃ መኩሪያ ፤

፭ኛ/ አለቃ ወልደየስ ፤

፮ኛ/ አባ ፍስሐ ፤

፯ኛ/ አባ አሥራት ዘገየ ፤

፰ኛ/ ሊቀ ጠበብት አክሊለ ብርሃን ወልደ ቂርቆስ ፤

፱ኛ/ ዓለቃ መርዓዊ ፤

፲ኛ/ ሚስተር ሳሊም ሳውድ ፤

## የጥናት ፕሮግራም ፤

በዚያን ጊዜ ትምህርት ቤቱ በሁለት የተከፈለ ነበር ።

፩ኛ/ የቀሳውስት ክፍል ፤ አስቀድመው ለቀሰሱና ከፍተኛ የሆነ ጠቅላላ ትምህርት ለሚፈልጉ ፤ ይኸውም የሦስት ዓመት ጥናት የሚሰጥበት ነበር ።

፪ኛ/ የዲያቆናት ክፍል ፤ ይኸውም ከአሁኑ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ጋር በመመሳሰል ስምንት ዓመት የሚፈጅ ሲሆን ፤ በተጨማሪ የቤተ ክርስቲያን ትምህርቶችን እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ፤ ዶግማቲክ ፤ ቲዎሎጂ ፤ ዜና አበውንና ዜማን የመሳሰሉትን እንዲማሩ ይደረግ ነበር ።

በመጀመሪያው ዓመት በትምህርት ቤቱ ውስጥ የነበሩት በጠቅላላው ፴፫ ተማሪዎች ብቻ ናቸው ።

## የሁለተኛው ደረጃ ትምህርት ቤት ፤

በ፲፱፻፴፫ ዓ/ ም/ ትምህርት ቤቱ ወደ ሁለተኛ ደረጃነት ከፍ እንዲል ተደረገ ። በዚህ ጊዜ የአንደኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ያለፉትን ተማሪዎች ለዘጠነኛ ክፍል ተቀበለ ። በኢትዮጵያ የ ሚሰጠውን የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ተመሳሳይ የሆነ ፈተና እንዲወስዱ የሚያስችል ትምህርት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ላሉት ተማሪዎች እንዲሰጥ ፕሮግራም ተዘጋጀ ።

በዚሁ ዓመት በ፲፱፻፴፫ ዓ/ ም/ የሕንድ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዓባል የሆኑት ዶክተር ሳይመን የዲሬክተርነቱን ሥልጣን ከአባ ማርቆስ ዳውድ ተረከቡ ። በትምህርት ቤቱ ለሚገኙ ሦስቱ ክፍሎች ፤ ለአንደኛ ደረጃ ፤ ለሁለተኛ ደረጃና ለሃይማኖት ትምህርት መምህራን ማሠልጠኛው ክፍል ከላይ በተጠቀሰው ዓመተ ምሕረት የሚከተሉት ሰዎች በአስተዳደሩ ኮሚቴ ነበሩ ።

፩ኛ/ ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ፤ ሊቀ መንበር

፪ኛ/ ዶክተር ኬ/ኤም ሳይመን ጸሐፊ

፫ኛ/ ክቡር ደጃሽማች ዘውዴ ገብረ ሥላሴ፤ ዓባል

፬ኛ/ » አቶ አበበ ረታ ፤ »

፭ኛ/ ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂ-፤ »

፮ኛ/ ሊቀ ሊቃውንት መሐሪ ትርፌ ፤ »

፯ኛ/ ክቡር ደጃዝማች አምኃ አበራ ፤ »

፰ኛ/ » ልጅ እንዳልካቸው መኰንን ፤ »

፱ኛ/ ክቡር አቶ ከበደ ሚካኤል ዓባል

፲ኛ/ » አቶ ሚሊዮን ነቅንቅ »

፲፩ኛ/ » አቶ አዲስ ዓለማየሁ ፤ »

## የሃይማኖት መምህራን ማሠልጠኛ ኮርስ ፤

በነዚህ ጊዜያት ትምህርት ሚኒስቴር ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሃይማኖትና የሞራል መምህራንን ስለፈለገ ፤ የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ትምህርት ቤትም ይህንን አስቸኳይ ፍላጎት ለማሟላት መምህራንን አሠልጥኖ ለማቅረብ አሰበ። እነዚህም ከስምንተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና የወደቁና የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ያላቸው ፤ ነገር ግን በመምህራን ማሠልጠኛው ውስጥ ገብተው ተፈላጊውን ጥናት ከወሰዱ በኋላ በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ግዛት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሃይማኖትና የሞራል ትምህርት ለማስተማር የፈለጉ ወጣቶች ነበሩ ። ተማሪዎቹም በተለይ ለሦስት ዓመት ጥናት ለተዘጋጀ የሃይማኖት ትምህርት መምህራን ማሠልጠኛ ኮርስ ውስጥ እንዲሰለጥኑ ተደረገ ።

## የኮሌጅ ክፍል ፤

የኮሌጁ ክፍል እንደ ኤውሮፓ ዘመን አቆጣጠር በ፲፱፻፴፰ ዓ/ ም/ በጥቅምት ወር የአርመን



www.ethiopianorthodox.org

ቤት ክርስቲያን ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ቴሬፊግፖላዲያን የኮሌጁ ዲን ሆነው እንዲሠሩ በተደረገበት ጊዜ ተመረቀ ። በዚሁ ዓመት በአእምሮ የበሰሉ የኮሌጅ ተማሪዎች በሚገኙበት ቦታ ያልበሰለ አእምሮ ያላቸው ሕፃናት ተማሪዎች ጋር መገኘት አስፈላጊ መስሎ ስላልታየ ፤ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ክፍል እንዲዘጋ ተደረገ ። የቅድስት ሥላሴ መንፈሴዊ ኮሌጅ ፤ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና የሃይማኖት ትምህርት መምህራን ማሠልጠኛ ክፍል በሚከተሉት የአስተዳደር ኮሚቴ ዓባሎች ሲመራ ቆየ ።

እነርሱም ፤

፩ኛ/ ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ፤ ሊቀ መንበር
፪ኛ/ ብፁዕ አቡነ ቴሬፊግ ፖላዲያን (ጸሐፊ)
፫ኛ/ ክቡር ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል ዓባል
፬ኛ/ ክቡር አቶ አበበ ረታ ፤ »
፭ኛ/ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ፤ »
፮ኛ/ ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ፤ »
፯ኛ/ ክቡር አቶ አበራ ጀምበሬ ፤ »

## የመንፈሳዊ ኮሌጅ በቀ- ኃ- ሥ- ዩኒቨርሲቲ ውስጥ መሆን ፤

የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቬርሲቲ ተመርቆ በተከፈተበት ጊዜ በኅዳር ወር ፲፱፻፷፩ ዓ/ ም. (እንደ ኤውሮፓ ዘመን አቆጣጠር ) መንፈሳዊ ኮሌጅ በዩኒቬርሲቲው ውስጥ ከሚተዳደሩት ኮሌጆች እንደ አንዱ ኮሌጅ ስለተቆጠረ ፤ ጠቅላላ አስተዳደሩ በዩኒቬርሲቲው ውስጥ ሆነ ፤ ብፁዕ አቡነ ቴሬፊግ ፖላዲያንም በ፲፱፻፷፫ ዓ. ም. ሥራቸውን ስለተው ፤ ዶክተር ጆሴፍ በእርሳቸው ምትክ ተጠባባቂ ሆነው እንዲሠሩ በ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቬርሲቲ ሾማቸው ።

## አዲሱ ፕሮግራም ፤

### የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት

የአሥራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች እንደ ሌሎቹ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃን መልቀቂያ ፈተና እንዲወስዱና እንዲሁም በተጨማሪ ከኮሌጁ ልዩ የሃይማኖት ትምህርት ፈተናዎችን እንዲፈተኑ በመደረጉ ነበር ። ለኮሌጁ የሚሰጠው ሥርተ ትምህርትና የፈተናውም ደረጃና ዓይነቱ የዩኒቤርሲቲው የትምህርት ፋኩልቲ ጉባኤ በአወጣውና በወሰነው ውሳኔ መሠረት ከ፲፱፻፷፯ ዓ/ ም/ ጀምሮ በሚገባ በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጎ ይሠራበታል

### የሃይማኖት መምህራን ማሠልጠኛ ፤

ይህ የሃይማኖት መምህራን ማሠልጠኛ ክፍል በ፲፱፻፷፯ ዓ/ም/ እንዲቀር ተደርጎ ነበር ።

ከኮሌጁ እንደተገኘው ፤ ይኸ የሆነበት ምክንያት የስምንተኛን ክፍል መልቀቂያ ፈተና ያላለፉ ተማሪዎች የከፍተኛ ጠቅላላ ትምህርትን ለመከታተል ካለመቻላቸው የተነሣ ሲሆን ፤ እንዲሁም በአንደኛ ደረጃ ትምርት ቤቶች ተመድበው ለማስተማር የማይችሉ መሆናቸው ስለተረጋገጠ ነበር ። ይሁን እንጂ ይህ ኮርስ ለጥቂት ዓመታት ያህል ይሰጥ በነበረበት ጊዜ ትምህርቱን ይከታተሉ የነበሩት ፺፱ ደቀ መዝሙርት በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሃይማኖት መምህራን ሆነው እንዲያስተምሩ በኮርሱ መጨረሻ ሰርቲፊኬት ተሰጣቸው ። በአሁኑ ጊዜ ከነዚህ ውስጥ ሁሉም ሳይሆኑ ብዙዎቹ በሚገባ በማስተማር ተግባር ላይ ይገኛሉ ። የትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር አስፈላጊውን የገንዘብ ዕርዳታ የሚለግስ ከሆነ ፤ በ፲፱፻፷፰ ዓ/ም/ ትምህርት ቤት በሚዘጋበት ጊዜ በክረምቱ ወራት እነዚሁ በየትምህርት ቤቱ ተመድበው በማስተማር ላይ የሚገኙትን መምህራን አስፈላጊው ጥሪ ተደርጎላቸው በመንፈሳዊ ኮሌጅ ውስጥ የስድስት ሳምንት የማስተማር ኮርስ እንዲሰጣቸው ታስቧል ።

ለወደፊቱ አዲስ የሃይማኖት መምህራን ማሠልጠኛ ኮርስ እንዲከፈት ታቅዷል ። የኮርሱም ተካፋይ ለመሆን የሚችሉት የአሥራ አንደኛን ደረጃ ትምህርት በሚገባ አጠናቀው በፈቃደኝ



www.ethiopianorthodox.org

ነት ይህንን የተባለውን ኮርስ ለመከታተል የሚችሉ ሰዎች ናቸው ። በኮርሱ ላይ በሚቆዩበት ጊዜ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተመድበው የሃይማኖትና የሞራል ትምህርት እንዲያስተምሩ የሚያስችላቸውን ተገቢ ዕውቀት እንዲያገኙ ይደረጋል ። ይህ አሳብ በዩኒቨርስቲውና በትምህርት ሚኒስቴር ከተደገፈና ከጸደቀ በኋላ ኮርሱ ከመስከረም ወር ፲፱፻፺፱ ዓ/ ም/ ጀምሮ በመንፈሳዊ ኮሌጅ ውስጥ እንዲከፈት ይደረጋል ።

## የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የፈጸመው ተግባር ፤

በመንፈሳዊ ኮሌጅ ውስጥ የሚገኘው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እስከ አሁን ድረስ ፺፫ ተማሪዎችን ለአሥራ ሁለተኛ ክፍል መልቀቂያ ወይም ለተመሳሳይ ትምህርት ፈተና አዘጋጅቶ አስፈትኗል ። ከዚህም በቀር ብዙዎቹ ከዚህ ትምህርት ቤት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በማቋረጥ ግማሾቹ በልዩ ልዩ መሥሪያ ቤቶች ተቀጥረው ይሠራሉ ። የቀሩትም በትምህርት ሚኒስቴር ውስጥ የአማርኛ አስተማሪዎች ለመሆን አስፈላጊውን የመምህርነት ኮርስ ወስደው በዚህ ተግባር ላይ ይገኛሉ ። ጥቂቶች ከዚሁ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተገቢውን የአሥራ ሁለተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና በመውሰድ በዚሁ ኮሌጅ ገብተው ትምህርታቸውን ይከታተላሉ ።

ኮሌጁ የአራት ዓመት የትምህርት ፕሮግራም በማዘጋጀት ተፈላጊውን ጥናት በሚገባ ተከታትለው ከግቡ ለሚያደርሱ ተማሪዎች የባችለር ኦቭ ቲኦሎጂ ዲግሪ እንዲያገኙ ሲያደርግ እንዲሁም ደግሞ ተፈላጊውን የትምህርት ደረጃ ሳያጠናቅቁ በመቅረት ውጤታቸው ዝቅ ያለውን ተማሪ ዎች ፤ በሌላ በኩል አስፈላጊውን ግዳጅ ከፈጸሙ ፤ የቲኦሎጂ ዲፕሎማ እንዲያገኙ ያደርጋል ። ይህንንም የአራት ዓመት ጥናት ተከታትለው ለዲግሪም ሆነ ለዲፕሎማ በኮሌጁ ውስጥ ገብተው የሚማሩ ደቀ መዛሙርት ከዚሁ ከኛው ከሁለተኛው ደረጃ ትምህርት ቤት ተምረው የወጡ ናቸው ። ስለዚህ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ በዚህ ኮሌጅ የሚገኘውን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ባለበት እንዲቀጥልና ከዚሁም አስፈላጊውን ጥናት በማጠናቀቅ ወደ ኮሌጁ ገብተው የሚማሩ ተማሪዎች እንዲገኙ ማድረጉ ተገቢ ነገር ነው ።

## በቀ- ኃ- ሥ- ዩ- የመንፈሳዊ ኮሌጅ ተመራቂዎች

በመንፈሳዊ ኮሌጅ በ፲፱፻፶፫ ዓ/ ም/ ገብተው በዩኒቢርሲቲው ደረጃ የሚሰጠውን የአራት ዓመት ጥናት በሚገባ በማጠናቀቅ በ፲፱፻፶፯ ዓ/ ም/ የጨረሱት ተማሪዎች የመጀመሪያዎቹ የመንፈሳዊ ኮሌጅ ተመራቂዎች ነበሩ ። በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የምረቃ ሥነ በዓል ሰኔ ፤ ፲፱፻፶፯ ዓ. ም. እነዚሁ ስድስት ወጣቶች የባችለር ኦቭ ቲኦሎጂ (ቢ- ቲ- ኤች) ዲግሪአቸውን ተቀበሉ ። እነዚህ ስድስት ተመራቂዎች በልዩ ልዩ የኃላፊነት ቦታዎች ተመድበው ለሀገራቸውና ለቤተ ክርስቲ ያናቸው በሚገባ ሲሠሩ ማየት ክብርና ደስታ የተመላበት የምሥራች ነው ።


### ተመራቂዎቹም ፤

፩ኛ/ አቶ አበራ በቀለ ፤
፪ኛ/ » አእምሮ ወንድም አገኘሁ ፤
፫ኛ/ » እጅጉ ደሳለኝ ፤
፬ኛ/ » ገብረ ክርስቶስ መኰንን ፤
፭ኛ/ » ሐጐስ ገብረ ማርያም ፤
፮ኛ/ » ጸጋዬ ሀብቴ ናቸው ።

የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የአራተኛ ዓመት ተማሪዎች ትምህርታቸውን በማቋረጥ ለአንድ ዓመት የብሔራዊ አገልግሎት ተግባር እንዲፈጽሙ በተደረገው ፕሮግራም መሠረት በ፲፱፻፶፯ ዓ/ ም/ ይህ ኮሌጅ አላስመረቀም ። ነገር ግን በ፲፱፻፶፰ ዓ/ ም/ አምስት ደቀ መዛሙርት አስመርቋል ፤ በዚሁ የምረቃ ሥነ በዓል ቀን አራቱ ተማሪዎችየባችለር ኦቭ ቲኦሎጂ (ቢ. ቲኤች) ዲግሪ እንደአገኙና እንዲሁም አምስተኛው ተማሪ ዲፕሎማ እንደተቀበለ ታውቋል ።



www.ethiopianorthodox.org



የመጀመሪያዎቹ የመንፈሳዊ ኮሌጅ ተመራቂዎች ከጥቂቶች መምህሮቻቸው ጋር

<u>የኮሌጁ አስተዳዳሪዎችና መምህራን ፤</u>

በ፲፱፻፶፰ ዓ/ ም/ በኮሌጁና በሁለተኛው ደረጃ የሚከተሉት አስተዳዳሪዎችና መምህራን ይገኛሉ ።

፩ኛ/ ዶክተር ኬ- ሲ- ጆሴፍ ፤ ተጠባባቂ ዲን
፪ኛ/ መላከ ሰላም ሳሙኤል ተረፈ ፤ የቀድሞ ተማሪ አሁን የተማሪዎች ዲን ፤
፫ኛ/ አባ አሥራት ዘገየ ሞግዚት ፤
፬ኛ/ አቶ ገብረ ክርስቶስ መኰንን ፤ የቀድሞ ተማሪ አሁን አስተዳዳሪ ፤
፭ኛ/ ዶክተ ቪ. ሲ. ሳሙኤል ፤
፮ኛ/ አባ ኤ- ቲ- ገብርኤል ፤
፯ኛ/ ዶክተር ሥርግው ሀብለ ሥላሴ ፤ የቀድሞ ተማሪ
፰ኛ/ ሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተ ማ/ ወ/ ፤ የቀድሞ ተማሪ
፱ኛ/ አቶ ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል ፤ የቀድሞ ተማሪ
፲ኛ/ ሊቀ ጠበብት አክሊለ ብርሃን ወ/ ቂ
፲፩ኛ/ አቶ አበራ በቀለ ፤ የቀድሞ ተማሪ



www.ethiopianorthodox.org

፲፪ኛ/ ሚስተር ኤም- አይ- ኩሪያኮስ ፤
፲፫ኛ/ » ኦ- ጂ- ቶማስ ፤
፲፬ኛ/ » ኬ- ሲ- ማቲው ፤
፲፭ኛ/ » ኬ- ዩ- ቶማስ ፤
፲፮ኛ/ አቶ አክሊሉ መዋዒ ፤ የቀድሞ ተማሪ
፲፯ኛ/ » ሉሌ መላኩ ፤ የቀድሞ ተማሪ
፲፰ኛ/ » መዝገበ ተክለ ሃይማኖት ፤

# የቅዱስ ጳውሎስ ሰዋስወ ብርሃን ትምህርት ቤት

ይህ ትምህርት ቤት በ፲፱፻፴፮ ዓ ም ተከፈተ ፤ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በገንዘባቸው የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ትምህርት ቤትን እንደከፈቱ ግርማዊት እቴጌም በራሳቸው መሬት ላይ በገንዘባቸው አሳንፀው የሥራውን አመራር ለብዙ ጊዜ በልዩ ጽሕፈት ቤታቸው ተቈጣጣሪነት አድርገው መሠረት እስኪይዝ ድረስ ከጠበቁ በኋላ ፤ ከበቂ ማደሪያ ጋር ለቤተ ክህነት አስረክበዋል ።

## ዓላማው

ይኸ ትምህርት ቤት በመጀመሪያ የተቋቋመበት መሠረታዊ ዓላማ በጠላት ወረራ ጊዜ የወንድ አካላቸውን ያጡትን ወጣቶች ሰብስቦ ለመርዳት ሲሆን የመጨረሻው ግን እነርሱንም ሆነ ሌላውን ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ለማሠልጠን ነው ።

በእርግጥም በዚሁ ዓላማ መሠረት ብዙዎች የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ወጥተውበት ይገ ፤ ኛል ። የዚህ ትምህርት ቤት ማደግና መስፋፋት ከፍ ያለው የግርማዊት እቴጌ ምኞት ነበር ።

## የትምህርት ቤቱ ደረጃ

ይኸ ትምህርት ቤት ከተቋቋመ ጊዜው ብዙ ሲሆን ፤ ደረጃው ፩ኛ ሆኖ እስከ ፰ኛ ክፍል ብቻ ነበር ። ይኸውም ሊሆን የቻለው በየጊዜው የሚገቡት አስተዳዳሪዎች ጥንታዊውን ትምህርት ከዘመኑ ጋር ለማቀናበር ቅር የተሰኙ በመሆናቸው የሀገርን (የቤተ ክርስቲያን) ትምህርት ብቻ በመመልከት ነበር ። ነገር ግን ከ፶—፶፪ ዓ ም ወዲህ አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ አሁን ሊቀ ሥልጣናት የዚሁ ትምህርት ቤት ዲሬክተር ሳሉ ባደረጉት ጥረት ሙሉ ፩ኛ ደረጃ ሆኖ እንደሌላው የመንግሥት ትምህርት ቤት ሁሉ ወጣቶች ትምህርታቸውን አጠናቀው ለ፪ኛ ደረጃ መግቢያ ፈተና እየቀረቡ በሚገባ ስለአለፉ ፤ አሁን በቅ. ሥላሴ መንፈሳዊ ኰሌጅ ሁለተኛ ደረጃ ክፍል በብዛት ይገኛሉ ።

## የአሁኑ ሁናቴ

በዚህ ትምህርት ቤት በአዳሪነት የሚማሩ 111 የሚሆኑ ተማሪዎች ሲኖሩ በተመላላሽነት የሚማሩ ደግሞ 614 የሚሆኑ ይገኛሉ ፡ በጠቅላላው ግን 725 ተማሪዎች ይገኛሉ ። አስተማሪዎችም 18 ያህል ይሆናሉ ። ትምህርት ቤቱም እያደገ እንደመሔዱ መጠን ፤ በአሁኑ ጊዜ የተፈለገውን ያህል እንኳን ባይሆን ልዩ ጥንቃቄ ተደርጐለት ልዩ ልዩ የእጅ ጥበባት ተቋቁመውለት ሥራውን በማካሔድ ይገኛል ።

ይኸ ትምህርት ቤት በበለጠ ሊሠራበት ቢፈለግ ፤ ሁሉም ነገር ምቹ ነበር ። በደረጃም ወደ ኰሌጅ ሊደርስ የሚችል ነበር ። ምክንያቱም ገቢው ሰፊ ሀብቱ ብዙ ስለሆነ ነው ። ቤተ ክህነቱ አተኵሮ ቢመለከተው ፤ ደኅና ወጭም ቢያደርግለት የቤተ ክርስቲያን ታላቅ መማሪያ ሊሆንና ልዩ ልዩ ጉባኤም ሊደረግበት የሚችል ትምህርት ቤት መሆኑ አይጠረጠርም ።

# የልዑል ራስ መኰንን መምህራን ማ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት

በሐረር ከተማ ጥምቀተ ባሕር ላይ የሚገኘው የልዑል ራስ መኰንን መንፈሳዊ ት/ ቤት ፲፱፻፵፬ ዓ ም ተመሠረተ ። ይህ ትምህርት ቤት በሐረርጌ ሀገረ ስብከት ጽ/ ቤት ተቈጣጣሪነት ሥር የሚተዳደር ሲሆን ፤ ለመምህራኑም ቀለብ ሆነ አለዳሪ ተማሪዎች የምግብ ወጭና ልብስ የሚች



www.ethiopianorthodox.org

ለው ይኸው ጽ/ቤት ነው ። ይህ ት/ቤት የተቋቋመው በግርማዊ ጃንሆይ መልካም ፈቃድ ነው።

የትምህርት ቤቱንም ሕንፃ የሰጡ ግርማዊነታቸው ናቸው ። ልዑል ራስ መኰንን በሐረር ለመንፈሳዊ ተግባር ከፍ ያለ ድካም ያደረጉ ስለሆነ ፤ ትምህርት ቤቱ የታላቁና የደጉ የልዑልነታቸው መታሰቢያ ይሆን ዘንድ በስማቸው ተሰየመ ።

የዚህ ትምህርት ቤት መቋቋም ዐቢይ ዓላማ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን በልዩ ልዩ መሥመር ለማገልገል የሚችሉ መንፈሳውያን ወጣቶችን ለማስገኘት ነው ። በዚህም መሠረት በዚህ ትምህርት ቤት ተምረው ከዚያም ወደመንፈሳዊ ኰሌጅ በመግባት ትምህርታቸውን ጨርሰው ዲግሪ ያላቸው ብዙ በከፍተኛ ሥራ ላይ የሚገኙ አሉ ። እንዲሁም በዚህ ት/ ቤት ከተማሩና የሁለተኛውን ደረጃ ትምህርት በቅድስት ሥላሴ መ/ት/ቤት ከአጠናቀቁ በኋላ ለከፍተኛ ትምህርት በውጭ አገር በመማር የሚገኙ አሉ ።

ይህ ትምህርት ቤት እስከ አሁን ያለው የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ብቻ ነው ። ተማሪዎቹም በዚህ ትምህርት ቤት የሚሰጠውን ትምህርት አጠናቀው ትምህርት ሚኒስቴር የሚሰጠውን የሁለተኛ ደረጃ መግቢያ ፈተና ሲአልፉ ወደ ቅድስት ሥላሴ ሁለተኛ ደረጃ ይመጣሉ ። በዚህም ዓይነት አሁን በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ በ፪ኛ ደረጃ ክፍል አያሌ ተማሪዎች ይገኛሉ ። ትምህርት ቤቱ እንደተቋቋመ ማለት በመጀመሪያዎቹ ስድስት ዓመታት ውስጥ ዓላማውን የተከተለ የጋለ እርምጃ ነበረው ፤ ይህም ማለት ብዙ የሀገር ትምህርት መሠረት ያላቸው ተማሪዎች በብዛት ይገኙበት ነበር ፤ አሁንም አሉ ፤ ግን ብዙዎች አይደሉም ፤ የጠቅላላ ተማሪዎች ቊጥር ከዱሮው ዛሬ ይበዛል ፤ ግን ለተፈለገው ዓላማ የሚሆኑት ደቀ መዛሙርት ቊጥር አነስተኛ ነው ።

እንደተመሠረተ በዚህ ትምህርት ቤት ገብተው እንዲማሩ የሚፈቀድላቸው ወንዶች ብቻ ነበሩ ዛሬ ግን ወንዶችና ልጃገረዶች ወጣቶች በአንድ ላይ ይማሩበታል ። አሁን በዚህ ትምህርት ቤት 30 አዳሪ ተማሪዎችና 556 ተመላላሽ በድምሩ 586 ተማሪዎች ሥጋዊና መንፈሳዊ ትምህርት አጣምረው በመማር ላይ ይገኛሉ ፤ ለትምህርት ቤቱ ሥራ መሪ ደመወዝና ሌላም አበል የሚከፈለው ከትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር ነው ።

---

# የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ፊት

ሁላችንም እንደምናውቀው ሁሉ በርከት ያሉ የአውሮፓውያን አገሮች የክርስትናን እምነት ከመቀበላቸው በፊት ኢትዮጵያ የክርስትናን እምነት ያለ አንዳች ደም መፋሰስ ተቀብላ ፤ ከተቀበለች በትም ጊዜ አንሥቶ እስከ ዚሬ ድረስ ከሕዝቧ ባህልና ኑሮ ጋር አቀላቅላ የቆየችና የክርስቲያን ደሴት ለመሆኗ ታሪክ ይመሰክራል ።

ዘመን እያለፈ ዘመን ተተክቶ በሔደ ቊጥር አዲሱ ዘመን አዲስ ሥራንና አዳዲስ ችግሮችን በማስከተሉ ለችግሮች መፍትሔ ለማስገኘትና ለሥራው መቀላጠፍ ሲባል እንደ ዘመኑ መኖርና ወገን ማፍራት አስፈላጊ ስለሆነም የኢትዮጵያ ቤተ ክርቲያን «ያለእኔ» የሚለውን ዘመን የሻረውን አነጋገር አግላ በክርስቶስ አንድ ከሆንቻቸው ከሌሎች ክርስቲያንኖች ጋር በሥራና በመንፈስ ለመተባበር በብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ መሪነት እንደ አውሮጳውያን አቈጣጠር በ፲፱፻፵፰ ዓ/ም/ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ አባል ሆነች ።

በዓለም አቀፍ ጉዳይ ላይ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከፍ ያለ ዝና ሊኖራት የምትችል ቤተ ክርስቲያን ነች ። ስለሆነም በልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ክርስቲያናዊ ድርጅት ውስጥ በአባልነት



www.ethiopianorthodox.org

ትገኛለች ። ከነዚህም ውስጥ «የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ጉባኤ «የአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤና» የመሳሰሉትም ይገኛሉ ። ይሁን እንጂ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ለመናገር የፈለግሁት በአርእስቱ ስለ ተጠቀሰው ክፍል ብቻ ነው ።

## የዓለም አብያተ ክርስቲያኒናት ጉባኤ ምንድነው ?

ይህ ጉባኤ ከሁለት መቶ የኦርቶዶክስ ፤ የፕሮቴስታንት ፤ የአንግሊካንና (የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን) የጥንት ካቶሊክ (Catholic) እየተባሉ ከሚጠሩት አብያተ ክርስቲያናት ተወጣጥቶ ለማጥናት ለማስተማር ፤ ለአገልግሎትና የክርስትናን እምነት አንድነት ለማፋጠን ታልሞ የተቋቋመ አንድ ከፍ ያለ ተስፋ የሚጣልበት ዓለም አቀፍ ክርስቲያናዊ ድርጅት ነው ።


ከ፹ ሀገሮች የተውጣጡ ልዩ ልዩ ሥርዓተ አምልኮትና ባህል ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት በአባልነት ይገኙበታል ። ምንም እንኳን በዶክትሪን ፤ በሀገር ስሜት በቋንቋ ፤ በታሪክና በሌሎችም ይህን የመሳሰሉ ምክንያቶች የዓለም አብያተ ክርስቲያናት የተለያዩ ቢሆንም የዚህ ድርጅት አባሎች «አንድ ጌታ ፤ አንድ እምነት ፤ አንዲት ጥምቀት አንድ እግዚአብሔርና የዓለም ሁሉ አባት» መኖሩን ያምናሉ ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም አምላክና አዳኝ መሆኑን ሁሉም ስለሚያምኑ የዚህ ማኅበር ቤተ ሰቦች አንድነት ከሁሉም ይልቅ ከዚህ እምነት ሥር የመነጨ ነው ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም ለዚህ ለተቀደሰ እምነት «እግሯን ለጠጠር ደረቷን ለጦር» አሳልፋ በመስጠት ብዙ የመሥዋዕትነት ዘመን ያሳለፈች ስለሆነ ለዚህ ድርጅት የመጀመሪያዋ አባል ነች ። ከሞላ ጎደልም የአባልነት ግዴታዋን ፈጽማለች ።

## የድርጅቱ ጉባኤዎች ፤

ለማኅበሩ ሕይወት ለመስጠትና አዳዲስ ሐሳቦችን አንቅቶ ለመመካከር ድርጅቱ ሦስት ዐበይትና በርከት ያሉ ንዑስ ጉባኤዎችን አድርጓል ። ይሁን እንጂ በጽሑፌ ላይ ልገልጽ የምፈልገው ስለ ዐበይት ጉባኤዎች ብቻ ነው ። እነዚህንም ዐበይት ጉባኤዎቹ የሚያደርገው በስድስትና በሰባት ዓመታት ጊዜ ነው ።

የመጀመሪያውና ድርጅቱም የተመሠረተበት ጉባኤ (Conference) እንደ አውሮጳውያን አቈጣጠር በ፲፱፻፵፰ ዓ/ ም/ ነሐሴ ፳፪ ቀን በአምስተርዳም ውስጥ ነው ፤ በዚህ ጉባኤ የተሰበሰቡት መልእክተኞች «አብሮ ለመኖር» ባላቸው ፍላጎት መስማማታቸውን ዐወጁ ።

የሁለተኛውንም ጉባኤ እንደ አውሮጳውያን አቈጣጠር በ፲፱፻፶፬ ዓ/ም/ በዩናይትድ እስቴትስ ኢባንስተን ውስጥ አድርጓል ። በዚህም ጉባኤ የተሰበሰቡት መልእክተኞች « አንድ ላይ እንድናድግ ይረዳን፤ ዘንድ ፤ራሳችንን በአዲስ መንፈስ ወደ እግዚአብሔር እናቀርባለን » ሲሉ ዐወጁ ።



የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መልእክተኞች
በኒው ዴልሂ ጉባኤ ላይ

ከዚህ ቀጥሎ በ፲፱፻፷፩ ዓ/ ም/ በሕንድ አገር ውስጥ በኒው ደልሂ ከተማ ሦስተኛው ጉባኤ ተደረገ ። በዚህም ጉባኤ ተካፋይ የነበሩት አባሎች ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ሲተረጎም የሚከተለውን ስሜት ያዘለ ዐዋጅ አሥፍረዋል ። ይኸውም «በአንዳንድ ነገሮች ላይ በአንድነት እንድንሠራ ገና ስሜታችን ሙሉ በሙሉ አልፈቀደም ፤ ሆኖም ለምንሻው አንድነት መሻሻል አሳይተናል ። ስለ ዚህ በየቦታው ባንድነት ልንሠራቸው የምንችውን ነገሮች እንፈልግ ፤ እነዚህንም ነገሮች በታማኝነት እየጸለይንና እየሠራን ጌታችን ኢየሱስ ክርስ



www.ethiopianorthodox.org

ቶስ ስለ ቤተ ክርስቲያን ለሚፈልገው አንድነት እንድከም» የሚል ነው ።

## አስተያየት

ከምናየው እንደምንረዳው የክርስትናን እምነት በበለጠ ለማጠንከር የሚረዳው የክርስቲያን መተባበር እንጂ መነጣጠል አይደለም ። ይህንንም በበለጠ የተረዳው ይህ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ከጊዜ ወደ ጊዜ ክርስቲያኖች አንድነታቸውን እንዲያጠነክሩ እንደረዳ ከጉባኤዎቹ ቃለ ጉባኤ ለመረዳት አያዳግትም ። ሆኖም አንድነትን ለማስገኘት ረጅም ጉዞ በትዕግሥት መጓዝ ያስፈልጋል የዚህ ድርጅት ግሥጋሤ በጣም የተፋጠነና አስደሳችም ነው ። በእውነቱ በአተምራት ኃይል ካልሆነ በቀር በ፲፫ ዓመት ውስጥ ከዚህ የበለጠ ለመደርጀትና ለመስፋት ያዳግታል ።

ከላይ በተጠቀሱት ጉባኤዎችም ሆነ በሌሎች ጉባኤዎች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የአባልነት ድርሻዋን ለመካፈል በርከት ያሉ ሰዎች ከዚህም ከዚያም መላኳ ይታወሳል ። ይሁን እንጂ የመልእክተኞቹና የአላላኩ ዘዴ አጉል ነበር ። ምክንያቱም ባጭሩ እንደሚከተለው ነው ።

አልፎ አልፎ በኢትዮጵያ ሬዲዮ ተልከው የሚሔዱትን የመልእክተኞች ስም ዝርዝር ሲነበብ ብንሰማም ለምን እንደሔዱ የቤተ ክርስቲያናችንን ድምፅ በጉባኤው የቱን ያህል እንዳሰሙ ጉባኤው በምን በምን ጉዳዮች ላይ እንደተነጋገረና በንግግሩም ወቅት ምን ዓይነት አሳብ እንዳቀረቡ የጉባኤውስ ውጤት ከምን እንደደረሰና ቤተ ክርስቲያናችን የተስማማችበትንም ያልተስማማችበትንም ውሳኔ ከቶ አንድም መልእክተኛ ሲያስረዳ አልተሰማም ። ታዲያ የዚህ ጉድለት አመጣጥ እንዴት ነው ? ከላኪዎቹ ወይስ ከተላኪዎቹ ? በጉባኤው መገኘትና በእግዚቪሽን ላይ መገኘት በጣም የተለያዩ ነገሮች ናቸው ፤ የነዚህን የሁለቱን ነገሮች ልዩነት አጥርቶ የማያውቅ ሊልክም ሊላክም አይገባውም ፤ በጉባኤው ላይ መሟገት አለ ። በመሟገቱም መርታትና መረታት ሞልቷል ። በጉባኤ ላይ ተገኝቶ ሳይሟገቱ መረታት ግን የደካማነት ጠባይ ነው እላለሁ ።

ይህንንም ምክንያት በመስጠት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስል በጻድቃንና በሰማዕታት እንዲሁም በመላእክት ስም የተሠሩትን አያሌ ግንቦች አለማለቴን ወይም መሸ ለጸሎት ነጋ ለመሥዋዕት የሚሉትን ዲያቆናት ፤ ካህናትና ጳጳሳት ብቻ አለመጥራቴ እንዲታወቅልኝ ሳሳስብ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስል ግንቡን ፤ ምእመኑን ዲያቆናቱን ካህናቱንና ጳጳሳቱን በመላ በሚያጠቃልል አስተሳሰብ ላይ በመመርኮዝ መሆኑን ለአንባብያን እገልጣለሁ ።

## የሥራ አመራር

የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባዔ የሥራ አቋም የሚመራው ጠቅላላው ጉባኤ በሚሰጠው መምሪያ ሲሆን ጠቅላላው እንቅስቃሴ የሚካሔደው በማእከላዊ ኮሚቴና ጄኔቭ ውስጥ በሚገኘው ጠቅላይ ጽ/ቤት ነው ። በጽ/ቤቱም ውስጥ ከሁለት መቶ ያላነሱ ቋሚ ሠራተኞች ከመኖራቸውም በላይ ሌሎች በ፺ ሀገሮች ተሰራጭተው የሚሠሩ አምስት መቶ ሠራተኞች አሉት ፤ ለሥራ ማስኬጃም በዓመት ፳፫ ሚሊዮን (የኢትዮጵያ ብር) ባጀት አለው ።

የድርጅቱ የሥራ አቋም በአራት ታላላቅ ክፍል የተከፈለ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ ጎልተው ና ደርጅተው የሚታዩት «የአብያተ ክርስቲያናት ተራድኦ ፤ የስደተኞችና የአገልግሎት ክፍል የሚባሉት ነው ። ይህ ክፍል አብያተ ክርስቲያናት በያሉበት በስደት ላይ ለሚገኙና ለሚሠቃዩ ሕዝቦች ሁሉ አገልግሎታቸውንና ዕርዳታቸውን በአንድነት ለማዳረስ የሚጥሩበትና የሚያከናውኑበት ክፍል ስለሆነ ይህ ርኅራኄ በዓለም ላይ ተነዝተው ይንከራተቱ ለነበሩ ፪፻፶ ሺህ ስደተኞች መጠጊያን አስገኝቷል ። ከዚህም ላይ አቅማቸው ያነሰ አብያተ ክርስቲያናትን በመርዳትና በልዩ ልዩ የሥራ መሥመር አብያተ ክርስቲያናት ጥረታቸውን እንዲያስተባብሩ በሰፊው ረድቷል ።

## የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ተራድኦ ጽ/ቤት በኢትዮጵያ

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ጋር ስለምታደርገው ግንኙነት በብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ፤ የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ መልካም ፈቃድ በ፲፱፻፵፩ ዓ. ም. አንድ ኮሚቴ ተቋቁማል ፤ ኮሚቴው ከተቋቋመ ወዲህ ለሥራ ቅልጥፍና ያገለግል ዘንድ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ አንድ ጽ/ቤት አቋቁሟል ፤ ለዚህ ጽ/ቤትም መቋቋም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስ ቲያን የቢሮና የመሣሪያ ስጦታ ስታደርግ የዓ ለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤም በትርፍ ጊዜው ለሚሠራ ኢትዮጵያዊ ዲሬክተር ደሞ ዝና ዲሬክተሩ ለሥራ ጉዳይ በሚዘዋወርበት ሰዓት የመጓጓዣና ልዩ ወጪ ከመስጠቱም በላይ ለጽ/ቤቱ ጸሐፊ ደሞዝ ይከፍላል ። በተጨማሪም በውሰት ስም አንድ እንግሊዛዊ ረዳት ዲሬክተር ልኮ ሰውዬው በሥራ ላይ ይገኛል ። ምንም እንኳን በርከት ያለውን ወጪ ድር ጅቱ ቢከፍልም ቀስ በቀስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስ ቲያን ጠቅልላ ትይዘዋለች የሚል እምነት በድር ጅቱ በኩል አለ ። ለተባለው ጽ/ቤት ከድርጅቱ የተሰጠውን «ላንድሮበር» ትተን ስለ ጽ/ቤቱ ወጪ የተነጋገርን እንደሆነ በ፲፱፻፷፰ ዓመተ ምሕ ረት ብቻ ፴፪ሺ ፰፻ ብር ከድርጅቱ ሲሰጥ ፲፰ሺ ብር ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሰጥቷል ። በእኔ አስተያየት ይህ አወጣጥ የትብብር ስሜት ያዘለ ነው ብዬ እገምታለሁ ። ራስን ለመርዳት ሳይሞክሩ እርዱኝ ማለት ነውር ነው በተቻለ መጠን ራስን እየረዱ ከሌላ ዕርዳታ መጠየቅ ግን ባያስመሰግንም አያስነውርም ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከድርጅቱ የም ትጠይቀው ዕርዳታ ሁሉ በዚህ ኮሚቴ ከተጠና በኋላ እንደ አስፈላጊነቱ ታይቶ ወደ ዓለም አብ ያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ይቀርባል ። ድርጅቱም ነገሩን ካመዛዘነ በኋላ ተገቢ ሆኖ ሲገኝ ወደ አባል አብያተ ክርስቲያናት ያስተላልፈዋል ። መስጠት የማይታክታቸው አብያተ ክርስቲያናትም የዕር ዳታ እጃቸውን ሲዘረጉ ከላይ በተጠቀሰው ኮሚቴ አማካይነት ዕርዳታው ለጠያቂዋ ቤተ ክርስቲያን ይቀርባል ።

በዚህ አኳኋን ኢትዮጵያ ሰፋ ያለ ችሮታ ተደርጎላታል ። ኮሚቴው ከተቋቋመ ወዲህ የተሰ ጠው ዕርዳታ እስከ ሁለት መቶ ሺ ብር ደርሷል ፤ ምንም እንኳን ድርጅቱ በሌላ ቦታ ከሚያደርገው ዕርዳታ ጋር ሲያመዛዝኑት በጣም ያነሰ ሆኖ ቢገ ኝም ድርጅቱ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ለመ ርዳት ያለው ፈቃድ አነስተኛ ነው ።

ከተደረጉት ዕርዳታዎች መካከል ጥቂቶቹን እጠቅሳለሁ ፤ በማኅበረ ሐዋርያት የተወጠነው የኩ ናማ የሥራ አቅድ በሚገባ ተደግፏል ። ይህ ማኅ በር በሹምቡኮ ለሚያሠራው ት/ቤት መርጃ ይሆን ዘንድ ፩፻፷፫ ሺህ ብር ዕርዳታ ለማግኘት ተስፋ ሲሰጠው ግማሹ ገንዘብ ለማኅበሩ ደርሷል ።

በባሌ ጠ/ግዛት አዲስ አማንያን ለሚያስተ ምሩ ሦስት አስተማሪዎች ለሁለት ዓመት ያህል ደመወዝ ከፍሏል ።

ለሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ግምቷ ፳ሺህ የሆነ ቦልስዋገን መኪና ከመርዳቱም በላይ የማኅበሩን የቅርብ ሠራተኞች መጓጓዣ በመቻል በልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ የሥራ ሠፈ ሮች(WORK CAMPS)ላይ እንዲሳተፉ ረድቷል ።

ቁጥራቸው በርከት ያሉ ወጣቶች የከፍተኛ ትምህርት እንዲያጡኑ ዕድል ሰጥቷል ፤ ድርጅቱ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ለመርዳት በርከት ያሉ የሥራ ትልሞች አሉት ፤ ከነዚህም ውስጥ በጣም ጠቃሚ ሆኖ የተገመተውና ከሁሉም ጎልቶ የሚታየው በዝዋይ ሐይቅ አካባቢ ሊሠራ በመጀ መር ላይ ያለው የካህናት ማሠልጠኛ ጣቢያ ነው። ት/ቤቱ ተሠርቶ ሲያልቅ ፪፻፶ ተማሪዎች እንደሚ ይዝ ይገመታል ። ት/ቤቱ በከፊል ራሱን የሚያ ስተዳድርበት አንድ ትልቅ እርሻ እንዲኖረው ተስፋ አለ ። ይህንን ትምህርት ቤት ለማሠራት በሚደረገው አስተዋጽዖ በዓለም አብያተ ክርስቲ ያናት ጉባኤ የተራድኦ ጽ/ቤት በኩል የአሜሪካን አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፳፩ሺ፪፻፶ ብር



www.ethiopianorthodox.org

ለመስጠትና ወደፊትም ዕርዳታውን በ፳፯ሺ፪፻፱ ብር ለማሳደግ ቃል ገብቷል ። የጀርመን አብያተ ክርስቲያናትም እንደዚሁ ፺ ሺህ ብር ለመርዳትና የዳንማርክም አብያተ ክርስቲያናት የ፳፭ ሺህ ብር እርዳታ ለመስጠት በመዘጋጀት ላይ ናቸው ፤ እነሆ እንግዲህ ለዚህ ት/ቤት ማሠሪያ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የ፩፻ሮ፪ ሺህ ፭፻ ብር ዕርዳታ ታገኛ ለች ማለት ነው ።

ማጠቃለያ

እነሆ ባጭሩ እንደዘረዘርሁት የዓለም አብ ያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስ ቲያን ያደረገውን ውለታ ከሞላ ጐደል ዘርዝሬ አቅርቤያለሁ ። በዚህ ጊዜ ከአንባቢያን የኢትዮ ጵያ ቤተ ክርስቲያንስ በበኩሏ ለድርጅቱ ምን አበርክታለች የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል ። ጥያ ቄው ከባድ ነው ሆኖም አስተሳሰባችን ሁልጊዜ በገንዘብ ዙሪያ ብቻ መዳከር አይገባውም ። እር ግጥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የአባልነት ድርሻ ምንም በዓመት በዓመት----ብር ከመክፈል በቀር ለድ ርጅቱ ያበረከተችው የገንዘብ ዕርዳታ እምብዛም ነው ። ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በታላቅ ተጋድሎ ጠብቃ የቆየችውን አፍሪካዊ (ኢትዮጵያዊ) የሆኑ ክርስቲያናዊ ቅርስና እንከን የሌለበት ኦርቶዶክሳዊ ቲኦሎጂ (እምነት) በየጉ ባኤው በማሰማትና ለጎብኝዎችም በማሳየት ከፍ ያለ ማበረታታትን ከማቅረቡም በላይ ድርጅቱ እንዲጠነክርና ከአሰበው ዓላማ እንዲደርስ የችግ ሩም ሆነ የደስታው ተካፋይ ለመሆን በሙሉ ፈቃድ አባል መሆኑ ብቻ እፁብ ድንቅ የሚያሰኝ ና ከፍ ያለ ግምት የሚጣልበት ዘመናዊ እርምጃ ነውና አሳቧን ይደልዎ ብለን በአንክሮ እንደግፋ ለን ። ይህም ኢንተርናሽናላዊ ግንኙነት የኢትዮ ጵያ ቤተ ክርስቲያን ነፃነት ከተመለሰ ወዲህ በዚህ በሃያ አምስት ዓመት ከፈጸመቻቸው ዓበ ይት ነገሮች አንዱ ነው።

ጸጋዬ ሀብቴ

# የመንፈሳውያን ማኅበሮች መቋቋም

የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግ ሥት በልዩ ልዩ የሥራ ዘርፎች ፤ በማኅበራዊ ኑሮ በፖለቲካ ፤ በኤኮኖሚና እንዲሁም በሃይማኖት ከፍ ያለ እንቅስቃሴ የተደረገበት ዘመን መሆኑ አያጠ ራጥርም ። ከዚህም የተነሣ በተለይም በመንፈሳዊ ረገድ በግርማዊነታቸው መልካም ፈቃድና ትእ ዛዝ የተቋቋሙት መንፈሳውያን ድርጅቶች ብዙ ዎች ናቸው ።

እንዲሁም በሕዝብ ይልቁንም በወጣቱ ትው ልድ ባለፉት ፳፭ ዓመታት ውስጥ ከተፈጸሙት ክርስቲያናዊ ተግባሮችና እንቅስቃሴዎች መካከል ዐበይት የሆኑት ማኅበሮች አቋምና ሥራ እንደ ሚከተለው ነው ።

## ፩ኛ/ ሃይማኖተ አበው

ሃይማኖት አበው በ፲፱፻፵ ዓ ም ግንቦት ፳፬ ቀን ተቋቁሞ «የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር » ተብሎ በመሰየም በአዲስ አበባ የኮሌጅ ተማሪ ዎች ተመሠረተ ። የበላይ ጠባቂ ግርማዊ ጃንሆይ ሲሆኑ የማኅበሩ አባሎች በጠቅላላ እስከ ፪ሺህ ወጣቶች እንደሚደርሱ ታውቋል ። ማኅበሩ መንፈ ሳዊ ስለሆነ የሳይንስ ዕውቀትና የፍልስፍና ብዛት ያላላው የወጣቱ አንጐል እግዚአብሔርን ከማወቅ ዳር ድንበር እንዳይወጣ ፤ በድቡሽትም ላይ እንደ ተሠራ ቤትም የዘመኑ ማዕበል ፤ ሞገድ እንዳይገለ ብጠው ከአበው የመጣውን የእምነት መሠረት ያጠነክራል ።

### ፩ኛ/ ዓላማው ፤

ሀ/ የማኅበሩ ዋና ዓላማ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ብላ የምታምነውን እምነት ከጠቅላላ ባህሏ ጋር አቀናብሮ ለወጣቶች በማስተማር የትዮጵያን ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ለመደ ገፍ ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

ለ/ ባለው ዕውቀት የአባቶችን ባህልና መንፈሳዊ ልማድ ጠብቆ አቆይቶ ወጣቶቹ የሀገሪቱም ሆነ የቤተ ክርስቲያናችን የነገ አባቶች ስለሚሆኑ ማኅበሩን ለተከታዩ ትውልድ የባህል ባንክ ለማድረግ ነው ።

ሐ/ የዘመኑ ወጣት በዘመናዊ የዕውቀት ብዛት ባልተደላደለ የአሳብ ትግል ሲባክን የሞራል ውድቀት እንዳይደርስበት በመንፈሳውያን መምህራን አማካይነት መንፈሳዊ ኃይልን ለማስጨበጥ ነው ። የማኅበሩ ዓላማ ከዚህ በላይ በፊደል የተዘረዘሩትንና የመሳሰሉትን የተከተለ ለመሆኑ እስከ አሁን ሠርቶ ባሳየው የሥራ ውጤት ከፍ ያለ ግምት የሚሰጠው ሆኖ ተገኝቷል ።

በዓላማው ወጣቶችን በመንፈስ የሚያበለጽግ ማኅበር ስለሆነ የስምንተኛው ሺህ የሰው መንፈስ ልጓሙ እንደተለቀቀ ፈረስ ጭልጥ ብሎ ጽድቅና ኃጢአት ተለይቶ ባልታወቀበት ሜዳ ሽምጥ በሚጋልብበት ጊዜ የሚሠራውን አጥቶ ብር ብር የሚለውን በምግበ ነፍስ ያለውን የወጣቱን ኃይል በአንድ የእምነትና የግብረ ገብነት ክበብ ውስጥ ወስኖ ለመያዝ ከዐላማው አንዱ በዚህ የቆመ ነው ። ሃይማኖተ አበው በመባል በስም ከፍተኛውን ማዕርግ የወሰደ በዕድሜ ገና ወጣት የሆነ ይህ ማኅበር ሠርቶ ያሳያቸው የሥራ ፍሬዎች በጣም በርከት ያሉ ናቸው ። ከሙሉ በከፍሉ የቀሩት ዋና ዋናዎቹም ከዚህ በታች ተጽፈዋል ።

ሀ/ ማኅበሩ ከኮሌጅ ተመርቆ የወጣ ወጣት የሚሠራበት አንድ የደረጃ ጽ/ቤት አለው ።

ለ/ ወጣቶችን ከቤተ ክርስቲያን ጋር ለማስተዋወቅ ሥርዓተ ቅዳሴውን በሚስማማ አኳኋን አዘጋጅቶ አሳትሟል ።

ሐ/ በወር በወሩ እየታተሙ የሚወጡ በጥሩ አቀራረብ ተዘጋጅተው ለወጣቶች የሚቀርቡ የአማርኛና እንግሊዝኛ ጋዜጦች አሉት ።

መ/ ስለሥራ ክንውን አዳዲስ አሳቦችን ለማንቃትና የየቅርንጫፎቹን ሠራተኞች ለማቀራረብ ሲባል በየዓመቱ አንድ ጠቅላላ ጉባኤ ይደረጋል

ሠ/ በየሳምንቱ እሑድ እሑድ በአራት ሰዓት ተኩል በቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለወጣቱ በሚስማማ አኳኋን የሥርዓተ ቅዳሴ ጸሎትና አእምሮን የሚያጐለምስ ትምህርት አዘጋጅቶ ያስተምራል ። ስለዚህ ዮሐንስ በራእዩ ለተጠማ ከሕይወት ውኃ ምንጭ ያለዋጋ እኔ እሰጣለሁ አለ ፤ አልፋና ዖሜጋ ብሎ የተናገረው መምህራን በጸጋ ተቀብለው በጸጋ ስለሚለግሡት የዚህን ዓይነት ትምህርት እንደሆነ ወጣት ሁሉ ሊገነዘበው ይገባል ። ውኃ ጥምን ይቆርጣል ፤ ቢጠጡት ያረካል ከእድፍ ያነጻል ትምህርትም የሕይወት ውኃ ስለሆነ ጽምዐ ነፍስን ድንቁርናንና ኃጢአትን አጥፍቶ ከነውር ያርቃል ።

፫ኛ/ ከሌሎች ማኅበሮች ጋር ያለው ግንኙነት

አሥራው (ሰዎች) ካሉ አዕፁቅ ጭፍሮች አይታጡም ። ይህን የመሰለ ማኅበርና ድርጅትም ካለ ቅርንጫፎች የሚሆኑ ሌሎች ማኅበሮች የሚቋቋሙበት ቦታ ስለማይገድ ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር እንደመሆኑ ዓላማውን በየጠቅላይ ግዛቱ ለሚገኙ ወጣቶች ለማዳረስ ቆርጦ የተነሣ ስለሆነ ከዚህ በሚከተሉት ጠቅላይ ግዛቶችና አውራጃዎች ቅርንጫፎች እንዳሉት ታውቋል ።

በሸዋ ጠ/ ግዛት

ሀ/ በናዝሬት ፤
ለ/ በወሊሶ ፤
ሐ/ በደብረ ብርሃን ፤

በሌሎችም ጠቅላይ ግዛቶች

ሀ/ በአሥመራ ፤
ለ/ በጎንደር
ሐ/ በሐረር
መ/ በአሰላ ፤

ሠ/ በጅማ ከተማ ሰፋ ያሉ ድርጅቶች ተቋቁመው በመሥራት ይገኛሉ ። የሃይማኖተ አበው ማኅበር ለጊዜው ያሉት ቅርንጫፎች እነዚህሲሆኑ ግንኙነታቸው የጠበቀ እንዲሆን በዋናው ጽ/ቤት አማካይነት በደብዳቤ በየጊዜው ግንኙነት ያደርጋሉ ። ከዚህም በተጨማሪ ዋና ጸሐፊው በየቅርን



www.ethiopianorthodox.org

ጫሮቹ እየተገኙ የምክርና የአሳብ ርዳታ ያበረክ ታሉ ። ይኸውም ማኅበሮቹ ባላቸው የሥራ ክን ውን ላይ ኃይላቸው በበለጠ እንዲደረጅ ለማድረ ግና የማስፋፊያን ዘዴ ለማግኘት ይረዳል ተብሎ ከፍ ያለ እምነት የተጣለበት ነው ። ከዚህም ሌላ በዓመት አንድ ጊዜ ጠቅላላ ጉባኤ ስለሚደረግ ጉባኤው ግንኙነታቸውን በበለጠ ያጠነክረዋል ተብሎ እምነት ሲጣልበት ከአሁን በፊት አንድነት የሰጠውን ጥቅም በማስታወስ ነው ።

፫ኛ/ ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጋራ ያለው ግን ኙነት ፤ በመሠረቱ ሃይማኖተ አበው ማኅበር ከኦርቶ ዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን የተወለደ እንደመሆኑ መጠን የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን እምነት እንዳይደክም ለመደገፍ ስለሆነ ከቤተ ክርስቲያን ጋር የጠበቀ ግንኙነት አለው ። ከቤተ ክርስቲያን ሥራ አንዱ የወንጌል ትምህርት እንዲስፋፋ ነው ። ስለዚህ በየሳምንቱ እሑድ ወጣቶችን በቤተ ክርስቲያን ሰብስቦ በማ ስተማር አንዱን ከባድ ሸክም ይዘላታል ።

ቤተ ክርስቲያንም በበኩሏ ወጣቶች ልጆቿ በሃይማኖት እንዲጸኑ በምግባር እንዲታነፁ የዘወ ትር ተግባሯ ስለሆነ ሥራው የሚቃናበት አንድ ጽ/ቤት የሚሆን ክፍል ለማኅበሩ አበርክታለች ። ከዚህም ጋር ወጣቶች በሃይማኖተ አበው አማካይ ነት ከሚሰጠው ትምህርት ተሳታፊዎች እንዲሆኑ ለመኪና ማመላለሻ ለቤንዚን የሚሆን በየሳምንቱ ፳ (ሀያ የኢት/ብር) ከመስጠት አልተቆጠበችም ። ወጣቶቹ በጆሮ የሰሙትን ሃይማኖታቸውን በጽ ሑፍ እንዲረዱ በየወሩ የሚወጣውን የአማርኛ ጋዜጣ በማሳተም ትረዳለች ።

ማኅበሩ በየዓመቱ ለሚያደርገው ስብሰባም «ርኅው ቤትየ ለኵሉ» ቤቴ ለሁሉ ክፍት ነው በማለት በዘመናዊው አቅድ ለሚራመድ ለዘመ ናዊው ወጣት በዘመናዊው ካቴድራል በቅድስት ሥላሴ እንዲደረግ በመፈቀዱ ግርማዊነታቸው በሚገኙበት እጅግ የሰውን መንፈስ በሚማርክ ሁኔታ በዓሉ ይከበራል ። ቤተ ክርስቲያንና ሃይማ ኖተ አበው በዚህ መንፈስ የተሣሠሩ ናቸው ። «ጥጃ ጠባ ከሆድ ገባ» ይባላል ። ቤተ ክርስቲያን አቅሟ በሚፈቅድላት መጠን ለማኅበሩ ብትለግሥ ቅርታ አይሰማትም ማኅበሩም ለእናት ቤተ ክርስቲ ያን ሙሉ ርዳታን ለመስጠት ታጥቆ የተነሣ ነው ። ስለዚህ ለሁሉም እግዚአብሔር ኃይል ይስጣቸው።

<u>ከዓለም አቀፍ አብያተ ክርስቲያናት ጋር ያለው ግንኙነት</u>

ዛሬ ዓለም በብቸኝነት ችግሩን ለመግፋት እን ዳልቻለ ተገንዝቦ የራቀው ተቃርቧል የተለያየው አንድ ሆኖአል ። ሰላም ባለሥልጣኖች በሚሰበሰቡ በት ጉባኤ እየተገኘ የሙጥኝ ይላል። እስከ አሁንም ደኅና ክብሩ ፤ አልተነካም ።

ቤተ ክርስቲያንም በሃይማኖት ሰበብ የነበረ ውን ክብረ ነክ ጭቅጭቅ ረስታ አንድነት ኃይል እንደሆነ ወደ ማስታወስ ተመልሳለች ። ስለዚህ ሃይማኖተ አበውም በጥቂት ጊዜ በዓለም ከፍ ያለ ዝናን ያተረፈ ስለሆነ ፤ ፩ኛ/ በ፲፱፻፶፯ ዓ/ ም/ መጨረሻ ላይ የዓለም ክርስቲያን ተማሪ ዎች ፌዴሬሽን (WSCF) እየተባለ ከሚጠራው ዓለም አቀፍ ማኅበር ጋር አባል ሆነ ። ፪ኛ/ ከዓለም አብያተ ክርስቲያናትም የጠበቀ ግንኙነት አለው ። አባልነቱ የስም ብቻ ሳይሆን ጐን ለጐን ተሰልፎ የሥራ ሞያውን ለማሳየት ስለሆነ ሃይማኖተ አበው ስሙ ከፍ ብሎ የተጠቀሰው ድርጅት በየጊዜው በሚያዘጋጀው ልዩ ልዩ የሥራ ቦታ ተካፋዮች የሚሆኑ የጥናት ጓዶችን ከመላክ ያላቋረጠ በመ ሆኑ በዚህ ዓመትም ኮሪያ በሚያደርገው የአንድ ዓመት የሥራ ድርጅት ተካፋይ ለመሆን አቶ አሸ ናፊ ሙኄ የተባለውን የማኅበሩ አባል የላከ ስለ ሆነ ወጣቱ በዚያው ሲሳተፍ ይገኛል ። ፫ኛ/ በቅ ርቡም ከደቡብ ዩናይትድ እስቴትስ የፕሬስ ቤተ ርያን ዩኒበርስቲ ተማሪዎች ማኅበር ጋር አዲስ ግንኙነት መሥርቷል ።

፬ኛ/ በአፍሪካ የክርስቲያን ተማሪዎች ፌዴ ሬሽን ጋር አባል እንደመሆኑ መጠን በቅርብ ጊዜ በሚደረገው የምሥራቅ አፍሪካ ተማሪዎች ስብ ሰባ ላይ ለመካፈል ማኅበሩ በመዘጋጀት ላይ እን ዳለ ከማኅበሩ ዋና ጸሐፊ ለማወቅ ተችሏል ።



www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ ሃይማኖተ አበው ከአፍሪካ እስከ ደቡብ ዩናይትድ እስቴትስ ከዚያም በዓለም ውስጥ በመመላለስ በስምንት ዓመታት ርምጃውን ያፋጠነ በመሆኑ ወደፊት ላለው አቅድም ምናል ባት ርምጃው የተቃና ይሆናል ተብሎ በተስፋ ይጠበቃል ።

## የገንዘብ ርዳታ

ገንዘብ የደም ሥር ነው ። ሰው የደም ሥሩ ከተቃወሰ የተሟላ ሕይወት አያገኝም ፤ የሚያስከትለውንም ጉድለት ለማብራራት ጥናቱን ሰፊ ጊዜ ለወሰዱ እስፔሻሊስቶች ትቼ ወደ ገንዘብ ጥቅም እመለሳለሁ ።

አንድ ማኅበራዊ ኑሮ ርምጃው የተቃና የሚሆነው የተሟላ ሀብት ሲያገኝ ነው ። ስለዚህ የማኅበሩ የበላይ ጠባቂ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በመሆናቸው ዕድሉ የተቃና ሆኖለት በየጊዜው በጠየቀ ቁጥር ሰፊ የገንዘብ ርዳታ ከግርማዊነታቸው ተደርጎለታል ። ከፍ ብለን እንደገለጽነው ቤተ ክርስቲያንም ሥራው የሚካሔድበትን አንድ ጽሕፈት ቤት ከመስጠቱም በላይ በየሳምንቱ ፳ (ሃያ ብር) የምትሰጥ ስለሆነ በየዓመቱ ፩ሺ፵ ብር (አንድ ሺህ አርባ ብር) ለማኅበሩ ታስረክባለች ማለት ነው ። የአማርኛ ጋዜጣ ማሳተሚያ ገንዘብ በመስጠትም ርዳታዋን ታቀርባለች ።

ከዚህም ሌላ ከዓለም ክርስቲያን ተማሪዎች ፌዴሬሽን በዓመት ፬ ሺህ (አራት ሺህ የአሜሪካን ብር) ርዳታ ያገኛል ።

ከዓለም አብያተ ክርስቲያንም ልዩ ልዩ ርዳታን የሚያገኝ ሲሆን በተለይም ዛሬ ማኅበሩ የሚገለገልበት ኮምቢ ቦልስዋገን የተሰጣቸው ከዚህ ድርጅት ነው።ስለዚህ ሃይማኖተ አበው ወደፊት እያደገ ሲሔድ ርዳታውም እየተስፋፋ እንዲሔድ እምነት የተጣለበት ነው ። ሀብታም ለመሆን መሥራት ያስፈልጋል ። ማኅበሩ እስከ አሁን ድረስ ሠርቶ ባሳየው የሥራ ውጤት ከውስጥም ከውጭም ርዳታ ሊያገኝ ችሏል ።

## የአሁንና የወደፊት ሁኔታው

ሰው ነገ የሚሆነውን የማያውቅ ቢሆንም ያለፈውንና ዛሬ የደረሰበትን የኑሮ ደረጃ በማመዛዘን ነገ እንዲህ ይሆናል የሚለውን እምነት ጨብጦ የአምስት የአሥር ዓመት የጥናት ፕላን በማሳየት ነቢይ ለመሆን ይሞክራል ። «እስመ ስሙ ይመርሆ ኀበ ግብሩ» አሁንም ሃይማኖተ አበው ከፍተኛውን ስም የወሰደ ስለሆነ ስሙን ከግቡ ያደርሰው ይሆናል ተብሎ ግምት የተጣለበት ነው ።

በዚህ ዓመት በ፲፱፻፺፰ ዓ/ም/ ካለፉት ዓመታት የተለየ አዲስ ፕሮግራም በማዘጋጀት አዲስ ዓምድ ከፍቷል ። በቤተ ክርስቲያን በኩል ያለው የወጣቱ ዕውቀት የተሟላ እንዲሆን ከልብ የሚደክም በት ስለሆነ በቤተ ክህነት የስብከተ ወንጌል አዳራሽ ውስጥ ይደረግ የነበረው ትምህርት በታላቁ ካቴድራል በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ እንዲሆን በመወሰኑ አድማጮች ሥርዓተ ቅዳሴንና ትምህርትን አንድ ጊዜ ሊሳተፉ ችለዋል ። ይህ ለወጣቶችም ሆነ ለቤተ ክርስቲያን አዲስ ምዕራፍ ነው ። ካልቀረቡ ጥቅምና ጉዳቱን ለማወቅ አይቻልም ወጣቶቹም ስለ ቤተ ክርስቲያናቸው ስሜት ሊያድርባቸው የሚችል ለቤተ ክርስቲያን ሙሉ ይዞታ ተካፋይ ሲሆኑ ነው ተብሎ በጥናት የተደረገ ስለሆነ ይህ የብዙዎችን ልብ ማርኳል ።

ስለዚህ የሃይማኖተ አበው ማኅበር እስከ አሁን ድረስ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ሲሠራቸው የቆየውን ልዩ ልዩ ሥራዎች ወደፊት እንዲገፋ እንጂ እንዳይቆሙ ታላቅ ጥረት ይደረጋል ። ማኅበሩ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር እንደመሆኑ መጠን ስብከተ ወንጌል ወዳልተዳረሰበት ሁሉ ትምህርት ለማዳረስ ቅርንጫፎችን በማቋቋም ሥራውን በየጠቅላይ ግዛቱ ይቀጥላል። ባሁኑ ጊዜ ከባድ የሆነው የተማሪዎች ችግር ተስማሚ የሆነ የመኖሪያ ቤት ማጣት ስለሆነ ፤ ይህን ችግር በመጠኑ ለማቃለል በማሰብ የቤቱ አሠራር ፕላን በመሐንዲስ ኮሌጅ አርቲክቶች በማስጠናት ላይ ይገኛል ፤ ይሁን እንጂ የማኅበሩ የወደፊት



www.ethiopianorthodox.org

አቅድ እንዲቃና የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ እን ዲሆን ከሥራ ጋር አጥብቆ እግዚአብሔርን የሚለ ምን ሲሆን ፤ የሁላችንም እርዳታ እንዲጨመርበት የክርስትና እምነታችን ያሳስበናል ።

### ማጠቃለያ

ብዙ ጊዜ ከአበው የሚገኘው ሁሉ ከአለፉት ዘመናት ወግ ታሪክ ለሚመጣው የሚበጁ ምክር ተግሣጽ ናቸው ። ወጣቶቹ ይህን በመገንዘብ ያለ ፈው የአበውን እውነተኛ እምነት ለማስታወስ የወደፊቱም የተከታዩ ትውልድ ዓላማ የተቃና እንዲሆን የማኅበሩን ስም «ሃይማኖተ አበው» ብለ ው ሰይመውታል ። በዘመናችን የሚሠራው ሥራ ሁሉ ዕውቀታቸው ከፍ ብሎ በሚገመቱ ሰዎች ተጠንቶ ስለሚቀርብ ያለድካም ከመከናወኑም በላይ ውጤቱ እጅግ ያማረ ይሆናል ። ስለዚህ ይህ ማኅበርም የአበውን ስም የወሰደ ዘመኑ ጨምቆ ባወጣቸው ወጣቶች የተመሠረተ በመሆኑ እስከ አሁን በቅርብ ጊዜ በጥናት የተሠሩ ሥራዎች አስደሳች መሆናቸውን እንደተገነዘብነው ሁሉ የወ ደፊት ፕላኖች ድካምን ሳያስከትሉ በበለጠ እንዲራ መዱ ተስፋ የሚጣልባቸው ናቸው ፤ ሃይማኖት ፤ ተስፋ ፤ ፍቅር ፤ እነዚህ ሦስቱ የማኅበራዊ ኑሮ መሠረት ናቸው ። ስለዚህ የሃይማኖተ አበው ማኅ በር ሃይማኖትን ተደግፎ በፍቅር በመራመድ ከሚ ጨበጠው ተስፋ ለማድረስ ሌት ተቀን ይጥራል ።

## ፪ኛ| የተምሮ ማስተማር ማኅበር

የአሁኑን ስም ሳይወስድ ይህ ማኅበር በ፲፱፻ ፴፱ ዓ/ ም/ በተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ በጥቂቶች ተማሪዎች ተጀመረ ። በዚያን ጊዜ ማኅበሩ መንፈሳዊ እንደመሆኑ መጠን ተማ ሪዎቹ መጽሐፍ ቅዱስን እንዲያጠኑና የተጣሉትን በማስታረቅ በመካከላቸው ሰላም ሰፍኖ እንዲኖር ይጥር ስለነበር ማኅበሩና ተማሪዎቹ አብረው ጐን ለጐን ያድጉ ጀመር ። ስለዚህ በ፲፱፻፵፱ ዓ. ም. በሚያዝያ ወር በተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ተማሪዎችና በግርማዊት እቴጌ መነን ት/ቤት ተማሪዎች በጥንቱም የማኅበሩ መሥራቾች ኅብ ረት በምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስ ቲያን ግቢ «ተምሮ ማስተማር» የሚለውን የአሁ ኑን ስያሜ በመውሰድ አባቴ ሐና ጅማን አባት አድርጎ ሥራውን ቀጠለ ። የበላይ ጠባቂም ልዑል አልጋ ወራሽ እንዲሆኑለት መረጠ ።

### ፩ኛ/ የማኅበሩ ዓላማ

ማኅበሩ መጀመሪያ በተፈሪ መኰንን ትምህ ርት ቤት ውስጥ ሳለ ዓላማው መጽሐፍ ቅዱ ስን ለልጆች ማስጠናትና የተጣሉትን ማስታረቅ እንደነበር ይታወሳል ። ዛሬም ቤተ ክርስቲያንን በበለጠ ለመደገፍ የተነሣ ስለሆነ ደንቡን አሻ ሽሎ ለምእመናን በማበርከት ከዚህ የሚከተሉትን ሠርቶ በማሳየት ዓላማውን ይገልጻል ።

ሀ/ መሠረታዊ የሆነውን የተዋሕዶ ሃይማ ኖት እምነትንና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክር ስቲያንንም ሥርዓት ማስተማር ።

ለ/ ድሆችን መርዳት ፤

ሐ/ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የሚሆኑ ትን ማሠልጠን ነው ። ይህ ማኅበር የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት የያዘውን ሁሉ በአባልነት የሚቀበል ሲሆን ደረጃቸው በሁለት ቀዋሚ ማኅበርተኞች አሉት ፤ እነርሱም ሙሉ አባል እጩአባል በመባል የታወቁ ናቸው ። በሙሉ አባል ማኅበሩን የሚያገለግሉ በሥራቸውና በመልካም ምሳሌነታቸው ተከታዩን ትውልድ ማስተማር እንዲችሉ በሕግ በሥጋው በደሙ የተወሰኑ ናቸው ። ዛሬ በማኅበሩ ሥራ በየክፍሉ ተመድ በው የሚያገለግሉ በሙሉ ይህን ዓላማ የፈጸሙ ናቸው ። ስለዚህ ተምሮ ማስተማር የሚያስተም ረው የቃል ትምህርትን ብቻ ሳይሆን መልካም አርአያ የሚሆነውን ሰው በመፍጠር ነው ። ሲያ ቅተው ይቀራል እንጅ ኑሮው እንዲቃናለት የማይ ወድ ሰው የለም ፤ ስለዚህ ይህ ማኅበር በቤተ ሰብ መካከል ጸጥታንና ሰላምን በመመሥረት የብዙ ዎችን ወጣቶች ቤት ሊያንፅ የሚችል ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

በሁለተኛው በኩል እጩ አባል ተብለው
የሚጠሩት በሥጋው በደሙ ያልተወሰኑ ሰዎች
ሲሆኑ ለሥጋው ለደሙ የሚያበቃ የማጥኛ ጊዜና
ለዚሁ አስፈላጊ ትምህርት የሚሰጣቸው ናቸው ።
«ካልተማሩ አያውቁ ካላወቁ አይጸድቁ» የሚለው
አነጋገር በሁሉ ዘንድ የተለመደ ነው ። ሥጋዬን
ያልበላ ደሜን ያልጠጣ የዘለዓለም ሕይወት የለ
ውም የሚል አምላካዊ አዋጅ እንዳለ ለሰው ሁሉ
ሥውር ምሥጢር ባይሆንም አልበቃሁም በሚል
ምክንያት ይጠግነዋል ። ስለዚህ የተምሮ ማስተ
ማር ማኅበር የዚህ ዓይነት ሰዎች የሚገባቸውን
ትምህርት እንዲያውቁ ያስተምራል ተምረው
ካወቁ በኋላም እንዲጸድቁ ይጥራል ። የአበል
አቀባበሉን ሊስት በሁለት የከፈለውም ስለ
ዚህ ነው ። በመነሻው ማኅበሩ የተቋቋመው ክር
ስቲያናዊውን ተግባር ሁሉ ሠርቶ ሥሩ ለማ
ለት ስለሆነ የማኅበሩ አባሎች በመከፋፈል ግዳጃ
ቸውን ለመፈጸም የሚያስችሉዋቸውና የማኅበሩ
ንም ሥራ ለማቃናት ይችላሉ በሚል እምነት የተ
ጠኑ ጉዳዮችን ከሥራ የሚያውሉ ብዙ ልዩ ልዩ
ኮሚቴዎች አሉት ። እነርሱም ፤

ሀ/ የሥራ አስኪያጅ ኰሚቴ ፤

ለ/ የትምህርት ኰሚቴ

ሐ/ የድርሰት ኮሚቴ ፤

መ/ የመዝሙርና የቴያትር ኮሚቴ ፤

ሠ/ የሕፃናት ፕሮግራም

ረ/ የበጎ አድራጎት ኮሚቴዎች ናቸው።ይህም
የኮሚቴ አመራረጥ ሁሉም ያለበትን ኃላፊነት
አስቦ ለመሥራት የሚያነቃቃው ስለሆነ የማኅበ
ሩን የሥራ እርምጃ በፍጥነት ሊያቃናው ችሏል ።

ከዚህም በላይ የየአንዳንዱን የሥራ ክፍል
ችግር ሊያጠና የሚችል ከየኮሚቴው ተወጣጥቶ
የተመረጠ ንዑስ ኮሚቴ ስላለ ባስቸኳይ ሊሠሩ
የሚገቡትን ጉዳዮች እያጠና ለዐቢይ ኮሚቴ በማ
ቅረብ ሥራውን ያስፈጽማል ። ይህም ከሐዋርያት
ሥራ የተወሰደ ሐዋርያዊ ተግባር ነው ። ሐዋርያት
ለስብከተ ወንጌል ሲፋጠኑ ያላመኑትንም በክርስ
ቶስ ሲያሳምኑ በመልካም የተመሠከረላቸውንመን
ፈስ ቅዱስና ጥበብም የመላባቸውን ከሕዝብ ወገን
ተመርጠው የቀረቡትን ሰባት ሰዎች በመሾማ
ቸው የቤተ ክርስቲያን ዓላማ እስከ መጨረሻ የተ
ቃና ሆኗል ።

የተምሮ ማስተማር ማኅበር የሚፈጽማቸው
ለቤተ ክርስቲያንና ለወጣቶች ጠቃሚ ሥራዎች
እጅግ ብዙ ናቸው ። ወጣቶች ተዋሕዶ ሃይማኖታ
ቸውንና የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት የቤተ ክር
ስቲያናቸውንም ሥርዓት ጠንቅቀው እንዲያውቁ ፤
ዓላማው ስለሆነ በየሳምንቱ እሑድ አራት
ሰዓት ተኩል በምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም
ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባሉት የራሱ መምህራን
ላይ ምርጥ መምህራንን ከየክፍሉ እየጋበዘ ጠቃሚ
ትምህርትን ይሰጣል ። ዛሬ በቤተሰብ ያለውንም
ችግር ተመልክቶ ፕሮብሌሙን ሊያቃልለው የሚ
ችለው ሕፃናት በዕድሜያቸው መጠን ተስማሚ
ውን ትምህርት ሲማሩ እንደሆነ በመገንዘብ በቅ
ድሚያ ለዚህ የሚያገለግል ፷፯ሺ (ሀያ ስድስት
ሺህ የኢት/ብር) የፈጀ ስምንት ክፍል ያለውን
አንድ ትልቅ አዳራሽ በምስካየ ኅዙናን መድኃኔ
ዓለም ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ውስጥ አሠራ።ሕፃ
ናት ወደቤተ ክርስቲያን የሚመጡት የጌታችን
የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስሥጋና
ክቡር ደሙን ለመቀበል ሲሆን ፤ ምንም ሕፃናት
መንፈሳቸው ከክፋት ከቂም በቀልና ከማናቸውም
ዓይነት ሥጋዊ ፍትወት የራቁ ቢሆንም የሚቀበ
ሉት ሥጋው ወደሙ ምን ያህል ጥቅም እንዳለ
ውና የሚያመጣውንም ጉዳት ስለማያውቁ ይህን
ገልጾ ማስተማር አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል ። ስለ
ዚህ ማይክሮፎኑን ከቤተ ክርስቲያኑ ጋር በማያ
ያዝ በአዳራሹ ውስጥ ሥርዓተ ጸሎቱንና ለዚህም
ጠቃሚዎች የሆኑትን ትምህርቶች በመስጠት በየ
ሳምንቱ እሑድ ፈሪሃ እግዚአብሔርን በሕፃናት
ልቡና ሲስል ያረፍዳል ።

የሕፃናት አእምሮም የተፈለገውን ቀለም ቢሰ
ጡት ሁሉን እንደሚቀበል እንደአዲስ ልብስ ስለ
ሆነ ሥርዓተ ጸሎትንና ብዙ ተፈላጊ ትምህርቶ
ችን የቀሰሙ ሕፃናት ብዙዎች ስለሆኑ ፤ ሕፃናቱ
ያገኙትን ጥቅም ወላጆች ሊመሰክሩ ይችላሉ ።
በዚህ ዓይነት ያደጉትም ሕፃናት እስከ መጨረሻ
ድረስ የቤተ ክርስቲያን ዐፀድ ሆነው ይኖራሉ
ተብለው ተስፋ የተጣለባቸው ናቸው ።



www.ethiopianorthodox.org

በየዓመቱ በዚህ ማኅበር አማካይነት እየተማሩ የሚያድጉ ሕፃናት ከዓመት ወደዓመት እየጨመሩ በመሔዳቸው በዚህ ዓመት የሚማሩት ብቻ ፪፻፶ (ሁለት መቶ አምሳ) እንደሆኑ ለማወቅ ተችሏል ።

በዚህ ዓይነት በጥሩ ሁኔታ የሚያድጉ ሕፃናት እነዚህ ብቻ አይደሉም ። በክረምት ወራት ተማሪ ቤት ሲዘጋ ሕፃናት በበጋ ወራት የተማሩትን እንዳያጠፉ ከመማርም እንዳይሰንፉ አርቆ በማሰብ በተለመደው አዳራሽ ኮርስ ከፍቶ የሃይማኖትና የመጽሐፍ ቅዱስ የቅዳሴ የሥስቱን ሥርዓተ ትምህርት እያስተማረ ሕፃናትን የሚያሳድግ ከመሆኑም በላይ ልጆች በተጨማሪ እንግሊዝኛ አማርኛና ሒሳብ እንዲያጠኑ ማኅበሩ መምህራንን አዘጋጅቶ ለሀገር ከፍ ያለ ርዳታውን ያበረክልታ ። ምክንያቱም ልጆች በክረምት ወራት በሥራ ፈትነት በሚሳተፏቸው መጥፎ ነገሮች የወደፊት የኅብረተ ሰባችን ጠንቅ እንዳይሆኑ በማሰብ ነው። ለትምህርቱ ተካፋዮች የሚሆኑ የልጆቹ ዕድሜ ከ፯—፲፯ ዓመት ድረስ የተወሰነ ሲሆን ፤ በ፲፱፻፹፯ ዓ. ም. ባደረገው የትምህርት ፕሮግራም መሠረት ኮርሱ ከሐምሌ ፩—ጳጉሜን ፫ ቀን ድረስ በሚገባ የሕፃናትን አንጐል በትምህርት ሲያጐለምስ ከከረመ በኋላ ፤ በመጨረሻ ወላጆቹን ጠርቶ የምስክር ወረቀት ከሽልማት ጋር በመስጠት ፤ የማኅበሩና የልጆቹ የሥራ ፍሬ አንድ ላይ ይገለጻል ።

ከማኅበሩ ዓላማዎች አንዱ መምህራን የሚሆኑትንና ሰባክያንን ማሠልጠን ነው ። ስለዚህ በክረምት ወራት የሚሠራው ሕፃናቱን ብቻ ለማስተማር አይደለም ። በአእምሮ ለጐለመሱ ለቤተ ክርስቲያን አጥብቀው ለሚያስቡ ለማኅበሩ አባሎችም ከፍ ያለ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ፤ የሃይማኖትና የግዕዝ ትምህርት ስለሚሰጥ ከዚህ ማኅበር የሚያድጉት ወጣቶች ለማኅበሩ ጌጥ ፤ ፈርጥ ሆነው ይገኛሉ ። ማኅበሩም ከከርሞ ወዲያ አድገው መሪና ደጋፊ የሚሆኑትን ሕፃናትና ወጣቶችን የሚከባከበውን ያህል ሽማግሌዎችንም በትምህርት ይረዳል ። በወር አንድ ጊዜ ቅዳሜ ማታ በልጆቻቸው አማካይነት ወላጆችን ጠርቶ የማኅበራዊ ኑሮ ውድቀት የሚያመለክተውን ችግር በመግለጽ ጠቃሚዎች ትምህርቶችን ያበረክታል ። ስሙንም የቤተሰብ ስብሰባ ብሎ የሰየመው ስለሆነ ፤ በዚህ ላይ የሚሰጠው ትምህርት የቤተሰብ ኃላፊነት ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነና የሚሰጠውንም ጥቅም የሚገልጽ ሲሆን ፤ በሌላ በኩልም የቤተሰብ ኑሮ ቢቃወስ የሚያስከትለውን አደጋ ያለፈውንና የሚመጣውን አሁንም ያለበትን ሁኔታ በማብራራት በማስተማሩ ማኅበሩ ሊመሰገን ይገባዋል ። ስለዚህ ማኅበሩ ስለኅብረተ ሰብ ሁኔታ ሊቃና የሚችልበትን መንገድ የሚገልጹ ፊልሞችን ከትምህርቱ ጋራ ስለሚያሳይ ወላጆች በዓይናቸው በማየት ፤ በጆሮአቸው በመስማት ያላቸውን ኃላፊነት ለመገንዘብ ችለዋል ።

በአሁኑ ጊዜ የወጣቱ ከባድ ችግር ለሀገሪቱ ለምታደርገው ፈጣን የሥልጣኔ ግሥጋሴ እንቅፋትን ይፈጥራል ተብሎ በብዙ አስተዋዮች ሰዎች የፍርሀትን መንፈስ ሲያስብባቸው መታየቱ የሚካድ አይደለም ። ይህ ሊሆን የቻለው በቤተ ክርስቲያን ቸልተኝነት እንደሆነ ጥልቅ አስተያየት የተወሰደበት ቢሆንም ፤ በተጨማሪ በየጊዜው ትችት የሚሰጠው ወጣቶች ጊዜያቸውን የሚያሳልፉበት ስሜታቸውን የሚያረኩበት መጫዋቻ ቦታ ባለመኖሩ እንደሆነም ነው ። ይህን በመገንዘብ መንፈሳዊ ሕሊናቸውን የሚማርክ መንፈሳዊ ትምህርት የሚሰጠውን ያህል የሰውነት ማዝናኛ የአእምሮ ማደሻ የሚሆኑ መጫወቻዎችን ያዘጋጀላቸው በመሆኑ የሰውን ሕሊና የሚያሳርፉ ብዙ ጠቃሚ ነገሮች ፤ ይሠራል ።

ይሁን እንጂ የሰው ሕሊና ሊያርፍ የሚችለው ሞግዚት አሳዳጊ አበባ አሳይታ ግምጃውን እንባይ አሳይታ ወርቁን በመቀበል ልጆችን እንድታታልል በመጫወቻ ብቻ አለመሆኑንም ተገንዝቦ ቤተ መጻሕፍት በመክፈት የወጣቶችን አእምሮ ለማጐልመስ ይጥራል ። ለጊዜውም ከ፪፻፵ በላይ መንፈሳዊንና የኑሮ ጥቅምን አብራርተው የሚገልጹ መጻሕፍት አሉት ።

የተምሮ ማስተማር ማኅበር ለሕዝብ የሚሰጠው አገልግሎት በዚህ ብቻ ተወስኖ የቀረ አይ



www.ethiopianorthodox.org

ደለም ። ከ፲፱፻፶፪ ዓ. ም. ጀምሮ የሌቱን ቁር የመዓልቱን ሐሩር ታግሦ በጃንሆይ ሜዳ ከጥር ፲ ቀን እስከ ፲፪ ቀን ድረስ በየዓመቱ ከመንፈሳዊ ኮሌጅ የወንጌል መልእክተኞች ማኅበር ጋር በመተ ባበር በዚያ ለተሰበሰበው ሕዝብ ጠቃሚ ትምህርት ይሰጣል ። ይህም በጀሮ የምትሰሙትን በሰገነት ስበኩ የሚለውን የክርስቶስን ትእዛዝ የተከተለ ነው ።

## ከሌሎች ማኅበሮች ጋር ያለው ግንኙነት

በአሁኑ ጊዜ መለያየት እንዲጠፋ ማኅበር እንዲሰፋ ዓለም በሙሉ ያሰበበት በመሆኑ ተኝቶም ትነሥቶም በሚያየው ራእይ በሚያልመው ሕልም የሰላምን ፍለጋ ለመከተል ነው ። ለዚህም መድኃኒቱ ተገናኝቶ መጠያየቅ እንደሆነ ታምኖበታል ። አንድነት በመገናኘት እንዲሁም በመጻጻፍ ጸንቶ ይኖራል ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የታወቀ የወንጌል ሰባኪ እንደነበረ ዛሬም ያን ጊዜ በነበሩት መምህራን ጥልቅ አስተያየት ይሰጠዋል ፤ ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያን የምትደገፍበት መናፍቃን የሚያፍሩበት ትምህርት በደብዳቤ መልክ እየጻፈ በየአገሩ ያስተላልፋቸው የነበሩት አሥራ አራት መልእክታት ናቸው ። በጽሑፍ ያሠፈራቸው ኃይለ ቃሎች የመናፍቃንን ጥርጣሬ ቀጥቅጠው የሚያጠፉ በመሆናቸው ለጳውሎስ መዶሻ የሚለውን ስም አትርፈውለታል ። የተምሮ ማስተማርም የቅዱስ ጳውሎስን ዓላማ የተከተለ በመሆኑ አሉ ከሚባሉት መንፈሳውያን ማኅበሮች ጋር ጐን ለጐን ተሰልፎ በማስተማሩ ስመ ጥሩነትን የወሰደ ከመሆኑም በላይ ፤ የመገናኛ ካርድ አበጅቶ ምርጥ ቃላትን በማሥፈር በየጊዜው ከማኅበሮች ጋር ይገናኛል ።

ከኢትዮጵያ ሐዋርያዊ ድርጅትም በጣም የቀረበ ግንኙነት ያለው በመሆኑ የመምህራን እጦት ፈጽሞ ገጥሞት አያውቅም ። የሐዋርያዊ ድርጅት ደራስያን (ሰባክያን) የተምሮ ማስተማር ማኅበር አስተማሪዎች ናቸው ።

## ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያለው ግንኙነት

ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያለው ግንኙነት ነፍስና ሥጋ ፤ አጥንትና ጅማት ሆኖ የሰውን ሕይወት የሚያንቀሳቅስ ነው ። መጀመሪያ ወጣቶች ቤተ ክርስቲያን እናታችን እግዚአብሔር አባታችን ብለው እንዲያምኑ ለወጣቶች ሰፋ ያለ ፕሮግራም ከፍቶላቸዋል ። ከቤተ ክርስቲያን የሚገኘው ርዳታም ገና ወጣቶችን በሙሉ ሊያረካ ባይችልም እጇዋን ከመዘርጋት የተቈጠበችበት ጊዜ አይገኝም ። በተለይም የተምሮ ማስተማር ማኅበር የተቋቋመው በምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ስለሆነ ፤ ከገዳሙ መሬት በአስተዳዳሪው አማካይነት ለቤት መሥሪያ የሚሆን ቦታ የተሰጠ ስለሆነ ፤ ገዳሙ ለማኅበሩ ይሠራል ። ይልቁንም ማኅበሩ የገዳሙ መነኰሳት ከዘመኑ ሥልጣኔ ጋር አብረው እንዲራመዱ ፈቃዱ በመሆኑ በምስካየ ኅዙናን ቤተ ክርስቲያን የሚያገለግሉ መነኰሳት የዘመኑን ትምህርት እንዲማሩበት መብራቱን ራሱ ችሎ ያሠራውን አዳራሽ ለመማሪያ በነፃ ፈቅዶላቸዋል ። ቤተ ክርስቲያኑና ማኅበሩ ተደጋግፈው የሚሠሩት መንፈሳዊ ሥራ እየጠነከረ ሔዷል ። በማኅበሩ ሕንፃ ውስጥ የሚካሔደው የዲያቆናትና የመነኮሳቱ የትምህርት ፕሮግራም ከሰኞ እስከ ዓርብ ድረስ በየዕለቱ ከምሽቱ ከ፩ ሰዓት እስከ ፪ ሰዓት ባለው ጊዜ ሲሆን ፵፪ ተማሪዎች ተግተው ነቅተው ይማራሉ ።

ምንም እንኳ በየሳምንቱ እሑድ በሙዳየ ምጽዋት ከምእመናን የሚገኘው ገቢ በጣም ያነሰ ቢሆንም ፤ ቤተ ክርስቲያን በበኩሏ ማኅበሩ የሚደረጅበትን መንገድ በመፍጠር ስጦታዋን ለግሣለች ። ማኅበሩ በቤተ ክርስቲያን የሚደገፈውን ያህል ከግርማዊ ጃንሆይ ፤ ከንጉሣውያን ቤተሰቦች፤ እንዲሁም ከሌሎች በጎ አድራጊዎች ለሕንፃው ማሠሪያ ከዚህ የሚከተለውን ሰፊ ርዳታ አግኝቷል ።



www.ethiopianorthodox.org

፩ኛ/ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ በየጊዜው በሙዳየ ምጽዋት መልክ ከሚሰጡት ርዳታ ሌላ፪ሺህ ብር ፤

፪ኛ/ ልዑል አልጋ ወራሽ ፩ሺህ ብር ፤

፫ኛ/ ልዕልት ተናኘ ወርቅ ፩ሺህ ብር ፤

፬ኛ/ ብፁዕ አቡነ ሉቃስ ፩፻ ብር ፤

፭ኛ/ ሊቀ ሥ/ሀብት ማርያም ወርቅነህ ፩፻ ብር ፤

፮ኛ/ አቶ አበበ ከበደ ፫፻፶ ብር ፤

፯ኛ/ ክቡር ራስ አንዳርጋቸው መሳይ ለማኅበሩ አዳራሽ የሚያገለግሉ ፪፻ (ሁለት መቶ) ወንበሮችን የሰጡ ስለሆነ ፤ ማኅበሩ ለአገር ያበረከተውን አገልግሎት ያህል ከትሩፋት አበጋዞች ምእመናን ስጦታ አልተነፈገውም ። በየጊዜው ወጣቶች ካለው የሚሰጥ ብፁዕ ነው የሚለውን የሐዋርያውን ቃል ከሥራ ላይ በማዋል ውራጃቸውን እየሰበሰቡ ነዳያንን መርዳት ከጀመሩ ብዙ ዓመታትን ያሳለፉ ቢሆንም በዚሁ ዓመት ከቀይ መስቀል ማኅበር ከፍ ያለ የልብስ ርዳታ ያገኘ በመሆኑ ፬ሺ.፬፻፹፬ የወህኒ ቤት እስረኞች ፤ የዕለት ጉርስ የዓመት ልብስ አጥተው በቀን ሐሩር በሌሊት ቁር ለሚጠበሱ ችግረኞች ድኆች ፩፻፶ ፤ እንደዚሁም በአንዳንድ ድርጅቶች ሥር ለሚገኙ ድኆች ስጦታውን ለማዳል ።

## የአሁኑ ሁኔታ

መሠረቱ ያማረ ሁሉ ፍጻሜው መልካም እንደሚሆን አስተያየት ለመስጠት ቀላል ነው ። የተምሮ ማስተማር ማኅበር ሰው መምረጥ ያውቃል። ስለዚህም የሠራተኛ ችግር ፈጽሞ ገጥሞት አያውቅም ። በዚሁም መሠረት ወጣቶች ወደቤተ ክርስቲያን የማይሔዱበትን ምክንያት የሚሔዱም እንዳሉ ሔደው የተሰማቸውን ማለት የኀዘንም ሆነ የደስታ ስሜት የሚገልጹበትን ጥያቄ አውጣጥቶ በየትምህርት ቤቱ በመላክ ላይ ይገኛል ። ይህም የወጣቶች ችግር ምንም እንኳ በትችት መልክ ፤ የሚቀርበው አስተያየት ግልጽ ቢሆንም የወጣቶችን አሳብ በሙሉ ለመጨበጥ ያስችላል ተብሎ እምነት የተጣለበት ነው ።

ከጥንት ጀምሮ ማኅበሩ የሚካሔደው በተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ተማሪዎች በግርማዊት እቴጌ መነን ት/ቤት ተማሪዎች ቢሆንም ዛሬ ዩኒቨርሲቲው የሚገኘው ባጠገቡ በመሆኑ ኮትኩቶ ካሳደጋቸው የራሱ ተማሪዎች ጋራ ለዩኒቨርስቲው ተማሪዎችና የዕውቀት ደረጃ ተመሳሳይ ትምህርት ስለሚሰጥ ከዓመት ወደዓመት እያደገ የሚሔድ ሆኗል ። ወደፊትም ወጣቶችና ቤተ ክርስቲያንን ለማገናኘት ብዙ እቅዶች ስላሉት በበለጠ ጥቅም ይሰጣል ተብሎ ተስፋ ተጥሎበታል ። ተስፋውም በጊዜው ጊዜ የሚፈጸም ስለሆነ አይቀርም ።

## የወንጌል መልእክተኞችና የእሑድ ት፡ ቤት ማኅበር

ይህ ማኅበር በ፲፱፻፷፪ ዓ/ም/አዲስ አበባ በሚገኘው የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ከተቋቋመ በኋላ ከፍተኛውን ቦታ ይዞ የሚገኝ ማኅበር ነው።በመጀመሪያ ሲቋቋም ሥራውን የሚያካሒዱት ተማሪዎችና ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ወጣቶች ነበሩ።ከ፲፱፻፸፯ ዓ/ም/ ጀምሮ ግን ምንም እንኳ በሥራ ላይ ያሉ የመሥራቾች ድጋፍ ባይለየውም ሥራው ፈጽሞ በተማሪዎች ብቻ የ ሚካሔድ ሆኗል ። ቀደም ብሎ በሥራ የተገለጸ ቢሆንም አሁን በያዝነው አርእስት በመጠራት ስያሜውን የወሰደው ሥራው በተማሪዎች ብቻ መካሔድ ከጀመረበት ጊዜ በኋላ ነው።

## ዓላማው

የዚህ ማኅበር ዋና ዓላማው ፩ኛ ፍጹም መንፈሳዊ በመሆኑ ወጣቶችን ወደ ቤተ ክርስቲያን ለማቅረብና የክርስቲያኖችን ልቡና ፈጽሞ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ለማዋሐድ ፤

፪ኛ/ መንፈሳዊ ትምህርትን የተጠሙ ምእመናንን በትምህርት እንዲረኩ ማድረግ ።

፫ኛ/ ሕፃናትን ከልጅነታቸው ጀምረው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሃይማኖትንና የቤተ ክርስቲያናቸውን ሥነ ሥርዓት ይዘው እንዲያድጉ ማድረግ ፤



www.ethiopianorthodox.org

፬ኛ/ በአንድ ሰንደቅ ዓላማ ሥር የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ሁሉ በተቻለ መጠን በአንድ እምነት ጸንቶ እንዲኖር ማንኛውም ሕዝብ ስለክርስቶስና ቤተ ክርስቲያናችንም የምትሰጠውን ትምህርት እንዲያውቅ ለማድረግ ይህን ሁሉ ለመሥራት የሚበቁ መምህራንን እያሠለጠነ መላክ ነው ። ስለዚህ ማኅበሩ ዓላማውን በመከተል «የወንጌል መልእክተኞች» ተብሎ የተሰየመ ሲሆን እውነተኛውን ኢትዮጵያዊ ባሕልና እምነት በሕፃናት አእምሮ ላይ ተስሎ እንዲኖር በየሳምንቱ እሑድ ወጣቶች መምህራንን በየቤተ ክርስቲያኑ በመላክ የኢትዮጵያን እምነት ለኢትዮጵያውያን ሕፃናት ያስተምራል እስከ አሁን ድረስ ባሳየው አገልግሎት ብዙ በመድከም ላይ የሚገኝ ስለሆነ ስሙን ከግብሩ ጋር አስተባብሮ ተገኝቷል ።

ማኅበሩ ትምህርት የሚሰጠው ቀዳሜና እሑድ እንዲሁም በአንዳንድ የዓመት በዓል ቀኖች ነው የቅዳሜ ትምህርት ከ፱ ሰዓት ጀምሮ በመንፈሳዊ ኮሌጅ በሚገኘው የስብከተ ወንጌል አዳራሽ ሲሆን የትምህርት አሰጣጡም የሰውን ልብ ለመማረክ በሚያስችል መጠን በዘመናዊ አቅድ የተዘጋጀ ነው ። የትምህርቱ አሰጣጥ ከዚህ እንደሚከተለው ነው ፩ኛ/ በውይይት መልክ የመጽሐፍ ቅዱስ፡ ጥናት ።

፪ኛ/ መንፈሳዊ አርእስቶችን እየመረጠ ወጣቶች በየትምህርት ቤታቸውና በጠቅላላ ከሰው ጋር ሊኖራቸው ስለሚገባ መንፈሳዊ መግባባት በክርክር መልክ እያቀረበ ወጣቶችን ያስምተራል ። ይህም በቤተ ክርስቲያን በኩል ያለውን የሥራ አለመከናወንና ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን ላይ ያላቸውን የቸልተኝነት መንፈስ ያቃናው ይሆናል ተብሎ ተስፋ የሚጣልበት ነው ።

፫ኛ/ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በይበልጥ ሰው ሁሉ ሊያውቃቸው የሚገቡትን ነገሮች በጥያቄና መልስ በማስተማሩ የዚህ ዓይነት ፕሮግራም የአድማጩን መንፈስ በጣም አድርጎ ማርኮታል ። ስለዚህ ይህ ማኅበር የሚሰጠውን ጥቅም በመመልከት በጽሑፍም ሆነ በቃል ከአድማጩ ሕዝብ ብዙ አስተያየት ይሰጣል ።

## ከሌሎች ማኅበሮች ጋር ያለው ግንኙነት

ማኅበሩ የተመሠረተበት ቦታ ለመንፈሳዊ ዓላማ ጥሩ ምንጭ በመሆኑ ለሌሎች ማኅበሮች አርአያ መሆንም የሚገባው ስለሆነ በአዲስ አበባም ሆነ በየጠቅላይ ግዛቱ በሚገኙትም ት/ቤቶች ለተቋቋሙት ማኅበሮች ሁሉ የሥዕልና የትንንሽ መጻሕፍትን ስጦታ ያላበረከተበት ጊዜ አይገኝም ። ሰማሁ ብሎ ከመናገር አየሁ ብሎ መመስከር ጉዳዩን የታመነ ማድረጉ ግልጽ ነው ፤ በቃል ከማስተማር በሥዕል በምሳሌ ማስተማር የሰውን ሕሊና በበለጠ ከተወሰነ የእምነት ግብ ማድረስ የሚችል መሆኑን የተገነዘበ ይህ ማኅበር በየሳምንቱ እሑድ በአዲስ አበባ በሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ወጣቶችን ሥዕል አሲዞ በመላኩ ከወጣቶችም ሆነ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያለው ግንኙነት ከፍ ብሎ የሚታይ ነው ።

ከዚህም ሌላ በየዓመቱ ከጥምቀት ዋዜማ (ከተራ) ጀምሮ እስከ ቃና ዘገሊላ በጃንሆይ ሜዳ በሚደረገው መንፈሳዊ በዓል ከተምሮ ማስተማር ጋር ተባብሮ በመሥራት አገልግሎቱን ለሕዝብ መስጠት ከጀመረበት አንሥቶ ሁለቱ ማኅበሮች ዓላማውን ለቆ ወደ ብልግና ሊለወጥ የነበረውን መንፈሳዊ በዓል መልሰው ወደ ቦታው እንደአገቡት በቦታው እየተገኙ በዓሉን የሚያከብሩ ሰዎች ምስክሮች ናቸው ፤ ከዚህ በላይ ከተገለጸው ማኅበርና በየሳምንቱ እሑድ በየቤተ ክርስቲያኑ በሚሰጠው አገልግሎት ሳይወሰን ከሌሎች ጠቅላይ ግዛቶች መንፈሳዊ ማኅበሮች ጋር ግንኙነት በማድረግ በመላ ኢትዮጵያ ትምህርትን ሲሰጥ ይገኛል።

## ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያለው ግንኙነት

የወንጌል መልእክተኞችን ማኅበር የወለደ ቅድስት ሥላሴ ትምህርት ቤት) ወይም መንፈሳዊ ኮሌጅ የቀሳውስትና የዲያቆናት ማሠልጠኛ ወደፊትም የሊቃውንት መገኛ ይሆናል ተብሎ እምነት የተጣለት ስለሆነ ፤ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቀኝ እጇዋ ነው ። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረውን ትምህርት በመደገፍ በየሆስፒታሉ በየቤተ ክርስቲያኑ ወጥተው



www.ethiopianorthodox.org

ወርደው በማስተማር ወጣቶቹ የቤተ ክርስቲያን እጅ እግር እንደመሆናቸው መጠን ማኅበሩ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያለው ግንኙነት እጅግ የጠበቀ ነው ።

ከዚህም በላይ ማኅበሩን የሚመሩት ወጣቶች የዛሬ ዲያቆናት የነገ ቀሳውስት በመሆናቸው የወንጌል መልእክተኞች ማኅበር ቤተ ክርስቲያንን በሙሉ ኃይሉ የሚደግፍ ሲሆን ወጣቶች ከቤተ ክርስቲያን እንዳይርቁ የሚያነቃቃና የሚያተጋ ማኅበራዊ ኑሮ እንዲደረጅ እጅግ የሚጥር በመሆኑ ራሱ ቤተ ክርስቲያን ነው ።

### የአሁኑ ሁኔታው

የወንጌል መልእክተኞችና የእሑድ ትምህርት ቤት ማኅበር ከአሁን በፊት ሠርቶ ባሳየው ጠቃሚ ሥራ ሁሉ ጥሩ ውጤትን ያስገኘ በመሆኑ ሐዋርያነቱ የተመሰከረለት ሲሆን ዛሬም በመንፈሳዊ በኩል የወጣቱ መንፈስ እያደረ እየቀዘቀዘ እንዳይሔድ በሚገባው በሚረዳው ለማስተማር አዲስ ፕላን በማዘጋጀት ይገኛል «እሾህ በእሾህ ይነቀላል ፤ ነገርም በነገር ይመለሳል» የዘመኑ ወጣቶችም በዘመኑ መንፈሳውያን ወጣቶች ከተቀደሰ ዓላማ ይደርሳሉ ተብሎ ተስፋ የሚደረገው ይህና ይህን የመሳሰሉ ማኅበሮች በርትተው ሲሠሩ ነው ።

## ፬ኛ| ማኅበረ ሐዋርት ፍሬ ሃይማኖት

ይህ ማኅበር በኤርትራ ጠቅላይ ግዛት በአሥመራ ከተማ በ፲፱፻፵፪ ዓ ም ተቋቋመ ። በብርሃናተ ዓለም ሐዋርያት ስም መሰየሙም በእውነት ሐዋርያትን ተከትሎ በሚሠራው ሥራ ፍሬ ሃይማኖትን ለምእመናን እንዲያበረክት ታጥቆ የተነሣ በመሆኑ ነው ።

### ዓላማው

፩ኛ/ ዋና ዓላማው ሀ/ ከነበረው እንዳይናወጥ ሥርዓቱ እንዳይለወጥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስን እምነት ለማጽናት ሃይማኖት እንዲስፋፉ ፤ ባህል እንዳይጠፉ ቤተ ክርስቲያንን በትምህርት ለመደገፍ ነው ።

ለ/ ካህናትን በሐዋርያነት እያሠለጠነ አምልኮተ እግዚአብሐር ወደሌለበት ትምህርት ወዳልተዳረሰበት ይልካል ።

፪ኛ/ ማኅበራዊ ኑሮ የሚደረጅባቸውንም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ለመሥራት ተቋቁሟል

ሀ/ የሕፃናት ማሳደጊያ ፤

ለ/ የሽማግሌዎች መጦሪያ ፤

ሐ/ የበሽተኞች መታከሚያ ድርጅትን አስፈላጊ በሆነው ሁሉ መሥራት ክርስቲያናዊ ቅዱስ ተግባር ስለሆነ ፤ ማኅበረ ሐዋርያት ሠርቶ በማሳየት ወደፊትም ሠርቶ ለማሳየት ታጥቆ የተነሣ ነው ።

ለማናቸውም ሥራ ኃይሉ የገንዘብና የዕውቀት ምንጭ ነው ። ስለዚህ ለጊዜው ገንዘብ ለማግኘትም ሆነ የሰውን ልጅ ዕውቀት ለማዳበር ማተሚያ ቤትን አቋቁሞ መጻሕፍትን በማሳተም ገንዘብ ማግኘት መቻሉን ስለተገነዘበ ኮከበ ጽባሕ የተባለ ማተሚያ ቤትን አቋቁሞ ፤

ሀ/ ጥንታውያን መጻሕፍትን እንደ ቀድሞ ሁኔታቸው ፤

ለ/ ግዕዙን ወደ አማርኛ አማርኛውን ወደግዕዝና ወደ ልዩ ልዩ ቋንቋ በማስተርጐም ፤

ሐ/ ለሕዝብ አገልግሎት የሚጠቅሙ ልዩ ልዩ የሃይማኖት የጸሎት መጻሕፍትን ፤

መ/ ጋዜጦችን እያዘጋጀ በማቅረብ ከፍ ያለውን አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል ።

ከዓላማው ከፍተኛው ተግባር የአበውን እምነት ለተከታዩ ትውልድ ማወራረስ ስለሆነ ማኅበሩ ከተቋቋመ ከ፲፱፻፵፪ ዓ ም ጀምሮ እስከ ፶፰ ዓ ም ድረስ በየቦታው ያቋቋማቸው የተመላላሽና የአዳሪ ትምህርት ቤቶች ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ናቸው ።

፩ኛ/ በአሥመራ ከተማ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ።

፩/ ማኅደረ ብርሃን ትምህርት ቤት ፲፯ ክፍል ያለው ነው ።

፪/ መርሐ ሕፃናት ፯ ክፍል ያለው ነው ።

፫/ ደብረ ደናግል ፫ ክፍል ያለው ነው ።

የደብረ ደናግል የአዳሪዎች መኝታ ቤት ፲፪



www.ethiopianorthodox.org

፬/ ቀራንዮ ት/ቤት ፬ ክፍል ያለው ነው ።

፭/ ደብረ ቤቴል ፮ ክፍል ያለው ነው ።

፲፪ኛ/ በሠራዬ አውራጃ መንደፈራ ።

፩/ ናዝሬት ት/ቤት ፯ ክፍል ያለው ነው ።

፪/ አዲኳላ ፫ ክፍል ያለው ነው ።

፲፫ኛ/ በደቀ መሐሪ (አካለ ጉዛይ) ።

፩/ ፈለገ ሰላም ት/ቤት ፮ ክፍል ያለው ነው ።

፪/ የመምህራን ማሠልጠኛ ት/ቤት ፬ ክፍል ያለው ነው ።

፲፬ኛ/ በከረን አውራጃ ።

፩/ ሰመርናሃ ት/ቤት ፪ ክፍል ያለው ነው ።

፲፭ኛ/ በኤርትራ ምዕራብ በኩናማ ወረዳ ልዩ ስሙ በሽቃ

፩/ የንጉሥ ባዜን ት/ቤት ፫ ክፍል ያለው ነው።

፪/ ገሊላዊት ቅድስት ማርያም ፲፬ ክፍልያለው ነው ።

ከዚህ በላይ እንደገለጽነው በኤርትራ ጠቅ ላይ ግዛት ብቻ በየአውራጃውና በየወረዳው በድ ምሩ ፷፰ ክፍሎችን የያዙ ፲፬ ትምህርት ቤቶችን አሠርቶ ወጣቶችን በመርዳት ላይ ስለ ሚገኝ ፤ በሃ ይማኖትም ሆነ በሌላ ሰብአዊ ተግባር የሚሰጠው ጥቅም ከዚህ በላይ በመሆኑ ግምቱ እጅግ ከፍ ያለ ነው ።

## ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያለው ግንኙነት ።

በየቦታው ትምህርት ቤቶችን አሠርቶ ወጣ ቶችን እንደ ሥጋዊ አባት በወተት በፍትፍት እንደ መምህርነቱም በዕውቀት በሃይማኖት እያሳ ደገ ለቤተ ክርስቲያን የሚያበረክት በመሆኑ የቤተ ክርስቲያን መሠረትና ጉልላት ነው ። ድምቀቱም አሸብርቆ በሩቅ ለሁሉ ይታያል ። ሐዳሪ ያለማኅ ደር አይሆንምና በትምህርት ቤት ያሠለጠናቸው ወጣቶች እየበዙ እንደመሔዳቸው መጠን ባሉት አብያተ ክርስቲያናት ላይ መጨመር አስፈላጊ ሆኖ ስላገኘው ከ፴፪ ዓ ም ጀምሮ እስከ ፶፰ ዓ ም ድረስ በኤርትራ ጠቅላይ ግዛት ውስጥ በየወረዳ ውና በየአውራጃው በዘመናዊ አቅድ ፮ ቤተ ክር ስቲያኖችን አሠርቷል ።

መጽሐፍ እንደሚናገረው የእግዚአብሐር ዓይ ኖች ወደ ወዳጆቹ ናቸው ። ከፈጣሪ የተገኘ ታላቁ ፍጥረት ሰውም ፈጣሪውን የሚመስልበት ብዙ ነገር ስላለው አትኩሮ የሚመለከተው ልዩ ልዩ ስጦታ አለው ። ለግርማዊ ጃንሆይ የተሰጣቸው ስጦታም በዘመናቸው የተጀመረው ሥራ ሁሉተከ ናውኖ ከፍጻሜ ሲደርስ ማየት ስለሆነ ማኅበረ ሐዋርያት በዘመናቸው የጀመረውን በዘመናቸው ሠርቶ ከፍጻሜ በማድረስ ፈጽሞ ደስ ያሰኛቸው በመሆኑ ፭፻ሺ (አምስት መቶ ሺህ የኢት/ብር) ያህል የለገሡለት መሆኑ በማኅበሩ ፕሬዚዴንት አማካይነት ለማወቅ ተችሏል ።

ለማስታወስ ያህል እንጂ ማኅበረ ሐዋርያት ሠርቶ ያሳየው የሥራ ውጤት በሙሉ ቢጻፍ ብዙ ዓምዶችን የሚይዝ ስለሆነ አልፎ አልፎ ጐልተው የሚታዩትን ብቻ ለማስታወስ ስንል እንጂ በሙሉ ለማተት አልሞከርንም ።

## ፲፮ኛ/ በወጣቱ ትጋት በአዲስ አበባና በየጠቅላይ ግዛቱ የተቋቋሙ ማኅበሮች ።

«በወንዶችም በሴቶችም ባሮቼ ላይ ከመን ፈሴ አፈሳለሁ ። ትንቢትም ይናገራሉ ጐበዛዝቱም ራእይ ያያሉ» አለ እግዚአብሐር ተብሎ በቢነዩ በኢዩኤል የተነገረው ትንቢት ምንም እንኳ በዓለ ጰንጠቆስጤ በሐዋርያት ላይ ተፈጽሞ ቢታ ይም ዓረፍተ ዘመን የማይገታው ረቂቅ ኃይል በመሆኑ ሥጋ ለለበሰው ሁሉ በየጊዜው ከመሰ ጠት ያቋረጠበት ጊዜ የለም ። ስለዚህ በልቡናው ያደረች ኃይል መንፈሳዊት የቃኘችው የዛሬው ትውልድ ለተከታዩ ሕዝብ አባት መሆን እንዳለ በት እየተገነዘበው በመሔዱ በመንፈሳዊም ሆነ በሥጋዊው ለሌላው ትውልድ የሚያወርሰውን ቅርስ ከአባቶቹ መቀበል ግዴታው እንደሆነ ያወ ቀው ይመስላል ። ምክንያቱም ይህ ለምን ቀረ ? ይህስ ለምን እንደዚህ አልሆነም ? ብሎ ከመቆርቆ ሩም በላይ የሥራ ተካፋይ ሲሆን በመታየቱ ነው። በዚህም መሠረት በአንድ በኩል ጉድለት ካለ ሙሉ ውጤት አለመኖሩን አውቆ በመሠልጠን ላይ የምትገኝ አገራችን ኢትዮጵያ የተሟላ ኃይል እንዲኖራት በማለት ከፍ ብለን በተራ ቁጥር ከጻ



www.ethiopianorthodox.org

ፍናቸው ማኅበሮች ሌሎች የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ማኅበሮች በአዲስ አበባና በየጠቅላይ ግዛቶቹ ተቋቁመው እንዲሠሩ በማድረጉ ወጣቱ ኃላፊነትን በመረከብ ላይ ይገኛል ። ኃላፊነትን ዐውቆ መሥራትም ከሁሉ የበለጠ ዕውቀት ነው ።

ስለዚህ በየጠቅላይ ግዛቱ ፣ በየወረዳውና በየአውራጃው ብዙ ስመ ጥሮች ማኅበሮች እንዳሉ ቢታወስም ፣ ለመረጃ ያህል አልፎን አልፎን የጥቂቶችን ማኅበሮችና የተቋቋሙበትን ጠቅላይ ግዛት እንጽፋለን ።

፩/ በአዲስ አበባ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አንቀጸ ብርሃን ፣

፪/ በሸዋ ጠ/ግዛት በናዝሬት ከተማ ኖኅተ ሃይማኖት ፣

፫/ በደብረ ብርሃን የሃ አ ቅርንጫፍ)ሃይማኖተ አበው ፣

፬/ በወሊሶ (የሃ. አ ቅርንጫፍ) ሃይማኖተ አበው፣

፭/ በአሩሲ ጠ/ግዛት አሰላ ከተማ ብርሃነ ወንጌል

፮/ በሐረር ጠ/ግዛት ከሣቴ ብርሃን ፣

፯/ በሲዳሞ ጠ/ግዛት ብርሃነ ሕይወት ፣

፰/ በጂማ ጠ/ግዛት መርሐ ጽድቅ ፣

፱/ በጎንደር (ሃይማኖተ አበው)

፲/ በመቀሌ

፲፩/ በአሥመራ ከተማ ፍኖተ ብርሃን ።

በነዚህና እነዚህን በመሳሰሉ ማኅበሮች ብዙዎች ወጣቶች እየተገኙ መጀመሪያ የሃይማኖትን ጋሻ አንግበው ከተጠመደባቸው የዘመኑ የመንፈስ አሽክላ ራሳቸውን ያዳኑ ከመሆናቸውምበላይ ብዙ ነፍስን ከሲኦል በማውጣት የዘመናችን አእላፍ መላእክት ናቸው ።

ገና ከጉልበት ሳለ መንፈሱ ሳይቀዘቅዝ ሕሊናው ሳይታክት በሚሠራው ሥራ ወጣቱን በብዙ ቦታ የልጅ ሽማግሌ አሰኝቶታል ። ርእሰ አበው ለመባል የአበውን ወግ ታሪክ ማወቅ አስቀድሞ እንደ አብርሃም ምግባርና ሃይማኖትን ገንዘብ ማድግ ያስፈልጋል ። አብርሃም በሃይማኖቱ ከበረ ፣ የብዙዎች ሰዎች አባት ይባል ዘንድ ማመኑም ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት ። እየተባለ ምስክርነቱ በዜጊው ለመረጃ የሚቀርበው በዘመኑ የነበረውን የባዕድ አምልኮና የሞራል ውድቀት ተፈትኖ ካለፈ በኋላ ጥሩ ውጤትን በማምጣት እንደሆነ ሙሉ በሙሉ ያመነበት የዘመናችን ተማሪ ከክፍል ወደ ክፍል ለመዛወር የፈተና ውጤታቸው እንደሚደመር እንደሌሎቹ ትምህርቶች ዋጋ ያለው መስሎ ባይገመት እንኳ የበለጠ የዚህን ዓለም ከባድ ፈተና ለማለፍ ራሱን ከተቀደሰ ቦታ ሲያውል ይታያል ። ከእግዚአብሐር የተሰጠውንም ለማወቅ መንፈሳዊውን ነገር ከመንፈሳውያን መምህራን በመጠየቅ በመራቀቅ ላይ ነው ።

ይህም መንፈሳዊ ዓላማ ከእግዚአብሐር ዘንድ የተሰጠውን ግዴታ ለመወጣት የሚያስችል መንፈሳዊ ኃይል ሲሆን ፣ ሁሉ እንደአንድ ልብ መካሪ እንደአንድ ቃል ተናጋሪ ሆኖ እርስ በርስ ለመተሳሰብና ለቤተ ክርስቲያኑ እንዲያስብ የሚያደርገው የፍቅረ እግዚአብሐርና የፍቅረ ቢጽ ሰንሰለት ነው ።

ታዳጊው የዘመናችን ወጣት በሥጋዊም ሆነ በመንፈሳዊ ዕውቀት ፈጣን ግሥጋሴ ማድረጉ ግን የታሪክ ድኅአደግ ባለመሆኑ ነው ። ሃይማኖት ለኢትዮጵያ ጠቀመ እንጂ አልጎዳም ። የክርስቲያን ደሴት ተብሎ መጠራት ቀላል ታሪክ አይደለም። የአምልኮተ እግዚአብሐርና የሃይማኖተ ኦሪት ታሪክ በንግሥት ማክዳ የሃይማኖተ ወንጌል ታሪክ በነገሥታቱ በአብርሃና ወአጽብሐ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ሳይደፈርስ መኖሩ ነገሥታቱ በአዋጅ ፣ ሴቱ ወንዱ በጠቅላላም ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ ለሃይማኖቱ ቀናተኛ የመጣበትን የጋራ ጠላቱን ለመመለስ ታጥቆ የሚዋጋ ጀግና ስለሆነ ነው ፣ ዛሬም በየትምህርት ቤቶች ማኅበሮች ተቋቁመው ወጣቶች ለሃይማኖት ቀናተኞች ሆነው መታየታቸው በግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ የገንዘብ ርዳታና ሃይማኖት የሌለው ሥልጣኔ መልህቅ እንደሌለው መርከብ ነው ብለው ለሕዝባቸው ባስተላለፉት መሪ ቃል ነው ።

ከአባ መዓዛ ገ/ ሕይወት



www.ethiopianorthodox.org

# ልዩ ካቢኔ

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ የመሪነትን ሥልጣን በእግዚአብሐር ፈቃድ ከያዙ ጀምሮ ጊዜው በፈቀደው በልዩ ልዩ አቅድ ሕዝቡን ለመምራት መልካም ፈቃዳቸው እየሆነ ሕግጋቱን በማሻሻል ጠቅላላ የመንግሥቱ አቅዋም ሳይነካ የሥራውን አቅድ ብቻ በመለዋወጥ ሲሠሩ ብዙ ጊዜያቸው ነው ። በዚሁም መሠረት በ፲፱፻፶፪ ዓ. ም. ታኅሣሥ ፲፪ ቀን በቅርብ ሁነው ልዩ ልዩ ጉዳዮችን እያጠኑ የሚያቀርቡ ሰዎች ተመርጠው በልዩ ካቢኔያቸው ሲሾሙ ፤ ከኢትዮጵያ ታላላቅ ጉዳዮች ውስጥ መንፈሳዊው ተግባር አንደኛ እንደሆነ በማመን በታሪክ ሰንሰለትም ተያይዞ የመጣ የሀገር ፍቱን መድኀኒት የሕዝብም ዕድገት የተገኘበት እንደሆነና አሁንም እንደሚገኝበት በማመን ከ፲፬ ክፍሎች ልዩ ካቢኔያቸው ውስጥ ፩ኛውን ክፍል ለመንፈሳዊ ጉዳይ ፈጻሚ ሰጡ ። ከመምሪያውም ውስጥ ታላቁ አንቀጽ «በሀገራችን ተመሥርቶ የቆየው መንፈሳዊ ተግባር አንዱስ እንኳ ሳይጓደል መሥራትና መቈጣጠር ነው ይላል ።

፲፬ቱ የልዩ ካቢኔ ክፍሎች ፤

፩ኛ/ የፖለቲካና የጠቅላላ ሥራ ክፍል
፪ኛ/ የሕግና የአዋጅ ማደራጃና መጠባበቂያ
፫ኛ/ የኤኮኖሚክና የፊናንስ ክፍል
፬ኛ/ የፕላኒንግና የጥናት »
፭ኛ/ የብሐራዊ እድገት »
፮ኛ/ የከተሞችና የሕንፃዎች ድርጅት »
፯ኛ/ የልዩ ጽሕፈት ቤት »
፰ኛ/ የፕሬስ ክፍል »
፱ኛ/ የፍርድ ጉዳዮች »
፲ኛ/ የፔርሶኔል »
፲፩ኛ/ የመንፈሳዊ ጉዳይ »
፲፪ኛ/ የንጉሣዊ ዜና ማደራጃና የቤተ መጻሕፍት »
፲፫ኛ/ የኤታ ማጀር ጽሕፈት ቤት »
፲፬ኛ/ የመረጃ ክፍል ናቸው ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ለመንፈሳዊው ጉዳይ ከፍ ያለ ግምት ሰጥተው ሲፈጽሙት ይገኛሉ ። በአዲስ አቅድ ሁሉን ለመሥራት አስበው ከሚያወጡት ፕላን ውስጥ መንፈሳዊውን ነገር ሳይረሱ ጐን ለጐን እንዲሐድ ያደርጋሉ ። ለዚህም ክፍል የመጀመሪያ ሠራተኛ ሁነው የተገኙት አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ አሁን ሊቀ ሥልጣናት የተባሉት ናቸው ። እርሳቸውም ይህን ኀላፊነት ከተረከቡ ጀምሮ በንጉሠ ነገሥቱና በቤተ ክህነቱ መካከል ስላለው ግንኙነት በተለይም ንጉሠ ነገሥቱን የሚመለከተውን ጉዳይ እያጠኑ ያቀርባሉ።

ተግባራቸው ፤

፩ኛ/ አዲስ ሊሠራ የሚገባው ነገር ቢኖር አሳብ እያቀረቡ ውሳኔ ያሰጣሉ ።

፪ኛ/ የተሠራውን ደግሞ እየተከታተሉው ጤቱ ምን ያህል እንደሆነ በማብራራት ያቀርባሉ ።

፫ኛ/ አስፈላጊ የሆነውን ትእዛዝ ተቀብለው ያስተላልፋሉ ።

ከዚህም ሌላ ይኸ የመንፈሳዊው ክፍል ካቢኔ የሌሎችንም ሃይማኖቶች ተግባር ስለሚመለከት የሃይማኖት መሪ የሆኑትን እያነጋገረ አስፈላጊ ሁኖ በአገኘው መንገድ እንዲረዱ ማስታወሻ ያቀርባል ። ከውስጥም ከውጭም በየጊዜው የሚቀርቡትን ጥያቄዎች በመንግሥትና በቤተ ክህነት ስም ያብራራል ። ስለዚህም የቤተ ክርስቲያንና የመንግሥት ግንኙነት በበለጠ ለሁሉ ግልጥ ሁኖ ሊታወቅ ተችሏል ።

ይኸም ድርጅት ኀላፊነቱን ለመወጣት ይችል ዘንድ ሥራውን በ፬ ታላላቅ ክፍሎች መድቦ ሲሠራ ይገኛል ። ይኸውም

ሀ/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ክፍል ፤

ለ/ የልዩ ልዩ የክርስቲያን እምነት ክፍል ፤
ሐ/ ከክርስትና ውጭ የሆኑት እምነቶች ክፍል
መ/ የአረማውያን ክፍል ናቸው ።

ከዚህም ላይ መመልከት ያለብን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ስለመንፈሳዊው ጉዳይ ምን ያህል እንዳሰቡበት የምንረዳው ከልዩ ካቢኔያቸው አንዱን ክፍል ለዚህ ደረጃነት በመስጠታቸው ነው ። ዓለም በሥጋዊው ፈቃድ ብቻ እየተመራ ድቀት



www.ethiopianorthodox.org

ሲያገኘው የኛ መሪ ግን በእግዚአብሔር መንፈስ እየተመሩ ሥጋዊውን ከመንፈሳዊው እያስተባበሩ ከዕለት ወደዕለት ዕድገት ለሀገሪቱ በበለጠ ለማ ስገኘት ችለዋል ።

## የወንጌል ድምፅ ራዲዮ

የኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅታችን በልዩ ልዩ አቅድ ከሚሠራቸው ሥራዎች ጋር በተለይ በዚህ የራዲዮ ጣቢያ አማካይነት ለኢትዮጵያው ያንና ለሩቅ ምሥራቅ ሁሉ የግብረ ገብነትና የሃ ይማኖትን ፤ የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ትምህ ርት በየዕለቱ ያስተምራል ።

### ዐላማው

ሀ/ ኢትዮጵያውያን በቀደመው እምነታቸው ጸንተው ለመኖር እንዲችሉ ፤

ለ/ ከክርስቶስ ትምህርት ውጭ ለሆኑ የወን ጌል እምነት በልቡናቸው እንዲቀረጽላቸው ለማ ድረግ ፤

ሐ/ ከኢትዮጵያ ውጭ ለሚኖሩ ተማሪዎችና ሌሎችም ልዩ ልዩ የመንግሥት ሠራተኞች ዕለ ታዊ ትምህርት እንዲደርሳቸው በማለት ነው ።

### መምህራት

መምህራኑም ከሀገር ትምህርት ጋር በዘመ ናዊ ዕውቀት የበሰሉና በጣም ከፍ ያለ ችሎታ ያላቸው ናቸው ። ስለጠቃሚ ትምህርታቸውም ከየጠቅላይ ግዛቶች ልዩ ልዩ አስተያየት በየጊ ዜው ይቀርብላቸዋል ። ለዚህም የራዲዮ ስብከት ክፍል በተለይ ሥራውን የሚያካሔድ ቦርድ አለው ።

አባሎቹም ፤

፩ኛ/ ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወር ቅነህ ሊቀ መንበር ፤

፪ኛ/ አቶ አበበ ከበደ አባል

፫ኛ/ መልአከ ሰላም ሳሙኤል ተረፈ »

፬ኛ/ አቶ መንክር ተድላ የቦርዱ ዋና ጸሐ ፊና የፕሮግራሙ ኀላፊ ናቸው ።

እነርሱም በሙሉ ልብ ስለሚሠሩና እር ዳታቸው ድርጅቱን ስላልተለየው ከፍ ያለ ውጤትን አስገኝተዋል ። አቶ አበበ ከበደ በምክር የለተ ለዩ ሲሆን ፤ ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወር ቅነህና መልአከ ሰላም ሳሙኤል ተረፈ በቦርዱ ውስጥ ከሚሰጡት አገልግሎት ሌላ በራዲዮ በሚ ሰጠው የስብከት ፕሮግራም ያለማቋረጥ ተካፋዮች በመሆናቸው ፤ ለምእመናን የሰጡት ትምህርት እጅግ በጣም ጠቃሚ ሆኗል ። በዚህም ሥራቸው ከድርጅቱ ዘንድ ደመወዝ ተከፍሏቸው ሳይሆን ፤ ቤተ ክርስቲያንን አፍቃሪዎች ፤ የንጉሠ ነገሥታ ቸውን አደራ ጣባቂዎች ከመሆናቸው የተነሣ ብቻ መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው ።

ከዚህ በላይ ስማቸውን ከገለጽነው ጋር አብረው በመሰለፍ ለዚህ ድርጅት ልባዊ አገልግ ሎታቸውን ያለመሰልቸት ያበረከቱና የሚያበረ ክቱ ብዙዎች ስላሉ ፤ ለነሱም ምስጋና ይገባቸዋል ።

አቶ መንክር ተድላ ድርጅቱ ገና ሲቋቋም ፤

፩ኛ/ የድርጅቱ መሣሪያ እስኪሟላ ድረስ ተጨማሪ አገልግሎት እንዲአበረክት በማሰብ የግል ቴፕሪኮርደራቸውን ለድርጅቱ ለ፯ ወራት ያህል በማዋስ ፤

፪ኛ/ የሰባክያኑንና የሥራተኞቹን ደመወዝ በየወሩ እያመጡ በመክፈል ፤


፫ኛ/ የሰርቪስ መኪና እስከ ተገኘበት ድረስ (ከ፪ ዓመታት በላይ) በቴፕ የተቀረጸውን ስብከት ወደ ብሥራተ ወንጌል ራዲዮ ጣቢያ ቴክኒሺያኑን አቶ ዘመድሁን ብዙ ወርቅን ጭምር በግል መኪ ናቸው በማመላለስና ስለሥራው እርምጃ መቃ ናት ከራዲዮው ፕሮግራም ኃላፊዎች ጋር እየተገ ናኙ ሐሳብ ለሐሳብ በመለዋወጥ ሥራውን በሚ ገባ በማካሔድ ፤

፬ኛ/ ስብከት በመስጠት ፤

፭ኛ/ « ድምፀ ተዋሕዶ» ለተባለው ባለ ፲፪ ገጽ የድርጅቱ ጋዜጣ አዘጋጅ ከመሆናቸውም በላይ ለማንኛውም መንፈሳዊ አገልግሎት ፈጥኖ ደራሽ በመሆን ከልብ የመነጨ አገልግሎታቸውን አበር ክተዋል ፤ እንዲሁም በማበርከት ላይ ይገኛሉ ።



www.ethiopianorthodox.org



አቶ መንክር ተድላ በግርማዊ ን. ነ.
ልዩ ካቢኔ የመፈሳዊ ክፍል ዲሬክተር

በተለይ ለዚህ የራዲዮ ስብከት ክፍል የሠራተኞች ደመወዝና የሥራ ማስኬጃ እንዲሆን በግርማዊ ጃንሆይ ተፈቅዶ የተመደበለት የወር ባጀት ፩ሺ፰፻ ብር ሲሆን ፤ በበጎ ፈቃድ ከሚያገለግሉት በቀር በቀለብ የተቀጠሩ ፫ ሰባክያን ፤ ፩ የራዲዮ ቴክኒሺያንና ፩ ታይፒስት ፤ በድምሩ ፭ ሠራተኞች አሉት ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችንም በሙሉ ልብ በሚደግፏት ንጉሠ ነገሥቷና በልጆቿ እጅግ በጣም እየተደሰተች ፤ ጥንታዊት እንደመሆኗ ዘመኑን ተከትላ ትምህርት መስጠቷና ወገኖቿን መጠበቋ ፤ እምነቷን ማጽናቷ የታወቀ ነው ። በዚህም ምክንያት ፤ ማቴሪያሊዝምና አቴይዝም በነገሡበት በዚህ ፳ኛው ክፍለ ዘመን ወጣቱን ትውልድ ዘመኑን ተከትላ ሳይንስ ባፈራው የጥበብ መሣሪያ መጠቀሟ ጥንታዊት ስትሆን ፤ ዘመናዊት አሰኝቶ በጣም አስመስግኗታል ።

ይህም ይታወቅ ዘንድ በኢትዮጵያም ሆነ በወንጌል ድምፅ የራዲዮ ጣቢያዎች ያለማቋረጥ ዘወትር የምትሰጠው መንፈሳዊ ትምህርት ለምእመናን ታላቅ ጥቅምን አበርክቷል ።

ከዚህ ላይ ቤተ ክርስቲያናችንን የምናመሰግንበት አቅሟ የሚፈቅደውንና ባጀቷ የወሰነውን ያህል በመሥራቷ ነው ።

በዚህ መልክ ምእመናን ቢረዳዱ ቤተ ክርስቲያናችን እንደሌሎች ሁሉ የበለጠ ድርጅት ለማቋቋምና ሥራውንም በትጋት ለማካሄድ ቁርጥ አሳብ ያላት ለወገኖቿም የምታስብ መሆኗ ጥርጥር የለበትም ።

ለዚህም ምስክር ይህ ፕሮግራም ያላንዳች መሰናክል እንዲራመድ መርዳቷ ለበጎ ሥራም ተባባሪ መሆኗ ሲሆን ይህ ምእመናን ወገኖቿን በጣም ያኰራል ።

ምእመናንም በአጭር ጊዜ ውስጥ በቀረበላቸው በዚህ አዲስ መንፈሳዊ ፕሮግራም እንደተደሰቱ ድርጅታችን እየተማመነ ሥራው በበለጠ ተስ ፋፍቶ ከተፈለገው ግብ ይደርስ ዘንድ የርዳታ ክንዶችን በኅብ ት መዘርጋትን ይጠይቃል ።

ይህ ድርጅት በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መልካም ፈቃድና ትእዛዝ ከተቋቋመበት ከ፲፱፻፶፯ ዓ. ም፥ አንሥቶ እስካሁን ድረስ የተጣለበትን አደራ በማክበር ሥራውን ያለምንም ጉድለት ሲያከናውን ይገኛል ።

የወንጌል ድምፅ ራዲዮ ጣቢያ ባለሥልጣኖችና ሠራተኞች በሁሉም ረገድ እርዳታቸውን በሚገባ ያበረክቱ ል ፤ ስለዚህም በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያኖችንና በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ስም እጅ በጣም ከፍ ያለ ምስጋናችንን እናቀርብላቸዋለን ።

በተጠቃለለ አነጋገር ፤ የዚህ ራዲዮ ጣቢያ መቋቋም ለክርስቲያናዊው ዓለም ሁሉ አጥብቆ የሚያስደስት ሲሆን ፤ በተለይ የክርስትና ደሴት ሁና የወንጌል ቃል ከጥንት ጀምሮ በሚነገርባት ኢትዮጵያ ላይ መሆኑ ፤ እኛን ኢትዮጵያውያንን በበለጠ ደስ ሊያሰኘን ይገባል ። ይህም ድርጅት በኢትዮጵያ ላይ እንዲቋቋም መልካም ፈቃዳቸው ለሆነው ለግርማዊ ጃንሆይ ከፍ ያለ ምስጋና ይገባቸዋል።

ስለራዲዮው ጣቢያ ድርጅት ጠቅላላ ጉዳይ ከዚህ እንደሚከተለው እንመልከት ።

# የብስራተ ወንጌል ራዲዮ ጣቢያ

የብሥራተ ወንጌል ራዲዮ በየካቲት ፲፱ ቀን ፲፱፻፶፭ ዓ/ም በግርማዊ ን/ነ/ ተመርቆ ተግፈተ ።



www.ethiopianorthodox.org



ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ። የካቲት ፲፱ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ. ም. የንጌል ድምፅ ሬዲዮ ጣቢያን መርቀው ሲከፍቱ ፤

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ይህን ሬዲዮ ጣቢያ መርቀው በከፈቱበት ዕለት በጣቢያው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም እንድታስተምርበት ፈቀዱ ። ወዲያውም ግርማዊነታቸው ለሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ በልዩ ካቢኔአቸው የመንፈሳዊ ክፍል ዋና ዲሬክተር ሠራተኞችን ቀጥረው የዚህን ፕሮግራም ሥራ እንዲያስኬዱ ትእዛዝ ሰጡ ። በዚህም መሠረት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ሬዲዮ ጣቢያ አማካኝነት የምትሰጠው በየዕለቱ የ፴ ደቂቃ ፕሮግራም አላት ።



www.ethiopianorthodox.org

በዚህ ዕለት ግርማዊ ን/ነ/ በብሥራተ ወንጌል ራዲዮ የሚዘጋጀውን የመጀመሪያውን ፕሮግራም ከፈቱ ።

የብሥራተ ወንጌል ራዲዮ የዓለም ሉተራውያን ፌዴራሲዮን ተብሎ በሚታወቀውና በሉተራውያን አብያተ ክርስቲያናት እየተረዳ በሚካሔደው ድርጅት የሚያገለግል የግል የራዲዮ ጣቢያ ነው። የዚህ ድርጅት ዋናው መሥሪያ ቤት በጄንቫ ስዊትዘርላንድ ሲሆን ከስድሳ (፷) በላይ ከሚሆኑ አህጉርና ከአምሳ (፶) ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ክርስቲያኖች ይወክላል ።

እ-ኤ-አ- በኅዳር ፲፱፻፶፬ ዓ /ም የዚሁ ድርጅት የመገናኛ ሥራ ኰሚቴ (የዓለም ሉተራውያን ፌዴራሲዮን የራዲዮ አገልግሎት ተብሎ የሚታወቀው ) በኢትዮጵያ የራዲዮ ጣቢያ እንዲሠራና እንዲካሔድ ከኢትዮጵያ መንግሥት ፈቃድ ተሰጠው ።

## ለምን በኢትዮጵያ ?

ለዚህ አያሌ ምክንያቶች ይሰጣሉ ። ዋናውና የመጀመሪያው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በአላቸው አርቆ አስተዋይነታቸው በተለይም የክርስትናን ሃይማኖት ለመጠበቅና ለማስፋፋት ባላቸው ጽኑ እምነት ሲሆን ኢትዮጵያ ከጥንት ተያይዞ በመጣው የክርስትና እምነቷ የታወቀች በመሆኗ ነው ። ይህንንም መላው ዓለም ደኅና አድርጎ የሚያውቀው ነው ። ከዚህም በቀር የአገሪቱ አቀማመጥ ድርጅቱ የክርስትና ትምህርት ለሕንድ ለመካከለኛው ምሥራቅና ለመላው አፍሪቃ ለማሠራጨት ባለው ጥረት ምቹ ሁኖ በመገኘቱ ነው ። ይህ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ በቂ የኤሌክትሪክ ኃይል መስጫ ጣቢያዎች ምቹ የመገናኛ ዘዴ ስላላትና የአየሯም ጠባይ ተስማሚ ሆኖ በመገኘቱ ለጣቢያው መቋቋም አይነተኛ ምክንያት እንድትሆን አድርጓታል።

## ዓላማው

ይህ የራዲዮ ጣቢያ የቤተ ክርስቲያን መሥራች የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን ለዓለሙ እንዲያዳርሱ ለሐዋርያቱ በሰጠው ቃል መሠረት ክርስትናን ለማስፋፋት በተለይ የቆመ ስለሆነ በፖለቲካ እምነትም ሆነ ወይም በመንግሥት ጉዳይ የማይገባና የማይመራ ነው ። ለዚህም አቋምና መሠረቱ መረጃው የክርስቶስን ቤዛነት ለዓለም ማስተማር የሚለው በጣቢያው መግቢያ በር ላይ የሚገኘው ጽሑፍ ነው ።

## የፕሮግራም ማዘጋጃ ስቱዲዮዎች

በጣቢያው በኩል የሚተላለፉት አብዛኛዎቹ ፕሮግራሞች የሚዘጋጁት አሥራ አንድ አገሮች ውስጥ በተቋቋሙት የመቅረጫ ስቱዲዮዎች ውስጥ ነው ። አሥራ አንዱ አገሮች ኢትዮጵያ ፤ ሴይሎን ፤ ሕንድ ፤ ኢራን ፤ ሊባኖስ ታንዛኒያ ፤ ማላዊ ፤ ደቡብ አፍሪቃ ፤ ማዳጋስካር፤ ካሚሩንስና ናይጄሪያ ናቸው ።


በእነዚህ አገሮች ውስጥ የሚገኙትን ስቱዲዮችና ፕሮግራሞቹንም የሚያዘጋጁት የአገሩ ቤተ ክርሲቲያኖች ናቸው ። ከዚህም በቀር ቤተ ክርስቲያኖች የአድማጮቻቸውን ፍላጎት ለማርካት ጥያቄዎችን በመመለስ ስለክርስትና እምነት አቋም የሚላክላቸውን በመቀበል ያገለግላሉ ። በኢትዮጵያ የሚገኙትም ስቱዲዎች በሙሉ አዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙ ናቸው ። በዋናው ጣቢያ ካሉት የመቅረጫ መሣሪያዎች በቀር ሁለት ሌሎች ሲኖሩ አንደኛው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሚመራው ነው ። ሁለተኛው ደግሞ በኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ የሚካሔድ ነው ። ሁለቱም ስቱዲዮች በየቀኑ የአማርኛ ፕሮግራም እያዘጋጁ ያቀርባሉ ። በነፃም ለአድማጮች ያስተላልፋሉ ።

## ሕዝብና ቋንቋዎች

በዚህ ራዲዮ ጣቢያ ከ፪፻ በላይ የሚሆኑ ሠራተኞች ይገኛሉ ። ከእነዚሁ ውስጥ በመቶ ፹፭ እጅ ያህል ኢትዮጵያውያን ሲሆኑ የቀሩት ከአሥራ አንድ ልዩ ልዩ አገሮች የመጡ ናቸው ። ሌሎች ፩፻፹ የሚሆኑት ደግሞ በየአገሩ በተቋቋሙት ስቱዲዮዎች ውስጥ በመሥራት በየቀኑ በሲንሀሊስ ፤ በቲሌጉ ፤ ታሚል ፤ ሂንዲ ፤ ፋርስ ዓረብኛ፤ ስዋሂሊኛ፤ ናያንጃ ፤ ማላጋሲ ፤ ዙሉ ፤ ሶዞ ፤ አፍሪካንስ ፤ ሀውሳ ፤ ፉላኒ ፤ ፈረንሣይኛ ፤ እንግሊዝኛና አማርኛ የሚሰሙትን ፕሮግራሞች ያዘጋጃሉ ።



www.ethiopianorthodox.org




## የእጅ ጥበብና የፕሮግራሙ ሁኔታ

በሾርት ዌቭ ራቅ ላሉ አገሮች የሚተላለፉት መንፈሳዊም ሆነ ሥጋዊ ፕሮግራሞችን በሙሉ የሚያሰራጩት ከአዲስ አበባ ከተማ ፴ ኪሎ ሜትር ራቅ ብሎ በሚገኝ ጌጃ በተባለው ቀበሌ የሚገኙት እያንዳንዳቸው መቶ ኪሎዋት ጉልበት ያላቸው ሁለት ታላላቅ ትራንስሚትሮች ናቸው ።

ጣቢያው ዛሬ በየቀኑ ፲፪ ሰዓቶች በመሥራት የክርስቶስን የዓለም ቤዛነትና የእግዚአብሔር ልጅነት የሚመሰክር ሲሆን በዚህ ላይ ለአዲስ አበባና ለአካባቢዋ የሚያገለግል አንድ ሌላ ተጨማሪ የሚዲየም ዌቭ ማሰራጫ በየቀኑ ፲ ሰዓቶች ያገለግላል ።

በጣቢያው የሚተላለፉት ፕሮግራሞች በሙሉ መንፈሳዊ ነክ ብቻ አይደሉም ። ክርስቲያኖች በአካባቢያቸው የሚታየውን የሚደረገውን ሁሉ ለማወቅ የሚፈልጉ ስለሆኑ የዓለም ወሬዎችን ውይይቶችን ማኅበራዊ ኑሮ ነክ ጉዳዮችን እስፖርትንና ሌሎችም እነዚህን የመሳሰሉ አርእስቶችን በሰ



www.ethiopianorthodox.org

ፊው ያቀርባል ። ምንም እንኳ አብዛኛዎቹ ፕሮግ ራሞች በክርስቲያን እምነት ላይ የተመሠረቱ ቢሆ ኑም ከመቶው ሰባ እጅ ትምህርት ነክ ጉዳዮች ናቸው ።

## አስተዳደርና የመተዳደሪያ ገንዘብ

ጣቢያው የሚተዳደርበት ገንዘብ በዓለም አካ ባቢ ከሚገኙ ክርስቲያኖች በሚደረገው መዋጮ ነው ። በአፍሪቃና በእስያ የሚገኙት አብያተ ክር ስቲያናት ፕሮግራሞችን ከማዘጋጀትና እንዲደመ ጡም ከማድረጋቸው በላይ ጣቢያው የሚተዳደር በትን ደንብና ውሳኔ በማዘጋጀት ይካፈላሉ ። እነ ዚህም ከአራቱ ክፍለ ዓለማት የተውጣጡ ሆነው ታላላቅ ከሆኑት የፕሮቴስታንት ማኅበር ወገኖች ናቸው ።

## ሰላምታ

ይህን ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በድል አድራጊነት ወደሚወዷት አገራቸው የገቡበትን የ፳፭ኛውን ዓመት በዓል ምክንያት በማድረግ የብ ሥራት ወንጌል ራዲዮ ጣቢያ ዲሬክተሮችና የቦ ርዱ ሊቀ መንበር ከኢትዮጵያ መሬት መንጭቶ ለመላው የአፍሪቃና የእስያ ሕዝብ ወንጌልን በራ ዲዮ አማካይነት ለማሰራጨት በመቻሉ ሁሉን ለሚ ሚችል አምላክ ምስጋና ያቀርባሉ ። እንደዚሁም የእግዚአብር አገልጋይና የኛም ንጉሠ ነገሥት ለሆኑት ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እግዚአብሔርን እናመሰግ ናለን ። በጌታችንና በመድኃኒታችን በየሱስ ክርስ ቶስ ስም አሁንና ለወደፊቱም የእግዚአብሔርን በረከት እንለምንላቸዋለን ።

ዶክተር ፍራንክሊን ፍራይ
የቦርዱ ሊቀ መንበር ፤
ዶክተር ሲጋርድ አስኬ
የራዲዮው የበላይ ዲሬክተር ፤
አቶ አማኑኤል ገብረ ሥላሴ
ስለቤተ ክርስቲያንና ስለመንግሥት ጉዳዮች
አማካሪ ፤
አቶ መንክር ኢሳይያስ በራዲዮ የመካከለኛው
መሥመር (ሚድየም ዌብ) አገልግሎት
ኤዲተር ፤



www.ethiopianorthodox.org

የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ጉባኤ ፤

# ታሪካዊ መግለጫ

« በዚህ ጉባኤ ገና ከጥንት ጀምሮ ጌታ ኢትዮጵያን የባረካት መሆኑን ተመለከትኩ ። የዓባይ ወንዝ በሚሊዮን ለሚቆጠሩ የሰው ዘር ሕይወትን ለመስጠት ከተራሮችዋ ቁልቁል ይፈሳል ። እንደዚሁም ከዚህ ፤ በኢትዮጵያ ተራሮች ላይ ከሆነው ጉባኤ ፤ የኦርቶዶክስን ሕዝብ ሊያጠነክር ያለ ፤ ብርሃን ሕሊና ( ኢንስፐሬሽን ) ቁልቁል ይፈሳል ። » አቡነ ቄርሎስ ስድስተኛው

ይህ ለጽሑፋችን እርእስት የሆነው ጉባኤ የታሰበው ፤ ቀጥሎ በተመለከተው ሰንጠረዥ ፤ ለተዘረዘሩት አብያተ ክርስቲያናት ነው ። ይህም አቀራረብ የሚያመለክተው የዛሬ አቀማመጣቸውን ነው ።

| የቤተ ክርስቲያኗ መጠሪያ | የጠቅላይ መሪው መጠሪያ | የቤተ ክርስትያኗ መሥራች ቅዱስና ክርስትና የታወጀበት ዘመን | የአማንያን ብዛት | መንበረ ባትሪያርኩ ያለበት ከተማና ሀገር |
|---|---|---|---|---|
| 1. የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤ. ክ. | የእስክንድርያው ፓፓና የመንበረ ማርቆስ በትሪያርክ | ቅዱስ ማርቆስ 49 ዓ. ም. ገደማ | 4,000,000 | ካይሮ ( የተባበረው አረባ ረፐብሊክ ) |
| 2. የአንጾኪያ ኦርቶዶክስ ቤ. ክ. | የአንጾኪያና የመላ ምሥራቅ ፓትሪያርክ | ቅዱስ ጴጥሮስ 37 ዓ. ም. ገደማ | 500,000 | ደማስቆስ ( ሶርያ ) |
| 3. የአርመን ኦርቶዶክስ ቤ. ክ. | (ሀ) በኤችሚያዜን የአርመኖች ጠቅላይ ካቶሊኮስ | ቅዱስ ጎርጎርዮስ | | ኤችሚያዜን ( አርመን ) |
| | (ለ) በታላቅዋ ቤት ኬልቅያ የአርመኖች ካቶሊኮስ | ከሣቴ ብርሃን 301 ዓ. ም. ገደማ | 4,500,000 | አንቲሊያ ( ቤይሩት ሊባኖስ ) |
| 4. የምሥራቅ የሶሪያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ( ሕንድ ) | የምሥራቅ ካቶሊኮስ | ቅዱስ ቶማስ ሐዋርያ በመጀመሪያው መቶ ዓመት ውስጥ | 1,500,000 | ኮታያም ( ኬራላ ደቡብ ሕንድ ) |
| 5. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን | የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ባትሪያርክ | ከሐዋርያት አንዱና ቅዱስ ፍሬምናጦስ 430 ዓ. ም. ገደማ | | አዲስ አበባ ኢትዮጵያ ። |



www.ethiopianorthodox.org

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ፤ በቀሩት ሕዝበ ክር ስቲያን ዘንድ ፤ በቃልም ሆነ በጽሑፍ ፤ እነዚህ የተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ልዩ ልዩ መጠሪያ ተሰጥቷቸዋል ። ከእነዚህም መጠሪያዎች ዋና ዋናዎቹ ፩/ ንዑሳን የምሥራቅ አብያ ተ ክርስ ቲያናት ፤ ፪/ አንድ ባሕርዮች (ማኖፊዚት) ፫/ ያዕቆባውያን ፤ ፬/ ቅጽጦች ፤ ፭/ እስክንድራው ያንና ፮/ የኬል ቄዶንን ጉባኤ የማይቀበሉ ናቸው።

ከእነዚህ ስሞች ፤ በየአንዳንዱ የአመጣጥ ታሪክ ዝርዝር ውስጥ ሳንገባ ፤ እንዲያው በጠቅላላ ስንመለከታቸው ፤ አንዱ በአንዱ ሲስቅ ጀንበር ጥልቅ በአለው መንፈስ ፤ ለምሳሌ ተዋሕዶዎች ፤ ሌሎችን ፤ ንስጥሮሳውያን ፤ ጸረ ማርያሞች ሁለት ባሕርዮችና እነዚህን የመሰሉ ስሞች እንደሚሰጥዋቸው ፤ ሌላው ሕዝበ ክርስቲያን ደግሞ፤ ለተዋሕዶ ክርስቲያኖች ከፍ ብለን እንዳነበብናቸው ያለ ስም ይሰጧቸዋል ። በዚህም ለእነርሱ ያለውን ሃይማኖታዊ አስተያየት ይገልጻል ።

በታሪክ ዘመን ውስጥ ጥቂት ወደ ኋላ የሔድን እንደሆነ ፤ ካቶሊኮችና መለካውያን ፤ ተዋሕዎችን መናፍቃን ሲሉ እናገኛቸዋለን ። እያደር ፤ ግን ፤ እንዲህ ያለውን አግባብ ያልሆነ ሥያሚያቸውን ለውጠው ፤ ሺዝማቴክ (ተቆርጠው የሔዱ) ሲሉ እናገኛቸዋለን ። ዛሬ ደግሞ ፤ በጣም ተሻሽለው ፤ ከእኛ የተለዩ ወንድሞቻችን ይላሉ ። እንዲያውም አንድ አንድ የሃይማኖት ቡድን ፤ ብሔራዊ አቋምን ለማግኘት በሚፈልጉበት ፤ ለምሳሌ፤ እንደ ግብፅ በአለ ሀገር ፤ ግብጻውያን ካቶሊኮች ለማለት እንዲመች ፤ ግብፃውያን ኦርቶዶክሶች እያሉ ሲጽፉ ይገኛሉ ። እንደዚህም እነዚህ የተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ቀስ በቀስ ፤ ብሔራዊ መለዮአቸው እየተጨመረ ፤ የግብፅ ኦርቶዶክስ ፤ የሶርያ ኦርቶዶክስ ፤ የአርመን ኦርቶዶክስ ፤ የሕንድ ሶርያ ኦርቶዶክስና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ እያሉ መጠራት ጀምረዋል ። በተለየ እነዚህ አምስቱም አብያተ ክርስቲያናት አባል በሆኑበት ፤ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ፤ በዚህ ስም ብቻ ነው የሚጠሩ ። እስከዚህ ያለው እነዚህን አብያተ ክርስቲያናት በሞላው ሕዝበ ክርስቲያን ማህል አድርገን ስንመለከታቸው ነው ። እነርሱን ለብቻ ወሰደን ፤ እንደ አንድ ክርቲያናዊ ቤተ ሰብ ስንመለከታቸው ደግሞ ፤ ቀጥሎ የተመለከቱትን ነጥቦች እንጠቅሳለን ።

አንደኛ እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ፤ አብያተ ክርስትያናት ዘሠለስቱ ቀደምት ጉባኤያት ሊባሉ ይቻላሉ ። ይኸውም እነዚህ አብያተ ክርቲያናት ፤ እስከ አራት መቶ ሃምሳ አንድ ዓመተ ምሕረት የአንዲት ቤተ ክርስቲያን አባል ሆነው ሲኖሩ ፤ አውጣኪስ በጫረው የምሥጢረ ሥጋዌ ጭቅጭቅ ምክንያት ፤ በዚሁ ዘመን በኬልቄዶን በሆነው ጉባኤ ቤተ ክርስቲያን ተከፋፍላ ፤ ሁሉም በየፊናው መሔዱ ሲታሰብ ነው ። ከዚያ ወዲህ ኬልቄዶናውያን (መለካውያን) ፤ በየጊዜው ጉባኤ ሲያደርጉ ዛሬ ከሰባተኛው ላይ ደርሰዋል ። ካቶሊኮች ደግሞ በበኩላቸው ወደ ሃያ አራተኛው ደርሰዋል ። የተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ግን ስለ ልዩ ልዩ ምክንያት እዚያው ሦስቱ ጉባኤዎች ላይ ቀርተዋል ። እነዚህም ሦስቱ ጉባኤዎች ቀጥለው የተመለከቱት ናቸው ።



www.ethiopianorthodox.org

| ጉባኤው | የጉባኤው ሰብሳቢ | ጉባኤው የተደረገበት ቦታ | የጉባኤው ዘመን | የጉባኤው መናፍቅ | ኑፋቄው | የጉባኤው ውሳኔ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| መጀመሪያው | ትልቁ ቆስጠን ጢኖስ | ኒቅያ ( የቱርክ ግዛት ) | 325 ዓ. ም. | አርዮስ (በእስክንድርያ የአንድ ቤ. ክ. አለቃ የነበረ) | ወልድ ፍጡር | (1) ዘተወልደ ወአኮ ዘተገብረ ዘዕሩይ ምስለ አብ በመለኮቱ (2) አርዮስ ውጉዝ |
| ሁለተኛው | ትልቁ ቴዎድዮ ስዮስ | ቁስጥንጥንያ ( የቱርክ ግዛት ) | 381 ዓ. ም. | መቅዶንዮስ ወሰባልዮስ | መንፈስ ቅዱስ ፍጡር | (1) መንፈስ ቅዱስ እግዚእ ማሕየዊ ዘሠረፀ እም አብ ንስግድ ሎቱ ወንስብሆ ምስለ አብ ወወልድ (2) መቅዶንዮስ ወሰባልዮስ ውጉዛን |
| ሦስተኛው | ዳግማዊ ቴዎድ የስዮስ | ኤፌሶን ( የቱርክ ግዛት | 431 ዓ. ም. | ንስጥሮስ | ማርያም ወላዲተ ሰብእ | (1) ድንግል ወላዲተ አምላክ (2) ንስጥሮስ ውጉዝ |

ሁለተኛ እነዚህ የተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ምንም ሳይገናኙ የቀሩበት ዘመን ብዛት ፤ የሀገር ርቀት ፤ አንዳንድ ጊዜም የዘር የቋንቋና የባሕል ልዩነት ደህና አድርጎ ባያስተዋውቃቸውም ፤ በመሠረቱ የሃይማኖት አባቶቻቸው አንድ ስለሆኑ ፤ የሃይማኖት መጻሕፍቶቻቸው አንድ ስለሆኑ ፤ ተመሳሳይ የሃይማኖት ባሕል ስለአላቸው ከዚያም ሁሉ በላይ ፤ በአንዲት የተዋሕዶ ሃይማኖት ስለሚያምኑ ፤ የአንዲት ቤተ ክርስቲያን ቤተ ሰብ መሆናቸው እየተሰማቸው ኖረዋል ። በዚህ ረገድ ፤ ለምሳሌ የአንጾኪያው ፓትሪያርክ ፤ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ አግናጥዮስ ሣልሳይ ፤ በጥር ወር ፲፱፻፶፯ ዓ/ም በሆነው የመሪዎች ጉባኤ ፤ ግርማዊ ጃንሆይ ለጉባኤው መክፈቻ ለአደረጉት ንግግር በሰጡት መልስ እንዲህ ይላሉ ፤ «በዚህ አጋጣሚ ጊዜ ፤ የኢትዮጵያ ገዥ እንደ መሆንዎ ፤ ግርማዊነትዎን በጣም ከፍ ባለ ግምት የምንመለከትዎት መሆናችንን እገልጽ ዘንድ የሚገባኝ ነው ። በጸሎተ ቁርባናችን ሁሉ ፤ ግርማዊነትዎን እናስባለን ። ይህንንም ስናደርግ በዘጠነኛው መቶ ዓመት የነበሩ እንደ ማር ሴቤር ዩስ ሙሼ ባር ኪፎ ያሉትንና ፤ በአሥራ ሁለተኛው መቶ ዓመት የነበሩ ማር ዲዩናስዮስ ባር ሳሊቢ ያሉትን ታላላቅ አባቶቻችንን በመከተል ነው ። እነርሱም በእምነት መሰሎቻችን ናቸው በማለት ፤ የኢትዮጵያን ነገሥታት ፤ በጸሎተ ቁርባን ጊዜ እንድናስታውሳቸው አዘውናል ። አብያተ ክርስቲያኖቻችንም ቢሆኑ ፤ ቢያንስ ቢያንስ ከአራተኛው መቶ ዓመት ጀምሮ የቀረበ ግንኙነት አላቸው ። ለምሳሌ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያው ጳጳስ ፤ ቅዱስ ፍሬምናጦስ ፤ ዛሬ በሰበካችን ውስጥ ከምትገኝ ከጢሮስ እንደ መጣ አስረጅ ጽሑፍ አለን ። ማር ያዕቆብ ባሬዴውስም በስድስተኛው መቶ ዓመት ኢትዮጵያን ጎብኝቷል ። እንደዚሁም ፤ ወደ ዚሁ ዘመን ፤ ተሰዓቱ ቅዱሳን ፤ የትውልድ ሀገራቸውን ሶርያን ትተው ወደዚሁ መጥተው ኖረዋል ። »

ይህንን የአንድነት ስሜት ከዘመን ዘመን በማሸጋገር ጥቂት ምክንያት የሆነ ደግሞ የግብጾች ፤ የሶርያውያን ፤ የአርመኖችና የኢትዮጵያውያን ኦርቶዶክሶች ጳጳሳት ፤ መነኮሳትና ምእመናን ፤ በኢየሩሳሌም ፤ ቅድስት ሀገር ፤ በጉርብትና አብሮ መኖራቸው ነው ። ነገር ግን ይህ ጉርብትናቸው ፤ አብዛኛውን ጊዜ የወሰን ባላንጣነትና ፤ የመሬት ተቀናቃኝነት መንፈስ ስለ ነበረውና አሁንም ስለ ፤ ለው ፤ የአንድነት ማጠንከሩን ጉዳይ ከግብ አላደረሰውም ።



www.ethiopianorthodox.org

# የጉባኤው አጀማመር

ስለዚህ የእነዚህ አብያተ ክርስቲያናትን የመገናኘት አሳብ በሥራ ለማሳወቅ አዲስ መንፈስ አዲስ ቦታ ፤ አዲስ አጋጣሚ ምክንያቶችና አዲስ ኃይልም አስፈለጉ ። ከጊዜ ወደጊዜ በመሸጋገር እነዚህ ሦስቱም ምክንያቶች ተገኙ ። የመጀመሪያው ከጥቂት ዓመታት በፊት በአደረጉት አንድ ንግግር ፤ የምሥራቅ ጀርመን የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን መሪ የነበሩት ዲቤልዩስ ፤ ይህ ሃያኛው መቶ ዓመት የአንድነት ዘመን ነው ባሉት ተገልጧል ። ለዚህ አስተያየት ጥሩው ማስረጃ ዛሬ ከመቶ ዘጠና አብያተ ክርስቲያናት በላይ አባሎች ያሉት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር የሚባለው ነው ። ከፍ ብሎ የጠቀስናቸው አምስቱም የተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ፤ የዚሁ ማኅበር አባሎች ናቸው ። ይህ አባልነታቸውም ፤ በዚህ በሃያኛው መቶ ዓመት በሕዝበ ክርስቲያን መንፈስ ከተቀረጸው የአንድነት መንፈስ ለመሳተፍ አበቃቸው ። በዚህ ረገድ ግርማዊ ጃንሆይ ጥር ፲፱፻፶፯ ዓ- ም- የሆነውን የምሥራቅ ኦርቶዶክስ መሪዎች ጉባኤ ሲከፍቱ በአደረጉት ንግግር «ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳትሆን የዓለም የፖለቲካ ኃይሎች ሳይቀሩ ቂም በቀላቸውን ወደ ጐን ትተው በጋራ ችግራቸው ለመነጋገር ሳያቋርጡ ይገናኛሉ - - - » ብለዋል ። ከጥቂት ዘመናት ወዲህ በእነዚህ ክርስቲያኖች ዘንድ የተፈለገው « - - - ሳያቋርጡ በመገናኘት - - - » የተባለው ሲሆን ፤ ይህን የተባለውን በሥራ ለማዋል አንዳንድ እርምጃ ወስዶ መንገድ መጥረግ አስፈለገ ።

አንደኛ እነዚህ የተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ፤ ከፍ ብሎ የተጠቀሰው ማኅበር አባሎች እንደመሆናቸው ፤ ይህ ማኅበር በሚያደርገው ትልልቅ ስብሰባ ሁሉ በመገኘታቸው ፤ እንደ ሌሎቹ ክርስቲያኖች እነርሱም በበኩላቸው መፈላለግ እንዳለባቸውና መኖራቸውንም ለሌሎቹ ክርስቲያኖች ማሳወቅ እንደሚገባቸው የመመካከሪያ አጋጣሚ ጊዜን አገኙ ።

ሁለተኛ ፤ የቤተ ክርስቲያን ስብሰባ በማድረግ በኩል ጥንታውያን የቤዛንሳ ነገሥታት ያደርጉ የነበረውን ብናስብ ፤ ይህ ምኞታቸው በሥራ እንዲውል ግርማዊ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጣም እንደሚረዱቸው በመገንዘብ ፤ ሁሉም ፊታቸውን ወደዚሁ መለሱ ።

ከእነዚህ ፊታቸውን ወደዚህ ከመለሱት ኦርቶዶክሶች የመጀመሪያው የአንጾኪያውና የመላው ምሥራቅ ኦርቶዶክስ ፓትሪያርክ ብፁዕ ወቅዱስ ሞራን ማር አግናጥዮስ ያዕቆብ ሣልሳይ ናቸው ። እኚህ ፓታሪያርክ ለምሳሌ ፤ እ- ኤ-አ-በጥር ወር ፲፱፻፷፫ ዓ- ም- አዲስ አበባ ላይ የሆነውን የምሥራቅ ኦርቶዶክስ መሪዎች ጉባኤ ሲከፍቱ ፤ ግርማዊ ጃንሆይ ለአደረጉት ንግግር መልስ ሲሰጡ ፤ እንዲህ ብለዋል ። «እንደ እውነቱ እኛ ታናሾቹ ከመንበረ ቅዱስ ጴጥሮስ ላይ ከተቀመጥን ጊዜ ጀምሮ ለአብያተ ክርስቲያናቱ መገናኘት አንድ መንገድ እንዲከፍት ለእግዚአብሔር እንደ ጸለይን ነበርን ። ሢመተ ፓትሪያርክም እንደተቀበልን ከወንድሞቻችን ከቤተ ክርስቲያናችን መጥረጶሊሶች ሁለቱ ኢትዮጵያን በጎበኙ ጊዜ ግርማዊነትዎ ይህን ስብሰባ እንዲጠሩ ለማሳሰብ በእነዚያ በሁለት መጥረጶሊሶች አማካይነት ማሳሰቢያ ልከን ነበር ።

«እንደዚሁም ዛሬ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ረዳት ዋና ጸሐፊ የሆኑት አባ ጳውሎስ በርጊስ ይህን የተዋሕዶ ኦርቶዶክሶችን የመሰብሰብ ጉዳይ በቅርብ ሆነው ለግርማዊ ጃንሆይ ያሳስቡ እንደነበር በቃል ይነገራል ። ከአርመን ቤተ ክርስቲያንም በጊዜው በአሜሪካ የአርመን ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ ፤ አሁን ግን በቁስጥንጥንያ የአርመን ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክ የሆኑት አቡነ አሽኖርክ ፤ ከሕንድም ቤተ ክርስቲያን አንዳ



www.ethiopianorthodox.org

ንድ ጳጳሳት በሃይማኖት ስብሰባው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መልእክተኞችን ሲያገኙ ሆነ ፤ በልዩ ልዩ ምክንያት በኢትዮጵያ ሲያልፉ ፤ የተዋ ሕዶ ኦርቶዶክሶችን መሰብሰብ እንደሚያስፈልግ ለግርማዊነታቸው በጣም አሳሰበዋል ።

ጉባኤው ሲዘጋጅ ።

ይህን ሁሉ በማሰብ ግርማዊ ጃንሆይ ቀዳ ማዊ ኃይለ ሥላሴ መልካም ፈቃዳቸው ሆኖ ለዚህ ታሪካዊ ስብሰባ አስፈላጊው ጥናት እንዲደረግ አዘዙ ። ይህንንም ንጉሥ ነገሥታዊ ትእዛዝ መሠ ረት በማድረግ የፕሮግራም ኮሚቴ የጽሕፈት ቤት ኮሚቴና የአስተናጋጅ ኮሚቴ በሚባሉ በሦስት ትልልቅ ኮሚቴዎች ተከፋፍሎ መላ የድርጅቱ ሥራ ተጀመረ ። ከእነዚህም ኮሚቴዎች የመጀመ ሪያው በሐረር ሊቀ ጳጳስና የፓትርያርኩ እንደ ራሴ በሆኑት በብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ሲመራ ፤ ሁለተኛው በክቡር አቶ አበበ ረታ የሕዝብ ጤ ጥበቃ ሚኒስትር ( አሁን የንግድና የእንዱስትሪ ሚኒስትር) ፤ ሦስተኛው ደግሞ በክቡር ባላምበራስ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል የሥራና መገናኛ ሚኒስትር (አሁን ብላቴን ተብለው የዘውድ አማ ካሪ) ተመራ ።

በልዩ ልዩ መንገድ ይህን የድርጅት ሥራ ከደንበኛ ሥራቸው ውጪ በአላቸው ጊዜና ኃይል የረዱ ከሚኒስትር ጀምሮ እስከ ሹፌር ድረስ ያሉ በግምት መቶ አምሳ ይሆናሉ ። ይህም በአጭር መንገድ ቃላትን የመውሰድ ሙያ ያላቸውን የዓ ለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ባልደረቦች የሆ ኑትን ከጄኔብ የመጡትን ሚስ ክሎዲን ሬይም ንና ሚስ ኤሌን ቦግልን ጨምረን ስናስብ ነው ።

በሠራተኞቹ በኩል አንድ ደንበኛ ባለሙያ ውን ያላገኘ የማስተርጐም ሥራ ነበር ። እንደሚ ታወሰው በጉባኤው ሱርስት ፤ አርመንኛ ፤ እንግ ሊዝኛ ፤ ዓረብኛና አማርኛ ተነግረዋል ። ለእንደዚህ ያለ ትልቅ ስብሰባ የታሰበው የአፍሪካ አዳራሽ ደግሞ ፤ ከአፍ እየተቀበሉ ከተናጋሪው እኩል በተፈለገው ቋንቋ ለሚያሰሙ አስተርጓሚዎች የተ ዘጋጀ ሥፍራና መሣሪያ አለው ። ግን ሥራውን ማን ይግባበት ! እውነት ነው ፤ ይህ ሳይታሰብበት አልቀረም ። ነገር ግን ቀደም ብሎ አንድ መቁረጫ ስላልተሰጠው በመጨረሻ ደቂቃ የተገኙት ሰዎች ገቡበት ። ሥራውም ጥቂት እንደ ነገሩ ሆነ ።

አንደኛ ፤ የጉባኤውን አደራጆች ብንወስድ የድርጅት አገልግሎታቸውን የሚሰጡ ከደንበኛ ሥራቸው ውጪ በአላቸው ኃይልና ጊዜ ነበርና እንደ ልብ ለማግኘት ጥቂት አስቸገሩ ። እንደዚ ሁም ከልዩ ልዩ የኢትዮጵያ መሥሪያ ቤቶች በመ ሆናቸው ለየስብሰባው መጠራራቱ ፤ ጉዳዩን ማስረ ዳቱም ጊዜ ወሰደ ።

ሁለተኛ ፤ በልዩ ልዩ ምክንያት የጉባኤው መጀ መሪያ ቀን ከቀጠሮ ወደ ቀጠሮ ይተላለፍ ጀመር ። በተላለፈም ቁጥር አዲሱን ቀጠሮ ማስታ ወቅ አንዳንድ ጥቃቅን ነገሮችንም ከሥር መጀ መር አስፈለገ ። ለምሳሌ ፤ የመጀመሪያው ቀጠሮ ለጥር ወር ፲፱፻፶፬ ዓ. ም. ነበር ። ነገር ግን ይህን ጥሪ የግርማዊት እቴጌ መነን ዕረፍት ሠረዘው ። ሁለተኛው ጥሪ ለመስቀል ፲፱፻፶፯ ዓ. ም. (እ. ኤ. አ.) መስከረም ፳፫ እስከ ጥቅምት ፩ ቀን ፲፱፻፷፬ ዓ. ም. ነበር ። ነገር ግን በዚህም ጊዜ ደግሞ የአን ጾኪያው ፓትርያርክ ሚመተ ጵጵስና ሊሰጡ ወደ አንድ ቦታ የሚሔዱበት ጊዜ ነበረና ተላለፈ። ሦስተኛው ቀጠሮ ደግሞ ለመስከረም ወር ፲፱፻፶፰ ዓ. ም. (እ. ኤ. ቄ. መስከረም ፲፭/፳፭ ቀን ፲፱፻፷፭ ዓ. ም. ) እንዲሆን ተወሰነ ። በዚህ ጊዜ ደግሞ ግር ማዊ ጃንሆይ የምሥራቅ አውሮፓ አገሮችን በኦፊ ሲዬል ይጎበኙ ስለነበር ተላለፈ ። ስለዚህም አራ ተኛና የመጨረሻው ቀጠሮ ተደረገ ። ይኸውም ጥር ፯ እስከ ፲፫ ቀን ፲፱፻፶፯ ዓ. ም. (እ. ኤ. አ. ጥር ፲፭ እስከ ፳፩ ቀን ፲፱፻፷፭ ዓ. ም.) ነበር ።

ሦስተኛ ፤ በያንዳንዱ ቀጠሮ የመዘጋጃው ጊዜ በጣም አጭር ነበር ። በመደጋገም እንደተነገረው እነዚህ ጉባኤው የታሰበላቸው የተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ለመጨረሻ ጊዜ በጉባኤ የተገናኙት የዛሬ ፩ሺ፭፻፲፭ ዓመት ነው ። ከይህን ያህል ዓመ ታት በኋላ ለሚደረግ ግንኙነት የመዘጋጀው ጊዜ ረጅም መሆን ነበረበት ።



www.ethiopianorthodox.org

አራተኛ ፤ እስከ መስከረም ፲፱፻፶፯ ዓ. ም. ድረስ ይህ ታሪካዊ ጉባኤ የታሰበው ለአምስቱ የተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ብቻ ነበር ። ከመስከረም ወር እኩሌታ ጀምሮ ግን የግርማዊ ጃንሆይ መልካም ፈቃድ ሆኖ ትልቅ የአሳብ ለውጥ ሆነ ። ይህም የአሳብ ለውጥ በዐዋጅ የታወቀው የኢትዮጵያን ሔራልድ በመስከረም ፲፮/፲፱፻፶፯ (እ· ኤ· አ· መስከረም ፳፮/ ፲፱፻፷፬ ዓ. ም.) ግርማዊ ጃንሆይ በዚሁ ወር በምሥራቅ ኤውሮጳ ያደርጉት ስለነበረው ንጉሣዊ ጉብኝት ፤ የዕለት ሐተታን ሲሰጥ «ዛሬ ግርማዊ ጃንሆይ ከቡልጋሪያው ኦርቶዶክሳዊ ፓትሪያርክ ከብፁዕ ወቅዱስ ምንሰኘር ቄርሎስ ጋር የጥሞና ንግግር አደረጉ ። በንግግሩም ላይ ግርማዊነታቸው ፓትረያርኩን በሚመጣው ጥር ወር የአብያተ ክርስቲያናት ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ከመላው ዓለም አዲስ አበባ ላይ ሲሰበሰቡ እርስዎንም እንደምናይዎት ተስፋ እናደርጋለን» አሉ ብሎ ባስታወቀው ነው ።

ይህ የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ጉባኤ ዓላማ መለወጥ ፤ የመጠኑም መስፋት ፤ አንደኛ በድርጅት መልክ የሚታሰቡ አንዳንድ እርምጃዎችን መውሰድ አስፈለገ ። ሁለተኛ ራሱ የአሳቡ ለውጥ አንዳንድ የተጠበቁ ፤ አንዳንድም ያልተጠበቁ ውጤቶችን አስከተለ ።

በዚህ ረገድ ከተወሰዱት እርምጃዎች ለምሳሌ ፤ የኬልቄዶናውያን (የመለካውያን) ጠቅላይ ፓትርያርክ ከሆኑት ከብፁዕ ወቅዱስ ምንሰኘር አቴናጎራስ ጀምሮ ፤ ለአሥራ አንድ የመለካውያን አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ፤ የግርማዊ ጃንሆይን የጥሪ ደብዳቤ መላክ ያስፈልግ ነበር ። እነዚህም የተጠቀሱት መሪዎች በምሥራቅ አውሮፓ ፤ በምዕራብ አውሮፓና በመካከለኛው ምሥራቅየሚገኙ እንደ መሆናቸው ፤ በእነዚህ አገሮች ያሉ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የዲፕሎማቲክ መልእክተኞች፤ ይህንኑ የጥሪ ደብዳቤ ለማድረስ ረድተዋል ። በተለይ ደግሞ ለዚህ ሥራ ሲል ፤ በክቡር ባላምበራስ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል የሥራና የመገናኛ ሚኒስትር የሚመራ ሦስት አባሎች ያሉት አንድ የልዑካን ጓድ ከኢትዮጵያ ተነሥቶ በካይሮ ፤ በቤይሩት ፤ በደማስቆስ ፤ በኢየሩሳሌም ፤ በቁስጥንጥንያ ፤ በአቴናና በቆጵሮስ ለሚገኙ ለዘጠኝ በፓትርያርክ በካቶሊኮስና በሊቀ ጳጳስና ደረጃ ላሉ የግሪክ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች የጥሪ ደብዳቤ አድሏል ። የዚህ ጉባኤ ዓላማ መለወጥ ፤ የመጠኑም መስፋት ፤ ካስከተላቸው ነገሮች ደግሞ ዋና ዋናዎቹ ቀጥሎ የተመለከቱት ናቸው ።

አንደኛ ፤ ከፍ ብሎ በተገለጹት መንገዶች ጥሪው የደረሳቸው ኬልቄዶናውያን (መለካውያን) የኦርቶዶክስ መሪዎች ፤ ጥሪው ከደረሳቸው ቀን ጀምሮ እስከ ስብሰባው ቀን የነበረው የአንድወር ተኩል ጊዜ ለመዘጋጀት በጣም አጭር ሆኖ አገኙት ። ሁለተኛ ፤ እንደ እስክንድርያው ግሪካዊ ፓትሪያርክ ፤ እንደ ቅዱስ ውብፁዕ አቡነ ክሪስቶፎሮስ ያሉ ፤ ከሰማንያና ከዘጠና በላይ የሆነ ዕድሜያቸው በስብሰባው በአካል ለመገኘት የሚያስችላቸው አልመሰለም ። ሦስተኛ ፤ የእያንዳንዱ ኦርቶዶክሳዊ ኬልቄዶናዊ መሪ ከስብሰባው መገኘት አለመገኘት ከብፁዕ ወቅዱስ የቁስጥንጥንያው ፓትርያርክ መምጣትና አለመምጣት ጋር የተያያዘ ነበር ። እኚህ የቁስጥንጥንያው ፓትርያርክ ግን ከግርማዊ ጃንሆይ ለተላከላቸው ጥሪ «ከአቅማችን በላይ በሆነ ምክንያት ልንመጣ ባለመቻላችን በጣም እናዝናለን ። ሆኖም እኛን የሚተኩ በሊቀ ጳጳስና ደረጃ ያሉ በኢትዮጵያ የግሪክ ኦርቶዶክስ ኪሙኖቴ ሊቀ ጳጳስ የሆኑትን ምንሱኘር ኒኮላን ወክለናል ሲሉ መለሱ» ይህን ተከትለው ሌሎቹም ኬልቄዶናውያን በልዩ ልዩ ምክንያት እንደዚሁ የመወከሉን መንገድ መረጡ ። ይህ የጥሪ ውጤት እንደ ታወቀ የስብሰባው ጥንተ ዓላማ መሪዎችን ለማገናኘት እንጂ ወኪሎችን ለመሰብሰብ ስላልነበረ ፤ የጉባኤው አደራጆች ጠቅላላ አስተያየት ፤ በግንቦትና በሚያዝያ ፲፱፻፶፯ ዓ· ም· ታስቦ ወደ ነበረው የተዋሕዶ መሪዎችን ብቻ ወደ መጥራት አሳብ ተመለሰ ። ስለብዙ ነገር ይህም አሳብ መልካም ሆነ ። መልካም የሆነበትም ይህ ነው ። አንደኛ ፤ ኬልቄዶናውያንና ተዋሕዶዎች የዛሬ ፩ሺ፭፻፲፭ ዓመት አባቶቻቸው በውግዘት የተለያዩ ፤ ከዚያም ወዲህ




www.ethiopianorthodox.org

ሳይገናኙ የኖሩ ፤ ዛሬ ድንገት በአንድ ጉባኤ ቢቀመጡ እንዲያው በጨዋነት ተያይቶ ለመበታተን ወይም አደገኛ ጭቅጭቅ ለማንሣት እንጂ ፍሬ ነገር ለመወያየት አይሆንም ሲሉ አሰቡ ። ስለዚህም በተዋሕዶዎች በኩል ሁለት የአሳብ ዝንባሌዎች መጥተው ነበር ። ማለት ብዙዎች ተዋሕዶዎች መጠራት ከአለባቸው ደኅና ነው ይጠሩ ። ነገር ግን ለብቻቸው ይሰብሰቡ ሲሉ አንዳንድ ተዋሕዶዎች ደግሞ መለካውያንም የሚጠሩ ከሆነ በስብሰባው ላንገኝ ነው ብለው መለሱ ። በመጨረሻ ይህን ሁኔታ ለማስተካከል በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ጳጳስ የሆኑት አቡነ ፊልጶስና አባ ፖል በርጊስ አዲስ መልእክት ይዘው ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ሔደዋል ።

## ጉ ባ ኤ ው

ከዚህ በኋላ የጉባኤው ተሳታፊዎች ፓትርያርኮች ማለት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ አግናጥዮስ ሣልሳይ የአንጾኪያው ፓትርያርክ ፤ ብፁዕ ወቅዱስ ባስኪን ቀዳማዊ የመላው አርመን ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ካቶሊኮስ ፤ ብፁዕ ወቅዱስ ኮሬን ቀዳማዊ የታላቂቷ ቤተ ኪልቂያ ካቶሊኮስ ፤ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ አውገን ቀዳማዊ የምሥራቅ ካቶሊኮስ (ሕንድ) ከነተከታዮቻቸው በጊዜ ቀጠሮአቸው አዲስ አበባ ገቡ ። ሲገቡም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ልዑል አልጋ ወራሽ ፤ በብፁዕ ወቅዱስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ስም ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስና ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ኢንተርናሺናል አይሮፕላን ጣቢያ ድረስ ሔደው ተቀበሏቸው።ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ ስድስተኛ የእስክንድርያው ፓፓና የመንበረ ማርቆስ ፓትርያርክ አዲስ አበባ የገቡት ስብሰባው በተጀመረ ማግሥት ነው።

ስብሰባው ጥር ፲፯ ቀን ፲፱፻፶፯ ዓ፦ ም፦ ከጠዋቱ በአራት ሰዓት በአፍሪካ አዳራሽ ተከፈተ ። ሲከፈትም ግርማዊ ጃንሆይ ፤ ልዑል አልጋ ወራሽ



ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ጉባኤ ላይ የመክፈቻ ንግግር ሲያደርጉ



www.ethiopianorthodox.org

መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ፣ ብፁዓን ወቅዱሳን ፓትሪያርኮች ፣ ልዑላንና ልዑላት ፣ እንዲሁም ክቡራን ሚኒስትሮች ፣ ኮር ዲፕሎማቲኮች ፣ የእኒሁ አብያተ ክርስቲያናት መልእክተኞችና እንዲሁም የውጪና የልዩ ልዩ ቤተ ክርስቲያን ወኪሎች በተመልካችነት ፣ የሀገር ውስጥ ጋዜጠኞች ነበሩ።

በአከፋፈቱ ሥነ ሥርዓት ፣ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ አግናጥዮስ ሚልሳይ ቡራኬ በኋላ የግርማዊ ጃንሆይ የመክፈቻ ንግግር ተሰማ ። እንደዚሁም የፓትሪያርኮቹ በሱርስት ፣ በአርመንኛ ፣ በእንግሊዝኛና በአማርኛ የተሰጡ መልሶች ተሰሙ ። የመክፈቻው ሥነ ሥርዓት እዚህ ላይ በጸሎት ተፈጸመ ። ነገር ግን ሁለት ፓትሪያርኮች ፣ ሦስት ካቶሊኮሶች ፣ አንድ እንደራሴ በትሪያርክና ከአምስት ልዩ ልዩ ነገዶች የሆኑ ፣ ከአምስት አህጉር የመጡ አራት ልዩ ልዩ ቋንቋዎች የሚናገሩ ፣ ነገር ግን በአንዲት ተዋሕዶ ሃይማኖት የሚያምኑ ሠላሳ አምስት ተከታዮቻቸው የአሉበት የአሥር ቀናት ጉባኤ ቀጠለ ።

ይህ ስብሰባ ከጥር ሦስት እስከ ጥር ስምንት ፲፱፻፶፯ ዓ· ም· የቆየ የአምስት ቀናት ዋዜማ ነበረው ። በዚህ የዋዜማ ጊዜ ውስጥ ከእነዚህ የተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት የተላኩ ሁለት ሁለት መንፈሳውያን ሊቃውንት ፣ ጉባኤ ዋዜማ በተባለው ስብሰባ ተገኝተው አሥራ አራት ገጽ የሚሆን የጉባኤውን ዝርዝር መርሐ ግብር አዘጋጅተዋል ። እንግዲህ ጉባኤው ደንበኛ ሥራውን የቀጠለው በዚህ ጽሑፍ መሠረት ነው ። በአሠራሩም ይህ ጽሑፍ መሥመር በመሥመር እየተነበበ ያልተፈለጉ አሳቦች ወደቁ ። የተረሱ አሳቦች ተጨመሩ ። አንዳንድ አሳቦች ደግሞ አቀራረባቸው ተለወጠ ። በዚህ ክርክር ሊቀ መንበሩ ክቡር አቶ አበበ ረታ ፣ ዋና ጸሐፊውም ክቡር አቶ አበራ ጀንበሬ ነበሩ ።

እዚህ ላይ ጉባኤው ገና ሥራውን በደንብ ሳይጀምር አንድ ከመርሐ ግብሩ ውጪ የሆነ በጉባኤ ዋዜማም ተነሥቶ የነበር አስቸጋሪ ክርክር ተነሣ፤ ክርክሩም የጉባኤው ተሳታፊዎች የልዑካን ቡድኖች አምስት ናቸው ወይስ ስድስት ? የሚል ነበር ፣

«ነገር ከሥሩ ፣ ውኃ ከጥሩ» እንደሚባለው ፣ ይህን ክርክር ለመረዳት በእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ ውስጥ ጥቂት ዓመታት ወደኋላ መሔድ ያስፈልጋል ። ምናልባት ከአንድ ሻያ ፣ ሠላሳ ዓመታት በፊት የእነዚህ አብያተ ክርስቲናት ቁጥር በጣም በጠቅላላ አነጋገር ሦስት ነበሩ ፣ እነዚህም የግብፅ ኦርቶዶክስ ፣ የሶሪያ ኦርቶዶክስና የአርመን ኦርቶዶክስ ናቸው ። እንደዚህም የሚሆን ፣ የሕንድ ቤተ ክርስቲያን ከሶሪያ ቤተ ክርስቲያን ጋርና የኢትዮጵያም ቤተ ክርስቲያ ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ጋር ስትቈጠር ነው ።

ስለዚህ ጉዳይ ፣ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ አግናጥዮስ እ· ኤ· አ· ነሐሴ ፯/፲፱፻፷፬ ዓ· ም· ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በጻፉት ደብዳቤ ፣ ማር ጎርጎርዮስ ባር ሔብራያ የተባለው የምሥራቅ ካቶሊኮስ በመጽሐፈ ቀኖናው (ስለ ቤተ ክርስቲያን ሕግጋት በጻፈው መጽሐፉ) የተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናትን የሶሪያ ፣ የቅብጥ ፣ የአርመንና የኢትዮጵያ ብሎ በአራት ብቻ እንደሚወስናቸው ይጠቅሳሉ።

ሆኖም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የእነዚህን አብያተ ክርስቲያናት ቁጥር የሚለውጥ አንድ የሆነ ነገር አለ ። ለምሳሌ ፣ የሕንድ ቤተ ክርስቲያን ከ፲፱፻፶ ዓ· ም· ጀምሮ በስምምነት የራስዋን ካቶሊኮስ በማግኘት እራስዋን ችላለች ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም ከ፲፱፻፶፩ ዓ· ም· ጀምሮ የራስዋ ፓትርያርክ ስለኖራት ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን ቀንበር ወጥታለች ። ይህም ለውጥ የእነዚህን አብያተ ክርስቲያናት ቁጥር አምስት ያደርገዋል ። በዚህም ሰው ሁሉ ተስማምቷል ።

ስምምነት የጠፋው ስድስተኛው ቁጥር ላይ ነው ። ለዚህ ስድስተኛው ቁጥር ተሟጋች የሆነው ዛሬ መንበሩ በቤይሩት አጠገብ በሚገኘው አንቴሊያንስ በሚባለው ዳር መንደር የሚገኘው ፓትርያርክ ፣ ግን የኪልቂያው እየተባለ የሚጠራው የአርመን ኦርቶዶክስ ካቶሊኮስ ነው ። ዛሬ ይህን መንበር የያዙት ካቶሊኮስ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቮሬን ቀዳማዊ ይባላሉ ። ይህን ስድስተኛ ቁጥር የሚቃወም ደግሞ በኤችሚያድዜን (አርመንያ) የመላው አርመን ኦርቶዶክሶች ጠቅላይ ካቶሊኮስ ነው ። ዛሬ



www.ethiopianorthodox.org

ይህን መንበር የያዙት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስኬን ቀዳማዊ ናቸው ።

በጉባኤው እነዚህ ሁለቱም ተገኝተው ነበር ፤ ከእነዚህም የኬልቂያው ካቶሊኮስ እንዲጠሩ ምክ ንያት ከሆኑት ነገሮች አንዱ ከተዋሕዶ ፓትሪያ ርኮች አንዱ የኬልቂያው ካቶሊኮስ አለመጠራት በጉባኤው ላለመሳተፋችን ምክንያት ሊሆን ይች ላል ያሉት ነው ።

የሆነ ሁኖ ይህ ጥያቄ ለጊዜው ለጉባኤው እንቅፋት እንዳይሆን ያህል አንድ ፍቺ ተሰጠው ወደፊት ግን አንድ ዘላቂ ነገር እንዲገኝለት ተስፋ እናደርጋለን ።

ይህን ካመለከትን ዘንድ ወደፍሬ ነገራችን እንመለስና ፤ ይህ ድንገት የመጣ ችግር ፤ አንድ ዓይነት ፍቺ እንዳገኘ ጉባኤው ወደሥራው ተመ ለሰ ። በሥራውም መርሐ ግብሩን እየተከተለ የሚ ከተሉትን ትልልቅ አርእስት ተራ በተራ አጠና ።

፩/ ቤተ ክርስቲያንና ዘመናዊው ዓለም ፤
፪/ በመንፈሳዊ ትምህርት አሰጣጥ ስለመተባበር ፤
፫/ በስብከተ ወንጌል ሥራ ስለ መተባበር ፤
፬/ የአብያተ ክርስቲያናት ግንኙነት ፤
፭/ ለጉባኤው የጽ/ቤት ስለማቋቋም ፤
፮/ የዓለም ሰላም ፤

በያንዳንዱ በእነዚህ አርእስት ብዙ ዝርዝር ነገሮች ፤ የአሳብ ውሳኔ ተሰጥቶባቸዋል ። ለምሳሌ በአንደኛው ፩/ ስለወጣቶች ፤ ፪/ የሰውን ልጅ ከቤተ ክርስቲያን ሕይወት ጋር ስለማዋሐድ ፤ ፫/ ስለቤተ ሰብ ኑሮና መንፈሳዊ ተሐድሶ ፤ ፬/ ስለ ክርስትና ትምህርት ፤ ፭/ ስለምንኩስና ኑሮ ፤ ፮/ ስለቤተ ክር ስቲያን አስተዳደርና ፯/ ስለቤተ ክርስቲያን ቀን አቈጣጠር ጉዳይ ተጠንቷል ።

እንደዚሁም በሁለተኛው ምዕራፍ ፩/ ስለመ ንፈሳዊ ትምህርት ይዞታ ፤ ፪/ ስለጋራ ሥርዓተ ትምህርት ፤ ፫/ ስለመተባበር ዘዴዎች ፤ ፬/ ወደ ውጭ አገር ሔዶ ስለመማርና ፭/ ስለመንፈሳዊ ትም ህርት መጻሕፍት ተዘርዝረዋል ።

በሦስተኛ ምዕራፍ ደግሞ ፩/ ስለሐዋርያዊ ተግባር መሠረታዊ ዓላማ ፤ ፪/ ስለጸሎትና ሐዋር ያዊ ሥራ ፤ ፫/ ስለሐዋርያዊ ሥራ መንፈሳዊ ኑሮን ስለማጠንከር ፤ ፬/ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ላሉ ስለ ሚደረግ ስብከተ ወንጌል ፤ ፭/ ስለስብከተ ወንጌል ዘዴዎችና ፮/ ስለሰባኪያን ማሠልጠን ጉዳይ ተጠና ።

በአራተኛው ፤ በአምስተኛውና በስድስተኛው ምዕራፎች እጅግም ብዙ ዝርዝር ውስጥ ሳይገባ አርእስቶችን ተከትሎ ጥናቱ ተፈጸመ ።

በጽሕፈት ቤቱ በኩል የሚቀጥሉትን አንዳ ንድ ነጥቦች መጥቀስ አይከፋም ። በዚህ ረገድ ጉባ ኤው አንደኛ ከራሱ ቀጥሎ ተጠያቂ የሚሆን ከየ አባል አብያተ ክርስቲያናት ሁለት ሁለት አባ ሎች ያሉበት አንድ ቀዋሚ ኮሚቴ አቆመ ። ሁለ ተኛ ጽሕፈት ቤቱ ጊዜያዊ በሚል ቅጽል ተሰጥ ቶት በአዲስ አበባ እንዲሆን አደረገ ። ሦስተኛ ፤ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መልካም ፈቃድ የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ኢትዮጵያዊ ሆኖም ጽሕፈት ቤቱ ቀዋሚ ሆኖ ለሥራው የሚያስፈል ገውንም ወጪ በአባሎች አስተዋጽኦ ገንዘብ እስ ኪሆን ድረስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክር ቲያን እንድትችል ተደረገ ።

ከዚህ በኋላ ጉባኤው በተቀዳሚ ግርማዊ ጃን ሆይን፤ ከዚያም ጉባኤውን በማደራጀት ያገለገሉትን ወሮታ የሚያሳስቡ ሦስት ልዩ ውሳኔዎች አወጣ ።

ከእነዚህ ከሦስት ውሳኔዎች አንዱ ፤ ግርማዊ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን የሃይማኖት ጋሻ ሲል ያውጃል ። ኤንሳይክሎፔዲያ ብሪታኒካ እንደ ሚጽፈው « - - - ይህ የሃይማኖት ጋሻ በላቲን FIDEI DEFENSOR የሚል ሥያሜ መጀመ ሪያ የተሰጠ በእንግሊዝ ንጉሥ ለኼንሪ ስምንተኛ ነው ። ሰጭው የሮሙ ፓፓ ሊዎ አሥረኛ ናቸው ። ንጉ ሡ እንዲህ የተሰየመውም ሉተርን በመቃወም ASSERTIO SEPTEM SACRAMENTORION ሰባቱን ምሥጢራት ማረጋገጥ የሚል መጽሐፍ ስለጻፈ ነው ። ይህንም የሚያትተው የሚስጢር ወረ ቀት BULL የተጻፈ እ. ኤ. አ. በ፲፭፻፳፩ ዓ. ም. ነው ። አሁንም እ. ኤ. አ. በ፲፭፻፵፬ ዓ. ም. ይህንኑ "FIDEI DEFENSOR" (የሃይማኖት ጋሻ) የሚል ስያሜ የእንግሊዝ ፓርላማ በጊዜው ለነበረው ኼንሪ



www.ethiopianorthodox.org

ለሚባለው ንጉሥ ሰጥቶታል ። ከዚያም ወዲህ ስያሜው ይኸው እስከዛሬ ድረስ የእንግሊዝ ነገሥታት ተጨማሪ ንጉሣዊ ቅጽል ሆኖ ይኖራል። መሰል ስሞች ለፈረንሣይ ነገሥታት ይሰጥ የነበረው "CHRISTIANISSIMUS" (የክርስቲያኖች ክርስቲያንና) ለእስፓኝ ነገሥታት ይሰጥ የነበረው SATHOLICUS የሚባሉት ናቸው ። በቢዛንስ ዓለም ቢበዛ ያው በሰዓተ ጸሎተ ቁርባን «እቀቦ ለንጉሥነ እግዚ» ተብሎ ይጸለያል እንጂ ፤ እንዲህ ያለ ስያሜ የለም ። ለክርስትና ሃይማኖት ስለአደረገው ግን ፤ ትልቁ ቈስጠንጢኖስ ብቻ « ከሐዋርያት እንደ አንዱ» (ኢሳአፓስቶሎስ) ተብሎ ተሰይሟል ።

ከጉባኤው ወዲህና ወደፊት ።

ጉባኤው ከተፈጸመ ከጥር ፲፰ ቀን ፲፱፻፶፯ ዓ· ም· ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ አሥራ አራት ወር ሆኗል ። እና አሁን ጥያቄዎቹ በእነዚህ አሥራ አራት ወራት ፤ በዚህ በምሥራቅ ኦርቶዶክስ ጉባኤ ስም ምን ተደረገ ? ወደፊትስ ምን ታስቧል ? የሚሉ ናቸው ። የእነዚህ የሁለቱም ጥያቄዎች መልስ ባጭሩ ሊነገር ይቻላል ።

ከፍ ብሎ እንደ ተመለከተው ፤ ጉባኤው ቃል ጠቅ ብሎ ለሥራው የሚያስብ ቀዋሚ ኮሚቴ ፈጥሯል ። ስለዚህ ጉባኤው እንዳለቀ ይህ ኮሚቴ ከጥር ፲፰ እስከ ፳፬ ቀን ፲፱፻፶፯ ዓ· ም· አዲስ አበባ ላይ ከቅድስት ማርያም አቅራቢያ በወይዘሮ ወለተ ዮሐንስ መንገድ በሚገኘው የጉባኤው ጽ/ቤት የመጀመሪያውን ስብሰባ አደረገ ። በዚህም ስብሰባ የኮሚቴው ሊቀ መንበርና ሁለት ምክትል ሊቀ መናብርት ተመረጡ ። ለጽሕፈት ቤቱም ለጊዜው የሚያገለግል የሥራ መምሪያ ተሰጠ ። እንደዚሁም ጠቅላላው የጉባኤው ሥራ ሰባት ኮሚቴ ለአንድ ለሠላሳ ልዩ ልዩ ሰዎች ተከፋፈለ ። ኮሚቴዎቹ ቀጥለው የተዘረዘሩት ናቸው ።

፩/ የእምነትን ጉዳይ የሚያጠና ኮሚቴ ፤

፪/ ሥርዓተ ጸሎትንና በጠቅላላ ሃይማኖታዊ ልምዶችን ለዘመኑ እንዲስማሙ ለማድረግ የሚሠራ ኮሚቴ ፤

፫/ የትምህርት ፕሮግራም ኮሚቴ ፤

፬/ የቀን አቈጣጠር ኮሚቴ ፤

፭/ የኢንዱስትሪንና የከተማን ኑሮ መለዋወጥ አጥኝ ኮሚቴ ፤

፮/ ከፍተኛ የመንፈሳዊ ትምህርት ቤትና የወንጌል ሰባክያን ማሠልጠኛ ኮሚቴ ፤

፯/ የአብያተ ክርስቲያናት አንድነት ኮሚቴ ፤

፰/ የጉባኤውን ሕገ ማኅበር አጥኝ ኮሚቴ ፤

፱/ የጉባኤው መጽሔት ቦርድ ፤

ለዚህ ሁሉ ሥራ ዋና መሣሪያ ተብሎ የተቈጠረ የጽሕፈት ቤቱ ነው ። ይህም ጽሕፈት ቤት በአደራው መሠረት ጉባኤውን ነክ የሆኑ ጽሑፎችን አጠረቃቅሞ ፤ ጠርዞ ፤ ለየሰዎቹ በመላክና እንዲሁም በማስቀመጥ ፤ ልዩ ልዩ ሥራ ከተሰጣቸው በየአባል አብያተ ክርስቲያናት ሀገሮች ከተሰራጩት ሰዎች ጋር በመጻጻፍና አገናኝ መኰንን በመሆን ፤ በጠቅላላም የጉባኤውን ሥራ በመሰለው መንገድ በማደራጀት ሠርቷል ። ሆኖም ይህ የሥራ ራፖር አይደለምና ከዝርዝር ውስጥ አልገባም ።

ይህ ጽሕፈት ቤት በጊዜያዊ መልኩ ሊቀጥል የነበረ እስከ ሐምሌ ፲፱፻፶፯ ዓ· ም· ድረስ ነበር ። ነገር ግን ስለልዩ ልዩ ምክንያት በጊዜ ቀጠሮው ጊዜያዊ ባሕርዩን ሊለውጥ አልቻለም ።

ይህም ሁኔታ ምክንያት ሆኖ ነሐሴ ማለቂያ ገደማ በ፲፱፻፶፯ ዓ· ም· የቀዋሚ ኮሚቴ ፕሬዚዴንት ፤ ዋናው ጸሐፊና ሁለት ሌሎች አባሎች የተሳተፉበት አንድ የአድሚኒስትራሲዮን ኮሚቴ አዲስ አበባ ላይ ስብሰባ አድርጎ ፤ አንደኛ ልዩ ልዩ እርምጃዎችን በመውሰድ ጽሕፈት ቤቱ ቀዋሚ የሚሆንበትን ጊዜ በጊዜው ጥር ፲፱፻፶፰ ዓ· ም· ካይሮ ላይ እንዲደረግ ታስቦ የነበረው ፤ ሁለተኛ የጉባኤው ቀዋሚ ኮሚቴ እንዲወስነው በቀጠሮ አስቀመጠው ። ሁለተኛ ለዚሁ ለተጠቀሰው ሁለተኛ ስብሰባ ቦታና ጊዜውን በመወሰን መርሐ ግብሩን በማዘጋጀት የቻለውን አደረገ ።

አሁን ይኸው የካይሮ ሁለተኛ የጉባኤው ቀዋሚ ኮሚቴ ስብሰባ አለፈ ። ነገር ግን ጽሕፈ



www.ethiopianorthodox.org

ቤቱ ገና እስከ ነሐሴ ፲፱፻፶፰ ዓ. ም. ድረስ በዚሁ በጊዜያዊ መልኩ ሊቀጥል ነው ።

ከነሐሴ ፲፱፻፶፰ ዓ. ም. በኋላ ግን በካይሮ ውሳኔ መሠረት ጽሕፈት ቤቱ ቀዋሚ ይሆናል ። የጽሕፈት ቤቱንም ሥራ ዋናው ጸሐፊ እንደቀድሞው ሙሉ ጊዜ በመሥራት ፈንታ በሌላ ሥራ ላይ ተደራቢ አድርጎ ይሠራዋል ። ይህም ሁኔታ እስከ የካቲት ፲፱፻፶፱ ዓ. ም. ይቀጥላል ። ይህ የቀዋሚው ኮሚቴ ሦስተኛ የስብሰባ ጊዜ ቀጠሮ ነው እስከዚህም እስከ ታሰበው ሦስተኛ ጉባኤ ያለው ጊዜ ባለፈው ሁለተኛ ስብሰባ የተሰጡት ልዩ ልዩ ውሳኔዎችና የተላለፈውም ሕገ ማኅበር በእርግጥ በሥራ ሊውል ይችል እንደሁ ለማየት ጥሩ የሙከራ ጊዜ ይሆናል ።

በመሠረቱ እስከ ነሐሴ ፲፱፻፶፰ ዓ. ም. የጉባኤው ሥራ እስከ አሁንም እንደ ነበረው በማንኛቸውም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዕዳ ሆኖ ሊቆይ ነው ። ይህ ዕዳ የሚለው ቃል ግን በፊደል ከሚጻፍ ይልቅ በአኃዝ ቢሆን በተሻለ ሊሰው ይገባልና ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ባለፉት አሥራ አራት ወራት ውስጥ በዚህ ጉባኤ ስም ያወጣቻውን ወጪ ቀጥሎ በተመለከተው ሠንጠረዥ አመለክታለሁ ። ስለሒሳቡ ትክክለኛነት የቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤቱን ሒሳብ የሚመረምሩ ኦዲተሮች ስለአሸጉበት አንዳንድ አስረጂ ጽሑፎች በቀላል ለመገኘት ሳይችሉ ቀርተው ፤ እዚህ የሰጠሁት ቁጥር ሒሳቡን ሳያሳንሰው አልቀረም ። ሁለተኛ ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ስም ለዚህ ጉባኤ ወጪ ከሆነው ምን ያህሉ እንደተከፈለና ምን ያህሉ በዕዳ እንዳለ ላጣራ አልቻልኩም ። ሆኖም ይህም እያደር ሊጣራ ይቻላል።ፍሬ ነገሩ ግን ቤተ ክርስቲያን ለዚህ ጉባኤ በጠቅላላ መልኩ ምን ያህል እንዳወጣች መታወቁ ነው

| ተ/ቁ | የወጪ ምክንያት | ከኢትዮጵያ |
|---|---|---|
| ፩/ | የግርማዊ ጃንሆይን ንጉሣዊ መልእክት ላደረሱ መልእክተኞች የጉዞ ወጪ | $. 6727.50 |
| ፪/ | ለጉባኤው ተሳታፊዎች የአይሮፕላን ወጪ | $.42,000.00 |
| ፫/ | ለስብሰባው የማደራጃና የመስተንግዶ ወጪ | $. 52914.43 |
| ፬/ | ለቢሮ ዕቃ መግዣ ወጪ | $. 3880.00 |
| ፭/ | ለስልክ ማስገቢያ | $. 530.00 |
| ፮/ | ባለፉት አሥራ አራት ወራት ለጽ/ቤቱ ሠራተኞች ደመወዝ ፤ ለአልዋንስ ለፖስታ መላኪያ ፤ ለቴሌግራም ፤ ለጽሕፈት መሣሪያና ለልዩ ልዩ ሥራ | $. 12,885.83 |
| ፯/ | ለቴሌፎን ፤ ለመብራት ፤ ለውኃና ለፖስታ ሣጥን ኪራይ | $. 738.75 |
| ፰/ | በባንክ ያለ ሒሳብ | $. 2606.47 |
| | ድምር | $. 122,282.98 |

(አንድ መቶ ሀያ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሰማንያ ሁለት ብር ከዘጠና ስምንት ሳንቲም ብቻ) ።

### መደምደሚያ ሃሳብ ።

ቀጥሎ የተመለከቱትን አንዳንድ አሳቦች በአንድ በኩል በጋዜጦቻችን ነፃ ዐምዶች በሚባሉት እንደሚሠፍሩት አሳቦች ዓይነት አድርገን እንቈጠራቸው ። በዚህም ዓይነት በአሳባችን ወደፊት ለመግፋት ከሁሉ አስቀድሞ ይህ ታሪካዊ ጉባዔ የተደረገላቸው እነዚህ የምስራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናትን ከኖሩበት ዛሬም ከሚኖሩበት የጂኦግራፊ አቀማመጥ የማኅበራዊ አካባቢና በጠቅላላ ከፖለቲካ ፤ ከኤኮኖሚና ከትምህርት ሥልጣኔ ደረጃቸው ጋር አስታኮ በዓይነ ልቡና መመልከት ያስፈልጋል ።

ነገሩን በዚህ አኳኋን ስንመለከተው ፤ ከእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት የአርመን ብቻ ስትቀር የቀሩት ሁሉም ምሥራቃውያን ናቸው ። ምሥራቅ ደግሞ እንደሚታወቀው ፤ የሃይማኖት ክፍል



www.ethiopianorthodox.org

ዓለም ናት ። በተጨማሪ እነዚህ አብያተክር ስቲያናት የሚገኙባቸው የአፍሪቃና የእስያ ክፍል የሆኑ አገሮች በአዲሱ የኤኮኖሚና የኢንዱስትሪ ቋንቋ በመሠልጠን ላይ ያሉ የሚባሉ ሀገሮች ናቸው ። በእንደዚህ ያለው ሁኔታ ውስጥ የእነዚህ መሪዎች ተገናኝቶ በውሳኔያቸው እንዳደረጉት ፤ በጉባኤ የአብያተ ክርስቲያኑና ፤ ዋና ዋና ሥራ ሊስት ማውጣት ፤ እያንዳንዱንም አርእስት በዝርዝር ማጥ ናትና ቀዋሚ ኮሚቴ መሾም ፤ ጽሕፈት ቤትም ማቋ ቋም የምሥራቃውያንን የሃይማኖት ኑሮ በስሜት ብቻ ሳይሆን በአእምሮም ጭምር ለመምራት የተ ነሡበት ይመስላል ።

በዚህ ረገድ በኢትዮጵያ ሥጋዊ ታሪክ በት ውልዳችን አንድ አዲስ ነገር ምንድነው ? ተብሎ ቢጠየቅ ፤ እንደሚመስለኝ ይህ የአምስት ዓመት ፕላን የሚባለው ነገር ነው ። እና ይኸው ጉባኤ የሾው ቀዋሚ ኮሚቴ ለምሳሌ ፤ የእንዱስትሪ መስፋፋት ፤ የከተማዎች ማደግና በጠቅላላ የዘመ ናዊው ሥልጣኔ ፤ የሰውን ልጅ ሕይወት እንዴት እንደሚጫነው ፤ እንዴትስ እንደሚነካውና እንደሚ ለውጠው ለማወቅ ጥናት ሲያቅድ የፕላንን ነገር ያሰበበት ይመስላል ። ሆኖም ባለፈው የቀዋሚው ኮሚቴ የካይሮ ስብሰባ ላይ የነበሩ አንድ አሜሪ ካዊ ፤ ስለተሰብሳቢዎቹ በግል አስተያየት ሲሰጡ "you are just starting to walk together" «ዩ አር ጀስት እስታርቲንግ ቱ ዎክ ቱጌዘር» እንዳ ሉት ፤ ይህን ፕላን በኅብረት ሆኖ በሥራ ለማዋል ገና ብዙ ይጠይቃል ።

ጥቂት ተጨማሪ ንባብ ።

ጥቂት ተጨማሪ ንባብ ለማድረግ ያህል ፤ ከሌ ሎች መጻሕፍት ጋር የሚከተሉትንም መመልከት አይከፋም ።

The Oriental Orthodox Churches, Addis Ababa Conference January 1965. Edited by the Interim Secretariat. Artistic Printing Press, Addis Ababa, August 1965.

፪/ የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያ ናት መሪዎች ጉባኤ የሰጣቸው ውሳኔዎች ፤ ትን ሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ፤ አዲስ አበባ መስከ ረም ፲፱፻፶፯ ዓ· ም· ፤

፫/ ዲያስኬፕሲስ አናቶሊኮን ኦርቶዶክስን ኢክሉሲዮን ፤ ክብፁዕ አቡነ ኒኮላዎስ አቴና እ ኤ ቁ/ ፲፱፻፷፭ ዓ ም ስለጉባኤው በግሪክኛ የተጻፈ ።

፬· በየአባል አብያተ ክርስቲያናት ጋዜጦችና መጽሔቶች ፤ በጉባኤው ጊዜ ስለጉባኤው የተጻፉ ጽሑፎች በዓረብኛ፤ በአርመንኛ፤ በአማርኛ ይገኛሉ።


5. ኢንሳይክሎፔዲያ ብሪታኒካ ፤ 23ኛው እትም ፤ (Defender of Faith) የሚለውን ይመ ልከቱ ።

ሰይፉ መታፈሪያ



www.ethiopianorthodox.org

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት አቋምና ሥራ



የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት ጽሕፈት ቤት

ኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ የራሷ የሆነ ባህልና ሥርዓት ያላት ጥንታዊት ሀገር እንደመሆኑዋ መጠን ሕዝቧም ጥንታዊና ታሪካዊ ሕዝብ ነው በእግዚአብሔርም ያለው እምነት እንደዚሁ ጥንታዊ ነው ። በኦሪት ዘመንም እንደ እሥራኤል በአንድ እግዚአብሔር አምኖና ሕገ እግዚአብሔርን ጠብቆ የኖረ ታላቅ ሕዝብ ነው በሐዲስ ኪዳንም ከመጀመሪያው መቶ ዘመን አንሥቶ በክርስትና ሃይማኖት ጸንቶ በመገኘቱ መንግሥታችን የክርስቲያን መንግሥት ሲባል አገራችንም የክርስቲያን ደሴት ስትባል ትኖራለች ።

ኢትዮጵያ ስለክርስቶስ ያላት እምነትና ትምህርት ጥንታዊ መሆኑ በታሪክ መልክ ቢያስደስትም የሥራው እርምጃና ፕሮግራም ጊዜ በሚፈቅደው መልክ እየተዘጋጀ ጊዜውን ተከትሎ መሥራት እንዳለበትና ከሕዝብ ጋር በትብብር መካፈልና መሥራት አስፈላጊ በመሆኑ በአዲስ አቅድ በአዲስ መንፈስ ከላይ በተዘረዘረው አኳኋን ለመሥራት ይህ ሐዋርያዊ ድርጅት ተቋቋመ ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ

የበላይ ጠባቂነት በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሥር በመካሔድ በ፷፫ሺ (ስድሳ ሦስት ሺህ ብር) የዓመት ባጀት ራሱን ችሎ በቦርድ እየተመራ እንዲሠራ መስከረም ፲፰ ቀን ፲፱፻ ፶፯ ዓ/ም/በአዲስ አበባ ከተማ ተቋቋመ ።

ሥርዓትና ባሕል እንግዳ ስለማይሆንበት በቀላሉ በበለጠ እንደሚረዳ በማመን ፤

ለ/ ክርስቲያኑን ሕዝብ ለማጽናት ።

የጊዜና የአካባቢ ለውጥ በማኅበራዊ ኑሮ በትምህርት በኤኮኖሚ እድገት መለዋወጥና በየ



የድርጅቱን ከፍተኛ ጉዳዮች የሚወስኑት የቦርድ አባሎች

<u>ድርጅቱም የተቋቋመባቸው መሠረታዊ ዓላማች ፤</u>

ሀ/ ከክርስትና ውጭ የሆኑትን ሕዝቦች ወደ ክርስትና ለመመለስ ፤ ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ጥንታዊ የክርስቲያን ሀገር ብትሆንም በልዩ ልዩ ምክንያት እስከ አሁን ድረስ ስብከተ ወንጌልን ለማዳረስና ሁሉንም ለማጥመቅ ባለመቻሏ በሀገሪቱ ውስጥ አያሌ ሰዎች ከክርስትና ውጭ ስለሚገኙና ከውጭ ሀገርም ከሚመጡ ሚሲዮኖች ይልቅ ይህ የሀገሩ ሚስዮን በሀገሩ ሠራተኞች ለሀገሩ ሕዝብ የበለጠ ጥቅም ለመስጠት እንደሚችልና የብሔራዊቱም ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖት

ጊዜውም የሚመጡ አዳዲስ አሳቦች ፤ ሃይማኖቶች፤ ወደ ሀገራችን በመግባታቸው የጥንቱ ክርስቲያን ሕዝብ ከጥንቱ ኑሮው ለየት እያለ በመሔዱ መንፈሱም እንደዚሁ እየዋለለ ሊሔድ ችሏል ። በዚህም ምክንያት በመሸጋገሪያ ዘመን ያለው ሕዝብ የያዘውን ሃይማኖት ጠንቅቆ በበለጠ እንዲያውቅና እንዲጠብቅ የማጽናት ትምህርት በዘመናዊ ምሳሌና የትምህርት አቅድ የቀለጠፈ ትምህርት ካላገኘ ቀስ በቀስ ቤተ ክርስቲያናችንን የሚርቅ መሆኑን በመገንዘብ የዚህ ድርጅት መቋቋም አስፈላጊ ሆኖ ተገኘ ።



www.ethiopianorthodox.org

ሐ/ የከተማውን ሕዝብ ለመጠበቅ ፤

የከተማ ኑሮ ከገጠሩ ኑሮ እየተሻሻለ በመሔዱና ከተማዎችም የትምህርትም ሆነ የሥራ የንግድ የሕክምና ምንጭ ሆነው በመገኘታቸው የገጠሩ ሕዝብ በነዚህና በሌሎችም ልዩ ልዩ ምክንያቶች ወደ ከተማ በብዛት ይጐርፋል ። በዚህም ምክንያት የከተማው ሕዝብ ቁጥር እየጨመረ ይሔዳል ። በየቦታውም ወደ ከተማው የሚጐርፈው ሕዝብ በመሠረቱ በጐሣ በባሕል ባኗኗርና በጠባይ ከተለያየ ምንጭ የወጣ በመሆኑ ልዩ ልዩ የማኅበራዊ ኑሮና የሞራል ችግሮችን ይፈጥራል ። ይህም የማኅበራዊ ኑሮና የሞራል ችግርን በየጊዜው ካልተቋቋሙት ለከተማው ሕዝብ ኅብረተሰብ ጎጂ በመሆኑ ታማኝና ጀግና ሃይማኖታዊ ትውልድ ሲያልፍ ተመሳሳዩ ትውልድ እንዲተካ የከተማ ሐዋርያ በማስፈለጉ ፤

መ/ ከኢትዮጵያ ውጭ ወንጌላውያንን ለመላክ

ኢትዮጵያ ጥንታዊት የክርስቲያን ሀገር በመሆኗ ብዙዎች የውጭ ሕዝቦች ይልቁንም ከአፍሪካውያንና ከሌሎች ጥቁሮች ሀገር ቤተ ክርስ ያን ሠርታ ሊቃውንት ልካ በመካከላቸው ሚስዮናዊ ተግባር እንድታከናውን በየጊተዜው ለቤተክርስቲያናችን ጥያቄ ያቀርባሉ ። ምንም እንኳን ከዚህ ቀደም በጥያቄው መሠረት አብያተ ክርስቲያናት አሠርታና ካህናትን ልካ በትሪንዳድ በቶባጎ ፤ በብሪቲሽ ጊኒና በኒውዮርክ በሱዳን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በመስጠት ላይ ብትሆንም ከዚህ የበለጠ ተጨማሪ ሐዋርያዊ ሥምሪት እንዲኖር ለማድረግ ፤

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ከግባቸው ለማድረስ የሚሠራባቸው የሥራ ክፍሎች ፤

ሀ/ የትምህርትና የማኅበራዊ ኑሮ አገልግሎት፤


ለ/ የድርሰትና የማስታወቂያ ፤

ሐ/ የሐዋርያት መልእክት ፤

መ/ የንብረት ክፍል ሲሆኑ ድርጅቱ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የሚከተሉትን የሥራ ፍሬዎች አሳይቷል ።

## የትምህርት ክፍል ፤

የትምህርት ክፍል ዘመናዊ ፤ መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶች የሚቋቋሙበትንና የሚስፋፉበትን መንገድ የሚያጠናና ከሥራ ላይ የሚያውል ፤ ለሚሲዮናዊ ተግባር ካህናትን የሚያሠለጥን ፤ በልዩ ልዩ መንገድ መንፈሳዊ ትምህርት የሚሰጥበትን ዘዴ የሚያጠናና በሥራ ላይ የሚያውል ሲሆን እስከ አሁን ከዚህ የሚከተሉትን ሥራዎች በመፈጸም ላይ ነው ።




አቶ አእምሮ ወንድም አገኘሁ የድርጅቱ
ተ/ ሥራ አስኪያጅ

ሀ/ በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል አካባቢ ፵ ዲያቆናትና ቀሳውስት ከመንፈሳዊ ትምህርት ጋር የአንደኛን ደረጃ ትምህርት እንዲማሩ አምስተኛ ክፍል ድረስ ያለው ትምህርት ቤት አሠርቷል ። ከዚህም ሌላ ድርጅቱ በየቦታው ቅርንጫፎችን ከማቋቋሙ በፊት ለ ሚስዮን ተግባር የሚውሉ መምህራንን ማዘጋጀት ስላለበት የሁለት ዓመት የመምራህን ማሠልጠኛ ኰርስ ከፍቶ በማሠልጠን ላይ ይገኛል ።

ይህን የትምህርት ክፍል ለማስፋፋት ከሕዝብ ጋር በሚያደርገው ትብብር ሕዝቡ «የእኛ» የሚል ማኅበራዊ ስሜት እንዲሰማውና በሥራ ተካፋይነትም እንዲበረታ ከሕዝብ ጋር በመተባበር ይሠራል ።



www.ethiopianorthodox.org



የድርጅቱ ሠራተኞች


በዚሁም መሠረት እማሆይ ደብሪቱ ጠቢቃቸው የተባሉ መነኰሲት በመናገሻ አውራጃ በርፈታ ወረዳ ለድርጅቱ በሰጡት አንድ አራት ክፍል ቤትና ኻያሺ ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ባለፈው ዓመት ያቋቋመው ትምህርት ቤት ስለጠበበ በተጨማሪ ድርጅቱ አንድ ሰፋ ያለ ትምህርት ቤት አሠርቶ ለጊዜው ፫፻ የአካባቢውን ሕዝብ ልጆች በማስተማር ላይ ይገኛል ። ይህም ትምህርት ቤት የካቲት ፲፫ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም/ በተመረቀበት ቀን የተማሪዎቹ ወላጆችና የአካባቢው ሕዝብ በእማሆይ ደብሪቱ ጠቢቃቸው መልካም አርአያነትና በድርጅቱም አገልግሎት በመደሰት ለጊዜው ፯፻ (ሰባት መቶ ብር) ለትምህርት ቤቱ ማስፋፊያ የረዱ ሲሆን ወደፊት የዚህን ት/ ቤት ዕድገት በቅርብ የሚከታተሉና የሚረዱ መሆናቸውን ገልጸዋል ። ድርጅቱም በትብብራቸው በመደሰት የአካባቢው ሕዝብ በማንኛውም ጊዜ የሚያደርገውን ማኅበራዊ ስብሰባ በዚህ ት/ቤት ግቢ እንዲያደርግ የትምህርት ቤቱን አዳራሽ ለሕዝብ አበርክቷል ።

በጎጃም ጠቅላይ ግዛት ከኢትዮጵያ ጠረፍ ቡለን ቀበሌ ለሁለተኛ ጊዜ የሕዝብ እንደራሴ ሆነው የተመረጡት የተከበሩ አቶ አበበ ጎበና የድርጅቱን ዓላማ በመደገፍ አንድ ጋሻ መሬትና አንድ ትምህርት ቤት አሠርተው ለድርጅቱ ስላስረከቡ ድርጅቱ አስፈላጊውን የትምህርት መሣሪያ፤ አስተማሪዎች ፤ የመጀመሪያ የሕክምና እርዳታ ፤ ለእርሻ ሙከራ የሚሆኑ የአትክልት ዘሮችን ልኮ ከነገደ ጋላ ከነገደ ሻንቅላና ከነገደ ሸናሻ የተሰበሰቡ ፪፻፶ ልጆችን በማስተማር ላይ ይገኛል ። አስተማሪዎቹም በተጨማሪ በአካባቢው ሕዝብ መካከል ሐዋርያዊ ተግባራቸውን ያከናውናሉ ።

በዚህ ቦታ ያለው ት/ቤት ከሌሎች ሁሉ ከባድ ወጭና ድካም የ ሚጠይቅ ቢሆንም ለሐዋ



www.ethiopianorthodox.org



ድርጅቱ በወልመራ የሠራው ት. ቤት በተመረቀበት ዕለት ከነበረው ሕዝብ በከፊል

ርያዊ ዘመቻ ምቹ ቦታ በመሆኑ ድርጅቱ ካለው አቅም ሊቆጠብ አይቻልም ።

በወላሞም አውራጃ በአውራጃው ግዛት ያሉት አብያተ ክርስቲያናት አገልግሎት እንዳይቋረጥ ፕሮግራም ከልማት ሥራ ጋር በማያያዝ ሰፋ ያለ አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል ። በዚህም ቦታ የሚሠለጥኑ ዲያቆናትና ቀሳውስት ትምህርታቸውን ከጨረሱ በኋላ በዚሁ አውራጃና ወረዳ የአውራጃው ግዛት የመገበሪያ ቦርድ ከድርጅታችን ጋር በመተባበር ዲያቆናትና ቀሳውስት የሚሠለጥኑበትና የአካባቢውም ልጆች የሚማሩበት አንድ ትምህርት ቤት አቋቁሞ ሥራውን በማካሔድ ላይ ይገኛል ። ከትምህርቱ ፕሮግራምም ጋር መንፈሳዊ ነክ የሆኑትን ጉዳዮች ሁሉ በትብብር ለመፈጸም የመገበሪያው ቦርድ ተስማምቷል ። ይህም ፕሮግራም መልክ እንዲይዝና የሕዝቡም ፍላጎት እንዲረካ የመገበሪያው ቦርድ ለሐዋርያዊ ድርጅት በዓመት ፲ሺህ (አሥር ሺህ ብር) እንዲሰጥ ፤ ድርጅቱ የትምህርቱን ፕሮግራም እንዲያካሒድ ከመደረጉ በላይ የመገበሪያው ቦርድ ለድርጅቱ ሥራ መጀመሪያ አንድ ጋሻ መሬት በሶዶ ከተማ አቅራቢያ ሰጥቶ አንድ ት/ቤት በመሥራት ላይ ይገኛል ። የዚህም ት/ቤት ሥራ እንዳለቀ ድርጅቱ ቀደም ብሎ የጀመረው የትምህርት



ድርጅቱ በመትከል አውራጃ ቡለን ቀበሌ ያቆመው ትምህርት ቤት ተማሪዎች



www.ethiopianorthodox.org

ፕሮግራም ከልማት ሥራ ጋር በማያያዝ ሰፋ ያለ አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል ። በዚህም ቦታ የሚሰለጥኑ ዲያቆናትና ቀ ውስት ትምህርታቸውን

በጎ አድራጎት ማኅበር አባል ሆኗል ። ሰብአዊ ርኅራኄ በቃል ስብከት ብቻ ሳይሆን በሥራም መገለጽ ስላለበትና ለሐዋርያዊ ተግባርም አስፈ



የድርጅቱ ሠራተኞች በመተከል አውራጃ ቡለን ቀበሌ በሚገኘው የድርጅቱ ጎ/ቤት አስተምረው ወደ ክርስቶስ የመለሷቸውን አማንያን ሲአጠምቁ

ከጨረሱ በኋላ በዚሁ አውራጃና ወረዎች በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ለአገልግ ሎት የሚመደቡ ይሆናሉ ። ለአካባቢው ልጆች የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት የሚሰጥ ሲሆን አሁን ቀደም ብሎ በ፲፱፻፺፯ ዓ/ ም/ በተጀመረው የትምህርት ፕሮግ ራም ፩፻፶ (አንድ መቶ ሃምሳ) ተማሪዎች በመ ማር ላይ ይገኛሉ ።

## የማኅበራዊ ኑሮ አገልግሎት ክፍል ።

ይህ ክፍል ለድሆች በሽተኞች መርጃና መታ ከሚያ ፣ ለእጓለ ማውታ ሕፃናት ማሳደጊያ ፣ ለችግረ ኞች መርጃ ፣ ለወጣቶች የትርፍ ጊዜ ማሳለፍያ የሚሆኑ ገግጅቶችን ለመፈጸም የሚቻልበትን ዘዴ በማጥናት ይሠራል ።

ይህ ክፍል ከግልና ከመንግሥት የማኅበራዊ ኑሮ አገልግሎት ድርጅቶች ጋር በመተባበር የሚሠራ ሲሆን በ፲፱፻፺፯ ዓ/ ም/ ከኢትዮጵያ ላጊ በመሆኑ ፤ ፩ኛ/ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጎ አድራጎትና ከአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የማኅበ ራዊ አገልግሎት ክፍል ጋር በመተባበር ለችግረ ኞች በሽተኞች የነፃ መታከሚያ ደብዳቤ በመጻፍ በቅዱስ ጳውሎስና በልዕልት ፀሐይ ሆስፒታል በማሳከም ይረዳል ።

ከድኩማን ረድኤት ድርጅት ጋርም በመተ ባበር እግርና እጅ የጎደላቸውንና የአጥንት መጉ በጥ በሽታ የያዛቸውን እየመረጠና ችግራቸውን እያረጋገጠ ወደ ድኩማን ረድኤት ድርጅት በመ ላክ ሰው ሠራሽ አካል በማስገባትና ተፍኪ ድኩማን ማሠልጠኛ ጣቢያ በመላክ የእጅ ጥበብ እንዲማሩ በማድረግ ልመናን እንዲተውና ራሳቸ ውን በመርዳት እንዲተዳደሩ ብዙዎችን ረድቷል ።

ከኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር ጋር በመ ተባበር ለችግረኞች ልብስ በማስመጣት ከመሥ ራቱም በላይ በመተከል አውራጃ በተቋቋመው

ት/ቤት ለሚገኙ ተማሪዎችና ወላጆች ፡ በመናገሻ አውራጃም በሚገኘው ት/ ቤት የሚገኙ ችግረኞች ተማሪዎችን በየጊዜው ይረዳል ። በተጨማሪም ለሁለት ዓመት በመምህራን ማሠልጠኛ ኰርስ የሚያደርጉበት መምህራን በየቦታው ለሥራ ከመመደቻው በፊት ከአስተማሪነት ትምህርታቸው ሌላ የቀይ መስቀል ማኅበር የመጀመሪያ ደረጃ ሕክምና እርዳታን እንዲማሩና በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታልም ልምምድ እንዲያደርጉ በማድረግ በኰርሱ ላይ ያሉትን አስተምሮልናል ። ይህም ዓይነት የሕክምና ትምህርት በየዓመቱ ይደረጋል ።

## የድርሰትና የማስታወቂያ ክፍል

ይህ ክፍል መንፈሳዊ መጻሕፍትን በብዛት በማሳተም በጊዜያችን ያለውን የመንፈሳዊ መጻሕሳዊ ድርሰቶችም ለምእመናን በሬዲዮ እንዲሰሙ በመጽሐፍ ፤ በመጽሔትና በጋዜጣ መልክ እንዲቀርቡ ያደርጋል ።

በዚህም መሠረት እስካሁን «የሴት ልጅ ዕድገት በሃይማኖት» የሴት ልጅ ጠቅላላ ዕድገት የተባሉ የቤተሰብን አያያዝ የተመረኰዙ መጽሔቶችን በየሦስት ወር እየታተመ የሚወጣ ትንሣኤ የሚባል መጽሔትና በሬዲዮም የተነገሩት ስብከቶች በመጽሐፍ መልክ ታትመው ለረጅም ጊዜ አገልግሎት እንዲሰጡ ከታሰቡት መጻሕፍት መካከል አንዱ «ስብከት» የተባለ መጽሐፍ ከመታተሙ በላይ አሥራ ሁለት ገጽ ያለው «ድምፀ ተዋሕዶ» የተባለ መንፈሳዊ ጋዜጣ በየወሩ እየታተመ ይወጣል ።



ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ከወላሞ ሶዶ የመገበሪያ ቦርድ ለድርጅቱ ትምህርት ቤት የተሰጠውን ፩ ጋሻ መሬት ሲረከቡ

ፍት ችግር የሚያቃልልበት ዘንዴ በማጥናትና ጥንታውያን የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ወደ አማሐርኛ እየተተረጐሙ የታሪክ ቅርስነታቸውን ለአዲሱ ትውልድ እንዲተርፍ የሚቻልበትን ዘዴ በማጥናት ይሠራል ። በየትምህት ቤቱ ላሉ ሕፃናትም የሚጠቅሙ የሃይማኖት ትምህርት መማሪያ መጻሕፍትን በማዘጋጀትና ልዩ ልዩ መንፈ

መንፈሳዊ ትምህርትም በጽሑፍ ብቻ እንዳይሆን ለመላው ኢትዮጵያዊ ሕዝብ በራዲዮ ዘወትር በየቀኑ ከአዲስ አበባ ከተማ ውጭ ላለው ሕዝብ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ከአርባ ደቂቃ እስከ ምሽቱ አንድ ሰዓት ከሃምሳ አምስት ደቂቃ ድረስ በአጭር ሞገድ በአርባ ዘጠኝ ሜትር ባንድ ለአዲስ አበባ ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ተሩብ እስከ



www.ethiopianorthodox.org

ምሽቱ  ሦስት ሰዓት ተኩል በመካከለኛ ሞገድ በዘጠኝ  መቶ ዘጠና አምስት ኪሎ ሳይክል  ያሰማል ።

## የሐዋርያት መልእክት ክፍል

ይህ ክፍል መንፈሳውያን ማኅበሮች በየቦታው እንዲስፋፉ የሚጥር ሲሆን በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በ ሚገኙ ለክህነት በሚዘጋጁት ዲያቆናት የተቋቋመ ማኅበረ እስጢፋኖስ መንፈሳዊ ማኅበር ፤ ዘወትር ቅዳሜና እሑድ ት/ቤቶች በሚዘጉበትም ጊዜ ከየትምህርት ቤቱ እየ ተሰበሰቡ ከአንየደኛ እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል በሚማሩ ተማሪዎች ድርጅቱ በሚሰጣቸው መን ፈሳዊ ትምህርት አማካይነት ያቋቋሙት ማኅበረ ክርስቶስ የደናግል ማኅበር ፤ ከስድስተኛ እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች ያሉበት ማኅበረ ሥላሴ የወንዶች ወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበር በድርጅቱ ሥር ተቋቁመው በመሥራት ላይ ይገኛሉ ፡ እንደዚሁም በየካ ሚካኤል አካባቢ በሚገኙ ወጣቶች የተቋቋመ የምሥክራቅ አዲስ አበባ ወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበር ፥ በቅዱስ ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ በሚገኙ ወጣቶች የተቋቋመ የዮሐንስ መንፈሳዊ ማኅበር ፥ በኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን አካባቢ በሚገኘው ሕዝብ የተቋቋመ የሐመረ ኖኅ የድኩማን መርጃ ማኅበርና በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ በሚገኘው ሕዝብ የተቋቋመ የገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ማኅበር ከድርጅቱ ጋር በጥገኝነት እንዲሠሩ ጠይቀው በትብብር  መንፈሳዊ  ማኅበራቸውን አቋቁመው በመሥራት ላይ ይገኛሉ ።

ድርጅቱ መንፈሳዊ ትምህርትን በበለጠ በወጣቶች በእስረኞችና በበሽተኞች ዘንድ ለማስፋፋት ዘወትር በየጊዜው በመድኃኔ ዓለም በዳግማዊ ምኒልክ ት/ቤት በመምህራን ማሠልጠኛ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፩ኛ ደረጃ በተስፋ ኮከብ ፤ በአስፋ ወሰን ፤ በልዑል መኰንን ፤ በግርማዊት እቴጌ መነን  ቅርንጫፍ ት/ቤት ፥ በሴቶች ወጣቶች ክርስቲያናዊ ማኅበር ፥ በእጓለ ማውታ ሕፃናት ማሳደጊያ ፥ በአዲስ አበባ ወህኒ ቤት በጠባይ ማረሚያና በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል መንፈሳዊ ትምህርትን ከመስጠቱም በላይ ለበሽተኞችና ለእሥረኞች በተጨማሪ የንስሐና የማጽናኛ ትምህርት ይሰጣል ። ታላላቅ በዓላት በሚከበሩበትም ጊዜና በሕዝብ ማኅበራዊ ስብሰባ ለምእመናን መንፈሳዊ ትምህርቱን በየጊዜው ይሰጣል ። በዚህ መልክ ሐዋርያነትን በተፈለጉበት ቦታ ሲልክ ከአዲስ አበባ ውጭ በመናገሻ አውራጃ በመተከልና በወላሞ አውራጃ ሐዋርያቱን ልኮ አገልግሎቱን በመስጠት ላይ ይገኛል ። ድርጅቱ እያደገ በሚሔድበት ጊዜ በጥሩ ይዞታና በቀለጠፈ አኳኋን እንዲሠራ ከድርጅቱ ሠራተኞች ሁለቱ ወደ ሩማንያ ሁለቱ ወደ ግሪክ ሀገር ለከፍተኛ ትምህርት ተልከዋል ።

## የንብረት ክፍል

የንብረት ክፍል የድርጅቱ ንብረት በየጊዜው የሚስፋፋበትንና ከሕዝብም በእርዳታ የተሰጡ ስጦታዎች በአገልግሎት መልክ ለሕዝብ ተመልሰው እንዲቀርቡ ያደርጋል ። በመናገሻ አውራጃና በመተከል አውራጃ ለትምህርት ቤት የተሰጠውን ቦታና ቤት በወላሞም ከመገበሪያው ቦርድ የሚሰጠውን ገንዘብና መሬት በአዲስ አበባም ያለውን የድርጅቱን ንብረት የሚመለከተውን ሁሉ ይፈጽማል ።

የድርጅቱ ዓላማዎች ቀደም ብሎ የተዘረዘሩ ቢሆኑም በሚመጡት ዓመታት ያለው እቅድ ፤

ሀ/ አሁን በጅምር ላይ ያለውን ፕሮግራም በበለጠ ማሟላት ፥

ለ/ በዛ ያሉ መንፈሳዊ ትምህርት የሚሰጥባቸውን መጻሕፍት ለማሳተምና በተጨማሪም ወደ አማርኛ የሚተረጎሙ መጻሕፍት ትርጉሙን ለሕዝብ ለማቅረብ ፤

ሐ/ ሐዋርያትን በብዛት ክርስትና ካልገባበት ቦታ ከመላካቸው በፊት ክርስትና ያልደረሰባቸውን ቦታዎች ፕሮግራም ለመጀመር የሚችልበትን ዘዴ ሰፋ ባለ እቅድ አስቀድሞ ለማጥናት ።

መ/የእሑድ ትምህርት ቤቶችንና መንፈሳዊ ማኅበሮችን በየቦታው በብዛት እንዲቋቋሙ ለማድረግ ፤

ሠ/ በወላሞ አውራጃ በተከፈተው የትምህርት ፕሮግራም አንድ በአውራጃዎችና በወረዳዎች ደረጃ ለማገልገል እንዲችል አንድ የመምህራን ማሠልጠኛ ጣቢያ ለማቋቋም ሲሆን ፤ ድርጅቱ



www.ethiopianorthodox.org

በፕሮግራም የሚሠራ ቢሆንም የሕዝብ ፍላጎትና እርዳታ በያለበት ቦታ ሁሉ ከሕዝብ ጋር በመተባበር አገልግሎቱን የማይቆጥብ ሲሆን ሕዝብ የእኛ በሚል ስሜት እንዲነሣና እንዲተባበር በማኅበርም በመሥራት የሀገርን ችግር በመካፈል ለማቃለል የሚችል መሆኑን በማመን ድርጅቱ ከሕዝብ ጋር በመሥራት አገልግሎቱን ለሕዝብ ለማቅረብ ዝግጁ ነው ።

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት የወጣቶችን መንፈሳዊ ሕይወት ይገነባል



ቅዳሜና እሑድ እንዲሁም ትምህርት ቤቶች በሚዘጉባቸው ወቅቶች በፈቃዳቸውና በቤተ ሰቦቻቸው አማካኝነት እየመጡ በድርጅቱ ሥር የሃይማኖት ፤ የግብረ ገብነትና የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ከሚማሩት ተማሪዎች በከፊል ።



www.ethiopianorthodox.org